ኑ፥ እንስገድለት

አምልኮ በአፍሪካ አብያተ ክርስቲያን
1ኛ መጽሐፍ

ትርጉም፡- በመስፍን ወልደ አማኑኤል
እርማት፡- በግርማዊ

Copyright © 1997 by SIM Ethiopia, Addis Ababa. Originally published in English under the title of "COME, LET US BOW DOWN..." Worship In The Christian Church In Africa, Book 1. Copyright © 1991 by the A.I.C. Theological Advisory Group (A.I.C. Kenya), Printed in Kenya, East Africa. All rights reserved.

ማውጫ

መግቢያ .....
አለተያየት.....
መቅድም .....
ክፍል አንድ፡- የአምልኮ ትርጉም 1
ጥናት 1፡- አምልኮ፡- ለእግዚአብሔር በረከት የምስጋና ምላሽ 2
ጥናት 2፡- አምልኮ፡- በፍጥረት ሥራ ውስጥ የእግዚአብሔርን ታላቅነት በማሰብ የመገረምና የመደነቅ ምላሽ 7
ጥናት 3፡- አምልኮ፡- ደስታን ባዘለ የቅድስና ፍርሃት ወደ እግዚአብሔር የመቅረብ ምላሽ..... 11
ጥናት 4፡- አምልኮ፡- እግዚአብሔርን መጠማት 17
ጥናት 5፡- አምልኮ፡- ለእግዚአብሔር ፈቃድ የመታዘዝ ምላሽ 22
ጥናት 6፡- አምልኮ፡- "በመንፈስና በእውነት ሊሆን ይገባዋል" 28
ክፍል ሁለት፡- የምናመልከው አምላካችን..... 37
ጥናት 7፡- ስለ እግዚአብሔር ሁሉን ነገር መረዳት ባንችልም፥ እግዚአብሔርን ልናውቅ እንችላለን:: 37
ጥናት 8፡- የእግዚአብሔር አንድነትና ሦስትነት (ሥላሴ) 44
ጥናት 9፡- እግዚአብሔር ቅዱስ ነው 53
ክፍል ሦስት፡- በዕብራውያን ነቢያት የታረመ አምልኮ 59
ጥናት 10፡- እግዚአብሔርን የማያስከብር አምልኮ 60
ጥናት 11፡- የሕይወት ግድፈት የሚያስከትለው ከንቱ አምልኮ ... 64
ጥናት 12፡- የተከፋፈለ አምልኮ ተቀባይነት የለውም 69
ጥናት 13፡- መንፈሳዊ ምንዝርና ከትክክለኛው አምልኮ ጋር ያለው አለመጣጣም 73
ክፍል አራት፡- የክርስቲያን አምልኮ በዛሬው ዘመን 78
እግዚአብሔርን ሰውነታችንን በማቅረብ ስለማምለክ.....79
ጥናት 14፡- ሰውነታችንን ለእግዚአብሔር ማቅረብ 79
ምስጋናችንን እያቀረብን እግዚአብሔርን ማምለክ.....84
ጥናት 15፡- በምስክርነት አማካኝነት እግዚአብሔርን ማመስገን 86
ጥናት 16፡- በዝማሬ ምስጋና ማቅረብ..... 90
አሥራታችንና መባችንን በማቅረብ እግዚአብሔርን ማምለክ 96
ጥናት 17፡- በስጦታችን እግዚአብሔርን የማክበር ጠቀሜታ..... 97
ጥናት 18፡- ስጦታችንን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የምንሰጥበት ክርስቲያናዊ የአፈጻጸም መምሪያ 101
በጸሎት ውስጥ ምስጋናችንንና አክብሮታችንን በማቅረብ እግዚአብሔርን ማምለክ 106
ጥናት 19፡- በጸሎት አምልኮአችንን ለእግዚአብሔር ማቅረብ 106
የእግዚአብሔርን ቃል በምንሰማበትና በምናደርግበት ጊዜ እምነታችንንና መታዘዛችንን እያቀረብንለት እግዚአብሔርን ማምለክ 111
ጥናት 20፡- የእግዚአብሔርን ቃል ስንሰማ እምነታችንንና መታዘዛችንን ለእግዚአብሔር ማቅረብ..... 111
ተቀጥላ፡- በመጽሐፍ ቅዱስ የአምልኮን ፍች የሚያሳዩ ተጨማሪ አሳቦች 116

መግቢያ

አምልኮ ከእግዚአብሔር ማንነትና ከእኛ ማንነት የተነሣ የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ዋነኛ ተግባር ሊሆን ይገባል። እግዚአብሔር ፈጣሪ ነው፣ እኛ ደግሞ የእርሱ ፍጥረታት ነን። "ምድርና በምድር ላይ የሚኖሩ ሁሉ፣ የእግዚአብሔር ናቸው፣ ዓለም በውስጥዋ ያሉት ሁሉ የእርሱ ናቸው። ምድርን በባሕር ላይ ያቆመ፣ መሠረትዋንም ጥልቁት ባላቸው ውቅያኖሶች ውስጥ ያደረገ፣ ራሱ እግዚአብሔር ነው" (መዝ. 24፡1-2)።

ፈጣሪያችን ከመሆኑም በላይ እግዚአብሔር አምላክ አዳኛችንም ሆኖአል። የእግዚአብሔር ፍቅርና ታማኝነት ለእኛ ለልጆቹ ምንጊዜም ታላቅ ነው። "እግዚአብሔር ሆይ! በሙሉ ልቤ አመሰግንሃለሁ... ወደ ተቀደሰው መቅደስህ እየሰገድሁ፣ ስምህን አመሰግናለሁ... ከሁሉ በላይ ከፍ ያልህ ሆነህ ሳለ፣ ትሑታንን ትንከባከባለህ፣ ትዕቢተኞችም ከአንተ ፊት መሰወር አይችሉም" (መዝ. 138፡1-6)።

አምልኮ ለክርስቲያኖች ዋነኛ ተግባር ብቻ አይደለም። ነገር ግን የእኛ አምልኮ፣ ፈጣሪያችንና አዳኛችንን የቱን ያህል እንደምንወደው ለዓለም የሚናገር ነው። እውነተኛ አምልኮ ለእግዚአብሔር ያለንን መሰጠት ለዓለም የምንመሰክርበት ነው። ትሑታን በሙሉ ልባቸው እግዚአብሔርን በእውነት ያመልኩታል። ነገር ግን ትዕቢተኞች እግዚአብሔርን ለማክበርና ለማምለክ ራሳቸውን እንዳይሰጡ በሌሎች ተግባራት በጣም የተወጠሩ ናቸው። እግዚአብሔር ትሑታንን ይወዳል። ነገር ግን ማክበር እንደሚገባቸው የማያከብሩትን ይተዋቸዋል።

በአፍሪካ ያሉት አብያተ ክርስቲያናት አሁን ካለው በላይ በእውነተኛ አምልኮ ላይ ትኩረት ማድረግ ይኖርባቸዋል። በቤተ ክርስቲያናችን እግዚአብሔር ብቻውን ማግኘት የሚገባውን አክብሮትና ክብር የመስጠት ትልቅ ጥያቄ አለ። አምልኮአችን ተሐድሶ ያስፈልገዋል።

" ኑ፥ እንሰግድለት" የሚለው የዚህ መጽሐፍ ዓላማ አምልኮ በአፍሪካ በሚገኙት የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ትናንሽ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድኖች አማካኝነት መጋቢዎቻችን፣ ሽማግሌዎቻችንና አማኝ ወገኖቻችን መጽሐፍ ቅዱስን እንዲያጠኑ ለመርዳት ነው። እግዚአብሔርን በተሻለ ሁኔታ ለማምለክ እግዚአብሔር በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አምልኮን በተመለከተ ያሰተማረውን ማወቅ ይኖርብናል።

በአብዛኛዎቹ አብያተ ክርስቲያኖቻችን አምልኮ ተረስቶ የቆየ ርእሰ-ጉዳይ ነው። የዚህ መጽሐፍ ዓላማ አምልኮ በትክክል ምን እንደሆነ ያውቁ ዘንድና እንዴት አድርገው በተሻለ መንገድ ለማምለክ እንዲችሉ ምእመናን መጽሐፍ ቅዱስን እንዲያጠኑ ለመርዳት ነው። የዚህ መጽሐፍ የመጨረሻ ግብ ግን የእውቀት ጥያቄ አይደለም፣ ነገር ግን ሁሉም አማኝ እግዚአብሔርን ይበልጥ ተቀባይነት ባለው መንገድ ማምለክ ይችል ዘንድ ለመርዳት ነው።

እኔ በግሌ ይህ መጽሐፍ በቤተ ክርስቲያናችን ሁሉ በሥራ ላይ እንዲውል የበኩሌን ደጋፍ ስሰጥ፥ በዚህ ርእሰ-ጉዳይ ላይ በሥነ-መለኮት አማካሪ ቡድን ጥናት በመደረጉ ደስታ ይሰማኛል። እንደዚሁም የሥነ -መለኮት አማካሪ ቡድን አጥኚ ቡድን አባላት በአምልኮ ላይ ስላከናወኑት መልካም ሥራ ምስጋናዬን ለመግለጽ እወዳለሁ።

ሬቭረንድ ሲላስ የጉ

የአፍሪካ ኢንላንድ ቤተ ክርስቲያን (ኤ.አይ.ሲ) ሰብሳቢ

ኪታሌ/ ፖኮት ቀጠና

የኤ.አይ.ሲ. ሥነ-መለኮት አማካሪ ቡድን ሰብሳቢ

አስተያያት

እንደ አውሮፓ አቆጣጠር በ1987 ሰኔ ወር የኤ. አይ. ሲ ብሔራዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤቶች ኮሚቴ ንዑስ ኮሚቴ የሆነው የኤ. አይ. ሲ. የሥነ- መለኮት አማካሪ ቡድን ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በአምልኮ ላይ ጥናት እንዲያደርጉ የሥነ--መለኮት አማካሪ ቡድን አጥኚ ቡድን አቋቋመ።

በአምልኮ ላይ ጥናት የሚያደርገው የሥነ- መለኮት አጥኚ ቡድን አባላት የኤ.አይ.ሲ. መጋቢዎችን፥ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤትና የመጽሐፍ ቅዱስ ኩሌጆች መምህራንን ያጠቃልላል። የሚከተሉት ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መጽሐፍ በአምልኮ ላይ ለማዘጋጀት በአባልነት ያገለገሉ ናቸው። መጋቢ አብርሃም ታሩስ፣ መጋቢ አሞጽ ሉያ፣ መጋቢ ዳንኤል ኪፐያቲች፣ መጋቢ ኤሪክ አዲስ፣ ሚ/ር ግሩሃመ ኑዬ፣ መጋቢ ይስሐቅ ዋንዮሙ፣ መጋቢ ዮናታን ቡቪ፣ መጋቢ ዮሴፍ ሙቶንጋ፣ መጋቢ ኪቢ ማዩ፣ መጋቢ ናታን ዚዮካ፣ ሚ/ር ማልኩልም ኩቢንስ፣ መጋቢ ሙሴ ቺንኩኝ፣ መጋቢ ፊሊፕ ኪቱር፣ ዶ/ር ሪቻርድ ጌሀማን፣ መጋቢ ስምዖን ሌሊና፣ መጋቢ ዊልያም ኩሳጊ። ከነዚህም አንዳንዱ አባላት ወደ ሌላ የኬንያ ክፍል ተዛውረዋል፣ ሌሎች ደግሞ ወደ ሌላ የአፍሪካ አገርና ለከፍተኛ ትምህርት ወደ ውጭ ተንቀሳቅሰዋል። ከዚህ የተነሣ ይህን ሥራቸውን ዳር ለማድረስ አልቻሉም። ነገር ግን እያንዳንዳቸው ለአጠቃላዩ የጥናት ፕሮጀክት ጠቃሚ የሆነ ሥራ አበርክተዋል።

ከዚህ ጥናት የመነጩ ሦስት መጻሕፍት ተዘጋጅተዋል፣ ሁለቱ በአምልኮ ላይ የተዘጋጁ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መጻሕፍት፣ "ኑ፥ እንስገድለት" አምልኮ -በአፍሪካ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን (መጽሐፍ 1 እና 2 በግለት ተከፍሏል)። እንደዚሁም - ተግባራዊ የአምልኮ መመሪያ ለመጋቢዎችና ለሽማግሌዎች የእግዚአብሔር ሕዝብ በእውነትና በመንፈስ ያመልኩ ዘንድ በኤ.አይ. ሲ. የአምልኮን-ተሐድሶ ለማምጣት መሪዎችንና መጋቢዎችን ለመርዳት።

ለዚህ ጥናት ብዙ ጥረትና ጊዜ ተሠውቷል። ከጥቅምት ወር 1987 (እ.ኤ.አ) ወዲህ በአምልኮ ሥራ ላይ የተሰየመው የሥነ-መለኮት አማካሪ ቡድን የጥናት ክፍል ለሦስት ቀናት የሥራ ምክክር በሦስት ወር አንዴ ዘጠኝ ጊዜ ያህል ተገናኝቷል። የተለያዩ የቡድኑ አባላት ጥናት በማድረግ በሥራ ምክክር በሚገናኙበት ጊዜ ሪፖርታቸውን ያቀርቡ ነበር። ሁላችንም መጽሐፍ ቅዱስ በአምልኮ ላይ ያለውን ትምህርትና ይህም በቤተ ክርስቲያናችን ላይ የሚያስከትለው ተግባራዊ የአምልኮ አፈጻጸም በመረዳት አድገናል።

"ኑ፥ እንስገድለት" 1ኛ መጽሐፍ በአምልኮ ትርጉምና አስፈላጊነት፥ በአምልኮ ጌታ፥ በዕብራውያን ነቢያትና በዛሬው ክርስቲያን አምልኮ በተደረገው እርማት ላይ ያተኩራል። የ"ኑ፥ እንስገድለት" 2ኛ መጽሐፍ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ባሉት የተለያዩ የአምልኮ ምላሾችና ልምምዶች ጥናት ተማሪዎችን ይመራል።

የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች በ1ኛ መጽሐፍ መጀመር ይኖርባቸዋል። አንደኛውን መጽሐፍ የጨረሰ የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪ ከዘፍጥረት እስከ ራእይ ያለውን የእግዚአብሔርን ሕዝብ አምልኮ በተሻለ ሁኔታ እንዲረዳ የሚያስችለውን 2ኛ መጽሐፍ መቀጠል ይችላል።

የእነዚህ ሁለት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መጻሕፍት ዓላማ በአምልኮ ላይ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መንፈሳዊ ተሐድሶን ማምጣት ነው። ብዙዎች በዛሬው ጊዜ በቤተ ክርስቲያናችን ያለው አምልኮ የክርስቲያን አምልኮ በትክክል መሆን ከሚገባው በታች እንዳሽቆለቆለ ያምናሉ። እግዚአብሔርን ከመራብና ከመጠማት ጉድለናል። ለእግዚአብሔር ግልጽ የሆነውን አምልኮ ከልባችን ከማቅረብ ጉድለናል። አምልኮ በአብዛኛው ቤተ ክርስቲያን ቅርጽ ብቻ ያለው፣ የልማድና ድግግሞሽ ብቻ ሆኖአል። የክርስቲያን አምልኮ የእግዚአብሔር ሕዝብ እርሱን በትክክል ከልባቸው ሳያመልኩ አብዛኛውን ጊዜ የትውፊትና የወግ ነገር ብቻ ሆኖአል።

ለእግዚአብሔር የሚገባውን አክብሮትና ክብር ልናቀርብ የምንችለው መጽሐፍ ቅዱስን ስናጠናና ስንታዘዝ ብቻ ነው። የእግዚአብሔር ሕዝብ በመላው አፍሪካ የእግዚአብሔርን ቃል *"ኑ፥ እንስገድለት፥ አምልኮ በአፍሪካ መንፈሳዊት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ"* በተሰኙት ሁለት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መጻሕፍት እርዳታ በሚያጠኑበት ጊዜ በአምልኮአቸው ተሐድሶ እንዲያገኙ በአምልኮ ላይ ጥናት ያደረገው የሥነ-መለኮት አማካሪ ቡድን ጸሎት ነው።

ዶ/ር ሪቻርድ ጂ.ጌሀማን

በአምልኮ ላይ ጥናት ያደረገው አጥኚ ቡድን የጽሑፍ አርታዒ
የኤ.አይ.ሲ ሥነ መለኮት አማካሪ ቡድን አስተባባሪ

መቅድም

በአነስተኛ ቡድኖች መጽሐፍ ቅዱስ የማጥናት ጥቅም፦

የዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት (መጽሐፍ) ዕቅድ የሥነ መለኰት አማካሪ ቡድን (TAG) ቀደም ሲል ካዘጋጀውና "ሁለትና ሦስት ሆነው በተሰበሰቡበት...": *ጸሎት በአፍሪካ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ* ከሚለው ጋር ተመሳሳይነት አለው። ዓላማውም የአነስተኛ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድን አባላት መጽሐፍ ቅዱሳቸውን በጎላ በሚመረምሩበት ጊዜ *በውይይት* መልክ ማጥናት ይችሉ ዘንድ ነው።

አብዛኛውን ጊዜ ሰባኪዎች መልእክት ያቀርባሉ። አስተማሪዎችም በገለጻ መልክ ያስተምራሉ። የአድማጮች ተሳትፎ ግን ጥቂት ነው። ጥበብ ሁሉ ሰባኪዎችና አስተማሪዎች ዘንድ እንዳለ ይታሰባል። እነርሱን የሚያዳምጡ ታዲያ የቀረበላቸውን ይጠጣሉ፤ ያምናሉ፤ ይቀበሉታልም። ነገር ግን የዚህ መጽሐፍ ዓላማ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስን በአነስተኛ ቡድኖች እንዲያጠኑና በውይይት ራሳቸው እንዲረዱት ለማገዝ ነው።

ይህ መጽሐፍ ለአነስተኛ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድን ውይይት የመሪው መመሪያ ነው። ጥያቄ ብቻ ሳይሆን ለጥያቄዎቹ መልስ ሊሆኑ የሚችሉትንም አሳቦች በውስጡ አካትቷል። እነዚህ መልሶች ሊሰጡ እንደሚችሉ ብቸኛ መልሶች ወይም እንደ መጨረሻና ፍጹም የሆኑ መልሶች ሆነው ሊታዩ አይገባም። መልሶቹ መልሱ ምን መሆን እንደሚገባው ለአነስተኛው ቡድን መሪ አሳብ በመስጠት ለመርዳት ነው።

ሌሎች የአነስተኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድን አባላት ጥያቄ ብቻ እንጂ መልስ የሌላቸውን *የተግሪ መሥሪያ ደብተሮች* ለራሳቸው መግዛት ይኖርባቸዋል። መጽሐፍ ቅዱስን የሚያጠኑት ተማሪዎች በሙሉ የመሪው መመሪያ ቢኖራቸው ጠቃሚ አይሆንም። መልስ ይሆናሉ ተብለው የተጠቆሙት አሳቦች በፊታቸው ሊኖሩም አይገባም። አጠቃላዩ ዓላማ ለመወያየትና ትርጉሙንና የምናዛምዳቸውን ነጥቦች ከመጽሐፍ ቅዱስ ለመፈለግ ነው። በእያንዳንዱ ጥያቄ ላይ ውይይት ከተካሄደ በኋላ ተማሪዎቹ ለተማሪው በተዘጋጀው *መሥሪያ ደብተር* ላይ ባለው ክፍት ቦታ መልሶቻቸውን መጻፍ ይችላሉ።

የአነስተኛ መጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድን ዋና ዓላማ መጽሐፍ ቅዱስ ምን እንደሚልና ከሕይወታቸው ጋር እንዴት እንደሚዛመድ ለመማር ነው። ብዙ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስ ምን እንደሚል የራሳቸው ግንዛቤ አላቸው። ነገር ግን ክርስቲያኖች መጽሐፍ ቅዱስ በትክክል ምን እንደሚያስተምር ለራሳቸው ሊማሩት ይገባል።

በቤርያ ያሉት አይሁዳውያን "በተሰሎንቄ ካሉት ይልቅ ቅን አመለካከት ያላቸው ስለነበሩ ቃሉን በታላቅ ደስታ ተቀበሉ፤ *የታሉንም እውነተኛነት ለማረጋገጥ በየቀኑ ቅዱሳት መጻሕፍትን ይመረምሩ ነበር*" (የሐዋ. 17:11)።

የእግዚአብሔርን ቃል የሚሰብኩና የሚያስተምሩ ሰዎች በቤተ ክርስቲያናችን መኖራቸው ጠቃሚ ነው። ነገር ግን ከዚያ የበለጠው ጠቃሚ ነገረ እያንዳንዱ አማኝ መጽሐፍ ቅዱስን ሌሎች በሚያስተምሩበት ጊዜ አሳባቸው በትክክል ከቃሉ ጋር የሚሄድ መሆኑን ወይም አለመሆኑን ለማረጋገጥ ለራሱ ሊያጠናው መቻሉ ነው። የዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መጽሐፍ ዓላማ ክርስቲያን ይህን ማድረግ እንዲችል ለመርዳት ነው።

ይህ መጽሐፍ የሚረዳህ መጽሐፍ ቅዱስን እንድታጠናው ብቻ አይደለም። ነገር ግን የመጽሐፍ ቅዱስን ትምህርት ከሕይወትህና ከልምምድህ ጋር ለማዛመድ በተጨማሪ ይረዳሃል። እግዚአብሔር አምላክ *ተግባራዊ ሰሆኑ የሕይወት ጥያቄዎቻችን መልስ ይሆን ዘንድ መጽሐፍ ቅዱስን ሰጥቶናል*። ስለዚህ ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መጽሐፍ ቅዱስ የሚለውን እንድትማር ብቻ ሳይሆን፥ ዛሬ ካለህበት ኑሮ ጋር እንዴት ልታዛምደው እንደምትችል ለማሰብም የሚረዳህ ነው።

ለመሪው ውይቱን እንዴት መምራት እንደሚችል የማወቅ ጥቅም፦

ጥሩ የአነስተኛ መጽሐፍ ቅዱስ ውይይት ቡድን መሪ ሁሉንም መልስ የማወቅ ግዴታ የለበትም። የእርሱ ተግባር የቡድኑን ውይይት መጽሐፍ ቅዱስ ምን እንደሚልና በዛሬው ጊዜ ከሕይወታቸው ጋር እንዴት ማዛመድ እንደሚችሉ በሚያደርጉት አሰሳና የፍለጋ ሥራ መምራት ብቻ ነው። ነገር ግን መሪውን ለመርዳት ይህ መጽሐፍ መሪው ክፍሉ ከመጀመሩ በፊት አጥንቶና አውቆ መግባት የሚያስችሉ መልስ ሊሆኑ የሚችሉትን አሳቦች ይዟል።

ጥሩ መሪ ጥቅሶቹን በሙሉ ራሱ አያነብም። ነገር ግን እያንዳንዱን የቡድኑን አባላት ከሚያጠኑት መጽሐፍ ውስጥ የተለያዩ ጥቅሶችን እንዲያነቡ ይጋብዛቸዋል።

ጥሩ የመጽሐፍ ቅዱስ ውይይት መሪ ብዙ ጊዜ የሚናገር አይደለም። አባላትን ቃሉን በሚያጠኑበት ጊዜ እንዲያስቡና እንዲናገሩም ያደፋፍራቸዋል። ወይም ለጥያቄዎቹ በሙሉ መልስ ሊሰጥም አይገባም። ከዚያ ይልቅ ተማሪዎቹን በጥናቱ ለተገኙት እንዲያካፍሉ እየረዳቸው እንዲያስቡና እንዲናገሩ ያደፋፍራቸዋል። በመጨረሻም የቡድኑ መሪ ከመሪው መመሪያ ላይ ያለውን ተጨማሪ አሳብ በመጨመር በጥናቱ ጊዜ የተነሡትን አሳቦች ሊያጠቃልል ይችላል።

ምንም እንኳን ጥሩ መሪ በውይይቱ ጊዜ አብዛኛውን ንግግር ባያደርግም ቃሉን በሚያጠኑበት ጊዜ ቡድኑን በማስተዋልና ሊረዳቸው በሚችል መንገድ መምራት ይችል ዘንድ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቱ በፊት ለራሱ ማጥናትና መዘጋጀት ይኖርበታል።

የመሪው መምሪያ መሪውን በአነስተኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ቡድን ጥናት ክፍለጊዜ እንደ *መሣሪያ* እንዲያገለግል የተዘጋጀ ነው። ሆኖም መሪው እንደ መገልገያ መሣሪያ እንጂ የእርሱ ባሪያ ሊሆን አይገባም። መሪው

ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መሣሪያ በመጠቀምና ውይይቱን ለመምራት ጥበብ ያስፈልገዋል። በእንድም ሆነ በሌላ ምክንያት አንዳንድ ጊዜ ውይይቱን ለማላጠርና አንዳንድ ጥያቄዎችን ለማስወገድ አስፈላጊ ሆኖ ልታገኘው ትችላለህ። የራስህ የሆኑትን አንዳንድ ጥያቄዎች ልትጨምር ትችል ይሆናል።

መሪዎች የፈጠራ ችሎታ ሊኖራቸውና ውይይቱን ግራኪና ጠቃሚ በሆነ መንገድ እንዴት መምራት እንደሚችሉ መማር ይኖርባቸዋል። ስለዚህ ይህ መጽሐፍ እንደ ማስተማሪያ መርጃ እንጂ እንደምንታሠርበት ነገር ሊታይ አይገባም።

የአነስተኛ መጽሐፍ ቅዱስ ቡድን ጥናት ዓላማ፦

የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት በውይይት መልክ በጣም አስደሳችና ጠቃሚ እንደሚሆን ትገነዘባለህ። ሰዎች ስብከት ከመስማት ይልቅ በውይይትና በግል ፍለጋ የበለጠ ይማራሉ። ምንም ድርሻ ሳይወስዱ በጸጥታ ከመቀመጥ ይልቅ ውይይት የበለጠ ግራኪ ነው። ለሌሎች የራስህን ግኝት ማካፈልና በአመለካከታቸው ላይ ለውጥ ለማምጣት ትችላለህ። ሁላችሁም መጽሐፍ ቅዱስን በመረዳት ረገድና በዛሬው ጊዜ እንዴት ከሕይወት ጋር ማዛመድ እንደሚቻል እርስ በርሳችሁ መረዳዳት ትችላላችሁ።

በተለይ ካልተጠቀሰ በስተቀር በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ያሉት ጥቅሶች በሙሉ የተወሰዱት በ1980 ዓ.ም ከታተመው አዲስ የመጽሐፍ ቅዱስ የአማርኛው ትርጉም ነው።

ሆኖም የመጨረሻው የዚህ መጽሐፍ ዓላማ ከመረዳት በላይ ነው። ግቡ እግዚአብሔርን ደስ በሚያሰኝ አምልኮ እንድታከብሩት እናንተን ለመርዳት ነው። *"ኑ፥ በእግሩ ሥር ወድቀን እንሰገድለት፣ ፈጣሪያችን በሆነው በእግዚአብሔር ፊት እንንበርከክ። እርሱ አምላካችን ነው፣ እኛም እርሱ የሚጠነቀቅልን ሕዝቦቹና የሚያሠማራን መንጋዎቹ ነን፣"* (መዝ. 95:6-7)።

ክፍል 1
የአምልኮ ትርጉም

ሕያው እግዚአብሔርን ማምለክ ለክርስቲያኖች ቀዳሚና ከሌላው ሁሉ የላቀ ተግባር ነው። ክርስቲያን ከምንም ነገር በላይ ሕያው እግዚአብሔርን በእውነት ሊያመልክ ይገባል። የእግዚአብሔርም ቃል በመዝሙር 29:2፥ "ክብር የሚገባውን የእግዚአብሔርን ስም አመስግኑ፤ የቅድስናው ክብር በሚገለጥበት ጊዜም ለእግዚአብሔር ስገዱ" በማለት ያስተምረናል። ክርስቲያን ምሁራንም እንደዚሁ፥ "የሰዎች መጨረሻ ግብ እግዚአብሔርን ማክበርና እርሱንም ለዘላለም ደስ ማሰኘት ነው" ሲሉ ተናግረዋል።

ያም ቢሆን አምልኮ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በየትኛውም ስፍራ ማብራሪያም ሆነ ገለፃ አልተሰጠበትም። ለመሆኑ አምልኮ ምንድን ነው? እግዚአብሔርን እንዴት አድርገን ማክበር እንችላለን? እንደ እግዚአብሔር ሰዎች በጎብረት ሆነን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አምልኮን እንዴት ልንፈጽም እንችላለን? በአዘቦቱ ቀናት እንደ ግለሰብ በግላዊ ኑሮአችን እግዚአብሔርን እንዴት ልናመልክ እንችላለን?

አምልኮ እርሱ ራሱን ሲገልጽልን ለሕያው አምላካችን የምንሰጠው ምላሽ ነው። እንደ ፈጣሪ አምላክ፥ አዳኝ፥ አረኛ/ጠባቂ/ እና መሪ ራሱን በተፈጥሮ (በፍጥረት)፥ በተግባራዊ ኑሮአችንና በቃሉ ሲገልጽልን እኛ ደግሞ ለሰሙ የሚገባውን ክብር በመስጠት እንመልሰለታለን። *ይህ እንግዲህ አምልኮ ነው።*

መዝሙረ ዳዊት በብሉይ ኪዳን ዘመን የነበሩ የእግዚአብሔር ሰዎች ለአምልኮ የሚጠቀሙበት የዕብራይስጡ ግጥም ስብስብ ነው። ብዙው የመዝሙረ ዳዊት ክፍል የተለያዩ ሰዎች በተለያዩ ሁኔታዎች ውስጥ ሆነው እግዚአብሔርን ሲያመልኩትና ሲያመሰግኑት የተጻፈ ነው። እነዚህ ግጥሞች አውታር ያላቸው የሙዚቃ መሣሪያዎችን በሚጠቀሙበት ጊዜ የሚዘምሩአቸው ነበሩ። መዝሙረ ዳዊት በዝማሬ ሲቀርብ ወደ 4,000 የሚጠጉ የመሣሪያ ተጫዋቾች ለአገልግሎት ይቆሙ ነበር (1ኛ ዜና 23:5)።

በርካታ የመዝሙረ ዳዊት ክፍሎችን በማጥናት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለውን የአምልኮ ትርጉም ለመረዳት እንሞክራለን። የምናጠናቸው የመዝሙረ ዳዊት ክፍሎች ከዚህ በታች ያሉትን አሳቦች ያመለክቱናል።

1- አምልኮ ስለ ብዙ በረከቶቹ (ወይም ጥቅሞቹ) ለእግዚአብሔር የአክብሮትና የምስጋና ምላሽ መስጠት ነው (መዝ. 103)::

2- አምልኮ እግዚአብሔር በፍጥረት ውስጥ ያለውን ኃያልነትና ክብር እያሰብን ለእርሱ በመገረምና በአድናቆት የምንሰጠው አጸፋዊ ምላሽ ነው::

3- አምልኮ ከቅዱስ ፍርሃት ጋር በፊቱ በመገኘት ደስታን ጨምሮ ለእግዚአብሔር ምላሽ መስጠት ነው (መዝ. 96)::

4- አምልኮ እግዚአብሔር አምላክን መጠማት ነው (መዝ. 63)::

5- አምልኮ ለእግዚአብሔር ፈቃድ በመታዘዝ ምላሽ መስጠት ነው (መዝ 40:1-10)::

ይህን የመጀመሪያው ጥናታችንን ክፍል መዝ. 40:1-10 ከመጽሐፍ ቅዱስ በጣም ጠቃሚ በሆነውና ክርስቶስ ኢየሱስ በዮሐንስ 4:15-26 ስለ አምልኮ ባስተማረው አሳብ እናጠቃልላለን::

ጥናት አንድ

አምልኮ:- ለእግዚአብሔር በረከት የምስጋና ምላሽ

መዝሙር 103

ዓላማው:- ዳዊት እግዚአብሔርን እንዲያመሰግን ምክንያት የሆኑትን ብዙ በረከቶች ከመዝሙር 103 በመመልከት÷ ከእግዚአብሔር የተቀበልናቸውንና ወደ አምልኮ ሊመሩን የሚችሉትን ብዙ በረከቶች ለማሰላሰል እንድንችል ነው::

የዓላማው ማብራሪያ:- አምልኮ እግዚአብሔር ባደረገልን ነገር ልብን ከሞላው አክብሮትና ምስጋና ይመነጫል:: በመዝሙር 103 ዳዊት ከእግዚአብሔር የተቀበላቸውን በርካታ በረከቶች ይዘረዝራል:: ዳዊት የእግዚአብሔርን በረከቶች በቆጠረ መጠን እርሱን በማክበር ምላሹን ይሰጣል:: ከዳዊት ልምምድ እግዚአብሔር ለእኛ የሰጣቸውን ብዙ በረከቶች ልናስታውስና ልንቆጥር እንችላለን:: ይህ ደግሞ እግዚአብሔር ለእኛ ስላሳየው በጐነት በአክብሮትና በምስጋና የአምልኮ ምላሻችንን እንድንሰጥ ያደርገናል::

አቀራረብ:- ብዙ ጊዜ ሰዎች ተስፋ ቆርጠው በኃዘን ይዋጣሉ:: ስለዚህ እግዚአብሔርን ማምለክ እንደማይችሉ ይሰማቸዋል:: ሰዎችን ደስተኛ እንዳይሆኑና ተስፋ እንዲቆርጡ

የሚያደርጋቸው ምንድን ነው? ተወያዩበት:: በዛሬው ትምህርታችን ከእግዚአብሔር ስላገኘነው ብዙ በረከት የማስታወስን ጥቅም ማለትም በረከታችንን በመቁጠር እግዚአብሔር ያደረገልንን ነገር ለማየት እንሻለን:: ይህ ደግሞ እግዚአብሔርን ለማክበርና ስላሳየንም በጐነት ለማመስገን እንድንፈልግ ይመራናል::

መዝ. 103ን አንብቡ::

1- **በመዝሙር 103:1-2÷ 20-22 ተደጋግሞ የሚታየው የትኛው ሐረግ ነው?** ("እግዚአብሔርን አመስግኑ" ወይም በጥንቱ መጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም "እግዚአብሔርን ባርኩ")::

2- **ዳዊት "እግዚአብሔርን አመስግኑ" ሲል ምን ማለቱ ነው? (103:1-2):: ሰው እግዚአብሔርን ሊያከብር የሚችለው እንዴት ነው?** እግዚአብሔር ሕዝቡን ሲባርክ እርሱን በማክበር ምላሽ እንሰጣለን:: ይህም ማለት ወንዶችና ሴቶች እግዚአብሔርን ያከብራሉ÷ ምስጋናም ያቀርባሉ.:: ወንዶችና ሴቶች እግዚአብሔርን በሚባርኩበት ጊዜ በእነርሱ ላይ ያፈሰሰውን መልካም ነገር እያሰቡ ነው:: አክብሮትና ምስጋና ለእግዚአብሔር የሚቀርበው እግዚአብሔር ለሕዝቡ ከሰጠው ብዙ በረከት የተነሣ ነው::

3- **መጽሐፍ ቅዱስ "በረከት" ሲል ምን ማለቱ ነው? ተወያዩበት::** በረከት እኛ ሳይገባን ከእግዚአብሔር በቸርነት የሚደረግ ስጦታ ነው:: **አንድ ሰው ሌላውን እንዴት መባረክ ይችላል?** መባረክ ማለት በቸርነት መስጠት÷ ጥሩ ነገር መሰጠት÷ ጥቅምን ማበርከት÷ እና በረከትን ለሌሎች ማስተላለፍ ማለት ነው:: አብዛኛውን ጊዜ ታላላቆች በሥራቸው ወይም በሥልጣናቸው ሥር ያሉትን ይባርካሉ:: እግዚአብሔር ወንዶችና ሴቶችን ይባርካል - ወላጆች ደግሞ ልጆቻቸውን::

4- **አንደ መዝሙር 103:1-2 አገላለጽ÷ ዳዊት እግዚአብሔርን ያከበረው እንዴት ነበር?** ዳዊት እግዚአብሔርን በነፍሱ አከበረ:: ይህም ማለት "በሁለንተናው ተሰጥቶ" አከበረ ማለት ነው:: ነፍስ የአንድን ሰው ሁለንተና ይወክላል:: ዳዊት እግዚአብሔርን በግማሽ ልቡ ብቻ አላመሰገነም:: ዳዊት ባለው ነገር ሁሉ እግዚአብሔርን አመሰገነ:: የማስታወስ ችሎታውን በመጠቀም እግዚአብሔር ያደረገለትን ማንኛውንም መልካም ነገር ባለመርሳት የሆነለትን በረከት ሁሉ አስታወሰ::

5- **ባለፈው አሑድ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እግዚአብሔርን እንዴት አመለክህ? በሙሉ ነፍስህ÷ በሙሉ**

ልብህ፥ ከሕይወትህ ውስጠኛው ክፍል ባለህ ነገር ሁሉ ወይስ እንዴት አመለክህ? ተወያዩበት::

6- **በመዝሙር 103:3-7 ባለው ክፍል ዳዊት ለራሱ ያስታወሳቸውን የእግዚአብሔር በረከቶች ዘርዝር?** እግዚአብሔር ይቅር አለው:: ደግሞም ፈወሰው (ቁ. 3):: እግዚአብሔር ምሕረቱንና ፍቅሩን በማሳየት ጠበቀው (ቁ. 4):: ጥሩ ነገሮችንና የውስጥ መታደስን /ቁ. 5/፥ ፍትህ ያለበትንና ትክክለኛውን ነገር አደረገ (ቁ. 6-7)::

7- **በምን ዓይነት መንገድ ነው የንስር ሕይወት የሚታደሰው?** (መዝ. 103:5):: ንስር እንደ ብዙዎች ወፎች አሮጌውን ላባ በየዓመቱ እያስወረደ አዲሶቹን በቦታው ያበቅላል:: በዚህ መንገድ ንስር በየዓመቱ ይታደሳል ማለት ነው:: ንስር ረጅም እድሜ ይኖራል:: አንዳንዶች እንዲያውም እስከ 100 ዓመት ድረስ ይኖራሉ:: ስለዚህ የወፎች ንጉሥ የሆነው ንስር በየዓመቱ የሚታደስና ረጅም እድሜም የተሰጠው ነው:: ይህም ጨርሶ ሳይጠፋ ተሃድሶ እንደሚያገኘው የእስራኤል ሕዝብ ምሳሌ ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ "በወጣትነት ጸናሁ እንደ ንስርም ጠንካራ ሆንሁ" ይላል::

8- **እንዴት ነው ሴቶችና ወንዶች (ሰዎች) በሕይወታቸው ተሃድሶ የሚያገኙት?** (103:5) እግዚአብሔር ያደረገላቸውን መልካም ነገር በማስታወስና እግዚአብሔር ፍላጐታቸውን እንዴት እንዳረካላቸው በማስታወስ ነው::

9- **ሁልጊዜ ተስፋ በሚቆርጥ፥ በማያመሰግን፥ ደስተኛም በማይሆን ኑሮ ከባድ እንደሆነና እግዚአብሔር እንዳልባረከው በሚሰማው ሰው ምን ይደርስበታል?** አስተሳሰቡ ጤናውን ያናጋል:: ተሃድሶ በማግኘት ፈንታ የማቆምና የመተው ነገር ይሰማዋል:: ይህ ደግሞ ጤናውን ሊነካ ይችላል:: ሰለሞን ከብዙ ዓመት በፊት በምሳሌ 17:22 ላይ "ደስ ያላት ልብ መልካም መድኃኒት ናት፤ ያዘነች ነፍስ ግን አጥንትን ታደርቃለች"(የ1962 የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም) ሲል ይህን ተረድቶአል:: በረከት መቁጠር ለእግዚአብሔር ክብርን ብቻ የሚያመጣ ሳይሆን፥ ነገር ግን በውስጥ ሰውነታችን፥ በአእምሮአችንና በስሜታችን፥ በውስጥ መንፈሳችንም ጭምር ተሃድሶን ያመጣል:: እግዚአብሔር ያደረገልህን ነገር ሁሉ በምታስታውስበት ጊዜና ስለዚህም ስታመሰግን የውስጥ አካላዊ ተፈጥሮህ እንደ ንስር ይታደሳል::

10- **እንደ መዝ. 103:8-14 አሳብ ለዳዊት የተደረገለትን መለኮታዊ ስጦታ ግለጽ::** የእግዚአብሔር ኀዘኔታ፥ ጸጋና ፍቅር ታላቅ ነው:: የእግዚአብሔር ፍቅር አይለካም:: የት ነው ምሥራቅ ምዕራብን የሚገናኘው? (103:12):: ሰማያት የቱን ያህል ከፍ ያሉ ናቸው? (103:11) እግዚአብሔር እንደ ሥራችን አይቀጣንም::

11- **የእግዚአብሔር ፍቅር መወዳደር የማይገባው ከምን ጋር ነው?** (103:15-18) የእግዚአብሔር ፍቅር የተነጻጸረውስ ከምን ጋር ነው? (103:15) የሰዎች ሕይወት ከእግዚአብሔር ፍቅር ጋር ተነጻጽሮአል:: ለምንድን ነው ግን የእግዚአብሔር ፍቅር ከሰዎች ሕይወት ጋር ያልተወዳደረው? ምክንያቱም የሰው ሕይወት እንደ ምድር አበባ ነው:: ከሰዎች አጭር ሕይወት ጋር ሲነጻጸር የእግዚአብሔር ፍቅር ዘላለማዊ ነው:: እግዚአብሔር ሁልጊዜ ዘላለማዊ ኪዳኑን ማለትም ከሕዝቡ ጋር ያደረገውን ስምምነት ይጠብቃል :: የሰጠውንም ተስፋ ሁልጊዜ ያስታውሳል (103:18)::

12- **በመዝ. 103:19 ላይ ከሚገኘው እውነት ምን ጥቅም እናገኛለን?** እግዚአብሔር አምላክ የጌቶች ጌታና የነገሥታት ንጉሥ ነው:: የእግዚአብሔር ዙፋን በሰማያት ያለ በመሆኑ በምድር ሁሉ ላይ ይገዛል:: ከዚህም የተነሣ በሚወደን አምላካችን ጥበቃና ቁጥጥር ሥር ነን:: በአጋጣሚ በተገኘ ዓለም ውስጥ አለመኖራችን እና በእግዚአብሔር ከጥፋትና ጉዳት መጠበቃችን እንዴት ዓይነት መባረክ ነው:: ኃይል ሁሉ የእግዚአብሔር ስለሆነ ጥንቆላ የሚሠሩትንም ልንፈራ አይገባም::

13- **ማግኘት ሳይገባው እግዚአብሔር በእርሱ ላይ ስላፈሰሰው ብዙ በረከት የዳዊት ምላሽ ምንድን ነው?** (103:20-22) ዳዊት እግዚአብሔርን ብቻ አላከበረም፥ ነገር ግን ሁሉን ሰውና ማንኛውንም ነገር እግዚአብሔርን እንዲያከብሩ ጥሪ ያቀርባል:: መላእክቶቹን፥ የሰማይ ሠራዊቶችን፥ ባሪያዎቹንና በየስፍራው የሚገኙትን የእግዚአብሔርን ሥራዎች በሙሉ::

14- **ባለፉት ጥቂት ዓመታት እግዚአብሔር አንተን የባረከበትን ነገር ለመዘርዘር (ለማሰብ) ጥቂት ጊዜ ውሰድ::** (ሁሉም መጻፍ ከቻሉ በረከታቸውን ለማሰብና በወረቀት ላይ ለመጻፍ እንዲችሉ ጥቂት ደቂቃዎች ስጣቸው:: መጻፍ ካልቻሉ ደግሞ እግዚአብሔር የሰጣቸውን ብዙ በረከት ለሌሎች ለማካፈል በቂ ጊዜ ይኑራቸው::)

15- እግዚአብሔር ያደረገልህን በረከት ሁሉ ስታሰብ ስለ እርሱ በልብህ ምን ይሰማሃል? ተወያዩበት። በተፈጥሮአችን አመስጋኝ ልንሆን ይገባል። እግዚአብሔር ስለሰጠን በረከት ክብርንና ምስጋናን እየሰጠን በፊቱ በአምልኮ መንፈስ ልንሰግድ ይገባል።

16- ለምን ይመስላችኋል ዳዊት "በረከቱን ሁሉ አትርሱ" በማለት መዝሙሩን የጀመረው? በተፈጥሮ አመስጋኝ ያለመሆን ዝንባሌ እናሳያለን። የእግዚአብሔርን በረከት እንዳናደንቅና እንዳናመሰግንም እንቸገራለን። ለተሰጠን በረከት ሁሉ እግዚአብሔርን እያከበርንና እያመለክን ለመሆናችን እንዴት እርግጠኛ መሆን እንችላለን? ስለ እግዚአብሔር በረከትና ሰጥታ ያለማቋረጥ ራሳችንን ለማስታወስ መቻል አለብን። በረከቱን ያስታወስን ጊዜ ብቻ ነው እርሱን ማምለኩና ማክበሩም ትውስ የሚለን።

17- ሰዎች በመዝሙርና በጸሎት ለማምለክ እንዲችሉ ለመርዳት አንተና ቤተ ክርስቲያንህ ምን ማድረግ ትችላላችሁ? ተወያዩበት። ባለፈው ሳምንት ውስጥ ሰዎች ስላገኙት በረከት በቤተ ክርስቲያን ጉባኤ ለሌሎች የማካፈል ዕድል ቢያገኙ አድማጮች እግዚአብሔርን ለማመስገን ይደፋፈራሉ።

18- በየዕለቱ በቤትህ እንድትጸልይና ቃሉን እንድታነብ የሚሰማህ ነገር አለ? ተወያዩበት። ሥራ በበዛበት ዕለት ብዙ ክርስቲያኖች ከጊዜ ወደ ጊዜ እግዚአብሔርን ለማምለክ እንዲችሉ ራስህን ለመርዳት ምን ማድረግ ይኖርብሃል? ተወያዩበት። በዚያ ዕለትና በዚያ ሳምንት እግዚአብሔር ስለሰጠህ በረከት ራስህን በማስታወስ ነው። ይህ እግዚአብሔር ለአንተ ስላሳየው በረከት በምላሹ እንድታከብረውና እንድታመሰግነው ፍላጐት እንዲኖርህ ሊያደርግህ ይገባል።

የእግዚአብሔርን ቃል ማድረግ፦ በየዕለቱ ከልብህ አምልኮና ምስጋና በርግጥ ይፈልቅ እንደሆነ ሕይወትህን ተመልከት። ይህ ባይሆን ችግሩ እግዚአብሔር ስለሰጠህ በረከት በየዕለቱ ሕይወትህን ለማስታወስ ሳትችል ቀርተህ ይሆን? እግዚአብሔርን ልታከብር የምትችልበትን ቢያንስ አምስት ነገሮች አሁን ለማሰብ ሞክር።

ጸሎት፦ እግዚአብሔር በሕይወታችሁ ስላደረገው ብዙ በረከት በማስታወስ እግዚአብሔርን በጸሎት መንፈስ እያመለካችሁና

እያከበራችሁ በቡድን ሆናችሁ ጥቂት ጊዜ ውሰዱ። መዝ. 116፡12-19 ያለውን ክፍል በአንድነት በማንበብ ፈጽሙ።

ጥናት ሁለት

አምልኮ፦ በፍጥረት ሥራ ውስጥ የእግዚአብሔርን ታላቅነት በማሰብ የመገረምና የመደነቅ ምላሽ

መዝሙር 29

ዓላማው፦ እንደ መዝሙር 29 አገላለጽ፥ ዳዊትን ወደ አምልኮ የመራውን የእግዚአብሔርን ታላቅነትና ኃያልነት በማሰብ፥ የእግዚአብሔርን የመፍጠር ታላቅ ኃይል በምናሰብበት ጊዜ እያንዳንዱ ለው በአድናቆትና በመገረም በፊቱ እንዲሰግድ ለማደፋፈር ነው።

የዓላማው ማብራሪያ፦ ተፈጥሮ ሰዎች እንዲደነቁ ወይም እንዲፈሩ ያደርጋቸዋል። ባለፉት ጊዜያት ሰዎች በዓለማችን ከፍጥረት የሚገኙትን የተለያዩ አካላት አምልከዋል። ለምሳሌ፦ ፀሐይ ወይም ጨረቃ ወይም በዛፍና በተራራ ላይ የሚኖሩትን ያልታወቁ መናፍስት ወይም ደግሞ ራሳቸውን በማዕበልና በደቄ የገለጹትን መናፍስት አምልከዋል። ሰዎች ሲፈሩና የምስጢንነት ስሜት ሲለማቸው እነዚህን በተፈጥሮ የሚገኙትን ኃይላት ወይም መናፍስት ለማምለክ ተገድደዋል። ይህ በትክክል ኃጢአት ነው።

ነገር ግን እግዚአብሔር ራሱን ለእኛ ሲገልጥ ፍጥረትን ተጠቅሞአል። እግዚአብሔር መንፈስ ነው። በማንም ሊታይ አይችልም። ነገር ግን እግዚአብሔር ኃይሉንና ክብሩን በፍጥረት ያሳያል። ፍጥረት የእግዚአብሔርን ታላቅነት የሚገልጥ ነገር ያቀርብልናል። ዳዊት የእግዚአብሔርን ታላቅነት በፍጥረት ውስጥ በሚመለከትበት ጊዜ ሁሉም ሰው እግዚአብሔርን እንዲያመልክ ጥሪ ያቀርባል። እኛም እንኳን ዛሬ በእግዚአብሔር ክብር ፊት በመገረምና በአድናቆት ልንሰግድ ይገባናል።

የትምህርቱ አቀራረብ፦ በሕይወታችን ዘመን ከጊዜ ወደ ጊዜ፥ በተፈጥሮ ውስጥ የተለያዩ ነገሮችን እንመለከታለን። እነዚህም ነገሮች እግዚአብሔርን በኃይሉና በታላቅነቱ ሁሉ እንድናስበው የሚያደርጉን ናቸው። ምናልባት ኃይለኛ ነጐድጓድ ወይም የሕንድ ውቅያኖስ የመጀመሪያ ዕይታችን ወይም ታላቅና ሰፋፊ ሸለቆዎችና

ተራሮች ወይም በምሽት ጊዜ በሰማይ ላይ የሚታዩት ከዋክብት ሊሆኑ ይችላሉ። በተፈጥሮ (በፍጥረት) እንድትፈራና እንድትደነቅ ስላደረጉህ ቀደምት ልምምዶችህ መጠነኛ ገለጻ አድርግ። ከፍጥረት በአንድ ነገር መገረምና መደነቅ ወይም የእግዚአብሔር ፍርሃት ተሰምቶህ ያውቃል? ተወያዩበት። ዛሬ በፍጥረት ታላቅ በሆነው ጌታ ፊት የመገረምና የመደነቅ ምላሽ ስለሆነው አምልኮ ልናጠና እንሻለን።

መዝሙረ ዳዊት 29ን አንብቡ።

1- **የዚህ መዝሙር ጸሐፊ የሆነውን መዝሙረኛ ለአምልኮ ያነሣሣው ሁኔታ ምን ነበር?** 29:ከ3-9 ያለው ከፍል ስለ ኃይለኛ ነጐድጓድ ይገልጻል። አስፈሪና ትልቅ ነጐድጓድ በሚኖርበት ጊዜ አንዳንድ ሰዎች ምን ይሰማቸዋል? ምንስ ያደርጋሉ? ተወያዩበት። ይህ መዝሙር እማኞች ምን ያደርጉ ዘንድ ያደፋፍራቸዋል? ተወያዩበት። (23:9) የነጐድጓድ ድምፅ በሚኖርበት ጊዜ ከኃይሉ የተነሣና በፍጥረት ጥፋት ሰዎች እግዚአብሔርን እንዲያከብሩ፥ እንዲያመሰግኑና እንዲያመልኩ ጥሪ ቀርቦላቸዋል።

2- **በቁጥር 3-9 ባለው ክፍል ስለ ኃይለኛ ነጐድጓድ በሚናገሩት ቃላት ወይም ሐረግ ላይ ተወያዩ**:- በቁጥር 3 ላይ ስለሚገኘው ነጐድጓድ ትንሽ የተባለ ነገር አለ ("የክብር አምላክ አንጐዳጐደ")። ከዚያ በኋላ "የእግዚአብሔር ድምፅ" የሚል ሰባት ጊዜ እናነባለን። (ስለዚህ መዝሙር 29 "የሰባት ነጐድጓድ መዝሙር" በመባል ሊጠራ ይችላል።) መብረቁ ነፋሱን (አየሩን) ሲሰነጥቅና በሽለቆም ውስጥ እየተንከባለለ ሲወርድ እግዚአብሔር ከነጐድጓድ በስተኋላ ይታያል። ነጐድጓድ በእርግጥ የእጅ ሥራው እንጂ የእግዚአብሔር ድምፅ አይደለም። ነገር ግን ነጐድጓድ ነጐድጓድን የፈጠረውን ታላቁን ጌታ ያስታውሰናል። በቀላሉ ነጐድጓድ የእግዚአብሔር ድምፅ መግለጫ ነው። "የእግዚአብሔር ድምፅ" በታላቅ ሞገስ የተሞላ ነው (29:4)። መብረቅ በሰማይ ላይ በሚታይበት ጊዜም ድምፅ ይሰማል (29:7)።

3- **ነጐድጓድ በእስራኤል ምድር በሚያርፍበት ጊዜ ያለውን ሁኔታ ግለጽ** (29:3-9)። ቁጥር 3 እና 4 የነጐድጓድን አቀራረብ ይገልጻሉ። በቁጥር 29:3 ላይ የተጠቀሱት" "ውኆች" በምዕራብ በኩል ያለው የሜዲትራንያን ባሕር ወይም ዝናቡ በሚዘንብበት ጊዜ ጠረፉን ይዞ በኩረብቶቹ ሥር የሚወርደውን (ያለውን) የጐርፍ ውኃ ማለቱ ይሆናል። ዝቅና ዝግ እያለ

የሚወረወር ነጐድጓድ ከርቀት የነጐድጓድ ድምፅ እየመጣ መሆኑን ያሳያል (ቁ.3)። በቁጥር 4 ላይ ድምፅ ከፍ ባለ ነጐድጓድ እየተጠጋ መምጣቱን ነው። ከቁጥር 5-7 ሙሉ ድምፁን በከፍታ ቦታ ላይ መጀመሩን ይገልጻል። መብረቁ ከፍ ካለ ተራሮችንና ጫካዎችን "እንደ እምቦሣ እንዲዘሉ" በሚያደርግ ነውጥ ከነጐድጓዱ ድምፅ ጋር ያበራል። ቁጥር 8-9 ድምፅ ወደ ምሥራቅ እንደሚያልፍ ይገልጻል። ድምፁ በሚያልፍበት ጊዜ የተጨማተሩ ቅጠሎችንና የወደቁ ዛፎችን በጫካ ውስጥ በኋላው ያስቀራል (ቁ. 9 ሀ)።

4- **የነጐድጓድን ድምፅ በምናስብበት ጊዜ ቁ. 9 "ለ" ምን ይላል? "በመቅደሱ ሁሉም ክብር እያሉ ይጮሃሉ"**። ምድር ድንጋጤና ፍርሃትን በሰው ልብ እንደሚያመጣና የእግዚአብሔር ድምፅ እንደተሰማበት የእርሱ መቅደስ ትታያለች። ማንኛውም የነጐድጓድ ኃያልነት በቤተ መቅደስ ውስጥ (ይህም ምድር ማለት ነው) "ክብር" እያለ ምስክርነቱን ይሰጣል።

5- **መጽሐፍ ቅዱስ ክብር ብሎ በሚናገርበት ጊዜ ምን ማለቱ ነው?** (ቁጥር 1፥2፥3 እና 9 "ለ" ን ተመልከት።) በመጀመሪያ ደረጃ "ክብር" በእነዚህ ቁጥሮች መብረቅ ብርሃንና እንደ ብቋድ የሚተኮሰውን የነጐድጓድ ድምፅ ያመለክታል። ነገር ግን ከተፈጥሮአዊው ድምፅ በስተኋላ ብርሃን፥ ግርማ፥ መፈራትና ክብር የተሳባሰው የፈጣሪ እጅ ይታያል። ፈጣሪያችን ይህን በሚመስል መንገድ ውበቱንና ተደናቂነቱን በፍጥረቱ ይገልጻል።

6- የነጐድጓዱን ድምፅ በመግለጽ መዝሙረኛው በቁጥር 10 እና 11 ይደመድማል። እግዚአብሔር በእነዚህ ቁጥሮች የተገለጸው እንዴት ነው? ንጉሡ በዙፋኑ ላይ እንደሚቀመጥ እርሱ በጥልቅ ውኃዎች ተቀምጧል። (ከጥልቁ ውኃዎች በላይ ይገዛል።) ያም ማለት የነጐድጓድ ድምፅ የሚያዘው ጌታ አሁን ነው። እርሱ ሁልጊዜ የበላይ ነው። የነጐድጓድን ድምፅ በመጀመሪያ ያመጣል። አሁን ደግሞ ፍጻሜውን ያደርግለታል። ለሕዝቡ ብርታትና ሰላምን የሚሰጣቸው እርሱ ነው ።

7- **ሰዎች ሁል ጊዜ በፍጥረት ውስጥ የሚፈሩት ምንድን ነው?** ተወያዩበት። ብዙ ሰዎች መብረቅን፥ የተወሰኑ ወንዞችን፥ መናፍስትን፥ የጨረቃ ግርዶሽን፥ መጥፎ ዕድሎችን፥ ግዙፍ እባቦችን፥ ጠንቋዮችን ይፈራሉ። በታላቁ የፍጥረት ጌታ የሚታመኑ ክርስቲያኖች እነዚህን ነገሮች ሊፈሩ የማይገባቸው ለምንድን ነው? ተወያዩበት።

8- **የነጐድጓድን ድምፅ ከተመለከተ በኋላ ዳዊት**

ሕዝቡን የጠራቸው ምን እንዲያደርጉ ነው? (29:1-2)። ለእግዚአብሔር ክብርና ኃይል እንዲሆንና እንድናመልከውና እንድናከብረውም ይመክረናል።

9- ለእግዚአብሔር ክብርና ኃይል መስጠት የምንችለው እንዴት ነው?(29:1-2)። የእርሱን ታላቅ ኃይልና ክብር በፍጥረት ውስጥ ካየን በኋላ እርሱን በማክበርና እግዚአብሔር በርግጥ ክብርንና ኃይልን የተሞላ ነው በማለት ምላሽ እንሰጣለን። እግዚአብሔር አምልኮአችን ኃይሉንና ክብሩን መግለጽ እንዲጀምር ያደርጋል። እኛም ለክብሩና ለኃይሉ ምስጋናችንን በመስጠት አፀፋውን እንመልሳለን።

10- እግዚአብሔር የእኛ ምስጋናና ክብር ይገባዋል /29:2/። ለእግዚአብሔር የምስጋና ባለዕዳዎች ነን። **ለእግዚአብሔር ስም የሚገባውን ክብር ለመስጠት አለመቻላችን ስለ እኛ ምን ያስረዳል?** ተወያዩበት። በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር ማን እንደሆነና የቱን ያህል ታላቅ እንደሆነ ለመረዳት አቅቶናል ማለት ነው። እግዚአብሔር የምድር ሁሉ ጌታ መሆኑን መረዳት ያቃታቸው የሚያመሰግኑ ፍጥረቶች ሆነናል ማለት ነው። የነጐድጓድ እያንዳንዱ "ጭብጨባ" ለእግዚአብሔር ክብርን እንድንሰጥ ጥሪ ያቀርብልናል። በውስጣችን የአድናቆት መንፈስ ሳይሰማንና በፊቱ ከክብሩና ከኃይሉ የተነሣ ሳንፈራ እግዚአብሔር ራሱን በገለጸበት ዓለም ውስጥ እንዴት ልንኖር እንችላለን?

11- **ዳዊት "በቅድስና ማደሪያ ለእግዚአብሔር ስገዱ" ሲል ምን ማለቱ ነው?**(29:2)። እግዚአብሔር አምላክ ቅዱስ ነው። ይህም ማለት ፈጣሪያችን በጣም ከፍ ያለና ከፍጥረቱም ሁሉ ራሱን የለየ ነው ማለት ነው። እርሱ በግርማውና በአስደናቂ ሁኔታ ይኖራል። እግዚአብሔር ከኃጢአት ሁሉ የራቀ ንጹሕና ጻድቅ ነው። የነጐድጓድ ድምፅ በመዝሙር 29 ላይ እግዚአብሔር ግርማውንና ኃይሉን የሚገልጽበት መንገድ ነው። እኛ በእግዚአብሔር ፊት ልንሰግድ እና ለእርሱ የሚገባውን አክብሮት፥ ምስጋናና ክብር ልንሰጥ ተጠርተናል።

12- **በመዝሙር 29 የተገለጸው አምልኮ በመዝሙር 103 ከተገለጸው ጋር በምን ይለያል?** በመዝሙር 103 ላይ ዳዊት እግዚአብሔር ስለሰጠው ብዙ በረከት ያስታውሳል። ስለ እነዚህ በረከቶች ከልቡ የመነጨ የአክብሮትና የምስጋና መንፈስ ነበረው። በመዝሙር 29 ከነጐድጓድ ድምፅ የተነሣ በመገረምና በፍርሃት እንደዚሁም በአክብሮት ተነሣሣ። እግዚአብሔርን

ከግርማው፥ ከኃይሉና ከክብሩ የተነሣ በመገረም፥ በአድናቆትና በቅዱስ ፍርሃት ልናመልከው ተጠርተናል።

በመዝሙር 103 የእግዚአብሔር በረከት በላያችን ከመፍሰሱ የተነሣ ለእርሱ ክብርን እንሰጣለን። በመዝሙር 29 ከቅድስናው፥ ከግርማውና ከኃይሉ የተነሣ ለእግዚአብሔር ክብርን እንሰጣለን።

የእግዚአብሔርን ቃል መፈጸም፦ ሕይወትህን መርምር። ከቅድስናው፥ ከግርማውና ከኃይሉ የተነሣ ለእግዚአብሔር ስም የተገባውን አምልኮና ምስጋና ትሰጣለህ? ለምሳሌ፥ ጥሩ ዝናብ በመስጠት እግዚአብሔር ራሱን በፍጥረቱ ውስጥ ስለገለጠ የአምልኮ ምላሽ ትሰጣለህ? ስለ ግርማውና ስለ ቅድስናው በዚህ ሳምንት ውስጥ እግዚአብሔርን በመደነቅ ልታመልከው ወስን።

ጸሎት፦ በፍጥረትና በመጽሐፍ ቅዱስ እንደተገለጠው ስለ ታላቅ ግርማውና ስለ ቅድስናው ምስጋና በማቅረብ፥ ክብርን በመስጠት፥ በአምልኮና በጸሎት መንፈስ በፊቱ ለመሰገድ በቡድን ጊዜ ውሰዱ።

ጥናት 3

አምልኮ፦ ደስታን ባዘለ የቅድስና ፍርሃት ወደ እግዚአብሔር የመቅረብ ምላሽ

መዝሙር 96

ዓላማው፦ እንደ መዝሙር 96 አሳብ፥ ለእግዚአብሔር ደስታ በተሞላበት ምስጋናና ቅዱስ ፍርሃት አምልኮ የማቅረብን አስፈላጊነት ለመመልከት ነው።

የዓላማው ማብራሪያ፦ በአሁኑ ጊዜ አንዳንድ ሰዎች ስለ እግዚአብሔር ፍቅርና ጸጋ ብቻ ከሚገባው በላይ ስለተነገራቸው፥ በአምልኮአቸው ሁሉ በዚህ ላይ ያተኩራሉ። አምልኮ ስለ እግዚአብሔር ፍቅርና እርሱም ስላሳየን በጐነት ምስጋና በተሞላበት ደስታ ዝማሬንና ምስክርነትን ያጠቃልላል። ነገር ግን ስለ ግርማው፥ ስለ ታላቅነቱና ስለ ፍትሐዊነቱ እግዚአብሔርን ልናመልክ ይገባል። በቅዱስ ፍርሃት፥ በአክብሮትና በመንቀጥቀጥ ልናመልከው ይገባል። ደስታ የተሞላበትን አክብሮት አስፈላጊነት፤ ስለ ፍቅሩና ስለ ቅዱስ መፈራቱ እንደዚሁም ስለ ታላቅነቱ አስረግጠን ልንናገር ይገባል።

የትምህርቱ አቀራረብ፦ የአፍሪካውያንን ባሕላዊ

የአምልኮ አመለካከት ከዘመኑ ክርስቲያኖች አምልኮ አስተሳሰብ ጋር አወዳድር ወይም አነጻጽር። አስተሳሰባቸው የሚመሳሰለውና የሚለያየው በምን መንገድ ነው? ተወያዩበት። ምናልባት ባሕላዊ አፍሪካውያን ለእግዚአብሔር ታላቅ አክብሮት ስላላቸው፥ በፊቱ በፍርሃትና በከበሬታ መንፈስ ይቀርባሉ። የባሕላዊ አምልኮ ቦታዎች ለአምልኮ ብቻ የተለዩ ናቸው። ሕፃናትና እንስሳት ወደ ቦታው እንዲቀርቡ አይፈቀድላቸውም። እግዚአብሔርን ይፈራሉ። ነገር ግን ክርስቲያኖች እግዚአብሔርን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በሚያመልኩበት ጊዜ እርስ በርሳቸው ይነጋገራሉ። ሕፃናቶቻቸው እንዲሯሯጡና ድምፅ እንዲያሰሙ፥ በጸሎትና ቃሉ በሚነበብበት ጊዜ ወጣ ገባ እያሉ እንዲረብሹ ይፈቅዱላቸዋል። አብዛኛውን ጊዜ በአፍሪካውያን ባሕላዊ አምልኮና በክርስቲያኖች አምልኮ መካከል ልዩነት ሊኖር የቻለው ለምንድን ነው? ምናልባት ባሕላዊ አፍሪካውያን በሚፈሩት አምላክ ታላቅነት ላይ ሲያተኩሩ፥ ክርስቲያኖች ግን በእግዚአብሔር ፍቅር ላይ በማተኮራቸው ምክንያት ("ምን ዓይነት ጓደኝነት ነው ያለን በኢየሱስ?") ታላቅነቱን ማሰብ አቅቶአቸው ይሆናል።

ዛሬ እግዚአብሔርን ስደስታ እያከበርነው እያለን በቅዱስ ፍርሃትና አክብሮት የማምለክን አስፈላጊነት ለማሰብ እንፈልጋለን።

መዝ. 96ን አንብቡ።

1- **ይህን መዝሙር በምታነቡበት ጊዜ መዝሙረኛው መልእክቱን የሚያስተላልፈው ለማን ነው?** እግዚአብሔርን እንዲያመሰግንና እንዲያመልክ የሚጠይቀው ማንን ነው? (96:1-9) "ምድር ሁሉ"፥ 96:3-10 "መንግሥታት"፥ 96:7 "የአሕዛብ ወገኖች"። ዳዊት ሕዝቡን ሁሉ፥ አሕዛብና የአይሁድ ወገኖች እግዚአብሔርን እንዲያመልኩ ጥሪ ያቀርባል።

2- **ከቍጥር 1-3 ባለው ክፍል ምን እንድናደርግ ነው የታዘዝነው?** የእግዚአብሔርን ስም አክብሩ፤ ክብሩንም በአሕዛብ መካከል አውጁ።

3- **ይህን እንድናደርግ የታዘዝነው ለምንድን ነው?** (96:4) ምክንያቱም እግዚአብሔር ታላቅ ስለሆነና አክብሮታችንም ስለሚገባው፥ እንደዚሁም ከአማልክት በላይ መፈራት ስለሚገባው ነው።

4- **ከአማልክት ሁሉ በላይ እግዚአብሔርን የምንፈራው ለምንድን ነው?** (96:5-6) በሁለት ምክንያቶች ነው። 1ኛ/

ምክንያቱም ሌሎች አማልክት ሁሉ ጣዖታት ስለሆኑ ነው። 2ኛ/ እግዚአብሔር ብቻ ፈጣሪ ስለሆነ ነው።

5- **እነዚህ ሌሎች አማልክት እነማን ናቸው?** (96:5)እንደ እውነተኛ አምላክ በሕይወት የሚኖሩ አይደሉም። በዚህ ቦታ ያገለገለው የዕብራይስጥ ቃል "በሕይወት የሌሉ ነገሮች" ይላቸዋል። በሌላ በኩል ደግሞ ራሳቸውን አምላክ የሚያደርጉና ሰዎችን ወደ ፍርሃት የሚመሩ ርኵሳን መናፍስትን ይጠቅሳል፤ ማለትም በሰዎች ልብ ፍርሃትን በመጨመር ከእግዚአብሔር ይልቅ እንዲያገለግሉአቸውና እንዲያመልኩአቸው የሚያደርጉ ርኵሳን መናፍስት ናቸው። እነዚህ አማልክት እንደ አውነተኛ አምላክ አይኖሩም። ሆኖም ግን ሰዎችን እንደሚያስጨንቁ ርኵሳን መናፍስት ሆነው ይኖራሉ።

6- **አፍሪካውያን ጥንት ያመልኩት የነበረው አምላክ እውነተኛ አምላክ ነበር ወይስ በቍጥር 5 እንደተጠቀሱት ከሌሎች አማልክት አንዱ ነበር?** አፍሪካውያን የእውነተኛው አምላክ እውቀት ነበራቸው። ነገር ግን በኃጢአት ምክንያት ስለ እርሱ ግልጽ የሆነ መረዳት አልነበራቸውም። እንደዚሁም ለፈጣሪ አምላክ የሚሰጡትን አምልኮ፤ ክብር ከተሰጣቸው ከሌሎች አማልክት አምልኮ ጋር ይቀያይጡ ነበር። አብዛኛውን ጊዜ በመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም የክርስቲያን አምላክ ስም ከአፍሪካውያን ባሕላዊ ስያሜ ጋር ተመሳሳይ ነው። አፍሪካውያን ስለ ፈጣሪ አምላክ እውቀት አላቸው። ነገር ግን አንዳንድ ጊዜ በአፍሪካውያን ቋንቋ አማልክት የሚባሉትን ሌሎች አካላት በተጨማሪ ያገለግሉ ነበር። እነዚህ መናፍስት ብዙ ሰዎችን አታልለዋል፤ ለእነርሱ መሥዋዕት እንዲያቀርቡና እንዲያከብሯቸውም አድርገዋል።

7- **እግዚአብሔርን እንጂ አማልክትን ልንፈራ የማይገባን ለምንድን ነው?** (96:4-6)፤ ምክንያቱም ሰማይንና ምድርን የፈጠረው እግዚአብሔር አምላክ ብቻ ነው ፤ ልንፈራ የሚገባን እርሱን ብቻ ነው። ነገር ግን እነዚህ የወደቁ ርኵሳን መናፍስት የተወሰነ ኃይል ያላቸው ፍጥረት ናቸው፤ ከእግዚአብሔርም ፍርድ በታች ናቸው። እግዚአብሔር አምላክ በሰማይና በምድር ላሉት ሁሉ ፈጣሪ ስለሆነ እርሱ የሁሉ በላይ ነው፤ እርሱ ሁሉን ቻይና ብቸኛ፥ እውነተኛ ሕያው አምላክ ነው (መዝ. 24:1-2)። መናፍስትን መፍራት የለብንም፤ ምክንያቱም ፈጣሪ አምላክ ኃይል ሁሉ አለው። እነዚህ መናፍስትም በእርሱ ሥልጣን ሥር ናቸው።

8- **እግዚአብሔርን እንድንፈራው ስንታዘዝ መጽሐፍ ቅዱስ ምን ማለቱ ነው?** (96:45ን እና ምሳሌ 1-7ን አወዳድሩ)። "የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው።" እግዚአብሔርን መፍራት እግዚአብሔርን ማክበር ነው፤ በፊቱ አክብሮት በሞላው ፍርሃት መቆም ነው፥ ሰነፎችን የሚቀጣውን ኃይሉን መፍራት ነው። በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአትን ላለመሥራት "መፍራት" አለብን። እግዚአብሔርን መፍራት ኃጢአትን መጥላት ነው (ምሳሌ 8:13)።

9- **ነገር ግን እግዚአብሔርን ማፍቀር ካለብን ልንፈራው የሚገባው ለምንድን ነው?** ልጆች አባታቸውን ማፍቀርና መፍራት አለባቸው። ፍቅርና ፍርሃት እርስ በርሳቸው የማይገናኙ አይደሉም። አባታችንን ከፍቅሩና ከመልካምነቱ የተነሣ እንወደዋለን። ነገር ግን እንዳንታዘዘው ደግሞ እንፈራለን። ምክንያቱም በእኛ ላይ ካለው ኃይልና ሥልጣን፥ ከፍቅሩና ከበጐነቱ፥ ከጻድቅነቱና ከቅድስናው የተነሣ እርሱ በጣም አስደናቂ ስለሆነ እግዚአብሔርን እንወደዋለን። ነገር ግን እንፈራዋለን፤ ከልብ እናከብረዋለን፤ በአክብሮትም በፊቱ እንቆማለን፤ ይህም ከታላቅነቱ፥ ከግርማውና ከቅድስናው የተነሣ ነው።

10- **እንደ ቁጥር 7 እና 8 አገላለጽ፥ እንዴት እናምልከው?** ለእግዚአብሔር ስም የሚገባውን ክብር ልንሰጠው ይገባል፤ ወደ መቅደሱም ስንገባ መሥዋዕት ልናመጣለት ይገባል።

11- **ክብርና ኃይልን ለእግዚአብሔር እንዴት መስጠት እንችላለን? እግዚአብሔር ክብርና ኃይል ቀድሞውኑ የለውም ወይ?** ተወያዩበት። የሰዎች ዋነኛ መጨረሻ እግዚአብሔርን ማክበር ነው። ፍጥረት እንኳን የእግዚአብሔርን ክብር በሚናገርበት ጊዜ እኛማ እንዴታ? ታላቅነቱን፥ እንዴት ታማኝና እውነተኛ እንደሆነ እና በሕይወታችን እንዴት አስገራሚ እንደነበር በምንናገርበት ጊዜ ለእግዚአብሔር ክብር እየሰጠን ነው። በቃል ይሁን በዝማሬ ስንመስክር ለእግዚአብሔር ስም የሚገባውን ክብር እየሰጠን ነው።

12- **አይሁዳውያን እግዚአብሔርን በቤተ መቅደስ በሚያመልኩበት ጊዜ ምን ዓይነት መሥዋዕት ነው ያመጡለት?** (96:8) የተለያየ የእንስሳት መሥዋዕት፥ የእህል በኩራት፥ የመጠጥ መሥዋዕት ይዘው ይመጣሉ። ባሕላዊ አፍሪካውያን ለአምልኮ በሚመጡበት ጊዜ የሚያቀርቡት መሥዋዕት ምን ዓይነት ነው? ተወያዩበት። አብዛኛውን ጊዜ

ለመሥዋዕትነት የሚያቀርቡት እንስሳትን ነው። ዛሬ እንደ ክርስቲያኖች እንስሳትን ለመሥዋዕትነት አናቀርብም። ዛሬ ለእግዚአብሔር ልናቀርብ የምንችለው ምን ዓይነት መሥዋዕት ነው? ተወያዩበት። በመጀመሪያ ደረጃ ስውነታችንን ለእግዚአብሔር ማቅረብ አለብን (ሮሜ 12:1)። እንደዚሁም የተሰበረውንና የተዋረደውን የንስሐ መንፈስ ያለውን ልባችንን ማቅረብ ይገባናል [መዝ. (51):17]። ዝማሬያችንን፥ የምስጋና ምስክርነታችንንና አምልኮአችንን ወደፊቱ ይዘን እንመጣለን (95:1-6)። ለእግዚአብሔር የምስጋና መሥዋዕት እናቀርባለን። በምንዘምርበት ጊዜ ወይም ምስጋና እያቀረብን ስንመሰክር (መዝ. 116:17)፥ አሥራታችንን፥ መሥዋዕታችንን፥ የሰብላችንን በኩራት፥ ለእኛ የሰጠውን መልካም ነገር በእትክልታችን ውስጥ ያለውን አበባ ሳይቀር፥ ሁሉን ዓይነት ዘርና እንስሳ፥ በሌቶችና በወንዶች የተዘጋጀውን የእጅ ሥራ (ሚል. 3:8-12) እናመጣለን። መጋቢዎቻችንን በሚያስፈልጋቸው እየረዳን ስናከብራቸው እግዚአብሔርን አክብሮን ማለት እንችላለን (1ኛ ጢሞ.5:17-18)።

13- **አምልኮ ከእግዚአብሔር ታላቅነትና ቅድስና ጋር ይሄዳል** (96:9፤99:1-5)። ቅድስናውን በምናስብበት ጊዜ እግዚአብሔርን እንድናመልክ ለምን ጥሪ ይቀርብልናል? ተወያዩበት። ስለ እግዚአብሔር ቅድስና በምንናገርበት ጊዜ ታላቅነቱን፥ ከፍ ማለቱን፥ መከበሩንና ድንቅነቱን፥ ንጽሕናውን፥ ጻድቅነቱን፥ ኃጢአት ያልነካው አምላክ እንደሆነ ማሰባችን ነው። እግዚአብሔር በቅዱስነቱ በፊታችን ሲገለጽ ለሰሙ የሚሆነውን ክብር እየሰጠን ልንሰግድለትና ልናመልከው ይገባል።

14- **በመዝሙር 99:1-5 ያለውን አሳብ አንብቡ።** ስለ እግዚአብሔር የተነገሩ ዐረፍተ ነገሮችንና እንደ እግዚአብሔር ሕዝብ ለእርሱ ልንሰጥ የሚገባንን ምላሽ ዘርዝሩ። እግዚአብሔር እንደ ንጉሥ ይገዛል። ስለዚህ በፊቱ ልንፈራና ልንንቀጠቀጥ ይገባል። ይኸውም ስለፈራን ሳይሆን ነገር ግን ለእርሱ ካለን ታላቅ አክብሮት የተነሣ ነው። አምላካችን ታላቅ፥ ቅዱስ፥ ከፍ ያለ አድናቆትን የተሞላ ነው። ስለዚህ እርሱን ከፍ ከፍ ልናደርግ፥ ስሙንም ልናከብር ይገባል። እግዚአብሔር ፍትሕንና ጽድቅን ይወዳል። ስለዚህ ከፍ ከፍ ልናደረገውና ከእግሩ ሥር ሆነን ልናመልከው ይገባል።

15- **እንደ ክርስቲያን ዛሬ በእግዚአብሔር ፊት ልንንቀጠቀጥና ልንፈራ ይገባናል ወይ?** ከሆነስ በምን ዓይነት መንገድ ነው በእግዚአብሔር ፊት ልንንቀጠቀጥ የሚገባን? ክርስቶስ

ኢየሱስን እንደ ግል አዳኛቸው አድርገው ያልተቀበሉ ሰዎች ካልተናዘዙ በስተቀር ስለ ኃጢአታቸው ስለሚቀጡ እግዚአብሔርን ሊፈሩት ይገባል። ነገር ግን ደኅንነትን ካገኘህ ቅጣትን ያመጣብኛል ብለህ እግዚአብሔርን ልትፈራው አይገባም። እግዚአብሔር ምን ጊዜም እግዚአብሔር ነው - ታላቅ፥ ቅዱስና ድንቅ። ለክርስቲያኖችም ቢሆን "የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው።" በፊቱ ልንንቀጠቀጥና በመታዘዝ ልንፈራው፥ እንዳናሳዝነውም ልንጠነቀቅ ይገባናል። ምክንያቱም ስለምንወደውና ከልባችን ስለምናከብረው ነው።

16- **የዚህ መዝሙር የመጨረሻዎቹ ቁጥሮች ዋነኛ ትኩረት ምንድን ነው?** (95:11-13) ሐሴት ማድረግ፥ በደስታ ዝማሬዎች መምነሽነሽ ነው።

17- **በእግዚአብሔር ፊት መፍራትና መንቀጥቀጥን ጨምሮ በሚያስተምር መዝሙር መደሰትንና ሐሴት የማድረግን ትኩረት እንዴት በጥምረት ማየት ይቻላል?** ተወያዩበት። በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ስለ እግዚአብሔር ያለን መገለጥ ከአፍሪካውያን ባሕላዊ አምልኮ የተለየ ነው። እግዚአብሔር አምላክ ቅዱስና ፍቅር ነው፤ እርሱ በጣም ከፍ ብሎ ያለ ነው። ደግሞም ወደ ሕዝቡ በምሕረትና በፍቅር የቀረበ አምላክ ነው። እግዚአብሔርን በቅዱስ ፍርሃት እንወደዋለን፤ በታላቅነቱ ደስ ይለናል። ልናመልከው በእግሩ ሥር ተደፍተን እያለን እንኳን በሚያስደስት መታመን እንደገፍበታለን፤ ሳንታዘዘው እንዳንቀር እየፈራን ሳለን እንኳን በደስታ እንታመንበታለን።

የእግዚአብሔርን ቃል ማድረግ፦ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በአንተና በሌሎች ክርስቲያኖች የሚካሄደውን አምልኮ አስብ። እግዚአብሔርን ደስ ከማሰኘት ጋር በልባዊ ፍርሃት ታመልከዋለህ? በአምልኮህ ጊዜ ለእግዚአብሔር ጤናማ የሆነ ልባዊ አክብሮት አለህ? በእሑድ ጠዋት አምልኮ ክፍለ ጊዜ ሰዎች የእግዚአብሔርን ማንነት ይለያሉ? የምታመልከውንስ አምላክ ቅዱስና ታላቅነት ይቀበላሉ? ካልሆነስ ስለዚህ ምን ታደርጋለህ? ጌታን በደስታና በምስጋና በምታመልክበት ጊዜ እንኳን በልባዊ አክብሮትና በመለኮታዊ ፍርሃት እንዴት ማደግ እንደሚቻል መወሰድ ስለሚገባቸው እርምጃዎች እርስ በርሳችሁ ተወያዩ።

ጸሎት፦ ቅዱስ አምላካችንን በማምለክ እንድታድጉ እርምጃዎች በመውሰድ ረገድ እግዚአብሔር እንዲረዳችሁ በመጠየቅ በአንድነት ጸልዩ።

ጥናት አራት

አምልኮ፦ እግዚአብሔርን መጠማት

መዝሙር 63

ዓላማው፦ መዝሙር 63ን በምናነብበት ጊዜ ስለ እግዚአብሔር ኃይልና ክብር ለመማር፥ ልናከብረው እንችል ዘንድ አምልኮ ከእግዚአብሔር ጋር መሆን፥ "እርሱን መጠማት" መፈለግን የሚያጠቃልል መሆኑን ለመረዳት ነው።

የዓላማው ማብራሪያ፦ አምልኮ ልናደርገው የምንፈልገው እንጂ ልናደርገው የሚገባን ብቻ አይደለም። አምልኮ ውጫዊ ቅርፅ ብቻ ያለው ምስጋና አይደለም። አምልኮ በእግዚአብሔር ፊት በመሆን ልናከብረውና ከእርሱም ጋር በመሆን ልንጠግብ ከልባችን የሚመነጭ ፍላጐት ነው።

የትምህርቱ አቀራረብ፦ እንደ ክርስቲያኖች እግዚአብሔር ባለበት ስፍራ ለመሆን እንወዳለን ወይስ እግዚአብሔርን የምናመልከው ግዴታ ወይም ልማድ ስለሆነብን ነው? ለብዙ ሰዎች አምልኮ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ልማዳዊ ነገር ነው። እግዚአብሔርን ከሙሉ ልባቸው ስለማይወዱት የመጸለይና የእግዚአብሔርን ቃል የማሰብ ፍላጐት ያጣሉ። እግዚአብሔርን የመጠማት ነገር የላቸውም።

ዛሬ መዝሙር 63ን በማጥናት ዳዊት እግዚአብሔርን እንደ ተጠማ ለማየት እንሞክራለን።

መዝሙር 63 ን አንብቡ

1- **የመዝሙር 63 ታሪካዊ መሠረት ምንድን ነው?** (የመዝሙሩን ርእስና ከቁጥር 9-11 ያለውን አሳብ ተመልከት።) የእባቶች ታሪክ ዳዊት ይህን መዝሙር የጻፈው ንጉሥ በነበረበት ጊዜና በይሁዳ ምድረ በዳ እያለ መሆኑን ያስረዳል። ይህ ደግሞ ዳዊት በልጁ አቤሴሎም በተሰደደ ጊዜ ነፍሱን ለማዳን ዮርዳኖስን አቋርጦ በምድረ በዳ ለተወሰነ ጊዜ የቆየበትን ወቅት ያመለክታል (2ኛ ሳሙ. 15:13-29)። የይሁዳ በረሃ ደረቅ ምድር በሙት ባሕር ምሥራቅ ጠረፍ ላይ ይገኛል።

2- **ንጉሥ ዳዊት ከእግዚአብሔር ጋር ምን ዓይነት**

ግንኙነት ነበረው? (63:1-2) ዳዊት ስለ እግዚአብሔር "የእኔ ጌታ " እያለ ይናገራል። ዳዊት ከእግዚአብሔር ጋር የቀረበ ግንኙነት አለው። ዳዊት እንደ ሰው የሚያውቀውን ጌታ እንደ ተጠማና እንደ ፈለገውም እናያለን።

3- **የይሁዳ ምድረ በዳ ዳዊት አሁን ካለበት ሁኔታና ስሜት ጋር የሚወዳደረው እንዴት ነው?** ፀሐይ ያቃጠለውና አሸዋማው መሬት ውኃ ያጣ ደረቅ ነበር። ውኃ ያጣው በረሃ ለዝናብ የሚጮህ ይመስላል። ያም ቢሆን ዳዊት ያለው ከእርሱ ጋር ጓደኝነት በሌለው ደረቅ ስፍራ ከቤቱ ርቆ ነበር። በኢየሩሳሌም ካለው ቤቱና ከእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ተራርቆ ነበር። ወትሮ ያደርግ እንደነበረው በቤተ መቅደስ እግዚአብሔርን ማምለክ አልቻለም። የይሁዳ ምድረ በዳ ለእርሱ መንፈሳዊ በረሃና ምድረ በዳ ሆነበት። ደረቅ መሬት ለውኃ እንደሚጮህ መንፈሱ ወደ እግዚአብሔር ጮኸ።

4- **ሰዎች ስለ እግዚአብሔር መገኘት (ሕልውና) ከፍተኛ ፍላጐት እንዳላቸው የሚሰማቸው መቼ ነው? ነገሮች በሚከናወኑላቸው ሠናይ ወቅት ወይስ ችግር ሲያጋጥማቸው?** ተወያዩበት። አብዛኛውን ጊዜ ሰዎች በሰላምና በደኅንነት ካሉበት ጊዜ ይልቅ በችግር ጊዜ ወደ እግዚአብሔር ያዘነብላሉ። ሰዎች ሲታመሙና የዝናብ እጦት ሲኖር እግዚአብሔር እንደሚያስፈልጋቸው ይገነዘባሉ።

5- **እንደ ቀድሞ አባቶች እግዚአብሔርን የማምለክ ጥማት የማይኖረን ለምንድን ነው?** ተወያዩበት። ከዘመናዊ የልማት እንቅስቃሴዎች፥ ከዘመናዊ ሆስፒታሎችና ከብዙ ምቾት የተነሣ ሰዎች እንደ ቀደመው ዘመን የእግዚአብሔር አስፈላጊነት ብዙም አይታያቸውም። የላይንስ ትምህርት እግዚአብሔርን አላስፈላጊ ያደረገው ይመስላል። ነገሮች በጥሩ ሁኔታ ሲካሄዱ ሰዎች ደስተኛና የረኩ ይመስላቸውና እግዚአብሔር እንደሚያስፈልጋቸው ብዙም አይገነዘቡም።

6- መዝሙር 42:1-4ን አንብቡ። **የመዝሙረ ዳዊት ጸሐፊ በመዝሙር 42 ላይ ሕያው እግዚአብሔርን የተጠማው ለምንድን ነው?** ምናልባት አስረኛ ምርኩኛ ስለነበረ ይሆናል። በወራሪ ንጉሥ ከኢየሩሳሌም ስለተባረረ እንደ ወትሮው ልማዱ በቤተ መቅደስ ውስጥ እግዚአብሔርን ሊያመልክ አልቻለም።

7- **ዳዊት እግዚአብሔርን በዚህ ጊዜ መጠማቱ**

ያልተለመደ ነበር ወይስ በስላምና በመትረፍረፍ ጊዜም ይፈልገው ነበር? (63:2)። ቍጥር 2 ዳዊት እግዚአብሔርን በቤተ መቅደስ የማምለክ ልማድ ነበረው። ዳዊት በምድረ በዳ ከእግዚአብሔር ጋር ጎብረት መፈለጉ እግዚአብሔርን በኢየሩሳሌም ባለው መቅደስ ውስጥ በውበቱ እንደሚያይበት ጊዜ ያህል ጠንካራ ነበር።

8- **ዳዊት እግዚአብሔርን በመቅደሱ ውስጥ ሊያመልክ የወደደው ለምንድን ነው?** (63:2)። ስለ እግዚአብሔር ተፈጥሮ አዲስ መረዳት ለማግኘት ኃይሉንና ክብሩንም ለማየት ዳዊት ወደ እግዚአብሔር ቀና ብሎ መመልከት ፈለገ። ዳዊት እግዚአብሔርን በየዕለቱ ፈለገው፤ መሥዋዕቶችን ሲመለከትና የብዙዎቹን ጸሎት በቤተ መቅደስ ውስጥ ሲሰማ÷ ስለ እግዚአብሔር ግርማና ስለማያቋርጥ ፍቅሩ ብዙ ሊማር ወደደ። እግዚአብሔርን በመቅደሱ ማየት ማለት በመንፈስ ሊያይ መቻሉን ነው። እግዚአብሔርን በዓይነ ሥጋው አልተመለከተውም፤ ነገር ግን እርሱን አሰበው።

9- **ዳዊት ሕይወቱን ለማዳን በሸሸበት ጊዜ በምድረ በዳ እግዚአብሔርን ሊያከብር የወደደው ለምንድን ነው?** በማጉረምረም ፋንታ እግዚአብሔርን አከበረ። ለምን? (63:3) ምክንያቱም የእግዚአብሔር ፍቅር ከሕይወት ይሻላል። ምንም እንኳ ዳዊት መንግሥቱንና ዙፋኑን ቢያጣም በኢየሩሳሌም ንጉሥ እንደነበረበት ጊዜ የማያቋርጥ ፍቅር ነዋሪ እንደሆነና ይህም ከሕይወት እንደሚሻል ተመለከተ።

10- **ዳዊት እግዚአብሔርን ያከበረው እንዴት ነው?** (63:3-5)። በከንፈሩ÷ እጆቹን ለጸሎት ወደ ላይ በማንሣትና በዝማሬ ነው። ሃይማኖተኛ አይሁዶች በሚጸልዩበትና እግዚአብሔርን በሚያመሰግኑበት ጊዜ እጆቻቸውን ወደ ኢየሩሳሌም የመዘርጋት ልማድ ነበራቸው።

11- **ዛሬ በከንፈራችን እግዚአብሔርን የምናመሰግነው እንዴት ነው?** ተወያዩበት። በምስክርነትና በዝማሬ ስለ እግዚአብሔር የማያቋርጥ ፍቅር እንናገራለን። በጸሎት አማካኝነት እግዚአብሔርን በከንፈራችን ማመስገን እንችላለን።

12- **አስከፊ በሆነ ችግር ውስጥ እያለን እንኳን እግዚአብሔርን ማክበር ግላዊ የሆነ ብድራትን ያመጣ ይሆን?** (63:5)። ዳዊት ከልምዱ በግል ከእግዚአብሔር ጋር ያለው ግንኙነት ደስታን እንደሚያመጣለት አውቋል። ምንም እንኳን ዳዊት

በስደት ምክንያት በበረሃ (ለሕይወቱ በሸሸበት ጊዜ) ቢገኝም÷ ከእግዚአብሔር ጋር ያለው የግል ግንኙነት በሞቀ ግብዣ እንዳለው የድሎት ምግብ አርክቶታል፣ ደስም አሰኝቶታል።

13- **ዳዊት እግዚአብሔርን የሚያመልከውና የሚያስበው በቤተ መቅደስ ጉብኝቱ ጊዜ ብቻ ነውን?** (63:6)። አይደለም። ዳዊት ሌሊት በመኝታው ላይ እያለ÷ ከመኝታው በፊት÷ ማለዳ ከእንቅልፉ ከመነሣቱ በፊት እግዚአብሔርን ያስባል።

14- **ዳዊት እግዚአብሔርን በመኝታው እያለ ያሰበው በኃላፊነት ስሜት ነው ወይስ በእግዚአብሔር ደስ ከመሰኘቱ የተነሣ?** (63:7-8)። ዳዊት በረዳው በእግዚአብሔር ይመካ ነበር። ከእግዚአብሔር ጋር ከነበረው የጠበቀ ግንኙነት የተነሣ በደስታ ዘመረ። ዳዊት የጸለየው በእግዚአብሔር ደስ ስለተሰኘ እንጂ የኃላፊነት ስሜት ስለተሰማው አይደለም።

15- **አብዛኛዎቹ ክርስቲያኖች እንደ ዳዊት ከእግዚአብሔር ጋር የቀረበ÷ ግላዊና የመተማመን ግንኙነት አላቸው?** ለምን እንደዚያ አልህ? ተወያዩበት።

16- **አብዛኛው ክርስቲያን በየማታውና በየጠዋቱ እግዚአብሔርን ያመልካል ወይስ አምልኮአቸው እሑድ ጠዋት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ብቻ የተወሰነ ነው?** ተወያዩበት። ብዙ ክርስቲያኖች የሚያስቡት እግዚአብሔርን ማምለክ የሚገባው በቤተ ክርስቲያን በየእሑዱ ብቻ ነው ብለው ነው። ነገር ግን አምልኮ በሕይወታቸው ዘመን ሁሉ የክርስቲያኖች ዕለታዊ ተግባር ሊሆን ይገባል።

17- **ዳዊት ከእግዚአብሔር ጋር ያለው የግል ግንኙነት በችግር ጊዜ ስሜቱን የነካው እንዴት ነው?**(63:9-11)። ዳዊት እግዚአብሔር ከጠላቶቹ እንደሚከላከለው÷ እንደገናም በእርሱ እንዲደሰትና ስሙንም ለማክበር እንዲበቃ ያስችለው ዘንድ ትምክህት ነበረው። ጠላቶቹ በሰይፍ እንደሚያልቁና በድናቸውም በተኩላዎች እንደሚበላ እምነት ነበረው።

18- አምልኮ እግዚአብሔርን ለማክበርና ከፍ ከፍ ለማድረግ እርሱ ባለበት ስፍራ ለመሆን መጠማትን ያጠቃልላል። እርሱን የማምለክ ፍላጐት ሲኖረን እግዚአብሔር ይከብራል። አምልኮ እንዳንድ የአምልኮ ሥርዓቶችን ከማከናወን በላይ ነው። አምልኮ ከልብ ይመነጫል። አምልኮ እግዚአብሔርን የበለጠ ለማወቅና

ለመውደድ እንደዚሁም ለማክበር በልብ ውስጥ ካለው ፍላጐት ይመነጫል።

እስኪ ለአንድ አፍታ ሕይወታችንን እንመርምር። ዳዊት እንዳደረገው እግዚአብሔርን እንፈልጋለን? እንጠማለን? ዳዊት እንዳደረገው ቀኑን ሁሉ በእግዚአብሔር ደስ ይለናል? ምስጋናን እንቀኝለታለን? ለምን ይህንን እናደርጋለን? ለምንስ አናደርግም? እያንዳንዱ ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን ግንኙነት እንዲያስብ/እንድታስብ ጥቂት ጊዜ ውሰዱ።

19- **አንድ ሰው እግዚአብሔርን መጠማት እንደሚገባው ሳይጠማ ሲቀር እግዚአብሔርን የበለጠ መጠማት ይችል ዘንድ ምን ማድረግ ይችላል?** ተወያዩበት። በቅድሚያ ዳግመኛ መወለድ ያስፈልጋል፣ ከኃጢአት ያድንህ ዘንድ ክርስቶስን ወደ ሕይወትህ መጋበዝ ይኖርብሃል።

ከዚያም እግዚአብሔር ለአንተ ያለውን ፍቅር በተረዳህ መጠን÷ የበለጠ እየወደድኸው ትሄዳለህ። የእግዚአብሔርን በረከትና ዕርዳታ÷ የአንተን ኃጢአተኛነት÷ ብሎም የእግዚአብሔርን አስገራሚ ፍቅርና ጸጋ በተገነዘብህ መጠን÷ ያ የበለጠ እንድትወደው ያደርግሃል። ይበልጥ ከእርሱ ጋር በተራመድህ÷ በተነጋገርህ÷ ባመለክኸውና የእርሱ አስፈላጊነት በተሰማህ መጠን እግዚአብሔርን የመጠማት ነገርህ ይበዛል። ብዙውን ጊዜ ከእንግዳ ጋር ጎብረት ለማድረግ ጥማት አይኖርህም። ነገር ግን ከምታውቀውና ከምትወደው ጓደኛህ ጋር ለመሆን ትጠማለህ።

የእግዚአብሔርን ቃል ማድረግ፦ ለእግዚአብሔር ያለህን ጥማት ለማሳደግ በዚህ ሳምንት ምን ልታደርግ ትችላለህ? ከእግዚአብሔር ኃይልና ፍቅር የተነሣ በዚህ ሳምንት ከልብህ እግዚአብሔርን ለመውደድና ለማክበር ትፈልግ ዘንድ በመጀመሪያ ወስን።

ጸሎት፦ እግዚአብሔር ለቃሉና ለጸሎት ጥልቅ ረሃብና ጥማት እንዲሰጥህ በጸሎት በፊቱ ስገድ።

ጥናት አምስት

አምልኮ፡- ለእግዚአብሔር ፈቃድ የመታዘዝ ምላሽ

መዝሙር 40:1-10

ዓላማው፡- አምልኮ በክንፈራችን እግዚአብሔርን ከማምለክ በላይ እንደሆነ ለመማር ሲሆን÷ ከመዝሙር 40:1-10 እንደምናነበው አምልኮ ለእግዚአብሔር ፈቃድ መታዘዝን ይጨምራል።

ዓላማውን ስለማብራራት፡- ለብዙ ሰዎች አምልኮ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በየእሑዱ የሚካሄድ ሥርዓት ነው። አምልኮ በክንፈራችን እግዚአብሔርን ማክበርና ማመስገን ነው። ነገር ግን አምልኮ ከዚያም በላይ ነው። አምልኮ ከእውነተኛ ልብ መውጣት ስላለበት÷ የሚጀምረውም በልባችን ለእግዚአብሔር ፈቃድ በመታዘዝ ነው።

የትምህርቱ አቀራረብ፡- ንጉሥ ሳያል በእግዚአብሔር ፈቃድ አማሌቃውያንን ለመውጋት ወጥቶ ነበር (1ኛ ሳሙኤል 15:1-31)። እግዚአብሔር ድልን በሰጠው ጊዜ ሳያል ወደ እስራኤል ተመለሰ። እግዚአብሔርን ከከብትና ከበጐች በተመረጠ መሥዋዕት እከበረው። ነገር ግን አምልኮው በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት አልነበረውም፤ ምክንያቱም የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ተላልፎ ነበርና። እግዚአብሔር የጠላቶችን እንስሳት ሁሉ እንዲያጠፋ አዝዞት ነበር። ሆኖም ሳያል ለእግዚአብሔር መሥዋዕት ለማቅረብ ከከብቶችና ከበጐች የተመረጡትን አልገደለም ነበር።

የሳሙኤል ምላሽ÷ "በውኑ የእግዚአብሔርን ቃል በመስማት ደስ እንደሚለው እግዚአብሔር በሚቃጠልና በሚታረድ መሥዋዕት ደስ ይለዋልን? እነሆ÷ መታዘዝ ከመሥዋዕት÷ ማዳመጥም የአውራ በግ ስብ ከማቅረብ ይበልጣል" (1ኛ ሳሙ. 15:22 -ከ 1962 ዓ.ም እትም የተወሰደ) የሚል ነበር።

እምልኮ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የአምልኮን ሥርዓት ከመፈጸም የሚበልጥ ነው። እምልኮ እግዚአብሔርን ከማክበርና ከማመስገንም በላይ ነው። እምልኮ ከልብ መውጣት ሲኖርበት÷ በልባችን ለእግዚአብሔር ፈቃድ ከመታዘዝ ይጀምራል። ሳያል እግዚአብሔርን ስላልታዘዘ የእርሱ እግዚአብሔርን በመሥዋዕቱ የማምለክ ሙከራ

ተቀባይነት ሳያገኝ ቀርቷል። ዛሬ መዝሙር 40ን እያጠናን አምልኮ ለእግዚአብሔር ፈቃድ መታዘዝን የሚያጠቃልል መሆኑን ለማሰብ እንፈልጋለን።

መዝሙር 40:1-10 አንብቡ።

1- **የዚህ መዝሙር ታሪካዊ መሠረት ምን ይመስላል?** (40:1-8)። ከቁጥር 1-3 ያለው አሳብ ዳዊት በችግር ውስጥ እንደ ነበረና ጌታ ግን እንደታደገው የሚያሳይ ይመስላል። ከችግሩ ለመውጣት እንዲረዳው ወደ እግዚአብሔር ጸለየ። አሁን ደግሞ እግዚአብሔር ስላዳነው ምስጋና ያቀርባል። አንዳንዶች ይህ መዝሙር የተጻፈበት አጋጣሚ በ1ኛ ሳሙኤል መጨረሻ ላይ በተጠቀሰው ታሪክ ውስጥ እንደሚገኝ ያምናሉ፤ የጺግላግ ጥፋት (1ኛ ሳሙ. 30:4-6)÷ የአማሌቃውያን መሸነፍ (1ኛ ሳሙ. 30:16-20)÷ የፍልስጥኤማውያን የድል ወሬ በጌልቦአ እና የንጉሥ ሳያል ሞት ሁሉም የተፈጸሙት በጥቂት ቀናት ውስጥ ነው (2ኛ ሳሙኤል 1:1)።

2- **ዳዊት የነበረበትን ችግር የገለጸው እንዴት ነው?** (40:2)። ረግረግ ጭቃ ባለበት ጉድጓድ ውስጥ ነበር። የአንድን ሰው እግር ተጭኖ ሊረግጠው የማያስችል ጭቃ ከሥሩ ያለው ውኃ ስለያዘ ወደ ጥፋትና መፍረስ የሚያመራ ሥዕል ያለው ጉድጓድ ነው። ብዙ በቆየ መጠን ይበልጥ እየሰመጠ ሄደ። ስለዚህ የነበረበት ችግር ያለምንም ተስፋ ወደ ሞት የሚመራ ነበር። ራሱን ጨርሶ ሊያድን በማይችልበት ሁኔታ ውስጥ ነበር።

3- **ዳዊት ከጥፋትና ከሞት ለመዳን ምን አደረገ?** (40:1)። እግዚአብሔርን በርጋታ ጠበቀ። **ያ ምንን ያመለክታል?** ወደ እግዚአብሔር ጸለየ፤ ነገር ግን ለጸሎቱ ወዲያው መልስ አላገኘም። ስለዚህ እግዚአብሔርን መልስ እስከሚሰጠው ጠበቀ። በምንጠይቀው ሰው ላይ ካልተማመንን በስተቀር በተለምዶ ለመልስ አንጠብቅም። በትዕግሥት እግዚአብሔርን መጠበቅ የእምነትና የተስፋ ጸሎትን÷ በትዕግሥት መግፋትን÷ እግዚአብሔር በራሱ ጊዜ ጸሎትን እንደሚሰማና መልስም እንደሚሰጥ ማመንን ያመለክታል።

4- **ዳዊት እግዚአብሔር ለጸሎት መልስ ከሰጠው በኋላ ያለበትን አዲስ ሁኔታ ግለጽ?** (40:2)። ሊቆም በማይችልበት ረግረጋማ ጉድጓድ ውስጥ በመሆን ፈንታ ዳዊት አሁን ከፍ ብሎ እግሮቹን ጠንካራ በሆነ ዓለት ላይ አኖረ።

5- እግዚአብሔር ሁልጊዜ እኛ በምንፈልገው መንገድ ነው ወይ ጸሎታችንን የሚመልሰው? ተወያዩበት:: አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር ጸሎታችንን በአዎንታ ይመልሳል:: አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ከጥሩ ምክንያት ጋር ጸሎታችንን በአሉታ ይመልሳል:: አንዳንድ ጊዜ ለመልሱ አንድንታገሥ ይጠይቀናል:: አንዳንድ ጊዜ ደግሞ እኛ ከጠበቅነው በተለየ መንገድ መልስ ይሰጠናል::

6- ረግረጋማ ከሆነ ጉድጓድ በመዳኑ፥ ለዚህ አስደናቂ የጸሎት መልስ ምላሽ የሚሰጠው እንዴት ነው? (40:3):: እግዚአብሔርን እያከበረ መዘመር ጀመረ:: አዲስ መዝሙር ብሉስ የጠራው ለምንድን ነው? ይኼ አዲስ ዝማሬ ነው ብሎ የተጠራው ለጸሎቱ አዲስና የተለየ መልስ ስላገኘ ነው:: እግዚአብሔር ብዙ ጸሎቶችን ከዚህ በፊት አንደመለሰለት አይጠራጠርም:: ቀደም ሲል ሊያመሰግንባቸው የሚገባው ብዙ ምክንያቶች አሉት:: ይህ ግን አዲስ የጸሎት መልስ ሲሆን፥ ምስጋና ለማቅረብም አዲስ ምክንያት ነበር::

7- ሰዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ምስክርነት የሚሰጡት እግዚአብሔር አዲስ ስላደረገላቸው ነገር ነው ወይስ አንዱን ነገር እየደጋገሙ ነው? ተወያዩበት:: ሰዎች ስለመዳናቸው ደግመው ደጋግመው ምስክርነት ይሰጣሉ:: ሁልጊዜ እግዚአብሔር አንዳንን ደግመን ደጋግመን አመስጋኝ መሆን በርግጥ መልካም ነው:: ነገር ግን በየሳምንቱ ስለሚያጋጥመን ስለ እግዚአብሔር ፍቅርና ጸጋ አዳዲስ ልምምዳችን አዲስ ዝማሬ ደግሞ ሊኖረን ይገባል::

8- የቃላቱ ትርጉም ምንድን ነው? "ብዙዎች ያያሉ ይፈራሉም እንደዚሁም በእግዚአብሔር ይታመናሉ"(40:3):: ዳዊት ተአምራዊ በሆነ የጸሎት መልስ ከጥፋት በሚድንበት ጊዜ ይህንን በዝማሬ በአደባባይ መሰከረ:: ይህ አስደናቂ የእግዚአብሔር ምሕረት ንስሐ ሊገቡ ያልፈለጉት ኃጢአተኞች አንኳን እግዚአብሔርን እንዲፈሩና በእርሱም እንዲታመኑ ይመራቸዋል:: ምክንያቱም እግዚአብሔር አምላክ ድንቅን የሚያደርግ አምላክ ስለሆነ ልንፈራውና ልንታመነው ይገባል::

9- ቁጥር 4 እና 5 የአዲሱ ዝማሬ አካል እንደሆኑ ይታሰባል:: ዳዊት በአዲስ ዝማሬ ውስጥ ምንን አጠቃለለ? ከትዕቢተኛ ሰዎች ወይም ከሐሰተኛ አማልክት ይልቅ በእግዚአብሔር የሚታመኑ ብሩካን እንደሆኑ ተገልጸአል (40:4):: ብንሞክር አንኳን

ልንዘረዝራቸው ስለማንችላቸው አግዚአብሔር ሊያደርግልን ስላቀዳቸው ብዙ መልካም ነገሮች ምስክርነት ይሰጣል (40:5)::

10- ከቁጥር 1-5 ከጥፋት ስላዳነው እግዚአብሔር የምስጋና ምስክርነት ነው:: በቁጥር 6-8 ያለው አሳብ ከቁጥር 1-5 ካለው አሳብ ጋር የሚዛመደው እንዴት ነው? ስለ እግዚአብሔር አስደናቂ የማዳን ሥራ ከተናገረ በኋላ ዳዊት ለጸሎቱ ስለሰጠው ምላሽ እግዚአብሔርን ለማክበርና ለማመስገን ምን ማድረግ ይገባዋል? የምስክርነት ዝማሬ በቂ ነው ወይ? አይደለም:: እግዚአብሔር የሚፈልገው ሁልጊዜ አንድንታዘዘውና ራሳችንን በመቀደስ ለእርሱ አንድናቀርብ ነው::

11- በቁጥር 6 ላይ የሚገኙትን የተለያዩ የመሥዋዕት ዓይነቶች ዘርዝር:: የብሉይ ኪዳን መሥዋዕቶች ሁለት ዓይነት ናቸው:: 1) የእንስሳት የደም መሥዋዕት እና 2) የእህል መሥዋዕት (የመብል ወይም የጥራጥሬ መሥዋዕት):: መሥዋዕቶች ለሁለት የተለያዩ ዓላማዎች ይውሉ ነበር:: 1)የእግዚአብሔርን ይቅርታ ለማግኘትና የሰውን ኃጢአት ለመናዘዝ (የኃጢአት መሥዋዕት)፥ 2) ከፍቅርና ራስን ከመስጠት የተነሣ ለእግዚአብሔር ራስን ለመለየት (የሚቃጠል መሥዋዕት)::

12- ዳዊት እግዚአብሔር እነዚህን መሥዋዕቶች አይፈልግም ያለው ለምንድን ነው? እነዚህ በዘሌዋውያን 1-4 ከእግዚአብሔር በትእዛዝ መልክ የተሰጡ አይደሉምን? (40:6):: ተወያዩበት:: አዎን እግዚአብሔር እነዚህን (መሥዋዕቶች) እንዲያቀርቡ እስራኤላውያንን አዝዞአል:: ይሁንና መሥዋዕቶችን ማቅረብ እግዚአብሔርን የመታዘዝ ምትክ አልነበረም:: መሥዋዕቶችን እያቀረቡ እግዚአብሔርን አለመታዘዝ መሥዋዕታችን በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት እንዳይኖራቸው ያደርጋል::

13- ዳዊት "ነገር ግን ጆሮዬን በስተኸዋል" ሲል ምን ማለቱ ነው? (40:6):: ሁለት የሚታሰቡ ትርጉሞች አሉ:: ቃሉ "በመበሳት" የሚጠቅስ ከሆነ ለጌታው በሕይወት ዘመኑ ለማገልገል ቃለ ለሚገባ አገልጋይ የሚሰጥ ምልክትን ማመልከቱ ሊሆን ይችላል (ዘጸአ. 21:6፤ ዘዳ.15:17) :: አገልጋይ በሕይወት ዘመኑ ጌታውን ሊታዘዝ ቃል ሲገባ ለመታዘዝ ቃል መግባቱ ምልክት እንዲሆን ጆሮው እንዲበሳ ይፈቅዳል:: ነገር ግን የዕብራይስጡ ትርጉም በሚፈልግበት ጊዜ ግልጽ የሆነው የ "መቆፈር" አሳብ የጆሮን ቅርጽ ማመልከቱ ይሆናል:: ስለ ውጫዊው የጆሮ ቅርጽ አሳብ ሰንዝሮአል::

እግዚአብሔር በጆሮ ላይ ቀዳዳን ማበጀቱ መስማት እንችል ዘንድ ነው። እግዚአብሔር በጆሮአችን ላይ ቀዳዳን ሲያበጅ የእግዚአብሔርን ቃል ሰምተን መታዘዝ እንችል ዘንድ ነው። ጆሮዎች የተሠሩት ለመስማት ነው። የእግዚአብሔርን አሳብ ቃሉን በምንሰማበት ጊዜ እንድንታዘዘው ይፈልጋል። ይሁንና በየትኛውም መንገድ ቢሆን እግዚአብሔር የፈጠረን እንድንታዘዘው ነው።

ዕብራውያን 10:5-7 ያለውን ክፍል አንብብ። ቊጥር 5 "ሥጋን አዘጋጀህልኝ" ብሎ መነበቡን አስተውል። በዕብራይስጡ መጽሐፍ እነዚህ ጥቅሶች የተወሰዱት የግሪኩ ትርጉም ከሆነው ከብሉይ ኪዳን መጽሐፍ ነው። ሆኖም መዝሙር 40:6 የተወሰደው ከዕብራይስጡ ብሉይ ኪዳን ነው። ወይም የዕብራይስጡ መጽሐፍ ቅዱስ ሲጻፍ በስሕተት ተሠርቷል፤ አሊያም የግሪኩ ተርጓሚዎች የብሉይ ኪዳን መዝሙር 40:6ን ሰፋ ባለ መንገድ ተርጉመውት ሊሆን ይችላል። ጆሮዎች በመታዘዝ ለመሰማት ተወስነዋል፤ ሰውነታችን ደግሞ በእግዚአብሔር የተፈጠረው ለመታዘዝ ነው። እግዚአብሔር ሰምተን እንታዘዘው ዘንድ ጆሮአችንን ሠርቶአል። የሰውነት አካላችንንም የቀረጸው እንደዚሁ ለመታዘዝ ነው። ነገር ግን "ጆሮዎቼን በሳሃቸው" የሚለው ሐረግ ቁልፍ ትርጉም መታዘዝ ለመሆኑ የሚከተለው ጥቅስ በግልጽ ያሳያል (ዕብ.10:7)። እግዚአብሔር ጆሮአችንን መብሳቱ ቃሉን ሰምተን እንድንታዘዝ ነው።

14- **እንደ ዕብራውያን 5-7፥ መዝሙር 40:5-7 ማንን ነው በትክክል የሚጠቅሰው?** ተወያዩበት። የመዝሙረ ዳዊት አሳብ ዳዊት ሊታዘዝ ቃል መግባቱን ያመለክታል። ነገር ግን እንደ ዕብራውያን መጽሐፍ ይህንኑ ሙሉ በሙሉ በመፈጸም ያሟላው ክርስቶስ ኢየሱስ ነው።

15- **እንደ መዝሙር 40:7-8 አሳብ፥ የክርስቶስን ሕይወት የምናጠቃልለው እንዴት ነው?** የመታዘዝ ሕይወት ነበረው በማለት ነው። እግዚአብሔር ለክርስቶስ አካላትን አዘጋጅቶለታል (ዕብ. 10:5)፤ "ፈቃድህን አደርግ ዘንድ ጌታ ሆይ" ሲል ይታዘዝ ዘንድ። ነገር ግን በመጀመሪያ ደረጃ ይሄ ስለ ዳዊት ሕይወቱን እግዚአብሔርን ለመታዘዝ ቃል ለገባው ተጠቅሷል። ይሁንና ዳዊት በፍጹምነት አልታዘዝም። እርሱ ኃጢአትን ሠርቷል። ከኃጢአት የራቀ ሕይወት በመምራት ኢየሱስ ግን ፍጹም በሆነ መንገድ ታዘዘል።

16- **ለምንድን ነው መጽሐፍ ቅዱስ ስለ መጽሐፍ**

ጥቅልል የሚጠቅሰው? መዝ. 40:7። በጥንት ጊዜ መጻሕፍት በቆዳ ሌጦ ላይ ተጽፈው ይጠቀለላሉ። ሁለት የእንጨት ተሽከርካሪዎች ነበሩ። አንደኛው ቆዳውን በሌላ ነገር ላይ የሚዘረጋ ሲሆን፥ ሌላው ደግሞ ጥቅሉ በሚነበብበት ጊዜ የሚተረትረው ነው። በዚህ ስፍራ የተጠቀሰው ጥቅልል ያለጥርጥር እምስቱ የሕግ መጻሕፍት ናቸው (የሙሴ መጻሕፍት)። ይህም በንጉሥ ዳዊት ዘመን የእግዚአብሔር ብቸኛ መገለጥ አካል ነበር። አንዳንዶች ይሄ (ምናልባትም ዘዳግም 17:14-15) ዳዊት ንጉሥ በሆነበት ጊዜ ሥራ ላይ የዋለ ትንቢት ነው ይላሉ።

የትኛውንም የቃሉን ክፍል ይጥቀስ፤ ይህ ሙሉ የሕግ መጽሐፍ ጥቅልል ስለ ክርስቶስና እርሱም የእግዚአብሔርን ፈቃድ ስለማድረጉ ይናገራል። በመዝሙር 40 ዳዊት የራሱን ታዛዥነት ያወራል። ነገር ግን በትክክል ከልምምዱ አለፍ ብሎ ነው የተናገረው። በመንፈስ ቅዱስ መሪነት የእግዚአብሔርን ፈቃድ ፈጽሞ ለማከናወን ስለሚመጣው ባለተስፋው መሢሕ ዳዊት አመለከተ።

17- **ከክርስቶስ ዘመን ወዲህ እኛ የእንሰሳት መሥዋዕት እናቀርብም።** የምናቀርበው መሥዋዕት የምስጋናና የአክብሮት ነው። (በመዝሙር 40:9-10 ላይ ያለውን የምስጋና ምስክርነት አስተውል)። አንዳንድ ጊዜ እንደ ክርስቲያን በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ለሌለው የምስጋናና የአክብሮት መሥዋዕት እናቀርባለን ወይ? እንዴት ነው ይህንስ የምንፈጽመው? ተወያዩበት። ቤተ ክርስቲያን ልንካፈል፥ በመዘምራን ቡድን ውስጥ ልንዘምርና ምስክርነታችንን ልንሰጥ እንችላለን። ነገር ግን በሳምንቱ መሃል በእግዚአብሔር ላይ እናምፃለን፤ በኃጢአትም ውስጥ እንኖራለን። እንዲህ ዓይነቱ ዓመፃ የእደባባይ አምልኮአችንና ምስክርነታችንን ተቀባይነት እንዳይኖረው ያደርጋል።

18- **እንዳንድ ሰዎች ለምስክርነት ትልቅ ትኩረት ይሰጣሉ።** ምስክርነታችንን ካልሰጠን እንደማንድን ይሰማቸዋል። በእንደበታችን ምስክርነት ከመስጠት የበለጠው ጠቃሚው ነገር የቱ ነው? የመታዘዝ ሕይወት። ከመታዘዝ የራቀ የማይገባ ሕይወት እየኖሩ ምስክርነት የሚሰጡ ሰዎች አይተህ ታውቃለህ? ተወያዩበት። መታዘዝ ቀዳሚና ከምስክርነትም የበለጠ ነው። "የምታደርገው ነገር የበለጠ ስለሚናገር የምትለውን ልሰማ አልችልም።"

የእግዚአብሔርን ቃል ማድረግ፤ እግዚአብሔር በኑሮህ ምን አደረገልህ? ምስጋናና ከበሬታ ልትሰጠው ምን አደረግህ? የእግዚአብሔርን ቃል ለመታዘዝ ሰውነትህን ለጌታ ሰጥተህ ነበር

ወይ? ወይም እግዚአብሔርን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እያከበርህ በኃጢአት ሕይወት ትኖር ነበር ወይ? ሕይወትህን በእግዚአብሔር ፊት ተመልከት።

ጸሎት፤ ለጸሎት በመጐንበስ እግዚአብሔር እርሱን ደስ በሚያሰኝ መንገድ ታመልከው ዘንድ እንዲረዳህ፥ ለእግዚአብሔር የሚታዘዝ ልብ እንዲሰጥህ፥ ስለቸርነቱ አመስጋኝነትህን ለማሳየት እንዲረዳህ ጠይቀው።

ጥናት ስድስት

አምልኮ "በመንፈስና በእውነት ሊሆን ይገባዋል"

የክርስቶስ ትምህርት በእውነተኛ አምልኮ ላይ

ዮሐንስ 4፡15-26

ዓላማው፡- የእውነተኛ ክርስቲያኖች አምልኮ ክርስቶስ በዮሐንስ 4፡20-24 ላይ እንዳስተማረው በመንፈስና በእውነት መሆኑን ለመማር ሲሆን፤ የክርስቲያኖች አምልኮ ትኩረትም በልብ ዝንባሌ ላይ እንጂ በውጫዊ ቅርጽ ወይም ሥርዓት ላይ መሆን እንደማይገባው ለመማር ነው።

የዓላማው ማብራሪያ፡- ከብሉይ ኪዳን የአምልኮን ምንነት ስናጠና ቆይተን ነበር። እነኚህ በብሉይ ኪዳን ያለውን አምልኮ ያስተካከሉ በጣም ጠቃሚ የሆኑ አሳቦች የዛሬውን የክርስቲያኖች አምልኮ መልክ ሰጥተውታል። ይሁንና፥ ክርስቶስ ብዙውን ዓይነት የብሉይ ኪዳን አምልኮ በራሱ አሟልቷል። ከዚህም በላይ ስለ እውነተኛ አምልኮ ባሕርይ ሙሉና የበለጠ መንፈሳዊ መረዳት እንዲኖር አድርጓል። ዛሬ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ክርስቶስ በአምልኮ ላይ የሰጠውን በጣም ጠቃሚ የሆነ ትምህርት ለማጥናት (ዮሐ. 4፡20-24)፥ እግዚአብሔርንም ደስ የሚያሰኘው አምልኮ የቱ እንደሆነ ከእርሱ ለመማር እንፈልጋለን።

የትምህርቱ አቀራረብ፡- ሳምራውያን እነማን ናቸው? በብሉይ ኪዳን ስለ ሳምራውያን ትውልድ ወይም ዜግነት የተጠቀሰ አሳብ የለም። የምናነበው ሰማርያ ከተማ የሰሜናዊው እስራኤል ዋና ከተማ ስለመሆኗ ነው።

ሳምራውያን መቼና ከየት ነው የተገኙት? አሥራዊያን

ከክርስቶስ ልደት በፊት በ722 ዓ.ከ.ል.በ የሰሜናዊውን የእስራኤል ከተማ በያዙ ጊዜ ታዋቂ የሆኑትን የአገሪቱን ዜጐች (27,800 አይሁዳውያን) ወደ አገራቸው ወሰዱ ። በምትኩ አሦራውያን እንግዳ የሆኑትን ሰዎች ከሌላ ቦታ አምጥተው በእስራኤል እንዲኖሩ አደረጉ (2 ኛ ነገ. 17፡19-41)። እነዚህ የአሕዛብ ወገን የሆኑ ሰዎች በሰማርያ ውስጥና አካባቢ የቀሩትን ከዝቅተኛ ክፍል የሆኑትን አይሁዳውያንን አገቡ። በዚህ መልክ የተገኙት ቅይጥ ሕዝብ (በሰሜን እስራኤል በሰማርያ የሚኖሩ ሕዝቦች)፥ ግማሽ ጐናቸው ከአሕዛብ ወገን ግማሽ ጐናቸው ደግሞ ከአይሁድ ወገን የሆኑት እግዚአብሔርን ማምለክ የቀጠሉ ሲሆን ከዚሁ ጋር ልዩ ልዩ የአረማውያን እምነቶችንና ልማዶችን አስተዋወቁ። እነርሱ የሙሴን የሕግ መጽሐፍ ብቻ እንጂ የነቢያትን መጽሐፍ አልተቀበሉም ነበር። በመጨረሻ ግማሽ ጐናቸው ቅይጥ የሆኑት ሳምራውያን በመሸቀጥ የራሣቸው የሆነውን የሳምራውያን ሃይማኖትና ባሕል ማቋቋም ጀመሩ። በመሆኑም የሳምራውያን ሃይማኖትና ባሕል ከአይሁዳውያንና ከአሕዛብ ልማድ የተወሰነ ክፍል በመውሰድ ተመሠረተ።

ስለዚህ ሳምራውያን በመካከለኛው ፓለስታይን ሰማርያ በምትባል ስፍራ የሚኖሩ የራሳቸው የሆነ ባሕልና ሃይማኖት የነበራቸው የተለዩ ሰዎች ነበሩ (ሉቃስ 17፡11)። ቀደም ሲል በአይሁዳውያን ቤተ መቅደስና የኢየሩሳሌም ቅጥር እንደገና መሠራቱን ተቃውመው ነበር (ዕዝ. 4፡1-10፤ ነህ. 4፡1-23)። ሳምራውያን አምልኮ መደረግ ያለበት በገሪዛን ተራራ ባለው በእነርሱ ቤተ መቅደስ ነው ሲሉ፥ አይሁዳውያን ደግሞ በኢየሩሳሌም ነው የሚል አቋም ነበራቸው። ከዚህም የተነሣ በአይሁዳውያንና በሳምራውያን መካከል ፉክክር ተጀመረ። አይሁዳውያን ከእነዚህ ቅይጥ ሕዝብ ጋር ማኅበራዊና ሃይማኖታዊ ስብሰባ ለማድረግ አልፈለጉም። ክርስቶስ በዚህ ምድር ላይ ይመላለስ በነበረበት ጊዜ አይሁዳውያን ከሳምራውያን ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት አልነበራቸውም። የአይሁዳዊ ሰው ከሳምራዊት ሴት ጋር መነጋገር ኢየሱስ በምድር ላይ በነበረበት ዘመን ያልተለመደ ነገር ነበር። ይህ ፈጽሞ የሚደረግ አልነበረም።

ክርስቶስ ኢየሱስ ከሳምራዊቱ ሴት ጋር ያደረገው ንግግር በአዲስ ኪዳን ውስጥ ክርስቲያናዊ አምልኮን በተመለከተ በጣም ጠቃሚ መልእክት አስተላልፎአል። ዛሬ ክርስቶስ ለሳምራዊቷ ሴት ስለ አምልኮ ያስተማረውን ትምህርት እንመለከታለን።

የዮሐንስ ወንጌል 4፡15-26 ያለውን አንብቡ።

1- ክርስቶስ ኢየሱስ በዮሐንስ ምዕራፍ 4 አምልኮን የሚመለከት ትምህርት የሰጠው በምን አጋጣሚ ነው?

ኢየሱስ በኢየሩሳሌም ዙሪያ በይሁዳ አያስተማረ ነበር (ዮሐ. 2፡13፥ 3፡36)። ከገሊላ ወደ ይሁዳ በሚያልፉበት ጊዜ ኢየሱስ በሰማርያ ሊያልፍ ግድ ሆነበት (4:4)። ከኢየሩሳሌም ወደ ገሊላ የሚያደርሱ ሦስት የተለያዩ መንገዶች ነበሩ። ነገር ግን በሰማርያ ወደ ገሊላ የሚያቋርጠው ከሁሉም አጭር ነበር። ከዚህም በላይ ኢየሱስ በሰማርያ ይፈጽመው ዘንድ ያለው ተልእኮ መኖሩን ያምን ነበር። መንገዱ ረዥም ከመሆኑ የተነሣ ኢየሱስ ደክመው። ስለሆነም ደቀ መዛሙርቱ በአቅራቢያ ካለው ከሰማርያ መንደር ምግብ ገዝተው እንዲመጡ አየጠበቃቸው በያዕቆብ ጉድጓድ አጠገብ ዕረፍት አደረገ (4:5-6)። በዚያ ተቀምጦ ሳለ ከቀኑ 6 ሰዓት ሲሆን ሳምራዊቱ ሴት ውኃ ልትቀዳ መጣች። ኢየሱስ ከእርሷ ጋር ንግግር ጀመረ (4:7-9)።

ኢየሱስ ነቢይ መሆኑን ስትገነዘብ አይሁዶች በኢየሩሳሌም እንደሚያመልኩ፥ ሳምራውያን ደግሞ ሰማርያ በሚገኘው በገሪዛን ተራራ ላይ እንደሚያመልኩ በአይሁዶችና በሳምራውያን መካከል ያለውን ልዩነት አስተዋለች።

2- ከሰማርያውያን ሴቶች አንጻር፥ አምልኮን በ-ተመለከተ በአይሁዶችና በሳምራውያን መካከል የነበረው ትልቅ ልዩነት ምንድን ነው? (4:20)። አይሁዶች በኢየሩሳሌም በሚያመልኩበት ጊዜ ሳምራውያን "በዚህ ተራራ" (ይህም በሰኬም ከተማ አጠገብ ያለው የገሪዛን ተራራ ነው) ያመልካሉ።

ለሳምራውያን በብሉይ ኪዳን የሚገኘው ቁልፍ ጥቅስ ዘዳግም 12:5 ነው። በሙሴ ጊዜ ወደ ከነዓን ከመግባታቸው በፊት አንድም ቦታ ገና አልተመረጠም ነበር። አይሁዶች የት ማምለክ እንዳለባቸው ገና ወደፊት የሚወሰን ጉዳይ ነበር። መጽሐፍ ቅዱስ በዘዳግም 12:5 ላይ፥ "ወደ መረጠው ስፍራ" እንደሚለው ሳይሆን "እግዚአብሔር የገሪዛምን ተራራ መረጠ" ተብሎ በሳምራውያን መጽሐፍ ውስጥ እንደ ሁነኛ የአምልኮ ቦታ ተመልክቷል። ትክክለኛው የአምልኮ ስፍራ ኢየሩሳሌም ነው ወይስ ገሪዛም ተራራ የሚለው አሳብ በአይሁዶችና በሳምራውያን መካከል ለዘመናት የቆየ ክርክር ነው። የሳምራውያን መጽሐፍ ቅዱስ በዚህ የተሳሳተ አሳብ እስከ ዛሬ ድረስ በሰማርያ ይገኛል።

3- እንደ አያት ቅድማያቶቻችሁ ትውፊት፥ አባቶቻችሁ ሊያመልኩ የሚገባቸው የት ነበር? ተወያዩበት። አንዳንድ ልማዶች በተወሰኑ ዛፎች አካባቢ ወይም በቤቱ አማኻኝ ስፍራ መሀል ሰመሀል በተተከለው ምሰሶ ግርጌ ወይም በጀምበር መውጫና መጥለቂያ ትይዩ ወይም በራስ ዳሽን ተራራ ትይዩ እንደሆነ ይናገራሉ።

4- ክርስቶስ እንደ አይሁዳውያኑ ኢየሩሳሌም ትክክለኛው የአምልኮ ስፍራ ነው በማለት ተከራክሯል? ክርስቶስ ለሳምራዊቷ ሴት የመለሰው እንዴት ነበር? (4:21) ክርስቶስ ለዘመናት በመካከላቸው የቆየው ክርክር አስፈላጊ ባለመሆኑ ወደ ጉን ጥሎታል። ክርስቶስ በዮሐንስ 4:21-24 ባለው ክፍል ላይ አስፈላጊው ነገር የአምልኮ ስፍራ የት መሆን አለበት የሚለው ሳይሆን፥ እንዴትና ማንን ማምለክ አለብን? የሚለው ነው ብሏል።

5- ዛሬ አንዳንድ ክርስቲያኖች የት ማምለክና መጸለይ ይገባናል ብለው ነው የሚያስቡት? ለአምልኮ አንዱ ቦታ ከሌላው ቦታ ይሻላል? ተወያዩበት። አንዳንድ ክርስቲያኖች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በሚጸልዩበት ጊዜ ለእግዚአብሔር እንደቀረቡ ያምናሉ። ክርስቶስ እንደዚህ ዓይነት አሳብ ካላቸው አንዳንድ ክርስቲያኖች ጋር ይስማማ ይሆን? (4:21) ተወያዩበት።

6- የክርስቲያኖች የአምልኮ ስፍራ ከቶ ጠቀሜታ ይኖረው ይሆንን? ተወያዩበት። እግዚአብሔርን በዛፍ ጥላ ሥር፥ በትምህርት ቤት ክፍል ውስጥ ወይም ለአምልኮ በተሠራ ሕንፃ ውስጥ ወይም በየትም ስፍራ ልናመልክ እንችላለን። የቦታ ጠቀሜታና ጎጂነት የሚለካው እግዚአብሔርን በመንፈስና በእውነት ለማምለክ ከመርዳቱ ወይም ከማቀቡ አንጻር ብቻ ነው። የምናመልክበት ስፍራ እግዚአብሔርን እንዳናስብ የሚያደርገን ከሆነ፥ ያ ቦታ ትክክለኛ ቦታ አይደለም? ከእግዚአብሔር ሰዎች ጋር የምታመልክበት ስፍራ ለአምልኮህ የሚረዳ ነው ወይስ አይደለም? ለአምልኮ የምትገለገልበት ስፍራ በደንብ እንዳታመልክ የሚከለክልህ ስፍራ ነው? ተወያዩበት። በእግዚአብሔርና በቃሉ ላይ በበለጠ ለማተኮር ይቻል ዘንድ የአምልኮ ቦታን ለማሻሻል ምን ማድረግ ይቻላል? ተወያዩበት።

7- ክርስቶስ የአይሁድ አምልኮ ከሳምራውያን እንደሚበልጥ ያመነው በምን መንገድ ነው? (4:22) ተወያዩበት። ሳምራውያን የብሉይ ኪዳንን ሕግ (ከዘፍጥረት - ዘዳግም) ብቻ ተቀብለው፥ የትንቢትና የግጥም መጻሕፍትን (ኢያሱ-ሚልክያስ) ያገልላሉ። ስለዚህ ሳምራውያን ስለ እግዚአብሔር የብሉይ ኪዳን ሙሉ መገለጥ የላቸውም። እግዚአብሔርን የሚያመልኩት ባለማወቅ ነው፤ የምናባቸውን አምላክ እንጂ በብሉይ ኪዳን መጽሐፍ የተገለጸውን ያህዌን አያመልኩም። አይሁዶች በሌላ ጉን ስለ እግዚአብሔር የተሻለ ትምህርት ነበራቸው። ስለሆነም ኢየሱስ፥ "የማታውቁትን ታመልካለችሁ" ብሎአቸዋል። ከዚህም

በላይ ደኅንነት ከአይሁድ እንጂ ከሳምራውያን አልመጣም። ያም ክርስቶስ የዓለም መድኃኒት እንደ አይሁዳዊ ሆኖ ተወልዷል (መዝ. 147:19-20፤ ኢሳይያስ 2-3፤ ሚኪያስ 4:1-2)።

8- በእነዚህ አምስት ጥቅሶች (ዮሐ. 4:20-24)፥ አምልኮና አምላኪዎች የሚለው ቃል ዘጠኝ ጊዜ ሥራ ላይ ውሎአል። አንተ በምታውቀው ቋንቋ አምልኮ ማለት ምን ማለት ነው? ተወያዩበት።

9- እግዚአብሔርን ስለማምለክ በምንነጋገርበት ጊዜ ምን ማለታችን ነው? እግዚአብሔርን ማምለክ ለእርሱ የሚገባውን ከፍተኛ ዋጋ በመስጠት እግዚአብሔርን ማክበር ነው። እግዚአብሔርን ማምለክ ሙሉ ታማኝነታችንንና ፍቅራችንን እንደዚሁም መሰጠታችንን ለእርሱ ማቅረብ፥ እግዚአብሔር ብቻ የእኛ ምስጋናና አድናቆት የሚገባው መሆኑን መመስከር ነው። አምልኮ ተቀባይነት ባለው የአክብሮት ምስጋና፥ ልባዊ ፍርሃት፥ እምነትና ታዛዥነት መንገድ ለእግዚአብሔር ምላሽ መስጠት ነው።

10- ከዚህ በፊት እንደተመለከትነው አምልኮ የሚካሄድበት ስፍራ ያን ያህል አስፈላጊ ካልሆነ፥ ለእውነተኛ ክርስቲያናዊ አምልኮ ከሁሉም የሚልቀው ነገር ምንድን ነው? (4:23-24) "በመንፈስና በእውነት ማምለክ"- ይህም የልብ ዝንባሌ ነው።

11-"በመንፈስና በእውነት" አብን ማምለክ ምን ማለት ነው?

በመንፈስ:- እውነተኛ አምልኮ ከሰውዬው ውስጥ ይወጣና በመንፈሱ አማካኝነት ይቀርባል። እውነተኛ አምልኮ ውስጣዊና መንፈሳዊ እንጂ፥ ውጫዊና ቁሳዊ አይደለም። እንደ የአምልኮ ስፍራን ከመሳሰሉት ቁሳዊ የአምልኮ መመዘኛዎች በተቃራኒ፥ በእውነተኛ አምልኮ ለእግዚአብሔር የሚገባውን ክብር ከሙሉ ልባችን እናቀርባለን።

በእውነት:- እውነተኛ አምልኮ በቃሉ እንደተገለጸው ከእግዚአብሔር እውነት ጋር ሙሉ በሙሉ በመስማማት የሚካሄድ ነው። አምልኮ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሊሆን ይገባል። እንደ እውነተኛ የሃይማኖት ትምህርት፥ ስለ እግዚአብሔር፥ ስለ ሰው፥ ስለ ኃጢአት፥ ስለ ክርስቶስ ኢየሱስ፥ ስለ መንፈስ ቅዱስ፥ ስለ ዳግም ልደትና ስለ ደኅንነት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርትን ያማከለ ነው። እግዚአብሔርን በእውነት ማምለክ ማለት የምትዘምረውን፥

የምትጸልየውንና በአምልኮ ውስጥ የምታከናውነውን ተግባር ሁሉ በትክክል ማለትና ማድረግ ማለት ነው።

12- በመንፈስ ዳግም ያልተወለደ ሰው እግዚአብሔርን በመንፈስና በእውነት ማምለክ ይችላል ወይ? ተወያዩበት። የለም አይችልም፥ ምንም እንኳን አንዳንድ የአምልኮ ሥርዓቶችን ቢፈጽምም።

13- ዮሐንስ 4:23 ስለ ትክክለኛ አምላኪዎች ይናገራል። እንዴት ትክክለኛ አምላኪ መሆን እንደሚቻል ከተረዳህ፥ ትክክለኛ አምላኪዎች አይደሉም ስለሚባሉት ሰዎች ግለጽ። እግዚአብሔርን ሳያመልኩት ይህንኑ እያደረጉ እንዳሉ ስለሚያስቡት ሰዎች ምንነት ተወያዩ። አንዳንድ ሰዎች ይበልጥ ጉዳዬ የሚሉት ወደ ቤተ ክርስቲያን መሄዳቸውንና ተለምዷዊ የቤተ ክርስቲያን የአምልኮ ሥርዓት መካፈላቸውን ነው። እነዚህ ሰዎች ሊታይና ሊሰማ በሚችል ውጫዊ ነገር ላይ ያተኩራሉ። ጸሎት በማቅረባቸው፥ ምጽዋት በመስጠታቸው፥ በኳየር ውስጥ በመዘመራቸውና መልእክት በማድመጣቸው እግዚአብሔር ደስ የሚለው ይመስላቸዋል። ራስን ዝቅ በማድረግና በመንፈሳዊ ዝንባሌ ለእግዚአብሔር ልባዊ አክብሮት ማቅረብን እንደ ዋነኛ ነገር አያዩቱም። እንደዚሁም በአምልኮ ላይ መጽሐፍ ቅዱስ ስለሚሰጠው ትምህርት ደንታ የላቸውም። በዋናነት የሚያተኩሩት በቤተ ክርስቲያን ወግና በልማድ በሚፈጸም ውጫዊ የአምልኮ ሥርዓት ላይ ነው።

14- እግዚአብሔር በእውነት የሚያመልኩትን እንዴት ይመለከታቸዋል? ስለ እነርሱ ምን ይሰማዋል? (4:23)። እግዚአብሔር ሕዝቡ እውነተኛ አምላኪዎች እንዲሆኑ በጉጉት ይጠብቃል። ይህ ማለት የእርሱ የሆኑት ብዙዎች እርሱ እንደሚፈልገው አያመልኩትም ማለት ነው።

15- እውነተኛ አምልኮ በጣም አስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው? (4:24)። ከእግዚአብሔር ማንነት የተነሣ ነው። እርሱ የእውነት አምላክ ስለሆነ፥ እግዚአብሔርን ልናመልክ የምንችለው የቃሉን እውነት ስንታዘዝ ብቻ ነው። እርሱ መንፈስ ስለሆነ፥ ልናመልከው የምንችለው በመንፈሳችን ብቻ ነው። እግዚአብሔር ከድንጋይ ወይም ከእንጨት የተሠራ አምላክ ባለመሆኑ፥ በየትም ቦታና በማንኛውም ጊዜ ሊመለክ ይችላል። ይህም የእርሱን ማንነት በማሰብ ማለትም የመንፈስና የእውነት ጌታ መሆኑን በማስታወስ የሚካሄድ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ እውነት ላይ በመመሥረትና ከልባችን በሆነ ነገር ልንቀርበው ይገባል።

16- **እግዚአብሔር "ከመንፈስና ከእውነት" ያልሆነውን አምልኮአችንን ይቀበል ይሆን?** (4:24)። የለም! ጅማሬ የሌለውና ዘላለማዊ ፈጣሪ የሆነው አምላክ በመንፈስና በእውነት እንድናመልከው የሚጠብቅብን አካላዊ መንፈስ ነው። የእግዚአብሔር ሰዎች ምንም ምርጫ የላቸውም። ልናመልከው ካስፈለገን በመንፈስና በእውነት ልናመልከው ይገባል።

17- አባቶቻችን እግዚአብሔርን በታማኝነት ያመልኩት ነበር። **አምልኮአቸውን በመንፈስና በእውነት ይፈጽሙ ነበር?** ተወያዩበት። በመንፈስና በእውነት ሊሰግዱ አይችሉም፤ ምክንያቱም የእግዚአብሔር ብቸኛና እውነተኛ ወደ እርሱ የሚያደርስ መንገድ ክርስቶስ መሆኑን ካለማወቃቸውና ዳግም ካለመወለዳቸው የተነሣ ነው (ዮሐ. 14:6)።

የእግዚአብሔርን ቃል ማድረግ፤ በአንተ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የአንተንና የሌሎችን ሰዎች አምልኮ አስብ። እግዚአብሔርን ደስ በሚያሰኝ መንገድ ነው እያመለክህ ያለኸው? አስብበት።

ጸሎት፤ እግዚአብሔርን ይበልጥ እንዴት አድርገህ በእውነት እንደምታመልከው ያስተምርህ ዘንድ አየጠየቅህ ጸልይ።

የክርስቲያናዊ አምልኮ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትርጉም ማጠቃለያ

1- አምልኮ ስለ እግዚአብሔር ማንነትና እርሱም ስላደረገልን ነገር እያሰብን ፍቅራችንንና መሰጠታችንን፥ ልባዊ ፍርሃታችንን፥ አክብሮታችንን፥ ምስጋናችንን፥ መታዘዛችንን ለእግዚአብሔር ሁልጊዜ ማቅረብ ነው።

2- ክርስቲያናዊ አምልኮ እግዚአብሔር ከሁሉም በላይ እንደሆነ መመስከር ነው፤ ምክንያቱም እርሱ ብቻ ፍቅራችን፥ መሰጠታችንና አክብሮታችን የሚገባው ነውና።

3- በክርስቲያናዊ አምልኮ የመነሻውን እርምጃ የሚወስደው እግዚአብሔር ነው። በቅድሚያ እርሱ ራሱን ለወንዶችና ለሴቶች በፍጥረት፥ በዕለት ተዕለት ኑሮአችን፥ በቃሉ መንፈስ መረዳት በሰጠን መጠን ይገለጥልናል። በመጽሐፍ ቅዱስ አምልኮ በሚያመልከው ሰው አይጀምርም። አምልኮ የሚጀምረው ትልቅ ዋጋ ኖሮትና አምልኮአችን ተገብቶት ራሱን በሚገልጽልን አምላክ ነው።

በክርስቲያናዊ አምልኮ ለእግዚአብሔር መገለጥ በቅዱስ ፍርሃትና ፍቅር በመስገድ ሰዎች ምላሻቸውን ይሰጣሉ።

4- እውነተኛና ሕያው የሆነውን አምላክ በምንመለከትበት ጊዜ ሁለት ዓይነት ስሜት ከሰው ልብ ይመነጫል። ቅዱስ ፍርሃትና ቅዱስ ፍቅር። ፍርሃት ያለ ፍቅር መሰበርን ያስከትላል። ፍቅር ያለ ፍርሃት ደግሞ ማስመሰል ይሆናል። እግዚአብሔር አምላክ ከእኛ በጣም ከፍ ያለ አምላክ ነው፤ ደግሞም የቅርባችን ነው። እግዚአብሔር ቅዱስ ስለሆነ ቅዱስ በሆነ ፍርሃት፥ መንቀጥቀጥና መታመን ባለበት አቀራረብ ምላሽ እንሰጠዋለን። እግዚአብሔር ፍቅር ስለሆነም፥ ደኅንነትን ክርስቶስን በማመን በጸጋ ብቻ ስለሰጠን፥ በምስጋና፥ በፍቅርና በአክብሮት ምላሹን እንሰጠዋለን።

5- አምልኮ የእግዚአብሔር ሕዝብ ለመጸለይ፥ ለማመስገን፥ ኃጢአቱን ለመናዘዝ፥ የእግዚአብሔርን ቃል ለማንበብ፥ ለመስማት፥ ለማስተማር፥ የጌታን እራት ለመዘከርና ምጽዋትን ለጌታ ለመስጠት በግልጽ በሚነሣሡበት ጊዜ የሚፈጸም ነው። የአደባባይ አምልኮ የእግዚአብሔር ሕዝብ በጎብረት የሚሆኑበት ትልቅ ምክንያት ነው።

6- ነገር ግን ክርስቲያናዊ አምልኮ ዙሪያውን በተከበበ ቤት ውስጥ ብቻ የተወሰነ አይደለም። ሕይወት ሁሉ ከአምልኮ ጋር የተያያዘ መሆን አለበት። እግዚአብሔርን በሁለንተናችን ስንወድ ነቅተን ባለንበት በእያንዳንዱ ደቂቃ እናመልከዋለን። እግዚአብሔርን በነገር ሁሉ ለመታዘዝ ስንሻ፥ ሁልጊዜ ስናከብረው፥ ስናመሰግነው፥ ከእርሱ ክብር ጉድለን ኃጢአታችንን በምንናዘዝበት ጊዜ፥ እርሱን እያመለክን ነን። እግዚአብሔርን በምናከብርበት ጊዜና የእርሱን ጸጋ ለሌሎች በምናውጅበት ጊዜ እግዚአብሔርን በማገልገል እያመለክን ነው።

7- እንደ ግለሰብ በግል ኑሮአችን እግዚአብሔርን እናመልካለን። እንደዚሁም ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር በቤተ ክርስቲያን ውስጥ፦

ሀ/ ስለሰጠን በረከት ስናከብረው፥

ለ/ ስለ ግርማውና ክብሩ አድናቆታችንንና መገረማችንን ስናቀርብለት፥

ሐ/ ከቅዱስ ፍርሃት ጋር ደስታችንንና ምስጋናችንን በምላሹ ስናቀርብ፥

መ/ ከልባችን ለእርሱ ጥማት ሲያድርብን፥

ሠ / በሳምንቱ ቀናት ሁሉ ለእግዚአብሔር ፈቃድ ስንታዘዝ፥

ረ / በመንፈስና በእውነት አምልኮአችንን ስናቀርብ በዚህ ሁሉ እናመልከዋለን።

8- ምንም እንኳ ስሜት የሌለው ባይሆንም፥ ክርስቲያናዊ አምልኮ በዋነኛነት የስሜት ማለትም የእድናቆት፥ የመገረም ጉዳይ አይደለም። ክርስቲያናዊ አምልኮ በመንቀጥቀጥ የመታዘዝና በአእምሮአችን ራሱን ለገለጸልን ጌታ የፍርሃትና የመደነቅ ምላሽ መስጠት ነው። አምልኮ ብቻውን ታላቅ ክብር ለተገባው ለእግዚአብሔር የእኛ መሰጠትና መታዘዝ ነው።

9- የእግዚአብሔር ሕዝብ ሊያመልከው ታዝዟል (መዝ. 96:8፤ 99:9)። ይህ የእኛ ዋና ተግባርና ኃላፊነት ነው።

ክፍል ሁለት

የምናመልከው አምላካችን

በአምልኮ በጣም አስፈላጊው ክፍል የምናመልከው አምላካችን ነው። እግዚአብሔር ቀድሞውኑ ባይኖር ኖሮ፥ አምልኮም ባላስፈለገም ነበር። እግዚአብሔር ራሱን እንደገለጸልን ሆኖ ባይገኝ ኖሮ፥ አምልኮአችን ከንቱ ይሆን ነበር።

እግዚአብሔርን በምታስብበት ጊዜ ወደ አእምሮህ ምን ይመጣል? አንተን በተመለከተ ይህ በጣም አስፈላጊ ነገር ነው። ስለ እግዚአብሔር በትክክል የምናውቀውና የምናምነው ነገር የምናቀርብለትን የአምልኮ ዓይነት ይወስናል። ስለ እግዚአብሔር ያለን እውቀት የአምልኮ ሁሉ መሠረት ነው። እውነተኛ አምልኮ ተፈጥሮአችንን ሁሉ ለእግዚአብሔር ማስገዛት ነው። በአምልኮ ላይ መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነ ጥልቅ ትምህርት ይኖረን ዘንድ ራሳችንን ለማዘጋጀት፥ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እግዚአብሔር ስለ ራሱ የገለጻቸውን አንዳንድ እውነቶች ከአሁን ጀምረን ለማሰብ እንፈልጋለን። ይህ መጽሐፍ የአምልኮ ጥናት በመሆኑ፥ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እግዚአብሔር የሚያስተምረውን በሙሉ ለማጥናት አንችልም ። ነገር ግን የሚቀጥሉት ሦስት ጥናቶች በአምልኮ የላቀ ክብር የተገባውን የእግዚአብሔርን ትልቅነት ለማሳየት ሆን ተብለው የተዘጋጁ ናቸው።

ጥናት ሰባት

ስለ እግዚአብሔር ሁሉን ነገር መረዳት ባንችልም፥ እግዚአብሔርን ልናውቅ እንችላለን።

ኢሳይያስ 40:12-26፤ ዕብራውያን 1:1-4

ዓላማው:- እንደ ኢሳይያስ 40:12-26 አገላለጽ፥ እግዚአብሔር በጣም ታላቅ ከመሆኑ የተነሣ ሙሉ ለሙሉ ሊታወቅ ወይም ሊረዱት የማይቻል መሆኑን ለማሳየት ነው። ይሁንና፥ በዕብራውያን 1:1-4 ያለው ክፍል እንደሚናገረው እግዚአብሔር በትክክል ከማንነቱ እናውቀው ዘንድ ለወንዶችና ለሴቶች ራሱን ሊገልጽ መርጧል።

የዓላማው ማብራሪያ:- በአንድ በኩል እግዚአብሔር ታላቅ

ስለሆነ ሙሉ በሙሉ ልንረዳው አንችልም። በሌላ በኩል ግን እግዚአብሔር ሴቶችና ወንዶች በግል እንዲያውቁትና እንዲያገለግሉት ይፈልጋል። ይህ ለመረዳት ከባድ ይመስላል። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረን ይህንኑ ነው ። እግዚአብሔር እኛ ማወቅ ከምንችለው በላይ ከፍ ያለ ነው። ይሁንና፥ እግዚአብሔር ቅርባችን ነው። ለሚያምኑትና ለሚታዘዙት ራሱን ሊገልጽ ይፈልጋል። በዛሬው ዕለት ለማጥናት የምንፈልገው ይህንኑ ነው ።

(ማስታወሻ፡- ይህን ጥናት ለመጨረስ ብዙ ጊዜ ያስፈልግህ ይሆናል። ከሆነም ይህን አንድ የጥናት ክፍል ሁለት የትምህርት ክፍል በመውሰድ መጨረስ ይቻላል።)

የትምህርቱ አቀራረብ፡- ጥንት ወንጌል ከመግባቱ በፊት፥ በሕዝባችን መካከል ሰዎች ስለ እግዚአብሔር ታላቅነት ምን እያሉ ያስተምሩ ነበር? ተወያዩበት። እፍሪካውያን ብዙ የተለያዩ ነገሮችን ብለዋል። በኬንያ ሔሬሮ የተባለው ጎብረተሰብ እግዚአብሔር ከፍ ባለ ቦታ ስለሚኖር እርሱ ወዳለበት መድረስ አንችልም ይላሉ። ኩኩዩዎች እግዚአብሔርን በታላቅነት ማየት አስፈሪ ስለሚሆን የነጉድጓድ ድምፅ በሚሰማበት ጊዜ ሰዎች ወደ ሰማይ እንዳይመለከቱ ያስተምሩ ነበር። ቶንጌ የተባሉት እግዚአብሔር ቦታዎችን ሁሉ የሚሞላ ገደብ-የለሽ እንደሆነ ይናገራሉ። አካን የተባሉት ደግሞ ከእርሱ በላይ ምንም የሌለ እርሱ ብቻውን የተትረፈረፈ እምላክ እንደሆነ ይናገራሉ። ሜንዴ የተባለው ጎብረተሰብ እንደዚሁ በላይ በከፍታ ያለ በማለት ይጠሩታል።

ስለ እግዚአብሔር ታላቅነት መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል? መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር በማንነቱ በጣም ታላቅ ስለሆነ ሰዎች ሙሉ በሙሉ ሊረዱት እንደማይችሉ ያስተምራል። ቅዱሳን መጻሕፍት እንደሚሉት፥ እግዚአብሔር ራሱን ይሰውራል (ኢዮ. 23:9፤ 34:29)፤ እግዚአብሔር ማንም ሊቀርበው በማይችል ብርሃን ይኖራል (1ኛ ጢሞ. 6:16)። እግዚአብሔር እጅግ ታላቅ በመሆኑ፥ ምሥጢራዊ ነው። እግዚአብሔርንና መንገዱን ሙሉ በሙሉ ልንረዳ አንችልም። ይሁንና፥ እግዚአብሔር በወንዶችና በሴቶች ሊታወቅ በመፈለጉ ራሱን በግል ገልጾላቸዋል።

ነቢዩ ኢሳይያስ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለማበረታታት በመሞከር ስለ እግዚአብሔር ታላቅነት የተናገረውን እንመልከት።

ኢሳይያስ 40:12-26 አንብቡ።

1- እግዚአብሔር ብቻ ሊያደርጋቸው የሚችላቸውና ሌሎች ግን የማይችሏቸው የተለያዩ ተግባራት የትኞቹ

ናቸው? (40-12-14)

ቁጥር 12 እንደሚለው የባሕሩን ውኃዎች ሁሉ በእጁ ይይዛል።

እርሱ ሰማይን በእጁ ይሠፍራል።

እርሱ የምድርን አፈር በቅርጫት ይይዛል።

እርሱ ተራሮችን በሚዛን ይመዝናል።

ቁጥር 13 ማንም አላስተማረውም።

ቁጥር 14 እርሱ ከማንም ምክርን አልጠየቀም።

ማንም እውቀትን አላስተማረውም፤ እርሱ ሁሉን ነገር ያውቃል።

2- ኃያላን (ታላላቅ) መንግሥታት ከእግዚአብሔር ጋር የሚወዳደሩት እንዴት ነው? (40:15-17)

ቁጥር 15 አሕዛብ ሁሉ በገንቦ ውስጥ እንዳሉ ጠብታ ናቸው።

ቁጥር 17 እነርሱ ከምንም ያነሱ ናቸው።

3- ታላቅ የሆነው እግዚአብሔር ከእንዳች ነገር ጋር ሊወዳደር ይችላልን? (40:18፥ 22-25) የለም! ቁጥር 18-25፥ እርሱ ከሌላ ከምንም ነገር ጋር መወዳደር አይችልም። አበበ ቢቂላ የተባለው ሰው በዘመኑ ከሌላ ከማንም ጋር መወዳደር አይችልም ነበር። ምክንያቱም በጊዜው እርሱ በማራቶን በጣም ጥሩ ሯጭ ነበር። ነገር ግን በአሁኑ ጊዜ የእርሱ ክብረ ወሰን ተሻሽሎአል። እግዚአብሔር ግን ሁልጊዜ ታላቅ ነው። ሁልጊዜም ከሁሉ የሚሻል ነው።

ቁጥር 22 እንደሚለው፥ ከሰዎች ሁሉ በላይ ለሆነው ለእርሱ፥ ሰዎች በፊቱ እንደ እንበጣ በጣም ትንሽ ናቸው። እርሱ ከፈጠራቸው ሁሉ በላይ ነው።

4- እግዚአብሔርን በዓለም ከሚገኙ ታላላቅ ሰዎች ጋር ልናነጻጽረው እንችላለን? (40:23-24) የለም! ለምን? ምክንያቱም ታላላቅ ሰዎች ሁሉ አንድ ቀን ያልፋሉ። እርሱ ግን ለዘላለም ይኖራል። እግዚአብሔር ገዢዎችን ከንቱ ያደርጋቸዋል። ነገሥታት ወይም ፕሬዚዳንቶች ሳይሆኑ እግዚአብሔር ይገዛል፤ የእነርሱ ኃይል የተወሰነ ነው፤ የእርሱ ግን ወሰን የለውም፤ የሕይወት ዘመናቸው አጭር ነው። እርሱ ግን ዘላለማዊ ነው። እርሱ ጅማሬና ፍጻሜ የለውም።

5- **ወደ ሰማይ ከዋክብት ተመልከት:: ስለ እግዚአብሔር ታላቅነት የሰማይ ከዋክብት ምን ይነግሩናል?** (4:26) ሊቆጠሩ የማይችሉ የከዋክብት ክምችት በእርሱ ዘንድ የታወቁ ናቸው:: እያንዳንዱን የፈጠረና በሰማይ ላይ ያኖራቸው እርሱ ብቻ ነው:: የእግዚአብሔር ኃይል ታላቅ ከመሆኑ የተነሣ የትኛውንም ከከዘ ካለበት ሰፍራ የሚነቀንቀው የለም::

6- **የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ስለ እግዚአብሔር ታላቅነት የሚያስተምረው አሳብ ከአፍሪካውያን ባሕላዊ እምነት ጋር የሚነጻጸረው እንዴት ነው?** ተወያዩበት:: የአፍሪካውያን ባሕላዊ ሃይማኖት ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ጋር አይቃረንም:: መጽሐፍ ቅዱስና የአፍሪካውያን ባሕላዊ እምነት እግዚአብሔርን ሙሉ በሙሉ ለመረዳት እንደማይቻል ይናገራሉ:: እግዚአብሔር ከዚህ ዓለም ካሉት ከማናቸውም ነገሮች ጋር አይወዳደርም::

ዕብራውያን 1:1-4 አንብቡ::

7- **እንደ መጽሐፍ ቅዱስ አሳብ፥ ይህ ታላቅና ልንረዳው የማንችለው አምላክና ፈጣሪ በሰዎች ዘንድ መታወቅ ይፈልጋልን?** (ዕብ. 1:1-4 ያለውን ተመልከት):: አዎን፥ እግዚአብሔር ራሱን ለሰዎች ገልጾአል:: እርሱ ሊመለክ፥ ሊከበር፥ ሊገለገልና፥ ሊታወቅ የሚገባው ብቻውን እውነተኛ የሆነ አምላክ ነው:: እርሱ ከሁሉም በላይ የሆነና የእጁም ሥራ አካል እንዳልሆነ ቢታወቅም፥ ራሱን ለፍጥረቱ ማለትም ለአዳምና ሔዋን ወንዶችና ሴቶች ልጆች ገልጾአል::

8- **እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን ዘመን ራሱን የገለጸው እንዴት ነበር?** (1:1) እግዚአብሔር ለሕዝበ እስራኤል በነቢያት አማካኝነት በተለያዩ መንገዶች ተናግሮአል፤ አብርሃም (ዘፍ. 12)፥ ሙሴ (ዘጸ. 3)፥ ዳዊት (2ኛ ሳሙ. 7)፤ ነቢያት ኢሳይያስ፥ ኤርምያስ፥ ዳንኤል:: ራሱን በቃሉ አማካኝነት፥ በድርጊት፥ በሕልም፥ በራእይና በሰው አምሳል ገልጾአል::

9- **በመጨረሻ፥ እግዚአብሔር ለወንዶችና ለሴቶች የተናገረው እንዴት ነበር?** (1:2):: በልጁ አማካኝነት (ዮሐ. 1:18-14፥ 6፥9፤ ቆላ. 1:15ን እንደዚሁም ተመልከት)::

10- ዕብራውያን 1:1-2 ወደ ብሉይ ኪዳን (ነቢያት) እና ወደ አዲስ ኪዳን መገለጥ (ወደ ልጁ) ያመለክታል:: አዲስ ኪዳን ከብሉይ ኪዳን ጋር ያለው ዝምድና ምንድን ነው? አዲስ ኪዳን

ከብሉይ ኪዳን ጋር ይቃረናል ወይ? ተወያዩበት:: የለም:: ምንም ዓይነት ተቃራኒነት የላቸውም (ይህም ማለት ብሉይና አዲስ ኪዳን እርስ በርሳቸው ይስማማሉ):: ብሉይ ኪዳን ከአዲስ ኪዳን በእውነተኛነቱ አያንስም:: ነገር ግን የብሉይ ኪዳን ተስፋዎች፥ አምሳያዎችና ትንቢቶች በአዲስ ኪዳን ተፈጽመዋል:: በብሉይ ኪዳን ውስጥ እግዚአብሔር በልጁ በኩል ስለሚሆነው የመጨረሻ መገለጥ ሲያዘጋጅ ቀለል ባሉ መንገዶች ተናግሮአል::

11 **ወንጌል ከመምጣቱ በፊት እግዚአብሔር ለአፍሪካውያን አባቶች ተናግሮአልን?** ከሆነ፥ እንዴት? (መዝ. 19:1-6፤ ሮሜ 1:20፥ 2:14-15) ተወያዩበት:: እግዚአብሔር በተፈጥሮና ሕሊና አማካኝነት ለሁሉም ሰው በመንፈሱ ይናገራል:: ይህም አጠቃላይ መገለጥ ይባላል፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር በተፈጥሮ ሕሊና አማካኝነት በሁሉም ስፍራ ለሚገኙ ሰዎች በአጠቃላይ ራሱን ስለሚገልጥ ነው:: ሰዎች ዓለምን (ፍጥረትን) በሚመለከቱበት ጊዜ የእግዚአብሔርን እጅ ማየት ይችላሉ:: እንደዚሁም የሰው ልጅ በሕሊናው አማካኝነት ስለ ትክክለኛውና ትክክል ስላልሆነው ነገር ስለ እግዚአብሔር ትእዛዝ የተወሰነ ነገር ያውቃል::

12- **እግዚአብሔር ወንጌል ከመምጣቱ በፊት ለአባቶቻችን ራሱን ከገለጠላቸው፥ በዚያ መገለጥ አማካኝነት ሊድኑ ይችላሉ?** (ሮሜ 12-16፥ የሐዋ. 17:30) ተወያዩበት:: የሙሴን ሕግ ፈጽሞ ያልሰሙት በሕግ አይፈረድባቸውም:: ፍርዳቸውን የሚያገኙት በተሰጣቸው ሕግ ማለትም በሕሊናቸውና በልባቸው ውስጥ ባለው ሕግ ነው:: ያንን ሕግ ጠንቅቀው ካልጠበቁ ፍርዳቸውን ይቀበላሉ:: ሁሉም ሰው ኃጢአትን ሠርቶአል የእግዚአብሔርም ክብር ጐድሎታል (ሮሜ 3:23):: ጥቂት ብርሃን ካገኙት አባቶቻችን ወንጌልን ሰምተን ላልተቀበልነው ቅጣቱ ይብሳል (ሉቃስ 12:47-48)::

13- **እግዚአብሔርን ለሰዎች እንደሚናገር የምታስበው ለምንድን ነው? ሰዎች እርስ በርሳቸው የሚነጋገሩት ለምንድን ነው?** ተወያዩበት:: ሰዎች የሚናገሩት ከሰዎች ጋር ለመግባባትና፥ አሳብ ለመለዋወጥ፥ጎብረት ለማድረግና ለመታወቅ ነው:: ምንም እንኳን እግዚአብሔር ሙሉ በሙሉ ባይታወቅና ልንረዳው ባንችልም፥ በትክክል ሊታወቅ ይችላል፤ ምክንያቱም ተናግሯልና ስለ ራሱም እውነተኛውን ነገር ገልጾልናልና::

14- **መጽሐፍ ቅዱስ በዕብራውያን 1:2-4 ባለው ክፍል**

ኢየሱስን እንዴት ገለጸው? ክርስቶስ የፍጥረት ሁሉ በኩር እንዲሆን ተወሰኖአል። ዓለም በክርስቶስ አማካኝነት ተፈጥሮአል። ኃያል በሆነው ቃሉም ተናግሮአል። "ልጄ የእግዚአብሔር የክብሩ ነጸብራቅ" ና "የባሕርዩ ትክክለኛ ምሳሌ" ነው። "ኃጢአታችንንም በራሱ ካነሣ በኋላ በሰማያት በግርማው ቀኝ ተቀመጠ።"

ዘፀብ. 1:2-4 ላይ የጠለቀ ማብራሪያ። ለባቱ ሐረጉች ወይም ገለጻዎች እያንዳንዳቸው ምን ይላሉ?

ሀ. "ሁሉን ወራሽ ባደረገው" (መዝ. 2:8ን ተመልከቱ)። እግዚአብሔር አብ ዓለምን ሁሉ እንዲወርስ ለልጁ ተስፋ ሰጥቶታል።

ለ. "ዓለማትን በፈጠረበት በልጁ" (ዮሐ. 1:1-3 ን ተመልከቱ)። እግዚአብሔር ወልድ ዓለምን ሁሉ የፈጠረውና ለራሱም ያደረጋቸው እርሱ ነው (ቆላ. 1:16)።

ሐ. "ልጁ የእግዚአብሔር ክብር ነጸብራቅ ነው" - ነጸብራቅ እንደ ፀሐይ ጮራ ነው። ክርስቶስ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ክብር እውነተኛ አምሳል ነው። ልክ የፀሐይ ጮራ፡ ብርሃን ሙቀትና ሌሎችንም ጥቅሞች ከፀሐይ ወደ ምድር እንደሚያወጡ፡ የእግዚአብሔር ልጅም የራሱን የእግዚአብሔር ክብርና ጸጋ ያሳያል።

መ. "የባሕርዩ ትክክለኛ" - የመግባቢያ ፍራንክ በሚሠራበት ጊዜ ቅርጽ ማውጫውን በቀለጠ ብረት ላይ በመጫን ይበጃል። ፍራንኩ ልክ ቅርጽ የለጠውን ቅርጽ ማውጫ ይመስላል። እንደዚሁም ሁሉ ክርስቶስ ኢየሱስ የእግዚአብሔርን ተፈጥሮ ትክክለኛ ማኅተም ይዞአል። እግዚአብሔር በትክክል የሆነው በክርስቶስ በኩል ተገልጦአል።

ሠ. "ሁሉን በሥልጣኑ ቃል እየደገፈ" -ልጁ ክርስቶስ ሁሉን ነገር መፍጠር ብቻ ሳይሆን፡ ነገር ግን ሁሉንም ነገር ደግፎአል። ዓለምን እንዳትፈራርስ ይጠብቃታል።

ረ. "ኃጢአታችንን በራሱ ካነጻ በኋላ ..." -ኢየሱስ በመስቀል ላይ በመሞት ከኃጢአት የመንጻትን መንገድ አዘጋጅቷል።

ሰ. "በሰማያት በግርማው ቀኝ ተቀመጠ" (መዝ. 110ን ተመልከት)። "ቀኝ" በጣም አስፈላጊ ስፍራ መሆኑን ያመለክታል። ከሞቱ፡ ከትንሣኤውና ከዕርገቱ በኋላ ክርስቶስ ኢየሱስ ሁሉም ለው ሊሰግድለትና ሊያመልከው ወደሚችልበት ከፍተኛው ስፍራ ተወሰደ (ፊልጵ. 2:9-10)።

በማጠቃለያው፡ ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔርን ባሕርይና ፈቃድ ለሰዎች ለመግለጽ ሰው የሆነ አምላክ ነው ማለት እንችላለን። እግዚአብሔር ባለፉት ጊዜያት በነቢያት የተናገረ ሊሆን፡ የእግዚአብሔር የመጨረሻ መገለጥ በልጁ በኩል ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ቃል ነው (ዮሐ. 1:1-3)። እግዚአብሔር የእርሱ ትክክለኛ አምሳል በሆነው በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ሙሉ በሙሉና በማጠቃለያው ላይ ተናግሯል።

15- **እግዚአብሔርን ልንረዳው እስከማንችል ድረስ ታላቅ ከሆነ እርሱን ማወቅ እንችል ይሆን?** ተወያዩበት። አዎን፡ እግዚአብሔር ታላቅ በመሆኑ ስለ እርሱ ያለውን ነገር ሁሉ ማወቅ ባንችልም፡ እግዚአብሔርን በትክክል እርሱን በገለጸው በኢየሱስ ክርስቶስ አማካኝነት ልናውቀው እንችላለን። እግዚአብሔርን በመጽሐፍ ቅዱስ፡ በፍጥረትና ራሱን ሊገልጽ በወደደው ነገር ሁሉ ልናውቀው እንችላለን።

16- **እግዚአብሔርን ማወቅ ማለት ምን ማለት ነው?** (ዮሐ. 17:3) ተወያዩበት። ጓደኛን ማወቅ ማለት ፍላጐቱን፡ ዕቅዱን፡ በተለያየ ጊዜያት እንዴት አድርጐ እርምጃ እንደሚወስድ ማወቅ ነው። እግዚአብሔርን ማወቅ ትልቅና ጥልቅ የሆነ ልምምድ ነው። ምክንያቱም እርሱ በጣም ታላቅ ነውና።

ያም ሆነ ይህ እግዚአብሔርን ማወቅ እንችላለን። እርሱ እንድናውቀው ይፈልጋል። የራሱ ሕዝብ ከእርሱ ጋር የግል ግንኙነት እንዲኖረው ይፈልጋል። አስቀድመን የእግዚአብሔር ጠላቶች ነበርን። ይህም በጠላት ግዛት ውስጥ ለሰይጣንና ለእርሱ ፍላጐት ባሪያ መሆን ነው። ነገር ግን እግዚአብሔር በክርስቶስ አዳነን፡ እንድናገለግለውና የበለጠም እናውቀው ዘንድ ወደ መንግሥቱ አፈለሰን። አምላካችን እንድንወደው፡ እንድናገለግለው ከእርሱ ጋር እንድንነጋገርና ኅብረትም እንዲኖረን ይፈልጋል። እግዚአብሔርን ማወቅ ማለት ይህ ነው።

ለበለጠ ግንዛቤ፡- እግዚአብሔርን ማወቅ ምንን ያጠቃልላል?

- በንስሐና በእምነት ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ጌታና እንደ አዳኝህ ለማወቅ መቅረብ ነው።

- በልብህ የመንፈስ ቅዱስን ድምፅ ማዳመጥ ማለት ነው። እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ አማኝ በክርስቶስ በሚያምንበት ጊዜ መንፈስ ቅዱስን ይሰጣል።

- የእግዚአብሔርን ቃል መስማትና በሕይወታችን ተግባራዊ ማድረግ።

- ራሱን ሊገልጽ እንደወደደ የእግዚአብሔርን ተፈጥሮና ባሕርይ ማወቅ ነው።

- የእርሱን ጥሪ መቀበልና ትእዛዙንም መፈጸም ነው።

- በኑሮአችን እርሱን ማወቅ የክርስቲያኖች ዓላማ ነው (ፊልጵ.

3:10፤ ኤፌ. 1:17)። አንድ የምታውቀው ጥሩ ሐኪም ካለ በእርሱ ስለምትታመን ሁል ጊዜ ወደ እርሱ ለመሄድ ትፈልጋለህ። የእግዚአብሔርን ፍላጐትና ዓላማ ባወቅህና አንተም ራስህን በዚያ ውስጥ ባስገባህ መጠን ግንኙነትህ የሚያድግ ይሆናል ።

17- **እግዚአብሔርን በግልህ ታውቀዋለህ?** ይህ ለራስህ እንድትመልስ የቀረበልህ ጥያቄ ነው። ንስሐ በመግባትና ክርስቶስን በማመን እግዚአብሔርን ለማወቅ መጀመር ትችላለህ። በጸሎት፡ ቅዱሳት መጻሕፍትን በማንበብና በየዕለቱ ከእርሱ ጋር በመራመድ እግዚአብሔርን በማወቅ ማደግ ትችላለህ።

የእግዚአብሔርን ቃል ተግባራዊ ማድረግ፡- በመዝጊያው የተሰያዩ ሰዎች ስለ እግዚአብሔር ሙሉ በሙሉ መረዳት ያቃታቸውን ነገሮች ይዘርዝሩ። ከዚያም እግዚአብሔር፥ ስለ ራሱና ፈቃዱን በተመለከተ እንድናውቃቸው የፈለጋቸውን ነገሮች ዘርዝር።

ጸሎት፡- እግዚአብሔር ታላቅ ስለሆነ በማመስገን በጸሎት በፊቱ ውደቅ (ስገድ)። በብሉይ ኪዳን ስለተናገረንና ራሱንም በነቢያት አማካኝነት ስለገለጸልን አመስግነው፤ በመጨረሻም በአዲስ ኪዳን ውስጥ ራሱን በክርስቶስ ኢየሱስ ስለገለጸልን አመስግነው። ስለዚህ እውነት የሚናገረውን ዝማሬ በማቅረብ ከፍለ ጊዜውን ፈጽም።

ጥናት ስምንት

የእግዚአብሔር አንድነትና ሦስትነት

(ሥላሴ)

ዓላማው፡- አንድ ብቻውን የሆነ እውነተኛና ሕያው አምላክ እንዳለና እርሱም ሦስት አካላትን ያካተተ አንድነት ስለመሆኑ መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረውን ለመረዳት ነው። ይህም እርሱን በመንፈስና በእውነት ለማምለክ ያስችለናል።

የዓላማው ማብራሪያ፡- ብዙ ክርስቲያኖች መጽሐፍ ቅዱስ ስለ አሐዱ-ሥሉስነት የሚያቀርበው ትምህርት ያደናግራቸዋል። ሌሎች ሃይማኖቶች ደግሞ ክርስቲያኖችን በሦስት አማልክት ያምናሉ በማለት ይወነጅሏቸዋል። ነገር ግን የሰማይና የምድር ፈጣሪ የሆነው አምላካችን በጣም ታላቅና ልንረዳው የማንችለው ነው። መጽሐፍ ቅዱሳዊው የክርስትና እምነት ሁልጊዜም እግዚአብሔር አንድ ሆኖ

በሦስት አካልነት እንደተገለጸ ያስተምራል፤ በአንድ አምላክነት ስለመኖሩም ትምህርት ይሰጣል። እግዚአብሔር አብ፥ እግዚአብሔር ወልድና እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ አንድ ዓይነት ይዘት ያላቸው በሥልጣንና በክብር ለዘላለም እኩል ናቸው። ዛሬ ይህን ስለ እግዚአብሔር ተፈጥሮ የሚያወሳውን ታላቅ እውነት እንማራለን።

[ማስታወሻ፡- በአሐዱ -ሥሉስነት ላይ የሚደረገውን ይህን ጥናት ለመጨረስ ብዙ ጊዜ ያስፈልግህ ይሆናል። ከፈለግህ በዚህ ርእስ ላይ ሁለት አና ሦስት ክፍለ ጊዜ የሚጠይቅ ትምህርት መስጠት ትችላለህ።]

የትምህርቱ አቀራረብ፡- መጽሐፍ ቅዱስ በአንድ በኩል እግዚአብሔር አንድ እንደሆነ በሌላ በኩል ደግሞ ሦስት እንደሆነ ያስተምራል። አንድ ዛፍ ሥር፥ ግንድና ቅርንጫፍ አለው፤በአንድ በኩል አንድ፥ በሌላ በኩል ደግሞ ሦስት የሆኑትን ቁሳዊ ምሳሌዎች መስጠት ትችል ይሆን? ውኃ ተን፥ በረዶና ፈሳሽ መሆን ይችላል፤ አንቁላል ከቅርፊት፥ ከአስኳልና ከነጭ ፈሳሽ ነገር የተሠራ ነው። እኩል ጐን ያለው ትሪያንግል አንድ ሊካፈል የማይችል ስፋት አለው። ይሁንና፥ ሦስቱም ጐኖች እኩል ናቸው። እያንዳንዱ ጐን ስፋቱን በሙሉ ይይዛል።

እነዚህ ስለ አሐዱ-ሥሉስነት የተሰጡት ምሳሌዎች የተወሰነ አገልግሎት አላቸው። በዝርዝር ከተገባ መጽሐፍ ቅዱሳዊውን የአሐዱ-ሥሉስነት ትምህርት በደንብ አይገልጹም፤ ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስ የማያስተምረውን ስለሚያስተምሩ ነው። ነገር ግን እርስ በርሱ ሳይቃረን አንድ ነገር በአንድ በኩል አንድ ሆኖ በሌላ በኩል ደግሞ ሦስት መሆን እንደሚችል ለማሣየት የተወሰነ አገልግሎት አላቸው። እግዚአብሔር በአንድ በኩል አንድ ሲሆን፥ በሌላ ወገን ደግሞ ሦስት በአንድ ነው።

በዚህ ክፍለ ጊዜ መጽሐፍ ቅዱሳዊውን የእግዚአብሔርን አንድነትና ሦስትነት በአንድነት ማጥናት እንፈልጋለን።

1- ብሉይ ኪዳን የሚያተኩረው በእግዚአብሔር አንድ መሆን ላይ ነው። ዘዳግም 6:4-5፤ ኢሳይያስ 44:6ን አንብብ። **እግዚአብሔር አንድ የሆነው በምን መንገድ ነው?** ተወያይበት። ብዙ አማልክት የሉም። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተገለጸው የፍጥረት አምላክ እግዚአብሔር አንድና ብቸኛ ነው። አምላክ የተባሉት ሌሎች ጣዖታት ናቸው። ሰይጣንና ክፉ መናፍስት እግዚአብሔርን መስለው ለመታየት ቢጥሩም፥ እውነተኛ አምላክ አይደሉም።

2- **እግዚአብሔር አንድ ከሆነ፥ አንድ አምላክ ብቻ ካለ ይህ እውነት ለምን አስፈላጊ ሆነ?** (ዘዳ. 6:4-5)። ወንዶችና ሴቶች ለእግዚአብሔር ፍጹም፥ ሙሉና ያልተከፋፈለ ታማኝነት፥ ፍቅርና ታዛዥነትን የመስጠት ዕዳ አለባቸው። "ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ በፍጹም ነፍስህና በፍጹም ኃይልህ ውደድ"። ከእርሱ በቀር ሌሎች አማልክት እንዳይኖሩን ታዝዘናል (ዘጸ. 20:3)። ደግሞም አንዱ ጌታ የሰዎች ሁሉ ፈጣሪ በመሆኑ፥ እግዚአብሔር የሰዎች ሁሉ አባት ነው። ከኃጢአት ለመዳን የሚቻለውም በአንድ መንገድ ብቻ ነው (የሐዋ. 17:29፤ ሮሜ 3:29-30)።

3- **እግዚአብሔር አንድ በመሆኑ ላይ የአዲስ ኪዳንና የብሉይ ኪዳን መገለጦች ይስማማሉ?** (ማር. 12:28-29፤ 1ኛ ጢሞ. 2:5)። አዎን፥ ኢየሱስ ክርስቶስና ሐዋርያት የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት የዕብራይስጡ መገለጥ መሆናቸውን የተቀበሉ አይሁዳውያን ናቸው። ሁሉም ብቻውን እውነተኛና ሕያው የሆነ አንድ አምላክ እንጂ ብዙ አማልክት እንደሌሉ አስተምረዋል።

4- ይሁንና፥ እግዚአብሔር ተብለው የተጠሩ አካላት በአዲስ ኪዳን ውስጥ እናገኛለን። **በሚከተሉት ጥቅሶች እግዚአብሔር በመባል የተጠሩትን አካላት ዘርዝር** (ዮሐ. 20:28፤ የሐዋ. 5:1-4፤ ሮሜ 1፤ ገላ. 9:5 ዕብ. 1:8)። አብ፥ ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስና መንፈስ ቅዱስ እያንዳንዳቸው እግዚአብሔር በመባል ተጠርተዋል።

5- **በክርስቲያኖች ጥምቀት ሥነ-ሥርዓት ጊዜ የሚነገሩት ቃላት ስለ እግዚአብሔር አሐዱ-ሥሉስነት ምን ያስተምሩናል?** (ማቴ. 28:19)። አማኞች በአንድ ስም መጠመቅ አለባቸው። ይህም የአብ የወልድና የመንፈስ ቅዱስ ስም ነው። እግዚአብሔር ሦስት በአንድ ነው። አንድ ስም፥ ነገር ግን ሦስት አካላት።

6- እንደ ሐሰተኛ አስተማሪዎች በቤተ ክርስቲያን ተቀባይነት ያጡ አንዳንድ ሰዎች አንዱ ጌታ ራሱን በሦስት የተለያዩ ቅርጾች ወይም መንገዶች ገልጿል ብለው ያስተምራሉ። እነዚህ የሐሰት አስተማሪዎች እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን ራሱን እንደ አብ ገልጿል ብለው ይናገራሉ። በክርስቶስ የሕይወት ዘመን እግዚአብሔር ራሱን እንደ ወልድ ገልጿል። ክርስቶስ ካረገ በኋላ ደግሞ እግዚአብሔር እንደ መንፈስ ቅዱስ ተገለጠ ብለው ያስተምራሉ።

የሚከተሉትን ጥቅሶች በማየት፥ እነዚህ ጥቅሶች ይህንኑ የሐሰት ትምህርት እንዴት እንደሚቃወሙ

ተመያዩበት። (ማቴ. 3:16-17፤ ዮሐ. 14:16-17፥ 17:12) ኢየሱስ ወልድ ወደ አብ ጸልዮአል፣ ይህም ሁለቱ አንድ አካል አለመሆናቸውን ያሳያል። ክርስቶስ ሲጠመቅ መንፈስ እንደ ርግብ ከላይ ወረደ፥ ድምፅም ከሰማይ ተሰማ። ይህ የሚያሳየው አብ፥ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ሦስት አካላት መሆናቸውን ነው። አጽናኙን ይልክ ዘንድ ክርስቶስ ኢየሱስ ወደ አብ መጸለዩ ሦስት አካላት መሆናቸውን ያሳያል።

7- ሌሎች ሃይማኖቶች የእግዚአብሔርን አሐዱ-ሥሉስነት አይቀበሉም። የይሖዋ ምስክሮች ኢየሱስ ክርስቶስ እውነተኛ አምላክ መሆኑን ይክዳሉ። ክርስቶስ ኢየሱስ አምላክ ስለመሆኑ ከወንጌላት ምን ማስረጃ እናገኛለን?

ሀ / ዮሐ. 1:1-4ን አንብብ። ይህ ክፍል ኢየሱስ እውነተኛ አምላክ እንደሆነና ስለ እግዚአብሔር አሐዱ-ሥሉስነት እንዴት እንደሚያስተምር አስረዳ? በመጀመሪያ ቃል ነበር (1:1 ሀ)፣ ቃል ምንም ነገር ሳይቀር ሁሉንም ፈጠረ (1:1-3)፣ ቃል እግዚአብሔር ነበር (1:1ሐ)። ቃል ሥጋ ሆነ በሰዎችም መሀል አደረ (1:14)፣ መጥምቁ ዮሐንስ ስለ ቃል ሊመሰክር በእግዚአብሔር ተላከ (1:6-7)።

ነገር ግን ምንም እንኳ "ቃል" እግዚአብሔር ቢሆንም (1:1)፥ ከእግዚአብሔር ጋር እንደነበረ ልብ በል (1:1)። "ቃል" እግዚአብሔርና ከእግዚአብሔር ጋር መሆን የሚችለው እንዴት ነው? ያ ሰው ጳውሎስ ሙቱዋ ነው፣ እርሱም ከጳውሎስ ሙቱዋ ጋር ነው" ትርጉም ያለው አነጋገር ነው? "ቃል" የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ እውነተኛ አምላክ ነው። ነገር ግን አንዱ እውነተኛ ሕያው አምላክ የሆነውን ሁሉ አይደለም። እግዚአብሔር አሐዱ-ሥሉስ ነው (ሦስት በአንድ ነው) ቃል እግዚአብሔር ነው፥ ከዘላለም እስከ ዘላለም "ቃል" ከእግዚአብሔር አብና፥ ከእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ጋር አለ።

ለ / ዮሐንስ 8:56-59 ያለውን አንብብ። ኢየሱስ አይሁዶች እንዲገድሉት ያደረጋቸው ምን ነገር ተናገረ? ኢየሱስም አለ፣ "አብርሃም ሳይወለድ እኔ አለሁ"። "እኔ ነኝ" የሚለው እግዚአብሔር አምላክ ራሱን ለሙሴ የገለጠበት መጠሪያ ስሙ ነው (ዘጸ. 3:14)። ይህም ለእግዚአብሔር አምላክ በጣም የተቀደሰ ስም ሆነ። ክርስቶስ "አብርሃም ሳይወለድ እኔ አለሁ" በማለት እግዚአብሔር ስለመሆኑ ይህን አስደናቂ ነገር ተናገረ። እንደ ሙሴ ሕግ ማንኛውም የእግዚአብሔርን ስም የሚሳደብ ሞት ይገባዋል (ዘሌ. 24:10-16)። አይሁዳውያን ሊወግሩት ድንጋይ ያነሡት ለዚህ ነው (ዮሐ. 8:59)።

ክርስቶስ ተሳዳቢ ነው ወይም ደግሞ የሰው አካል ለብሶ ወደ ምድር የመጣ እውነተኛ አምላክ ነው::

ሐ / ዮሐንስ 10:30-33 አንብብ (አውደ ምንባቡን ተመልከት 10:22-33):: ኢየሱስ ይሳደባል ብለው አይሁዳውያን እንዲያስቡ ክርስቶስ የተናገረው ምንድን ነው? "እኔና አባቴ አንድ ነን" ብሎ መናገሩ ነበር:: አይሁዳውያን አንድ አምላክ ብቻ እንዳለ አጥብቀው ያምኑ ነበር:: ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱን ከእግዚአብሔር ጋር አንድ የሚያደርግ ይመስላል:: ስለዚህ ስለ ስድቡ (ለርግማኑ÷) የእግዚአብሔርን ስም በተሳሳተ መንገድ በመጠቀሙ ሞት ይገባዋል ብለው አሰቡ::

መ/ ዮሐንስ 20:28ን አንብቡ:: ቶማስ ኢየሱስ ከሞት እንደተነሣ ባመነ ጊዜ ምላሹ ምን ነበር? ቶማስ ኢየሱስን "ጌታዬና አምላኬ" ብሎ ጠራው::

8- አንዳንድ ሰዎች ኢየሱስ ክርስቶስና መንፈስ ቅዱስ በዝቅተኛ (ባነስ ደረጃ) አምላክ እንደሆኑ ያስባሉ፤ ይህም ማለት ከእግዚአብሔር ሥር ያሉና ከእግዚአብሔር አብ ጋር ሊተካከሉ የማይችሉ እንደሆኑ ማለት ነው:: እግዚአብሔር አብ÷ እግዚአብሔር ወልድና እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ በማንነታቸው አንድ እንደሆኑና ዘላለም በኃይልና በክብር እኩል እንደሆኑ እንድናምን የሚያደርገን ምንድን ነው?

ሀ/ 1ኛ ቆሮ. 3:16ን አንብብ:: አብና ወልድ አንድ ናቸው::

ለ/ ሮሜ 8:9ን አንብብ:: ወልድና መንፈስ ቅዱስ አንድ ናቸው::

ሐ/ ዮሐ. 10:30፤ 14:23ን አንብብ:: አብና ወልድ አንድ ናቸው::

መ/ 2ኛ. ቆሮ. 13:14፤ ማቴ. 28:19ን አንብብ:: አብ÷ ወልድና መንፈስ ቅዱስ እኩል ካልሆኑ በስተቀር ትክክል ሊሆን በማይችል መንገድ በአንድነት ተጣምረዋል::

ሠ/ ዮሐ. 5:21-23ን አንብብ:: ወልድ ከአብ ጋር እኩል ኃይል አለው፤ እኩልም ክብር እንደ አብ ይቀበላል:: እግዚአብሔር ወልድ ከአብ ጋር በማንነቱ ተመሳሳይ ካልሆነና በኃይልና በክብር ለዘላለም እኩል ካልሆነ÷ እግዚአብሔር አብ ፍጥረቱ በክብርና በኃይል እኩል እንዲሆን እንዴት ፈቀደ?

ረ / ኤፌ. 4:4-6፤ 5:18-20 ን አንብብ:: የእግዚአብሔር አብ÷ ወልድና መንፈስ ቅዱስን ስም በምንጠራበት ጊዜ ቋሚ የሆነ የአጠራር ሥርዓት የለም:: ይህ የሚያመለክተው የትኛውም የሥላሴ አካል ከሌላው እንደማይበልጥ ነው::

9- ኢየሱስ "የእግዚአብሔር ልጅ ነው" ሲል መጽሐፍ ቅዱስ ምን ማለቱ ነው? ይህን ሲል ኢየሱስ መሠረቱ ከእግዚአብሔር እንደሆነና ከእግዚአብሔር አብ እንደሚያንስ መናገሩ አይደለምን? (ዮሐ. 3:16):: በተለያየ ባሕል ውስጥ ላሉ ሕዝቦች ልጅ የሚለው አሳብ ያነሰ መሆኑን (ከአባት ጋር እኩል አለመሆኑን) ያሳያል :: ልጅ የሚገኘው ከአባት ተግባር ሳቢያ ነው::

ሙስሊሞች በተለመደው ሰብአዊ የግንኙነት መንገድ እግዚአብሔርን የልጁ አባት ብሎ ማሰቡ በጣም ያስቆጣቸዋል:: ሙስሊሞች በዚህ ዓይነቱ አስተሳሰብ መቆጣታቸው አግባብ ነው:: ነገር ግን ይህንን ያስተማሩት ክርስቲያኖች ናቸው ማለታቸው ስሕተት ነው:: ምክንያቱም ሙስሊሞች የመጽሐፍ ቅዱስን ትምህርት አይረዱምና ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር በተለምዶ የሥጋ ግንኙነት አማካኝነት ማለትም ሰብአዊ አባቶች ልጅ በሚያገኙበት መንገድ እንደወለደ ጨርሶ አያስተምርም::

ከዚህም በላይ የመጽሐፍ ቅዱስ አትኩሮት ክርስቶስ የበታች በመሆኑ ላይ ሳይሆን÷ ነገር ግን እርሱ እግዚአብሔርን በመምሰሉ ላይ ነው:: ዋናው ትኩረት ክርስቶስ እግዚአብሔርን መምሰሉ እንጂ ከእግዚአብሔር ማነሱ አይደለም:: የእግዚአብሔር ልጅ የሆነው ኢየሱስ የእርሱን ምስል ይዞአል:: ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ማንኛውም ፍጡር ከእግዚአብሔር አብ የተወለደ አይደለም:: ኢየሱስ ክርስቶስ ከእግዚአብሔር አብ ጋር ለዘላለም በመኖሩ ሁልጊዜ በፍጥረቱና በማንነቱ እንደ እግዚአብሔር ነው::

ያዕቆብና ዮሐንስ "የነጐድጓድ ልጅ" የተባሉት በምን መንገድ ነው? (ማር. 3:17):: በሥጋ የነጐድጓድ ልጆች አይደሉም:: ነገር ግን የነጐድጓድ ባሕርይ አላቸው:: ከነጐድጓድ ጋር የሚመሳሰል ነገር አላቸው:: እንደ ነጐድጓድ ናቸው::

እንደ ዮሐንስ 5:16-18 አገላለጽ አይሁዶች ክርስቶስን ለመግደል የፈለጉት ለምንድን ነው? በአይሁዶች አእምሮ እግዚአብሔር አባቴ ነው ብሎ ሲናገር ከእግዚአብሔር ጋር እንደ ልጅ ለየት ያለ ግንኙነት (ዝምድና) እንዳለው ማመልከቱ ነው:: አይሁዶች "እግዚአብሔር አባታችን ነው" ብለው ያምናሉ:: ነገር ግን ኢየሱስ እግዚአብሔርን አባቴ ብሎ ጠራው:: ይህ ለአይሁዶች ስድብ መሆኑ ነው:: ምክንያቱም ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ ከእግዚአብሔር አብ ጋር እኩል ወይም እንደ እርሱ መሆኑን አስተምሮአልና::

10- **ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር አብ ከወልድ እንደሚበልጥ አይናገርም? መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር አብ ከወልድና ከመንፈስ ቅዱስ በላይ እንደሆነ አይናገርም ?** ማለትም አብ የመጀመሪያው እንደሆነና የበለጠ ሥልጣን እንዳለው::

ሀ / ፊልጵስዩስን 2:5-11ን አንብብ:: **በእነዚህ ቊጥሮች ውስጥ ጳውሎስ ኢየሱስ ክርስቶስ በትክክል አምላክ እንደሆነ ያስተማረው የቱጋ ነው?** በፊልጵስዩስ 2:6 ላይ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ባሕርይ እንዳለውና ከእርሱም ጋር እኩል እንደሆነ ጳውሎስ አስተምሯል :: **ወልድ ከአብ ዝቅ የተደረገው ለምንና በምን መንገድ ነው?** ኢየሱስ አምላክ-ሰው ሊሆንና ለእኛ ሲል በመስቀል ላይ ለመሞት ክብሩን በእግዚአብሔር ዘንድ ተው (2:7-8):: ኢየሱስ ክርስቶስ ሰማያዊ ክብሩን በእግዚአብሔር ዘንድ ትቶ በፈቃዱ ባሪያ ሆነ:: ክርስቶስ በመስቀል ላይ የመሞቱ ታዛዥነት የመጨረሻ ውጤት ምንድን ነው? (2:10-11):: አንድ ቀን በሰማይ፥ በምድርና ከምድር በታች የሚገኙ ሰዎች ሁሉ በክርስቶስ ፊት ዝቅ ብለው በመስገድ ያመልኩታል:: በመሆኑም ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔርን ትክክለኛ ባሕርይ ይዞና ከእግዚአብሔር ጋር እኩል ሆኖ እኛንም ከኃጢአት ሊያድነን ክብሩን ተው::

ለ / ዮሐንስ 14:28ን አንብብ:: **አብ ከወልድ የሚበልጠው በምን ዓይነት መንገድ ነው?** አብ ከወልድ የሚበልጠው ወልድ ከአምላክ በሚያንሰበት፥ ከእግዚአብሔር ጋር እኩል ባልሆነው ወይም ከእግዚአብሔር ጋር አንድ ዓይነት ተፈጥሮ በሌለው መንገድ አይደለም:: ነገር ግን በእግዚአብሔር የደኅንነት ሥራ ዕቅድ ወልድ ለአብ ይገዛል:: አብ ወልድን ላከው (ዮሐ. 3:16):: በደኅንነት ሥራ አብ የመጀመሪያ ነው፤ ወልድ ሁለተኛ፤ መንፈስ ቅዱስ ደግሞ ሦስተኛ:: አብ ምንጭ ነው፤ ወልድ አብ የሚሠራበት መንገድ ነው፤ መንፈስ ቅዱስ ወኪል ነው:: ወደ አብ በወልድ በኩል በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት እንጸልያለን::

11- **የአሐዱ-ሥሉስነት ትምህርት የሚገኘው በአዲስ ኪዳን ብቻ ነው ወይስ በብሉይ ኪዳንም ጭምር?**

ሀ / ዘፍ. 1:26፤ 3:22፤ 11:5-7፤ ኢሳ. 6:8ን አንብብ:: **በእነዚህ ጥቅሶች ስለ አሐዱ-ሥሉስነት አብ የሚሰጥ ምን ማስረጃ ታገኛለህ?** ስለ እግዚአብሔር የሚጠቅስ የተውላጠ ስም ብዙ ቊጥር አንደኛ፥ የእኛ የመሰለ መጠሪያ ስለ አሐዱ-ሥሉስነት የሚናገር ሊሆን ይችላል:: ነገር ግን ይህ ሙሉ በሙሉ ግልጽ አይደለም፤

የተውላጠ ስም ብዙ ቊጥር ምን እንደሆነ የሚገልጽ ሌላ ተጨማሪ ማስረጃ አለ::

ለ/ መዝ. 45:6-7ን አንብብ:: **ስለ አሐዱ-ሥሉስነት ማስረጃ የሚሰጥ ምን አብብ ታገኛለህ?** ቊጥሮቹ የእግዚአብሔር ስም ከአንድ በላይ ቊጥር ባላቸው አካላት እንዳገለገለ ያሳያል:: በመዝሙር 45 የተጠቀሰው እግዚአብሔር ሲሆን፥ "አምላኩ" "አምላክህ" ነው:: ይህ በዕብራውያን 1:8 ላይ ለእግዚአብሔር ልጅ እንደተጠቀሰ ተመልክቷል::

ሐ / ኢሳይያስ 9:6ን አንብብ:: **እንደሚወለድ ትንቢት የተነገረለት ልጅ ማን ነው?** እርሱ በሥጋ የተገለጠው መሢሕ ነው::

መ / ማጠቃለያ:- በብሉይ ኪዳን ውስጥ ስለ አሐዱ-ሥሉስነት ግልጽ የሆነ ትምህርት አይገኝም:: ነገር ግን በአዲስ ኪዳን ውስጥ ኋላ የተሰጠው መገለጥ በብሉይ ኪዳን ለተሰጡት ብዙ ትምህርቶች ጠቃሚ የሆነ ማብራሪያ ያቀርባል:: ይህ አባብ በርግጥ በእግዚአብሔር አንድነት ላይ አክራሪ አቋም ባላቸው አይሁዶች ዘንድ እንግዳ ነገር ነው::

12- **በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ "አሐዱ-ሥሉስነት" የሚለውን ቃል ካላገኘን፥ በእግዚአብሔር አንድነትና ሦስትነት የምናምነው ለምንድን ነው?** በመጀመሪያ እግዚአብሔር ራሱን በሥራው ገልጧል:: እግዚአብሔር ለአይሁዶች ራሱን ከሰማይ እንደ እውነተኛ አምላክ ገልጧል:: በራሱ ጊዜ (ዘመኑ ሲሞላ) ክርስቶስ ኢየሱስ በሥጋ መጣ:: ደቀ መዛሙርቱም እንደ አምላክ ለይተው ተቀበሉት:: በበዓለ ኀምሳ መንፈስ ቅዱስ ቤተ ክርስቲያንን ሞላት:: ደቀ መዛሙርቱ መንፈስ ቅዱስን እንደ አምላክ ተረድተው ሲቀበሉት፥ በአንዳንድ በኩል አስቀድመው እንደ አምላክ ከተቀበሉት ከኢየሱስ ክርስቶስ እንደሚለይ ተገንዝበዋል::

ስለሆነም፥ ሐዋርያቱ መንፈስ ቅዱስ እውነተኛ አምላክ እንደሆነ ለመግለጽ የሚያስችሉትን መለኮታዊ ክስተቶች ለማብራራት በእግዚአብሔር ተመርተዋል::

13- **ስለ እግዚአብሔር ሦስትነትና አንድነት የተሰጠው ይህ አስደናቂ እውነት እንዴት ወደ አምልኮ ሊመራን እንደሚችል ተወያዩ::** እግዚአብሔር በመላ ማንነቱ ፍጹም ነው:: እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን መፍጠር ሳያስፈልገው በራሱና በማንነቱ ሙሉ ነው:: እግዚአብሔር ለኅብረት እኔና

እናንተን መፍጠር አያስፈልገውም፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር አብ፥ እግዚአብሔር ወልድና እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ከጥንት ጀምሮ የፍቅር ኅብረት ነበራቸው። እግዚአብሔር ፍቅር ነው፤ በፍቅሩም ፍጹም ነው። ለማፍቀርም በፍጥረቱ መደገፍ አያስፈልገውም። እንደ አሐዱ-ሥሉስ አብ፥ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ፍጹም የሆነውን ፍቅር ፍጹም በሆነው ማኅበራዊ አንድነትና ኅብረት ገልጸዋል፤ ተለማምደዋልም። እግዚአብሔር ያለ እኛ ሊኖር ይችላል። ነገር ግን በእርሱ ዘንድ በታወቀ ምክንያትና ለክብሩም ሲል በማንነቱ ወስን የሌለውና ፍጹም የሆነው እውነተኛ እግዚአብሔር አንዲያፈቅሩ ወንዶችና ሴቶችን በመልኩ ሊፈጥራቸው መረጠ። ይህ አንድናመልከው አያደርገንምን?

የእግዚአብሔርን ቃል ተግባራዊ ማድረግ፡- ስለ እግዚአብሔር ማንንትና ከአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ለእኔና ለአንተ ስላደረገው ታላቅ የደኅንነት ሥራ አስብ። እግዚአብሔር በሥላሴ አማካኝነት ለአንተ የፈጸማቸውንና እንድታመልከው የሚገፋፋህን ነገሮች በወረቀት ላይ ዘርዝር።

ጸሎት፡- ለመረዳት ከአእምሮአችን በላይ የሆነውን የእግዚአብሔርን ታላቅነት አያስብህ በማመስገን በአምልኮ ስገድ። ራሱን ለእኛ ስለገለጸም አመስግነው። እግዚአብሔር አብን፥ ወልድን፥ መንፈስ ቅዱስን በሕይወትህ ስላከናወኑት የደኅንነት ሥራ አመስግን።

ጥናት ዘጠኝ

እግዚአብሔር ቅዱስ ነው

ኢሳይያስ. 6፡1-8

ዓላማው፡- በኢሳይያስ 6፡1-8 እንደተመለከተው የእግዚአብሔርን ቅዱስነት ለማጥናትና እኛም በዚህ ቅዱስ አምላክ ፊት እንዴት በአምልኮ ምላሹን መስጠት እንዳለብን ለመማር ነው።

የዓላማው ማብራሪያ፡- እግዚአብሔር አእምሮአችን ሊረዳው ከሚችለው በላይ በጣም ትልቅ እንደሆነ ተምረናል። ይህም ሆኖ፥ እግዚአብሔር አምላክ በሰዎች ለመታወቅ ይፈልጋል። በዛሬው ዕለት እግዚአብሔር ምን እንደሚመስል (ማለትም ከዐበይት ባሕርያቱ አንዱ የሆነውን) እናጠናለን። *ይኸውም ቅድስናው ነው።*

የትምህርቱ አቀራረብ፡- ሕዝቦች ዋስትና ሲያጡና ስለወደፊቱ ነገር እርግጠኛነት በማይሰማቸው ጊዜ በመንግሥት ደረጃ የአሠራር ለውጥ ማድረግ ስጋት ያስከትልባቸው ይሆን? መሪያቸው በድንገት ከሥልጣን ሲወርድ ወይም ሲሞት የሕዝቡን ስሜትና ፍርሃት ለመግለጥ ሞክር። ተወያዩበት። በዛሬው ዕለት ንጉሥ ያዝያን በሞተበት ዓመት ኢሳይያስ ምን እንዳጋጠመው ለማጥናት እንፈልጋለን። ንጉሡ በሞተበት ጊዜ ስለወደፊቱ ሁኔታ ፍርሃት ነበር። በዚህ የፖለቲካ ለውጥ ጊዜ ኢሳይያስ ወደ እግዚአብሔር ተመለከተ። እግዚአብሔርም ስለ ራሱ ቅድስና የሚናገር ታላቅ ራእይ ሰጠው።

ኢሳይያስ 6፡1-8ን አንብብ።

1- ኢሳይያስ በቊጥር 1 የተመለከተውን ግለጽ።

ሀ/ እግዚአብሔር በዙፋኑ ላይ ተቀምጦ ነበር። ይህም እግዚአብሔር እንደ ንጉሥ መግዛቱን ያመለክታል። የዚህ ምድር ገዢዎች ይሞታሉ፤ ነገር ግን እግዚአብሔር የራሱ በሆነው ዓለም ላይ መግዛቱን ይቀጥላል። እርሱ ሁልጊዜ ሉዓላዊ ነው። ሁልጊዜ ሁሉን የሚቆጣጠር ታላቅና ዘላለማዊ ጌታ ነው። እግዚአብሔር እንደ ሰው አይሞትም።

ለ / ዙፋኑ "ከፍ ያለ ልዕልና ያለው" ነበር። ይኸውም እርሱ ከፍጥረቱ ከፍ ያለ፥ የራቀና የተለየ መሆኑን ያሳያል። ተራ ሰው ዝቅተኛ በሆነ ወንበር ሲቀመጥ፥ ተፈላጊ ሰው ግን ለየት ባለ ስፍራ ላይ ይቀመጣል። ነገር ግን እግዚአብሔር አምላክ ከፍ ባለ ዙፋን ላይ

ከፍ ብሎ ነበር::

ሐ / እግዚአብሔር አምላክ ረጅም መጐናጸፊያ ለብሶ ነበር:: "መጐናጸፊያውም ቤተ መቅደሱን ሞልቶት ነበር::" ተራ ሰዎች እስከ ጉልበታቸው የሚደርስ አጭር ልብስ ይለብሳሉ:: በጣም ተፈላጊ የሆኑ ነገሥታት ግን ረጅም ቀሚስ ይለብሳሉ:: የእግዚአብሔር አምላክ መጐናጸፊያ በቤተ መቅደስ ያለውን የዙፋኑን ክፍል እስከሚሞላ ድርስ በጣም ረጅም ነበር:: ለማንም ሰው በእግዚአብሔር ፊት መቆም የሚያስችል ስፍራ አልነበረም:: የቀሚሱ ዘርፍ የእርሱን ክብርና ንጉሥነቱን ይናገራል::

2- **እንዲህ ዓይነት ሰው ወዳለበት ስፍራ መግባት ምን ስሜት ይፈጥርብሃል?** ተወያዩበት:: አንድ ወጣት ከቀጣሪው ፊት በሚቀርብበት ጊዜ ወይም ቃለ መጠይቅ ሊያደርገው በተዘጋጀ የትምህርት ቤት ኃላፊ ፊት በሚቆምበት ጊዜ ፍርሃት ሊሰማው ይችላል:: በርግጥም በክብርና በድምቀት በተቀመጠው ሕያውና እውነተኛ እምላክ ፊት በምንቀርብበት ጊዜ ቅዱስ ፍርሃትና መንቀጥቀጥ ሊያድርብን ይገባል::

3- **ዙፋኑ ባለበት ክፍል ውስጥ ከእግዚአብሔር ጋር የነበሩትን ሌሎች አካላት ግለጥ::** (ኢሳ. 6:2ን ተመልከት):: አብራራ:: በሁለት ክንፎቹው በአንድ የተወሰነ ቦታ ያለማቋረጥ የሚበሩ ሱራፌሎች ነበሩ:: (ሱራፌል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በዚህ ቦታ ብቻ የተጠቀሱ ሲሆን፥ እግዚአብሔርን ሊያገለግሉ በተለይ ለእርሱ የተፈጠሩ ናቸው):: ዓይኖቻቸውንና እግሮቻቸውን የሚሸፍኑት ለምንድን ነው? ተወያዩበት:: እግዚአብሔር በጣም ታላቅ ስለሆነ ሱራፌሎች በክብሩ፥ በድምቀቱና በቅድስናው ሁሉ ሆኖ ወደ እርሱ ሊመለከቱ አይችሉም:: ይህም ልክ ዓይኖቻችንን ሳንሸፍን ፀሐይን መመልከት እንደማንችል ማለት ነው:: ምንም እንኳን ሱራፌሎች ኃጢአት ባይኖራቸውም (ምንም ዓይነት ኃጢአተኛ ፍጡር በእግዚአብሔር ፊት ሊቆም አይችልም)፥ የተፈጠሩ አካላት ናቸው:: እግራቸውን የመሸፈናቸው ምልክት ትሕትናቸውን ያሳያል:: የተፈጠሩት ሱራፌሎች በእግዚአብሔር በፈጣሪያቸው ፊት መሆን የሚገባቸው አልነበሩም::

4- **ሱራፌሎች የሚናገሩት ምን ነበር?** (6:3):: "ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ታላቁ አምላካችን ሆይ" እያሉ ይጣሩ ነበር:: "ቅዱስ" ለሚለው ቃል ትኩረት ለመስጠት ሦስት ጊዜ ተደጋግሞ ተጠቅሶአል:: ይህ የተሟላና ሁለንተናዊ ቅድስናን ያመለክታል::

5- **ሱራፌሎች እግዚአብሔርን "ቅዱስ" እያሉ መጣራታቸው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ምንን ያመለክታል?** ቅድስና ከእግዚአብሔር ጉባሬ ውስጥ ወሳኙ ክፍል ነው:: "ቅዱስ" የሚለው ቃል መለየት ወይም መቁረጥ ማለትነው:: ይኸውም እግዚአብሔር የፍጥረቱ ክፍል አይደለም ማለት ነው:: እግዚአብሔር ከፍጥረቱ የተለየ ነው:: በቅድስናው እንደ እርሱ ያለ ማንም የለም (1ኛ ሳሙ.2:2፤ ዘጸ. 15:11)::

በተጨማሪም፥ ቅድስና ስለ ንጽሕናው ይናገራል:: እግዚአብሔር ከኃጢአት የራቀ ነው:: እርሱ ጨርሶ ንጹሕና ፍጹም፥ ከኃጢአትና ከርኵሰት የራቀ ነው (ዕንባቆም 1:13):: ቅድስና የጻድቅነቱን አስደናቂ ባሕርይ ያሳያል:: ("ክብሩም በዓለም ሁሉ የሞላ ነው" 6:3)::

6- **ወደ እግዚአብሔር ፊት የሚቀርብ ነገር ሁሉ ምን ይሆናል?** ተወያዩበት:: ቅዱስ የሆነ ብቻ በእግዚአብሔር ፊት መሆን ይችላል::

ሀ / በሚቃጠለው ቍጥቋጦ አጠገብ የነበረው መሬት ቅዱስ ነበር (ዘጸ. 3:5):: ሙሴ በጥንቃቄና በአክብሮት እንዲቀርብ ተነግሮታል::

ለ / በመገናኛ ድንኳን ውስጥ የነበሩ ዕቃዎች ቅዱስ ነበሩ (ዘኍ.4:15)::

ሐ / ለእግዚአብሔር የሚቀርቡ ስጦታዎች ቅዱስ ነበሩ (ዘጸ. 28:38)::

መ / የሰንበት ቀን ቅዱስ ነበር (ዘፍ. 2:3) ::

7- **እግዚአብሔር ቅዱስ ከሆነ የእግዚአብሔር ሕዝብ ምን መሆን ይገባቸዋል?** ቅዱስ መሆን ይገባቸዋል::

ሀ / ሕዝቡ ቅዱስ እንዲሆኑ ተጠርተዋል (ዘሌ. 19:2):: ቅድስና እግዚአብሔር ለሕዝቡ የሰጠው መለኪያ ነው (1ኛ ጴጥ. 1:15)::

ለ/ የእርሱ ሕዝብ ኃጢአታቸው ይቅር ሊባል ይገባል:: የብሉይ ኪዳን መሥዋዕቶች ምክንያታቸው ይኸው ነበር (ዕብ. 9:21-22)::

ሐ/ ሕዝቡ ንጹሕ ካልሆነው ነገር ርቀው ለእርሱ የተለዩ መሆን ነበረባቸው (2ኛ. ቆሮ. 6:16-18)::

መ/ ኃጢአተኛ ከእግዚአብሔር ፊት ለዘላለም መራቅ አለበት (ራእይ 22:14-15):: ለምሳሌ አዳምና ሔዋን ኃጢአት ከሠሩ በኋላ ከዔድን ገነት ተባርረዋል::

ረ / ኃጢአት መቀጣት አለበት (ሮሜ 6:23)::

8- እግዚአብሔር በክብር የተቀመጠበት ስፍራ ምን ሆነ? (6:4)። አብራራ። ሕንፃው መሠረቱ በመናወጡ ተጐድቶአል። "የመድረኩ መሠረት" የሚለው ቃል ኢሳይያስ በቆመበት ስፍራ ያለውን የበር መቃን መሠረት የሚያመለክት ነው። መቅደሱ በጭስ የተሞላ በመሆኑ እግዚአብሔር ከፍጥረቱ ዓይን ተሠውሮ ነበር። (በሌላ ጊዜ የክብር ደመና ወይም ጉም የእግዚአብሔርን ፊት በሚሸፍንበት ጊዜ ማለትም በእርሱ ፊት እንዳይሆኑ በማገድ ያለውን ሁኔታ አወዳድር ዘጸ. 19:16-18፥ 34:35፣ ዘኁ. 9:15-23)።

9- ኢሳይያስ እግዚአብሔርን በመላው ቅድስና በ-ተመለከተበት ጊዜ የተናገረውን አብራራ (6:5)።

ኢሳይያስ የእግዚአብሔርን ቅድስና በሚያይበት ጊዜ፥ እርሱ ኃጢአተኛ ፍጥረት ብቻ መሆኑን ተገነዘበ (6:5)።

"ወዮልኝ"- የጥፋት ድምፅ (ፍርድ ሊመጣ ተቃርቦአል)።

ኢሳይያስ ከፍርድ በታች እንደሆነ አውቆአል።

"እኔ ጠፍቻለሁ" - የሞት ጥላ አንጎበበታል።

10- ኢሳይያስ ራሱን የናቀው ለምን ይመስላችኋል? (6:5)

ሀ / ምክንያቱም እርሱ ንጹሕ አልነበረም- "ከንፈሩ የረከሰበት ሰው።" ሱራፌሎች (6:2)፥ ምንም እንኳ ንጹሕና ቅዱስ ቢሆኑም፥ እግዚአብሔርን ላለማየት ፊታቸውን በመሸፈን ምስጋናን አቀረቡለት። ሱራፌል እግዚአብሔርን መመልከት ያልተገባቸው ፍጥረታት ናቸው። ነገር ግን ኢሳይያስ ፍጥረት ብቻ አይደለም። ንጽሕና የጐደለው ኃጢአተኛም ነበር። የኢሳይያስ ቃላት አስተሳሰቡን ከመግለጻቸውም በላይ ከተግባሩም ጋር ተዛምደዋል። ኢሳይያስ ንጹሕ አለመሆኑን አወቀ።

ለ / ምክንያቱም "ከንፈሮቹ በረከሱበት ሕዝብ መካከል" ኖሯል። እስራኤላውያን ኃጢአተኛ ሕዝብ ነበሩ። አንድ ሰው የእግዚአብሔርን ቅድስና በሚገነዘብበት ጊዜ የራሱን ኃጢአተኛነትና በአካባቢው ያለውን ኃጢአት መገንዘብ ይጀምራል። ምሳሌነታቸው ለእርሱ ፈተና ስለነበር፥ የሌሎች ኃጢአት በኢሳይያስ ላይ ተጽዕኖ አሳድሯል።

ሐ / ምክንያቱም የሠራዊት ጌታን አየ። እግዚአብሔር ቅዱስ ስለሆነ፥ በብሉይ ኪዳን ሰዎች እርሱን ካዩ እንደሚሞቱ ያስባሉ። ነገር ግን ኢሳይያስ አልሞተም። ከዚያ ይልቅ ኢሳይያስ ይቅርታን

አገኘ።

11- እግዚአብሔር ኢሳይያስን ሊያነጻና ይቅር ሊል ምን አደረገ? (6:6-7)

ሀ/ "የእሳት ፍም" (ይኸውም "የሚያቃጥል ከሰል") የመንጻት ምልክት ነው። እሳት ያጠራል። ንጹሕ ያልሆነውን ነገር ሁሉ ያቃጥላል።

ለ/ ማንጻት ከእግዚአብሔር ብቻ ይገኛል። "መሠዊያ" የሚገኘው በእግዚአብሔር ፊት ነው። ይቅርታን ሊሰጥ የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ ነው። ከኃጢአታችን ሳንነጻ በእግዚአብሔር ፊት ልንቆም አንችልም (መዝ. 24:3-4)።

ሐ / የኢሳይያስ በደል ተወገደ (6:7)።

የሚቃጠለው አካል ኃጢአትን በመወከል ከመሠዊያው ተወስዶ በኢሳይያስ ከንፈር ላይ ተደረገ። ("የረከሰ ከንፈር" 6:5)። በመሠዊያው ላይ የኃጢአት ዕዳ ይከፈላል፣ ይሰረያል።

12- የእግዚአሔርን ቅድስና የተመለከቱ ሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ሰዎች እነማን ናቸው? ኢዮብ (ኢዮብ 42:5-6)፥ ጴጥሮስ (ሉቃስ 5:8)፥ ዮሐንስ (ራእይ 1:17)።

13- የኢሳይያስ ኃጢአት ይቅር ከተባለ በኋላ እግዚአብሔር ከኢሳይያስ ምን ፈለገ? (6:8)

ሀ / "ማንን እልካለሁ?" እግዚአብሔር ኢሳይያስ ይቅር ከተባለ በኋላ ተናገረ። ለኢሳይያስ የመመለስ ዕድል ለመስጠት እግዚአብሔር ጥያቄ አቀረበለት። ሥልጣን የእግዚአብሔር ነው። እርሱም እስካሁን ይገዛል።

ለ / የኢሳይያስ ምላሽ ፈጣን ነበር። በፊት ተስፋ አልነበረውም። ነገር ግን አሁን ከኃጢአት የመንጻት ዋስትና አገኘ። እግዚአብሔር ከፊቱ አላራቀውም። ይህ ሁኔታ ኢሳይያስ እግዚአብሔርን ለማገልገል እንዲፈቅድ አደረገው።

ሐ / አንድ ሰው በማንኛውም ስፍራና ማንኛውንም ነገር በማድረግ እግዚአብሔርን ለማገልገል የሚዘጋጀው ስለ ኃጢአቱ ሲወቀስና የኃጢአቱን ይቅርታ ዋስትና ሲገነዘብ ብቻ ነው(መዝ. 51:13-15ን) ተመልከት።

እግዚአብሔር አምላክ ኢሳይያስን ሊልከው ፈለገ። አንድ ሰው ስለ እግዚአብሔር ቅድስና ራእይ ሲቀበል የራሱን ኃጢአተኛነትና

ስለ ይቅርታም አስፈላጊነት ግንዛቤ ይኖረዋል። እግዚአብሔር ወንዶችና ሴቶችን ለአገልግሎት ሊጠቀምባቸው የሚፈልገው ከዚያ በኋላ ብቻ ነው።

14- **ይህ የእግዚአብሔር ቅድስና ራእይ ኢሳይያስን ወደ አምላኩ የመራው እንዴት ነው?** (6፡8-9) ተወያዩበት።

ሀ / ኢሳይያስ እግዚአብሔርን ሲያምንና ሲታዘዝ ለእግዚአብሔር ስም የተገባውን ክብር እየሠዋለት ነበር። እርሱን ከመውደዳችን፥ ከማድነቃችንና ስለ ደኅንነት ሥራው በምስጋና ከመሞላታችን የተነሣ ለእግዚአብሔር የምንሰጠው አገልግሎት በራሱ የአምልኮ ሥራ ነው።

ለ / ከዚያ በላይ ግን ኢሳይያስ ስለ ቅዱስ እግዚአብሔር ያየው ራእይ በሕይወቱ ላይ ትልቅ ምልክት ትቶአል። ኢሳይያስ አዘውትሮ፥ "የእስራኤል ቅዱስ" የሚለውን ሐረግ ተጠቅሞአል (5፡19፥ 30፡12፥ 43፡3)።

15- **ዛሬ እግዚአብሔር ራሱን ለእኛ ለየት ባለ መንገድ በሚገልጥበት ጊዜ፥ ይህ በእኛ ላይ ምን ዘለቄታዊ ውጤት ሊያስከትል ይገባል?** ራሱን በመግለጥ እግዚአብሔር የነካቸውን ሰዎች የምታውቅ ከሆነ በምሳሌነት ጥቀስ።

የእግዚአብሔርን ቃል ተግባራዊ ማድረግ፡- ብዙ መላእክት፥ ሕያው የሆኑ ፍጥረታት፥ ሽማግሌዎች እግዚአብሔርን በዙፋኑ ላይ ተቀምጠ በጉንም በዙፋኑ ፊት ሲያዩ፥ "በሰማይና በምድር፥ ያሉ ፍጥረታት ከምድር በታችና በባሕር ሁሉ" ይህን መዝሙር ዘመሩ።

"በዙፋኑ ላይ ለተቀመጠውና ለበጉም ምስጋና፥ ክብር፥ ውዳሴ፥ ኃይል ለዘላለም ይሁን!" ሲሉ ዘመሩ (ራእይ 5፡13)። ቅዱስ ለሆነው እግዚአብሔር የአምልኮ ዝማሬ በማቅረብ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናታችሁን ፈጽሙ። እንደዚሁም በዚህ ሳምንት ለእግዚአብሔር ስለ ታላቁና አስደናቂው ቅድስና የአምልኮ መዝሙር ለመዘመር ተለማመዱ።

ጸሎት፡- ስለ ቅድስናውና ኃጢአታችንን ይቅር ለማለት ስለ ተሰጠን ጸጋ እግዚአብሔርን ለማምለክ በጸሎት ስገዱ። በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል ኃጢአትህን ይቅር ስላለ አክብረው።

ክፍል ሦስት

በዕብራውያን ነቢያት የታረመ አምልኮ

በእስራኤል የኋለኛው ዘመን የእስራኤል ልጆች ለእግዚአብሔር የሚሰጡትን ትክክለኛ አምልኮ ትተው ነበር። ሰዎች እግዚአብሔርን በቤተ መቅደስ የአምልኮ ሥርዓት አማካኝነት ሲያመልኩት፥ በተመሳሳይ ጊዜ ጣዖታትንም ያመልኩ ጀመር። እግዚአብሔርን በከንፈራቸው ቢያመልኩትም ቅሉ ልባቸው ከእርሱ የራቀ ነበር። ሥርቆት፥ ግድያ፥ አመንዝራነትና ለበአል መሠዋት ተግባራቸው ሆነ። ከዚያ በኋላ መጥተው በመቅደስ ውስጥ በእግዚአብሔር ፊት ቆመው ከጠላታቸው የዳኑ መሆናቸውን ይናገራሉ (ኤር. 7፡9-10፤ 29፡13)። በዚህ ሁኔታ እግዚአብሔር አምልኮአቸውን ሊቀበል አልፈለገም። ምክንያቱም አምልኮአቸው በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት እንዳያገኝ ኃጢአት አግዶ ነበርና።

ስለዚህ የነቢያት አገልግሎት የእስራኤልን አምልኮ ማጽዳት ነበር። በልባችን እግዚአብሔርን ማምለክ ያቃተን እንደሆነ እርሱን እናዋርዳለን።

ይህ ነቢያት እግዚአብሔር አይሁዳውያን መሥዋዕት እንዲያቀርቡ የሰጣቸውን ትእዛዝ የተቃወሙ የሚያስመስሉትን ተከታታይ ጥቅሶች ትርጉም ያብራራል (ኢሳ. 1፡1፤ ኤር. 7፡21፤ ሆሴዕ 6፡6፤ አሞጽ 5፡25፤ ሚክ. 6፡6-8)። እነዚህ ነቢያት በሙሴ ዘመን በእግዚአብሔር የተመሠረተውን የአምልኮን አስፈላጊነትና እሴት አልተቃወሙም። ነገር ግን እውነተኛ አምልኮ ለእግዚአብሔር ካለው የፍቅርና የመሰጠት ልብ የሚወጣ መንፈሳዊ ነገር ነው። የእግዚአብሔርን ትእዛዝ እየተቃወምን እርሱን በትክክል ልናመልክ አንችልም። ከሁሉም በላይ እግዚአብሔር ሕዝቡን እንዲታዘዙለትና በሕጉም መሠረት እንዲኖሩ ይፈልጋል። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እግዚአብሔርን ደስ በሚያሰኝ መንገድ የምናመልከው በመታዘዝ ሕይወት ስናመልከው ብቻ ነው።

ነቢያት የእስራኤላውያንን አምልኮ ለማንጻትና በእግዚአብሔርም ዘንድ ተቀባይነት ያለው ለማድረግ እንዴት እንደጣሩ ለማሳየት ከነቢያት መጻሕፍት በርካታ ክፍሎችን እናጠናለን።

ጥናት አሥር

እግዚአብሔርን የማያስከብር አምልኮ

ሚልክያስ 1:6-14

ዓላማው፡ እግዚአብሔር የሚፈልገውን ትክክለኛ መሥዋዕት ለእርሱ ባለመስጠት እስራኤላውያን እግዚአብሔርን እንዴት እንዳሳከሩት ለማጥናትና እኛም በተመሳሳይ መንገድ እግዚአብሔርን እንዴት እንደምናዋርደው ለመረዳት ነው።

የዓላማው ማብራሪያ፡- አምልኮ ለእግዚአብሔር በትክክል የሚገባውን ክብሬታ መስጠት ነው። እግዚአብሔር ፈጣሪያችንና አዳኛችን እንደመሆኑ መጠን ልናከብረው በምንፈልግበት ጊዜ ከእኛ የተመረጠው ነገር ሊሰጠው ይገባዋል። ነገር ግን የእስራኤል ልጆች ከእንስሳት የታመሙትን፥ መራመድና ማየት የተሳናቸውን ለመሥዋዕትነት በማቅረብ እግዚአብሔርን በአምልኮአቸው አዋረዱት። የተመረጠውን ነገር ለእግዚአብሔር በመስጠት እግዚአብሔርን የማክበርን አስፈላጊነት ከነቢዩ ሚልክያስ መማር ይኖርብናል።

የትምህርቱ አቀራረብ፡- ስጦታን በማበርከት ከእኛ በላይ ላሉት (አባታችን ወይም መምህራችን ወይም አንዳንድ መሪዎቻችን) ሰዎች ክብሬታን ለማሳየት በምንሞክርበት ጊዜ የምንሰጣቸው ምን ዓይነት ስጦታ ነው? ልንሰጥ በምንችላቸው የተለያዩ ስጦታዎች ላይ ውይይት አድርጉ። ልናከብረው የምንፈልገው ሰው ያረጀ፥ አገልግሎት የሰጠና ጥሩ ያልሆነ ነገር ብንሰጠው ምን ያስብ ይሆን? ተወያዩበት። በዛሬው ዕለት የተመረጠውን ነገር ብቻ ለእግዚአብሔር በማቅረብ ለእርሱ ክብር የማሳየትን አስፈላጊነት ለማስብ እንፈልጋለን።

ሚልክያስ 1:6-14 ያለውን ክፍል አንብቡ።

1- አግዚአብሔርን ራሱን በዓለም ካሉት ሰዎች ጋር በማወዳደር ስለ ራሱና እርሱ ከእኛ ስለሚጠብቀው ግዴታ ብዙ ትምህርት ይሰጠናል። በ1:6 እግዚአብሔር ከማን ጋር ነው የተወዳደረው? ከአባትና አለቃ ጋር ነው የተወዳደረው።

2- አይሁዶች ልጅ ለአባቱ ለማሳየት ስለሚገባው አክብሮት ታላቅ ሥነ ሥርዓት አስተምረዋል። በአሁኑ ዘመን ልጅ ለአባቱ ክብር ማሳየት የሚገባው በምን ዓይነት መንገድ ይመስልሃል?

ተወያዩበት። ለአባት ፍቅርና መታዘዝን፥ እንደዚሁም ክብሬታን ማሳየት አለበት። እንደ 1:6 አገላለጽ ባሪያ ለጌታው ማሳየት የሚገባው አመለካከት ምን ዓይነት ነው? አክብሮት።

3- እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን ልጆች አባትና ጌታ የነበረው በምን ዓይነት መንገድ ነው? እግዚአብሔር ፈጣሪያቸውና አዳኛቸው ከግብፅም ያወጣቸው ነበር። ከእነርሱ ጋር ቃል ኪዳን ፈጽሞ ነበር (ሚልክያስ 2:10)። እስራኤላውያን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ለመፈጸም ቃል ገብተው ነበር (ዘጸ. 19:3-8)። ዛሬ እግዚአብሔር ለክርስቲያኖችም እንደዚሁ አባትና ጌታ ነውን? አዎን። እንደ ክርስቲያን እግዚአብሔር አባት የሚሆንልን በምን ዓይነት መንገድ ነው? ተወያዩበት። ስለ ፈጠረን ሕይወታችንን ለእርሱ እናስረክባለን። እንደ አባት ይጠብቀናል፤ የሚያስፈልገንንም ይሰጠናል። በክርስቶስ በማመን ልጆቹ እንሆን ዘንድና አባታችንም ብለን እንድንጠራው እግዚአብሔር ወደ ቤተሰቡ ተቀብሎናልና (ገላ. 4:4-17)።

4- ከአይሁዶች መካከል የእግዚአብሔርን ስም ያቃለለ (የሰደበ) ማን ነው? (1:6) ካህናት።

5- እነርሱ እግዚአብሔርን ያቃለሉት እንዴት ነው? (1:7-8) በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት የሌለው ምግብ በመሠዊያው ላይ በማኖር ነበር። [መሥዋዕት አብዛኛውን ጊዜ የእግዚአብሔር ምግብ ወይም ጎብስት በመባል ይጠራል (ዘሌዋ. 21:6፥8፤ 17:21-22 ፥22-25፤ ዘኁ. 28:2፤ ዘሌዋ. 3:11-16)]።

6- ካህናት የረከሰ ምግብ በመሠዊያው ላይ ለእግዚአብሔር ያቀረቡት እንዴት ነው? (1:8)። ምክንያቱም ዓይናቸው የታወረ፥ አንካሳና የታመሙ እንስሳትን በመሠዋታቸው ነው። ይኼ ከእግዚአብሔር ትእዛዝ ውጭ ነበር። ነውር የሌለውንና አካሉ ያልተጐዳውን መሥዋዕት ብቻ ማቅረብ ነበረባቸው (ዘሌዋ.22:20-25፤ ዘዳግ. 15:21)።

7- አንድ የመንግሥት ባለሥልጣን ይህንን በመሰለ ስጦታ ይደሰታል? (1:8) ሊኖር የሚችለው መልስ የለም የሚል ነው። እንዲህ ዓይነቱን ስጦታ ለእግዚአብሔር ስናቀርብ ጸሎታችን ይሰማ ይሆን? (1:9-10) ባለሥልጣኑ የማይረባውን ስጦታ የማይቀበል ከሆነ እግዚአብሔርማ እንዴታ! ጸሎታችንም እንደዚያው አይመለስም።

8- "የቤተ መቅደሱን በር የሚዘጋ ምነው ከእናንተ

አንድ ሰው እንኳ በተገኘ" ሲል ምን ማለቱ ነው? (1:10) ተወያዩበት:: እንዲህ ዓይነቱ አምልኮ ዋጋ የሌለው ነው:: የረከሠ ምግብ በመሠዊያው ላይ ከማቅረብ ጨርሶ አለማምለክ ይመረጣል:: "የቤተ መቅደስ በሮች" የሚያመለክቱት ከውጭው አደባባይ የሚቃጠል መሥዋዕት ወደሚደረግበት የካህናት አደባባይ የሚመሩትን ታጣፊ በሮች ነው:: ለካህናት የሚቃጠል መሥዋዕት ወደሚገኝበት ቤተ መቅደስ መግባትና ፍጹም ያልሆነ መሥዋዕት ለማቃጠል እሳቱን ማንደዱ ከንቱ ነበር:: እርሱ የማይቀበለውን አምልኮ በማቅረብ እግዚአብሔርን ከማዋረድ ጨርሶ አለማምለክ ይሻላል::

9- የሚከተለው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል፥ 1:11፥ የወደፊቱን አምልኮ በሚልክያስ ዘመን ከነበረው የአይሁድ አምልኮ ጋር ያነጻጽራል:: ሚልክያስ በትንቢቱ እንደተናገረው፥ በወደፊቱና በሚልክያስ ዘመን በአይሁዳውያን መካከል የሚገኙ የተለያዩ ንጽጽሮች ወይም ውድድሮች የትኞቹ ናቸው? አይሁዳውያን እግዚአብሔርን በአንድ ቦታ ማምለክ ሲገባቸው (ዘዳ.12:13):: የወደፊቱ አምልኮ በማንኛውም ስፍራ ሊካሄድ ይችላል የነቢያት ተስፋ አሕዛብ እንኳን ሳይቀሩ ለእግዚአብሔር ስም የሚገባውን አምልኮ እንዲሰጡ ነው:: ነቢዩ ሚልክያስ ካለመታዘዛቸው የተነሣ የአይሁድን አምልኮ እርባና ቢስ አድርጉ በሚፈርድበት ጊዜ እንኳን እግዚአብሔር አንድ ቀን በተገቢው መንገድ እንደሚመለክ የወደፊቱን በእምነትና በተስፋ ያያል:: ንጹሕ የሆነውን መሥዋዕት ያቀርቡለታል፤ የእግዚአብሔርም ስም ታላቅ ይሆናል::

10- **ለእግዚአብሔር የሚቀርበው ዕጣን ትርጉም ምንድን ነው?** (1:11) ዕጣን ለእግዚአብሔር ስናቀርብ ወደ ሰማይ የሚወጣ ጸሎታችን ምሳሌ ነው:: ዕጣን በወደፊት አምልኮ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ጸሎት የሚወክል ከሆነ፥ "ንጹሕ መሥዋዕት" ምንን ይወክል ይሆን? (1:11) እኅብሮታችንና ምሥጋናችን ሳይቀር ክርስቲያኖች ዛሬ የሚያቀርቡትን መሥዋዕት ይወክላል::

11- **አይሁዳውያን ስለ አምልኮ ያላቸው አመለካከት ምንድን ነው?** (1:12-13) በአምልኮአቸው እግዚአብሔርን ለማክበር በተሰጣቸው ዕድልና ባገኙት ጥቅም ደስ መሰኘት ሲገባቸው ለአምልኮ የደከሙና የሰለቹ ነበሩ:: አምልኮ አድካሚ እየሆነ መጣ፥ ሸክም ሆነ እና ተቃለለም::

12- **ነቀፋ ባለው መሥዋዕታቸው በሚያዋርዱት**

አይሁዳውያን ላይ የነበረው የእግዚአብሔር አመለካከት ምን ነበር? (1:14) ይረግማቸዋል::

13- **በአምልኮአቸው የሚያዋርዱትን አይሁዳውያን እግዚአብሔር የረገማቸው ለምንድን ነው?** (1:14):: ምክንያቱም እግዚአብሔር ታላቅ ንጉሥ ነው:: ከዚህም የተነሣ የእግዚአብሔር ስም በሕዝቦች ሁሉ ዘንድ ሊፈራ ይገባዋል:: አይሁዶች በዓለም ሁሉ ለሚገኙት አሕዛብ እንዴት ብርሃን መሆን ይገባቸው ነበር? ወንዶችና ሴቶች በሙሉ የነገሥታት ንጉሥ የሆነውን ማምለክ እንደሚገባቸው በማሳየት:: ነገር ግን አይሁዶች ይህን ግዴታቸውን ባላማሟላት ሳቱ:: ውርደትንም ለእግዚአብሔር አመጡ::

14- አይሁዶች ለዘላለሙ ንጉሥ ስም የማይገባውን መሥዋዕት በማምጣት እግዚአብሔርን አዋረዱት:: **እኛ ክርስቲያኖች በአምልኮአችን እግዚአብሔርን የምናዋርደው እንዴት ነው? አይሁዳውያን እንዳደረጉት እኛ ማድረግ የምንችለው እንዴት ነው?** ተወያዩበት:: እግዚአብሔርን በጣም ትንሽ በመስጠት ልናመልከው እንችላለን:: ብዙውን ገንዘብ ለእኛ ስናስቀር ለእግዚአብሔር ትንሿን ሣንቲም መስጠት እንችላለን:: በአሥራት አንታመንም:: ከጊዜያችን በጣም ጥቂቱን ብቻ ለእግዚአብሔር እንሰጣለን፤ ያውም ሁለት ሰዓት በየሳምንቱ ቤተ ክርስቲያን ስንሄድ ብቻ:: በሕይወታችን ውስጥ ያልተናዘዝነው ኃጢአት ሞልቶ እያለ ለእግዚአብሔር በየእሑዱ ምስጋናችንን ልናቀርብ እንችላለን::

15- **ለስሙ የሚገባውን ስጦታ ባለማቅረብ እግዚአብሔርን በምናሳዝንበት ጊዜ አምልኮአችን ደስ ያሰኛዋል ወይ?** ተወያዩበት:: የለም:: ለአምልኮ ወደ ቤተ ክርስቲያን ጨርሶም ሳንሄድ እንችላለን:: እግዚአብሔር ደስ የማይሰኝበትን መሥዋዕት ከማቅረብና ግብዝ ከመሆን የቤተ መቅድሱን መዝጊያ መዝጋትና የቤተ ክርስቲያንን የአምልኮ ከፍለ ጊዜ አለመካፈል ይመረጣል::

16- **አምልኮአችን እግዚአብሔርን ደስ እንዲያሰኝ ልናደርግ የምንችለው እንዴት ነው?** ተወያዩበት:: በቅድሚያ አምልኮአችን እግዚአብሔርን እንዳሳስከበረ መቀበል አለብን:: ምክንያቱም የተመረጠውን ልንሰጠው አልቻልንምና:: ስለዚህ ንስሐ መግባት ብቻ አይበቃም:: ነገር ግን በልባችን የተመረጠውንና እንደ ልጆቹ እግዚአብሔር ከእኛ የሚፈልገውን ሁሉ በመስጠት

እናከብረዋለን::

የእግዚአብሔርን ቃል ተግባራዊ ማድረግ:- የግል አምልኮ ልማድህን አስብ:: መልካም ያልሆነ አምልኮ ለእግዚአብሔር ታቀርባለህ? እግዚአብሔር በአምልኮህ ደስተኛ ነው? እግዚአብሔር አምልኮህ እርሱን እንደማያስከብረው ካሳየህ መንገድህን ለመቀየርና እግዚአብሔርን በትክክል ሊያስከብር የሚችለውን ዓይነት አምልኮ ለማቅረብ ወስን::

ጸሎት:- እርሱን ደስ በማያሰኘው አምልኮ በማቃለልህ እግዚአብሔርን ይቅርታ እየጠየቅህ በጸሎት ሰግድለት:: ለእግዚአብሔር የሚገባውን ክብር ለመስጠት የእርሱን እርዳታ ፈልግ::

ጥናት አሥራ አንድ

የሕይወት ግድፈት የሚያስከትለው ከንቱ አምልኮ

ኤርምያስ 7:1-26

ዓላማው:- ኤርምያስ 7:1 አምላኪው ከእግዚአብሔር ጋር ትክክለኛ ግንኙነት ከሌለው፥ ትክክለኛ የአምልኮ ሥርዓት (የጸሎትና የዝማሬ ሥርዓት) ዋጋ እንደማይኖረው ለማሳየት ነው:: ሕይወታችን በፊቱ ንጹሕ ካልሆነ የእግዚአብሔርን ጥበቃና በእርሱ ዘንድ ተቀባይነት ማግኘት እንደማንችል ለማሳየት ነው::

የዓላማው ማብራሪያ:- ብዙ ሰዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ልማዳዊውን አምልኮ ለመከተል ይፈልጋሉ:: እግዚአብሔርን በትክክለኛ የአምልኮ ሥርዓት በማምለክ ደስ እንደሚያሰኙት ያስባሉ (መዝ. 51:16-17):: ይኸውም በታማኝነት ወደ ቤተ ክርስቲያን ቢሄዱ፥ ቢዘምሩ፥ ቢጸልዩ የእግዚአብሔር ቃል ሲሰበክ ቢሰሙ እና እንደ ቤተ ክርስቲያናቸው ወግ ምጽዋታቸውን ቢሰጡ እምልኮአቸው እግዚአብሔርን ደስ እንደሚያሰኘው ያስባሉ:: ነገር ግን ትንቢተ ኤርምያስ 7:1-26 የተመረጠው እምልኮአችን እንኳን ሕይወታችን በእግዚአብሔር ፊት እስካልሆነ ድረስ ዋጋ እንደሌለው ያስተምራል::

በኤርምያስ 7:1-26 ያለውን ክፍል አንብቡ ::(ይህ የምንባብ ክፍል ረጅም ስለሆነ ጥያቄዎቹን በምታነቡበት ጊዜ ጥቅሶቹን አንድ በአንድ ልታነቡ ትችላላችሁ)::

የትምህርቱ አቀራረብ:- ኤርምያስ በነቢይነት ያገለገለው ኢየሩሳሌም በ 587 ዓ.ዓ እስከተደመሰሰችበት ጊዜ ድረስ በነበሩት የመጨረሻዎቹ አርባ ዓመታት ውስጥ በገዙት አምስት ነገሥታት (ከኢዮስያስ እስከ ሴዴቅያስ) ዘመን ነው:: የይሁዳ በባዕዳን ጠረኞች የመወረሯ አደጋ በጣም የተረጋገጠ ነበር:: ነገር ግን አይሁዳውያን እግዚአብሔር ኢየሩሳሌምን ከነቤተ መቅደሷ እንድትፈርስ እንደማይፈቅድ ተማመኑ:: እግዚአብሔር ኢየሩሳሌምን ለራሱ አልመረጣትም ወይ? እግዚአብሔር በኢየሩሳሌም በሚገኘው ቤተ መቅድስ ውስጥ ሊመለክ አላቀደም ወይ? ከቤተ መቅደሱ የተነሣ ኢየሩሳሌም ከወራሪ ጦር እንደምትጠበቅ አመኑ::

ነገር ግን በዚህ የምንባብ ክፍል እግዚአብሔር በርግጥ ከቤተ መቅደስ፥ ከቤተ ክርስቲያን፥ ከመሥዋዕት ወይም ከቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ጉዳይ እንደሌለው እንመለከታለን:: እግዚአብሔር ሕዝቡ በእምነት ሕይወታቸውና ለቃሉ ባላቸው ታዛዥነት እንዲያመልኩት ይፈልጋል::

ዛሬ እግዚአብሔርን በሕይወታችን ሳናከብረው በትክክለኛ የአምልኮ ሥርዓት ማምለክ (በዝማሬ፥ ጸሎት፥ ምጽዋትና ስብከተ ወንጌል) በፊቱ ከንቱ እንደሆነ፣ እኛ እንደ ክርስቲያኖች በመላ የመታዘዝ ሕይወት እግዚአብሔርን ልናከብረው ካልቻልን ቤተ ክርስቲያናችንና የአምልኮ ፕሮግራሞቻችን የማይጠቅሙ መሆናቸውን ለማየት እንፈልጋለን::

1- **ነቢዩ ኤርምያስ የእግዚአብሔርን ቃል እንዲሰብክ የታዘዘው የት ነበር?** (7:1-2) አይሁዶች ለአምልኮ ይገቡበት በነበረው የቤተ መቅደስ መግቢያ ደጃፍ ነበር::

2- **ኤርምያስ የእግዚአብሔርን ቃል እንዲሰብክ የታዘዘው ለማን ነበር?** (7:1-2) ለይሁዳ ሰዎች:: ይህ መልእክት የተሳለፈው በግምት ከክርስቶስ ልደት በፊት 608፥ ኢዮአስ ከሞተ በኋላና ኢዮአቄም የተባለው ልጅ መንገሥ በጀመረበት ጊዜ ነበር:: ኢዮአቄም የአባቱን የኢዮስያስን ቅን መንገድ አልተከተለም:: ነገር ግን ወደ ባዕድ አምልኮ ተመለሰ:: መጥፎ የሆኑትን ካህናትና ነቢያት ሾመ (በኤር. 7:1-26 ያለው መልእክት እንዲሰጥ ያስፈለገበትን ሁኔታ ስለሚመለከት ምዕ. 26 ከቁጥር 1 ጀምሮ ያለውን ክፍል ተመልከቱ::)

3- **የመልእክቱ ዋና አሳብ ምን ነበር?** (7:3) እግዚአብሔር በእስራኤል ምድር እንዲቆዩ ከማድረጉ በፊት መንገዳቸውንና ሥራቸውን ማስተካከል ነበረባቸው::

4- ሐሰተኛ ነቢያት ለሕዝቡ ይናገሩ የነበረው ምንድን ነው? (7:4) ቤተ መቅደሱ ሊጠፋ እንደማይችል ነበር:: "ይህ ነው ቤተ መቅደሱ" በማለት ሦስት ጊዜ ተደጋግሞ መነገሩ እግዚአብሔር ቤተ መቅደሱን ለስሙ ክብር ስላቆመው ኢየሩሳሌም በጠላቶቿ ልትጠፋ አትችልም የሚል ጠንካራ የአነጋገር ዘይቤ ነበር:: እግዚአብሔር የራሱ መቅደስ ያለበትን ኢየሩሳሌምን በርግጥ ከጠላት ይከላከላል::

5- በ 7:5-7 ኤርምያስ በ7:3 ላይ ያለውን ዋና መልእክት እንደገና ያቀርባል:: አይሁዶች መንገዳቸውንና ተግባራቸውን መቀየር ያለባቸው እንዴት ነው? (7:5-7) ማኅበራዊ ፍትሕ መስፈን አለበት (ደካሞችንና ራሣቸውን መከላከል የማይችሉትን ሰዎች መጉዳቱ ሊያበቃ ይገባዋል):: ስግብግብነትን ለማስፈን የሚደረገው ጠብ መቆም አለበት:: ለሌሎች አማልክት መስገዱም እንደዚሁ መቆም አለበት::

6- ዛሬ በአገራችን በሚገኙት የተለያዩ ማኅበራዊ የፍትሕ አልባነት ጉዳዮች ላይ ተወያዩ:: አንዳንድ ራስ ወዳዶች ረብ የሌለው ጥቅም ለማግኘት እንዴት ነው ሌላውን አለአግባብ የሚገፉት? ተወያዩበት:: እንደዚህ ያሉት ማኅበራዊ ፍትሕን የሚያጓድሉ ሰዎች ዛሬ በቤተ ክርስቲያን አምልኮ ይሳተፋሉ? ተወያዩበት::

7- በ7:9 ቀደም ሲል የተናገረውን ይደግማል:: እግዚአብሔር ከጠላቶቻቸው ይጠብቃቸው ዘንድ ሊናዘዙና ሊተዉ የሚገባቸውን የኃጢአት ዓይነቶች ዘርዝር:: ስርቆት÷ ግድያ÷ ዝሙት÷ ከንቱ መሐላና ባዕድ አምልኮ::

8- በ7:9 ላይ የተጠቀሱት የኃጢአት ዓይነቶች በዛሬው ጊዜ ወደ ቤተ ክርስቲያን በሚሄዱ ሰዎች ይፈጽማሉ? ተወያዩበት::

9- አይሁዶች የቅይጥ አምልኮ ጥፋት ፈጽመዋል (እግዚአብሔርን በቤተ መቅደስ ውስጥ ማምለክ÷ ከዚያ በኋላ ደግሞ ለከነዓናውያን አማልክት መሥዋዕት ማቅረብ 7:9÷17-19):: በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ ክርስቲያኖች የክርስትናን እምነት ከአፍሪካውያን የሃይማኖት ልማድ ጋር በመቀላቀል ቅይጥ አምልኮ ያካሂዳሉ? (እንደዚሁም 1ኛ ቆሮ. 10:21ን ተመልከቱ):: ተወያዩበት:: አንድ ክርስቲያን እግዚአብሔርን አሐድ ጠዋት ቢያመልክና በሳምንቱ መሀል ስለቸገረው ጉዳይ ወደ ጠንቋይ ዘንድ

ቢሄድ ቅይጥ አምልኮን በማካሄድ በደል ይፈጽማል:: አንድ የክርስቲያን ቤተሰብ አስከሬኑን በቤተ ክርስቲያንና በመጋቢው ቡራኬ ቢቀብርና ከዚያ በኋላ ደግሞ የሕዝቡን ሃይማኖታዊ ወጐች ቢከተል የማይገናኙ ነገሮችን እያደባለቀ ነው:: አብዛኛው ክርስቲያን አንድነት የሌላቸውን ሁለት ነገሮች በማዋሃድ በሁለት ዓለም ውስጥ ይኖራል:: ይኸውም በአንድ ወገን በክርስቶስ÷በሌላ ወገን ደግሞ በርኩሳን መናፍስትና በባሕላዊ ሃይማኖት ልዩ ኃይላት ያምናል ማለት ነው::

10- ቤተ መቅደሱ የወንበዴዎች ዋሻ ተብሎ የተጠራው ለምንድን ነው? (7:11):: ተወያዩበት:: ዋሻ የእንስሳት መጠለያና ዕረፍት የሚያገኙበት ቦታ ነው:: የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ወንጀል የሚፈጽሙና ጠበኞች ጥበቃ የሚያገኙበትና ተመቻችተው የሚቀመጡበት ቦታ ሆነ::

11- በዛሬው ጊዜ የእኛ ቤተ ክርስቲያን የወንበዴዎች ዋሻ መሆን ትችላለች? እንዴት? ተወያዩበት:: የእግዚአብሔርን ሕግ የሚጥሱ ሰዎች ለአምልኮ ወደ ቤቱ በሚመጡበት ጊዜ ቤተ ክርስቲያን እንደዚሁ የወንበዴዎች ዋሻ ልትሆን ትችላለች:: ምክንያቱም በከተማም ሆነ በመንደር ቤተ ክርስቲያን እንደዚህ ላሉ ሕግን ለሚተላለፉ ሰዎች አከብሮት ትሰጣለችና ነው:: ወደ ቤተ ክርስቲያን በመሄዳቸው ከጓደኞቻቸው ከበሬታ ያገኛሉ:: ከዚያ በኋላ የእግዚአብሔርን ሕግ ለመጣስ ከቤተ ክርስቲያን ይወጣሉ::

12- በትንቢተ ኤርምያስ 7:12-20 የተሰጠውን ማስጠንቀቂያ አብራራ:: እግዚአብሔር ቀደም ሲል በሴሎ ያደረገውን ነገር ከኃጢአትዋ የተነሣ በኢየሩሳሌም ላይ ያደርጋል:: የቃል ኪዳን ታቦት መቀመጫ የነበረችው ሴሎ በኢያሱ ዘመን (ኢያ.18:16፤ 1ኛ ሳሙ. 1:3) ከእስራኤል ኃጢአት የተነሣ በ 1050 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት (ዓ.ክ.ል.በ) ተደምስሳ ነበር:: አሁንም እስራኤል ኃጢአትዋን የማትናዘዝ ከሆነ ተመሳሳይ ጽዋ ይጠብቃታል::

13- በ7:21 ላይ የእግዚአብሔር ቃል ትርጉም ምንድን ነው? የሙሉ መሰጠት መግለጫዎች በመሆናቸው (ዘፍ. 22:2-12÷ 13)÷ የሚቃጠሉ መሥዋዕቶች ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሔር የተለዩ ነበሩ:: የሚቃጠሉ መሥዋዕቶች ሊበሉ አይገባም:: ከኃጢአት የተነሣ እግዚአብሔር ውጫዊ የሆነውንና በሥርዓት የቀረበውን የእይዩዳውያን አምልኮ አልተቀበለውም:: ስለዚህ የሚቃጠለውን መሥዋዕት አንዲበሉ በመናገር ለአምልኮአቸው ያለውን የከረረ

ጥላቻና ተቃውሞ ያሳያል። (ይህ ከሙሴ ሕግ የሚቃረን በመሆኑና የሚቃጠል መሥዋዕት ለመብል ስለማይፈቀድ፡ አይሁዳውያን ጨርሶ የሚሞክሩት ነገር አልነበረም።) እግዚአብሔር የአይሁዶችን አምልኮ ሁሉ ባለመቀበሉ የሚቃጠለውን መሥዋዕት ምናልባት ሊበሉ ይችሉ ይሆናል።

14- የመጽሐፍ ቅዱስን የመጀመሪያዎቹን መጻሕፍት በምናነብበት ጊዜ እግዚአብሔር አምላክ በርግጥ አስራኤላውያንን የሚቃጠል መባና መሥዋዕት እንዲያቀርቡ አዝዞአቸው ነበር (ዘሌ. 1፡7ን ተመልከቱ)። **እግዚአብሔር አስራኤላውያን መሥዋዕት እንዲያቀርቡ አልታዘዙም ሲል ምን ማለቱ ነበር?** (7፡22-26) ይህ በጣም ጠቃሚ ለሆነው ነገር ቅድሚያ የመስጠት ጥያቄ ነው። መሥዋዕት ማቅረብ ከሰዎች የሚጠበቅ የመታዘዝ መግለጫ ነበር። ምንም እንኳን እግዚአብሔር ከሲና ተራራ ላይ ሆኖ አስራኤላውያንን መሥዕዋት እንዲያቀርቡ ያዘዛቸው ቢሆንም፡ ለሕግጋቱ በሙሉ፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ተገዢ እንዲሆኑ ይፈልግ ነበር። በሕጉ በሙሉ የመታዘዝ ሕይወት ሳይኖር መሥዋዕት ማቅረብ መሥዋዕታቸውን ዋጋ ያሳጣዋል። ከሁሉ የበለጠው ነገር እግዚአብሔርን መታዘዝ እንጂ መሥዋዕት ማቅረብ አይደለም። እስራኤላውያን በመጀመሪያ ደረጃ እግዚአብሔርን ከሙሉ ልባቸው ቢታዘዙ ኖሮ፡በእርሱ ዘንድ ተቀባይነት ሊያስገኝ በሚችል መንገድ መሥዋዕቶቻቸውን ሊያቀርቡ በቻሉ ነበር።

15- **እግዚአብሔር በየእሑዱ ስናመልከው ከእኛ የሚፈልገው ምንድን ነው?** ተወያዩበት። በሳምንቱ መሀል ታዛዥነትን ይፈልጋል። እግዚአብሔር ደስ የሚሰኘው በሳምንቱ መሀል ከሙሉ ልባችን ስናመልከው፡ በሁሉም መንገድ ስናገለግለውና ስንታዘዘው ብቻ ነው። ለሚሰቶቻችንና ለባሎቻችን ታማኞች መሆን ይገባናል። በንግድ ተግባራችንና በመደበኛ ሥራችንም እንደዚሁ ታማኝነት ይፈለግብናል። በትክክል ባመኑትና ባላመኑት መካከል ልዩነት ሊኖር ይገባል። **እሑድ ጠዋት ቤተ ክርስቲያን መሄድና በቤተ ክርስቲያን የአምልኮ ሥርዓት መካፈል በሳምንቱ ውስጥ በኃጢአት የምንገኝ ከሆነ ዋጋ አለው ወይ?** ተወያዩበት። የለውም። በትክክል ኃጢአታችንን ተናዝዘን፡ ካልተመለስንና እግዚአብሔርን ማገልገል ካልጀመርን፡ የአምልኮ ሥርዓት መከተሉ ጥቅም አያስገኝም። **በአፍሪካ ባሕላዊ ሃይማኖት ንጹሕና በሌላቸው ሰዎች የሚደረግ አምልኮ ጥቅም ያስገኛላቸዋል?** ተወያዩበት። አያስገኝም። ንጹሕ ካልሆኑ በአምልኮ ጊዜ እንዲቀላቀሉ አይፈቀድላቸውም።

የእግዚአብሔርን ቃል ተግባራዊ ማድረግ፡- ቤተ ክርስቲያንህ እግዚአብሔርን በትክክል ለማምለክ ጠቃሚ ናቸው ብላ የምታስባቸውን የአምልኮ ቅርጾች (ከቤተ ክርስቲያን አምልኮ ጋር የተያያዙትን ወጐችና ልማዶች) ሁሉ ዘርዝር። ከዚያም የእስራኤላውያን አምልኮ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት እንዳያገኙ ያደረጉትን ኃጢአቶች ዘርዝር። ራስህን እንዲህ ብለህ ጠይቅ፡ በቤተ ክርስቲያን የምናደርገው አምልኮ እግዚአብሔርን ደስ ያሰኛል ወይስ ሰዎች በየእሑዱ እንዳያመልኩ የቤተ ክርስቲያናችንን በሮች እንዝጋ? ወይስ እነዚያን ኃጢአቶች ለማስቆም ምን እናድርግ?

ጸሎት፡- ለእግዚአብሔር በፊቱ ንጹሕ ያልሆነውንና ዋጋ የሌለውን አምልኮ ስለማቅረባችሁ በጸሎት ይቅርታ ጠይቁት፤ እርሱን ደስ ሊያሰኘው በሚችል መንገድ ማምለክ እንድትችሉም እርዳታውን ጠይቁ።

ጥናት አሥራ ሁለት

የተከፋፈለ አምልኮ ተቀባይነት የለውም

ሕዝቅኤል 14፡1-11

ዓላማው፡- አምልኮአችን እግዚአብሔርን ደስ የሚሰኘው እርሱን ብቻ ያመለክን እንደሆነ፤ ከእርሱ በቀር ሌሎችን አማልክት ካገለገልን ግን አምልኮአችን ተቀባይነት እንደማይኖረው ለመማር ነው።

የዓላማው ማብራሪያ፡- ብዙ ሰዎች ሌሎችን አማልክት እያገለገሉ በተመሣሣይ ጊዜ እግዚአብሔርን ማምለክ ይፈልጋሉ። ከጠንቋዮች እርዳታ ይፈልጋሉ፤ ከአባቶች (ከሙታን መናፍስት) ጋር ይነጋገራሉ፤ በመተት አማካኝነት ከጉዳት መጠበቅን ይፈልጋሉ (እነዚህ ሁሉ ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጭ ናቸው)። ከዚያ በኋላ በየእሑዱ ወደ ቤተ ክርስቲያን ይሄዳሉ። እንዲህ ዓይነቱ አምልኮ የተከፋፈለ አምልኮ ሲሆን፡ ብቻውን ቀናተኛና ሕያው በሆነው አምላክ ዘንድ ተቀባይነት የሌለው ነው። ደስ ልናሰኘው ከፈለግን እግዚአብሔር ቀናተኛ አምላክ መሆኑን አውቀን እርሱን ብቻ ማምለክና ማገልገል መቻል አለብን።

የትምህርቱ አቀራረብ፡- ታደሰ ሕመም ተሰማው። በአካባቢው ባለው ሆስፒታል እርዳታ ባለማግኘቱ ለምን እንደታመመ ለማወቅ መናፍስትን ወደሚጠሩ ሰዎች ሄደ። ጠንቋዩ ለአባቱ ተገቢውን የቀብር ሥርዓት ባለመፈጸሙ የሙታን መናፍስቱን እንዳሳዘነ ይነግረዋል። ስለዚህ ታደሰ የቀብር ሥርዓቱን በተመለከተ ባሕላዊውን መንገድ መከተል ተገቢ እንደሆነ አሰበ። ከዚያ በኋላ በሕመሙ የበለጠ እንዳይጠቃ መከላከያ የሚሆን መተት ተደረገለት። ከዚህ በኋላ ተሻለው። ይህን ነገር እንኳን እየፈጸመ ከርስቶስ ኢየሱስን ማገልገል የሚፈልግ የተጠመቀ ክርስቲያን በመሆኑ ታደሰ ለአምልኮ በታማኝነት ወደ ቤተ ክርስቲያን ይመጣ ነበር። **እግዚአብሔር በታደሰ አምልኮ ደስ እንዳልተሰኘ ታምናላችሁ? ለምን?** ተወያዩበት። በዛሬ ዕለት እግዚአብሔርን ብቻ የማምለክን ጥቅም ለማሰብ እንፈልጋለን። ይህም እግዚአብሔር ቀናተኛ አምላክ በመሆኑ ባልተከፈለ ልብ የሚቀርብ አምልኮ ነው።

የሕዝቅኤል 14 ታሪካዊ መሠረት፥ የባቢሎናውያን ሠራዊት በ 597 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት ኢየሩሳሌምን በከበቡ ጊዜ 10, 000 አይሁዳውያንን ባሪያ በማድረግ በምርኮ ወሰዱ። ከእነዚሁ መሀል 25 ዓመት እድሜ የሆነውና በኢየሩሳሌም ካህን ለመሆን ይዘጋጅ የነበረው ወጣቱ ሕዝቅኤል ይገኝበታል። ነገር ግን በምርኮ ምድር ካህን ሊሆን አልቻለም። ከ 5 ዓመት በኋላ 30 ዓመት ሲሞላው እግዚአብሔር ነቢይ እንዲሆን ጠራው። ስለዚህ የሕዝቅኤል አገልግሎትና ተግባር በባቢሎን አገር በምርኮ ለሚገኙት አይሁዳውያን ነቢይ መሆን ነበር።

ሕዝቅኤል 14፡1-11 ያለውን ክፍል አንብብ።

1- ከ 14:1 እንደምንመለከተው፥ ወደ ሕዝቅኤል የመጣው ማን ነበር? ለምን? በባቢሎን ምድር በምርኮ ይኖሩ የነበሩት አይሁዳውያን ሽማግሌዎች ከእግዚአብሔር ምክር ለመጠየቅ ወደ ሕዝቅኤል መጡ። ከእግዚአብሔር ዘንድ ቃልን በመጠበቅ በሕዝቅኤል ፊት ተቀመጡ። ስለሚኖራቸው ጥያቄ ከእግዚአብሔር መልእክት ለማግኘት በምርኮ የሚገኙት አይሁዳውያን አብዛኛውን ጊዜ ወደ ሕዝቅኤል ይመጡ ነበር (ሕዝ.20:1፥ 33:10)።

2- **እግዚአብሔር የሚመልስላቸው እንዴት ነበር?** (14:2-5)። እግዚአብሔር አምላክ ከእነዚህ ሰዎች ጋር ለመነጋገር አልፈለገም። ጥያቄዎቻቸውን እንኳን ለማንሣት ዕድል አልሰጣቸውም።

3 **እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር ያልተነጋገረው ለምንድን ነው?** (14:3)። ምክንያቱም በልባቸው ውስጥ ጣዖት አቁመው ነበር። ጣዖት በልባችሁ ውስጥ ማቆም የምትችሉት እንዴት ነው? ይኼ ምን ማለት ነው? ተወያዩበት። ጣዖት ውጫዊና የሚታይ ነገር ነው (በእንጨትና በድንጋይ ፊት መሰገድ) ወይም ውስጣዊና መንፈሳዊ ሊሆንም ይችላል። አእምሮአቸው ስለ አሕዛብ አምልኮ ማሰብ ቀጠለ። ስለ እነዚህ አማልክት ውበትና ኃይል ማሰብን ወደዱ። ምንም እንኳን እነዚህ አይሁዳውያን ሽማግሌዎች በእነዚህ ጣዖታት ፊት በአሕዛብ አምልኮ ልማድ ንቁ ተሳትፎ ባይኖራቸውም፥ ልባቸውና መንፈሳቸው ወደ ሐሰተኞች አማልክት አጋድለው ነበር። እግዚአብሔር እምላካቸውን በሙሉ ልባቸው፥ በሙሉ ነፍሳቸው፥ በሙሉ ጉልበታቸውና ኃይላቸው አልወደዱትም።

ለእግዚአብሔር ያላቸው ፍቅርና የመሰጠት ነገር የተከፋፈለ ነበር። እንደዚያም ሆኖ የእስራኤል አምላክ ወደ ሆነው እግዚአብሔር ለጥያቄ ይመጡ ነበር። ነገር ግን ልባቸው በምድሪቱ ጣዖታት ላይ የመደገፍ ፍላጐት ነበረው።

4- ምንም እንኳን እንደ ቊጥር 3 አሳብ እግዚአብሔር ለእነዚህ ሰዎች መልሰ ለመስጠት ጨርሶ ባይፈቅድም፥ ዝም ሊላቸው ግን አልቻለም። **እንደ ቊጥር 4፥ 5ና 8 አሳብ እግዚአብሔር ምን ተናገራቸው?** በእነርሱ ላይ የፍርድን ነገር አስተላለፈ። የተቀበሉት ቅጣት ለሌሎች እንደ ማስጠንቀቂያ ነበር። እግዚአብሔር የተገባቸውን ነገር በማድረግ በትክክለኛው መንገድ አስተናገዳቸው። እንደዚያም ቢሆን በበጐነትና በጸጋ የተሞላ ነበር። በተፈጸመባቸው ቅጣት ተጨባጭ ትምህርት አማካኝነት እግዚአብሔር የተቀሩት አይሁዳውያን ወደ እርሱ እንደሚመለሱ ተስፋ አደረገ።

5- **እንደ 14:6 አሳብ በልቡ ጣዖት ከሚያቆም ወገን ጋር እግዚአብሔር ጎብረት ያደርግ ይሆን?** አያደርግም። ይህ ወገን ምን ማድረግ አለበት? ንስሐ መግባትና ከጣዖት አምልኮ ፊቱን መመለስ።

6- የጣዖት አምልኮ ሁለት እርምጃዎችን የሚያጠቃልል ሲሆን፥ እንደኛው ከሌላው ጋር የተዛመደ ነው። **እንደ 14:7 አሳብ፥ እነዚህ ሁለት የጣዖት አምልኮ እርምጃዎች የትኞቹ ናቸው? (የአንድ ሣንቲም ሁለት ገጽታዎች ናቸው)።** ሁለቱ እርምጃዎች ከእግዚአብሔር "ራሱን ይለያል"፥ ከዚያም

"ጣያትን ያቆማል" የሚሉት ናቸው። የመጀመሪያው እርምጃ በጣያት አምልኮ ለእግዚአብሔር ያለህን የመጀመሪያ ፍቅር መተው ነው። ሁለተኛው እርምጃ እግዚአብሔር አምላክን በሉላ በተፈቀረ (በተወደደ) ነገር መተካት ነው፥ ይህም ጣያትን በልብ ውስጥ ማቆም ነው።

7- **ጣያት አምላኪ እግዚአብሔር አምላኩን ደስ ሊያሰኝ በሚችል መንገድ ማምለክ ይችላል ?** (14:7-8) በፍጹም አይችልም። እግዚአብሔር ጸሎቱን አይሰማም። እንዲያውም እግዚአብሔር ይፈርድበታል።

8- **በአሕዛብ መካከል ዛሬ ጣያት ናቸው ተብለው እንደ ምሳሌ የሚጠቀሱት የትኞቹ ናቸው?** ተወያዩበት። አንድ ሰው ከሙታን ጠሪ መናፍስት ወይም ደግሞ ከጠንቋይ እርዳታን ቢፈልግ፥ ይህ የጣያት አምልኮ ነው። ምትሐት በሚፈጽም አንድ ሰው ዋስትና ለማግኘት ቢፈልግ ይህ የጣያት አምልኮ ነው። ሰዎች የመጀመሪያውን ቦታ ለገንዘብና ለንብረት ቢሰጡ፥ እግዚአብሔርንና እርሱ ለሕይወታቸው ያለውን ፈቃድ ቢዘነጉ ይህ የጣያት አምልኮ ነው። ሰዎች በጎብረተሰቡ ውስጥ ስለሚኖራቸው የሥልጣን ወንበር ወይም ደግሞ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ይህንንም ለማግኘት ሲሞክሩ የእግዚአብሔርን ሕግ ቢተላለፉ ያ የጣያት አምልኮ ነው። ሰዎች ባለጸጋ ለመሆን ማንኛውንም ነገር ያደርጋሉ (ያጭበረብራሉ፥ ይዋሻሉ፥ ይሰርቃሉ)። ከእግዚአብሔርና ከእርሱ ሥራ ይልቅ ሥራቸውን ያስቀድማሉ። እግዚአብሔር አምላካችንን በሙሉ ልባችን ሳንወድ ስንቀር፥ ከእኛ ፍጹም የሆነ አምልኮና ታማኝነት ሲቀር በጣያት አምልኮ ውስጥ ገብተናል ማለት ነው።

9- **የክርስትናን አምልኮ ሌሎች አማልክትን ከማገልገል ጋር የማንደባልቀው ለምንድን ነው? የአሁኖቹ** አማልክት ብልጽግና፥ ኩራት፥ የሥልጣን ቦታ ሊሆኑ ይችላሉ? (ዘጸ. 20:4-5)። ተወያዩበት። ምክንያቱም እግዚአብሔር አምላክ ቀናተኛ አምላክ (ጌታ) ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ቀናተኛ አምላክ ነው ሲል ምን ማለቱ ነው? ተወያዩበት። ቅንዓት ለአንተ ብቻ የሚገባውን መብትህን ሌላው ሰው ሲነፍግህ በውስጥህ የሚቀሰቀስ ስሜት ነው። ባል ሚስቱ ታማኝነቷን ስታጐድልበት ቅንዓት ይነሣሣበታል። ባል ስላገባት እርሷ ለእርሱ ብቻ የተሰጠች ናት። እርሱ ደግሞ ለእርሷ ታማኝ ባይሆን ይኼ ቀናተኛ ያደርጋታል። በእርሱ ወይም በእርሷ የሚታይ ማንኛውም ታማኝነት የጐደለው ነገር ሁለታቸውንም ቀናተኞች ያደርጋቸዋል።

እግዚአብሔር አምላክ ሰማይንና ምድርን የፈጠረ፥ ከኃጢአታችን ያዳነን በመሆኑ፥ በሕዝቡ የመመለክና የመገልገል መብት ያለው እርሱ ብቻ ነው። እርሱን ብቻ እንድናመልክ እንጂ አምልኮአችን ለሌሎች አማልክት የተከፈለ እንዲሆን አይፈቅድም። እግዚአብሔር ቀናተኛ አምላክ ነው (ዘጸ. 20:5)፤ ስሙ ቀናተኛ ስለሆነ (ዘጸ. 34:14)÷ ስለ ቅዱስ ስሙ ይቀናል (ሕዝ.39:25)። ሌሎች አማልክትን እያገለገልን እግዚአብሔርን ማምለክና ማገልገል አንችልም። እግዚአብሔር እርሱን ብቻ እንድናመልከው ይጠብቅብናል። የራሳችንን ፍላጐትና ምኞት ጨምሮ የማናቸውንም አምልኮ አይፈቅድም።

የእግዚአብሔርን ቃል ተግባራዊ ማድረግ፦ የክፍሉ አባላት ከትዳር ጓደኞቻቸው ጋር ብቻ ሊኖራቸው ይገባል ብለው የሚያስቡትን የተለዩ መብቶችን ይዘርዝሩ። ይህም ማለት ባል ከሚስቱ ብቻ የሚጠብቀው እና ሚስትም ከባሏ ብቻ የምትጠብቀው ማለት ነው። እነዚህ መብቶች ሳይከበሩ ቢቀሩ ምን ዓይነት ስሜት ይሰማሃል? አሁን ደግሞ እግዚአብሔር እንደ ፈጣሪህና እንደ አዳኝህ በአንተ ላይ እርሱ ብቻ ያለውን መብት ዘርዝር። ይህም ማለት እግዚአብሔር ብቻ በሕዝቡ ላይ ምን ዓይነት መብት ነው ያለው? ለእግዚአብሔር ብቻ የሆነውን ይህንን መብት አስቀርተሃል? እግዚአብሔር በአሳብህ÷ በስሜትህና በተግባርህ ተደስቶአል?

ጸሎት፦ ለተሟላ አምልኮና አገልግሎት መላ ሕይወትህን ለእርሱ ለመስጠት እንዲረዳህ በመጠየቅ ለክርስቶስ ኢየሱስ ራስህን አየሰጠህ ጸልይ።

ጥናት አሥራ ሦስት

መንፈሳዊ ምንዝርና ከትክክለኛው አምልኮ ጋር ያለው አለመጣጣም

ሆሴዕ 4:10-14፤ 9:1-9

ዓላማው፦ እግዚአብሔር ከተመረጠው ሕዝብ ጋር ካለው የተለየ ግንኙነት የተነሣ በአምልኮአችንና በአገልግሎታችን ታማኝ የመሆንን አስፈላጊነት ለማሰብ፥ እግዚአብሔርን መተውና አመንዝራ የመሆንን ማለትም ለእግዚአብሔር ታማኝ አለመሆንን (የመንፈሳዊ

ምንዝርናን) አደጋ ለማስታወስ ነው።

የዓላማው ማብራሪያ፡- እግዚአብሔር በእርሱና በሕዝቡ መካከል የፈጠረው ልዩ ግንኙነት ከመጽሐፍ ቅዱሳዊ ጋብቻ ጋር ተነጻጽሮአል። እግዚአብሔር ሙሽራው ሲሆን፥ ቤተ ክርስቲያን ደግሞ ሙሽሪት ናት። የእግዚአብሔር ሕዝብ ለእርሱ ታማኝነት ማሳየት ሲያቅታቸው ይህ ሁኔታ ወደ ምንዝርና ይመራቸዋል (መንፈሳዊ ምንዝርና ማለት ነው)። እግዚአብሔር አምላክን እያመለክን፥ ሌሎች አማልእክትን የማገልገሉ ሙከራ በእርሱ ዘንድ የሚያስጠላ ነገርና ፈጽሞ ተቀባይነት የሌለው ነው።

የትምህርቱ አቀራረብ፡- ሆሴዕ ሰማርያ በ722 ዓ.ክ.ል.በ በአሦራውያን እጅ ከመውደቋ በፊት ለመጪረሻዎቹ 40 ዓመታት በሰሜናዊው እስራኤል በትልቅ የጣዖት አምልኮ ውስጥ በመግባት በተጨማለቀ ሁኔታ ውስጥ በነቢይነት ያገለግል ነበር። ሆሴዕ እግዚአብሔር አምላክ ለሕዝቡ ያለውን የፍቅር ጽናትና ወደ እርሱ እንዲመለሱ የሚፈልግ መሆኑን በማሳየት እስራኤልን ከጣዖት አምልኮ ለማስጠንቀቅ በእግዚአብሔር የተጠራ ነቢይ ነበር።

ሆሴዕ እምነት ሳጐደለችው ሙሽራ እግዚአብሔር ስላለው ፍቅር የማስተማሪያ መሣሪያና ለመልእክቱ ሕያው ምሳሌ ሆነ። እግዚአብሔር ለሆሴዕ ታማኝ እንደማትሆን ፈትኖ ያወቃትን ጐሜር የተባለችዋን ሴት እንዲያገባ አዘዘው (ሆሴዕ 1:2፥ 3:1-2)። ሦስት ልጆች ተወለዱ። ስማቸውም ከእግዚአብሔር መልእክት ባለው ስያሜ ተጠራ (ሆሴ. 1:4፥ 2:23)። ነገር ግን ሚስቱ ሌሎች ወንዶችን ፍለጋ ትታው ኮበለለች። ሆሴዕ ለሚስቱ ያቀረበው አቤቱታ እግዚአብሔር እስራኤል ወደ እርሱ እንዲመለስ ያቀረበው ተመሳሳይ ጥሪ ነበር። አይሁዳውያን ጥሩ ፍሬና ውጤት ያለው ምርት እንደሚሰጣቸው በማመን በአል የተባለውን የከነዓናውያን አምላክ ያመልኩ ነበር። እነርሱም እግዚአብሔርን በመተው እንደ አመንዝራ ሴት ሆኑ።

በሆሴዕ 4:10-14 ያለውን አንብብ።

1- እንደ 4:12 አሳብ፥ የእስራኤላውያንን ተግባር አብራራ። እንጨት ለሆነው ጣዖት ተናገሩ፤ ከእንጨት በትርም መልስ አገኙ። እነዚህ የእንጨት ጣዖቶች ለቤቱ የተመደቡ ጣዖቶችና ከእንጨትም የተሠሩ ሊሆኑ ይችላሉ (ተራፊም በመባል ይጠራሉ 3:4፤ ሕዝ. 21:21ን ተመልከት)። ጣዖትን በሚያመልኩበት ጊዜ አስማት በሚፈጽሙበት በትር አማካኝነት ከአማልክቶቻቸው ስለወደፊቱ ለማወቅ ሙከራ አደረጉ። በዚህ ተግባር (ሙከራ) ሁለት በትሮች ቀጥ ብለው እንዲቆሙ ይደረግና የጥንቆላ ጸሎት

እየተደገመ እንዲወድቁ ይደረጋል። ፊት ይሁን ኋላ፥ ግራ ይሁን ቀኝ በትሮቹ የሚወድቁበት አቅጣጫ ከአማልክቶቻቸው እንደመጣ መልእክት ተደርጐ ይተረጐማል (ሕዝ.21:21-22)።

2- በዚህ ዓይነቱ የጣዖት አምልኮና በምንዝርና መንፈስ መካከል ያለው ዝምድና ምን ይመስላል? (4:12)። ተወያዩበት። ሁለቱም ለእግዚአብሔር ያለመታመን ውጤቶች ናቸው። ጣዖት አምልኮ የምንዝርና መንፈስ ውጤት ነው። አጋንንትና ርኩሳን መናፍስት የእግዚአብሔርን ሕዝብ እርሱን እንዲተዉትና ከመናፍስት ጋር በመነጋገር ከእነርሱ ምሪትና እርዳታ እንዲያገኙ ይነዱዋቸዋል። ይሄ የጣዖት አምልኮ ነው።

3- በ 4:13 የተገለጹት ሌሎች ተግባራት የትኞቹ ናቸው? መሥዋዕትን ማቅረብና የሚቀርቡትን መባዎች ማቃጠል ናቸው።

4- ይህ የሚፈጸመው የት ቦታ ነበር? (4:13) በተራራ ጫፍ ላይና በአንዳንድ ዓይነት ዛፎች ሥር። በፍልስጥኤምና በመካከለኛው ምሥራቅ ጣዖትን ለማምለክ በጣም የሚወደዱ ስፍራዎች የተራራ ጫፍና ኩረብታማ ስፍራዎች ናቸው። እንደዚሁም ከፀሐይ ንዳድ ርቀው በጥላቸው ሥር ተቀምጠው ለማምለክ እንዲችሉ የሚመርጧቸው የዛፍ ዓይነቶች አሉ።

5- ከባዕድ አምልኮ ሌላ ምን የተለየ ተግባር አብሮ ይካሄዳል? (4:14)። ርኵሰት ይፈጽማሉ። እነዚህ "የቤተ መቅደስ አመንዝራዎች" ለከነዓናውያን አማልክት (አስታሮት ወይም ባአል)" አገልግሎት ራሳቸውን የሰጡ ሴቶች ናቸው። ይኸው የባዕድ አምልኮ አካል ለዚሁ ሃይማኖታዊ አገልግሎት ራሳቸውን ከሰጡት ሴቶች ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት መፈጸምን ያጠቃልላል። በዚህ ዓይነቱ ተግባር አዋቂዎች ተሳትፎ የሚያደርጉ እንደመሆናቸው መጠን፥ ወጣት ሴቶችና ወንዶችም በዚህ ርኵሰት ሥራ ይተባበራሉ። የርኵሰት ሥራቸው እያደገ ከመሄዱ የተነሣ እግዚአብሔር ምሕረቱን ነፍጐ ለርኵሰት አሳልፎ ሰጣቸው፤ ከዚህም የተነሣ በመንፈሳቸው የተበላሹ ሆኑ (ሮሜ 1:22-26፥28)።

6- ነቢዩ ስለ ምንዝርና የሚናገረው ለምንድን ነው? (4:10-13)። **ይህ በቀላሉ የሚያመለክተው ከወንድና ከሴት ጋር የሚደረገውን ርኵሰትና በቤተ መቅደስ የሚካሄደውን ምንዝርና ነው? ተወያዩበት።** ምንዝርና በእነዚህ ጥቅሶች ለእግዚአብሔር የሚያሳዩትን ያለመታመን ሕይወት የሚናገር ነው። እስራኤል ለአምላኩ ታማኝ ባለመሆኑ የሆሴዕ ሚስት

ጭሜር ምንዝርና ስለ እስራኤላውያን ተጨባጭ የማስተማሪያ መንገድ ነው። የምንዝርና መንፈስ ከእግዚአብሔር ርቀው እንዲሄዱ መራቸው። እነርሱም ለእግዚአብሔር የታመኑ አልነበሩም። የእርሱ ሙሽራ ለመሆን በእግዚአብሔር የተጠሩ የእግዚአብሔር ሰዎች በሌሎች አማልክት አምልኮ ተጠምደው ቢውድቁ እንደ አመንዝራዎች ያልታመኑ ይሆናሉ።

ሆሴዕ 9:1-9 ያለውን አንብቡ።

7- **ሆሴዕ እስራኤላውያንን እንዳይፈጽሙ ያዘዛቸው ምንድን ነው?** (9:1 ሀ)። "ደስ አይበላችሁ።" ሆሴዕ ሕዝቡ በግብጥው ጊዜ ደስ በተሰኘበትና ጥሩም ጊዜ ባሳለፈበት ወቅት ወደ እነርሱ መጣ። እስራኤላውያን በዳግማዊ ኢዮርብአም አገዛዝ ወቅት በብልጽግና አድገው ነበር። ለተወሰነ ጊዜም በሰላም ይኖሩ ነበር። ዋስትና እንዳላቸውና ደስተኛም እንደሆኑ ተሰማቸው። ከጥሩ ምርት የተነሣም በወቅቱ ደስ ይሰኙ ነበር። ነገር ግን ሆሴዕ በዚህ ሐሴት እንዳያደርጉ አስጠነቀቃቸው።

8- **ለምንድን ነው ሐሴት ማድረግ ያላስፈለጋቸው?** (9:3)። ምክንያቱም ፍርድ እየመጣ ነበር። ምርታቸውም ወደፊት ይከስማል (9:2)። ከዚህም በላይ በምድሪቱ ዋስትና አይኖራቸውም፤ ነገር ግን ወደ ግብፅና ወደ አሦር ይወሰዳሉ (9:3)።

9- **ፍርድ በእነርሱ ላይ የሚመጣው ለምንድን ነው?** (9:1 ለ)። ምክንያቱም ለእግዚአብሔር ታማኞች አልነበሩም። እርሱን በመተዋቸውና ምንዝርናን በመፈጸማቸው ፍርድ ይመጣባቸዋል።

10- **"በእህሉ አውድማ ሁሉ ላይ ግልሙትና ወድደሃል" ሲባል ምንን ለማመልከት ተፈልጌ ነው?** እስራኤላውያን ጥሩ አህል በመውቂያቸው ላይ መኖሩን ወድደዋል። ይህንንም ከሚያከብራቸው አማልክት እንደ ተቀበሉ አምነዋል። አይሁዶች ብቻውን እውነተኛና ሕያው ከሆነው አምላክ ይልቅ ለእነዚህ አሕዛብ አማልክት መባቸውን (ስጦታቸውን) ከምስጋና ጋር አቅርበዋል።

11- **በ9:4-9 እግዚአብሔር ምን ሌላ ፍርድ እንደሚመጣ ተናገረ?** ለወደፊቱ ከቤተ መቅደሱ ወደ ምርኩ አገር ርቀው ስለሚሄዱ የወይን ጠጅ መባና መሥዋዕታቸውን ማቅረብ አለመቻላቸውን ነው። ከዚህ በኋላ የመጠጥን ቁርባን አያፈስሱም። መሥዋዕታቸውንም በቤተ መቅደስ ውስጥ አያቀርቡም። በግብጥው ዕለት ሐሴት አያደርጉም (9:5)። እነርሱና ንብረታቸው ወደ ግብፅ ይጋዛሉ (9:6)፤ ቅጣትም ያገኛቸዋል (9:7-8)።

12- **በዛሬው ዕለት እኛም የጣዖት አምልኮ (መንፈሳዊ ምንዝርና እናካሂዳለን)?** ተወያዩበት። **ከሆነም ለእግዚአብሔር ታማኝ ሆነን ያልተገኘነውና፥ ሌሎችንም አማልክት ያገለገልነው በምን መንገድ ነው?** ተወያዩበት። ብዙዎች ለሥልጣንና ለብልጽግና ረሃብተኞች ናቸው። ሙሽራዋ አርግዛ እያለች እንኳን ወንዶችና ሴቶች ለክብርና ለዝና ሲሉ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የገንዘብ እርዳታ ዘመቻ ይካሄዳል። እግዚአብሔርን የሚወዱትና የሚያገለግሉት ሰዎች ለገንዘብ አሰባሰብ ዘመቻ ይጋበዛሉ፤ ሰዎች በወንዶችና በሴቶች ለመታየትና ለመከበርም እርዳታቸውን ይሰጣሉ። በዛሬ ጊዜ የብዙ ሰዎች አማልክት ብልጽግና፥ ሥልጣን፥ ዝናና፥ ማዕረግ ናቸው።

13- **የእኛ ጣዖት አምልኮ ሳይቀጣ ያልፋል?** ተወያዩበት። ምንም እንኳን ሰላም፥ የተትረፈረፈ ምርትና ልብስ በዛሬው ጊዜ ያለን ቢመስልም፥ እግዚአብሔር አምላክ እርሱን በምንተውበት ጊዜ ያለ ቅጣት አይተወንም። **እግዚአብሔር አምላክ የጣዖት አምልኮን በዘመናችን እንዴት አድርጎ ይቀጣል?** ተወያዩበት። ይኼ በተፈጥሮ አደጋ መልክ (በመብረቅ፥ በረሃብ)፥ በበሽታና ሞት ወይም በሌላ ዓይነት ችግር አማካኝነት ወይም በጦርነትና በግጭት መልክም ሊከናወን ይችላል። ቅጣት ከእግዚአብሔር ምሕረት የተነሣ ሊዘገይ ቢችልም፥ በዚህኛው ዓለምም ባይሆን እንኳ ከሞት በኋላ ባለው ሕይወት በርግጥ ይመጣል።

14- **እግዚአብሔር የበለጠ የሚጠላው የዳኑትን የእርሱን ሰዎች አለመታመን ነው ወይስ ጌታን ጨርሶ ያላወቁትን ወንዶችና ሴቶች አለመታመን ነው?** ተወያዩበት። ኃጢአት ሁሉ ኃጢአት ስለሆነ ላይቀጣ አይቀርም። ነገር ግን እግዚአብሔር አምላክ ወንጌልን ጨርሶ ካልሰሙትና ከርስቶስን ካላመኑት ይልቅ ጌታንና ቃሉን ያወቁትንና ያልታመኑትን በጽኑ ይቀጣል (ሉቃስ 12:43-48)። ደኅንነታችንን በትክክል ካገኘን በኋላ ለክርስቶስ ታማኝ አለመሆን ከፉ ሥራ ነው።

የእግዚአብሔርን ቃል ተግባራዊ ማድረግ፦ የሚከተለውን አሳብ አስተውል፣ ድነሃል? (ከዳንህ ከክርስቶስ ጋር ጋብቻ ፈጽመሃል።) ለእግዚአብሔር ታማኝ ነበርህ ወይስ በሌሎች አማልክት (ብልጽግና ወይም ሥልጣን፣ ጥንቆላ፥ ሟርት፥ መናፍስት ወይም ምትሀት) እየታመንህና እየተደገፍህ ነው? ለእግዚአብሔር ታማኝ ካልሆንህ ያሰቅጣት የሚተውህ ይመስልሃል?

ጸሎት፦ ታማኝ ሆነህ ስላልተገኘህ እግዚአብሔር ይቅር እንዲልህ እየጠየቅህና በእርሱ እርዳታና ችሎታ ታማኝ ልትሆንለት ቃል እየገባህ ጸልይ።

ክፍል አራት

የክርስቲያን አምልኮ በዛሬው ዘመን

አምልኮ ለእግዚአብሔር የተገባውን ነገር ሁሉ ማቅረብ ነው። "የታረደው በግ ኀይል፥ ሀብት፥ ጥበብ፥ ብርታት፥ ክብር፥ ውዳሴ፥ ምስጋና ለመቀበል የተገባው ነው " (ራእይ 5:12)። የእግዚአብሔር ታላቅነት ከልክ በላይ ስለሆነና በዓለም ላይ ከሚገኙት ሁሉ ስለሚበልጥ፥ ምስጋናችን፥ አድናቆታችን፥ አክብሮታችን፥ መታዘዛችንና እምነታችን ይገባዋል።

አምልኮ በቤት ውስጥ ከቤተሰብ አባላት ጋር በመሆንና በቤተሰቡ ኃላፊ መሪነት በየዕለቱ መደረግ ይኖርበታል። አምልኮ በእያንዳንዱ ሰው በቀኑ ውስጥ ሁሉ እርሷ ወይም እርሱ ሲያመሰግኑና ክብርን ለእግዚአብሔር ሲሰጡ በእምነትና በመታዘዝ መከናወን ይኖርበታል። አምልኮ የእግዚአብሔር ሕዝብ በጎብረት በቤቱ በአንድነት ሲሰባሰቡ መፈጸም ይኖርበታል።

እግዚአብሔርን ልናመልክ የምንችልባቸው መንገዶች አሉ። እግዚአብሔርን በየቀኑ 24 ሰዓት ሙሉ ልናመልከው ይገባል።

1/ ስውነታችንን እንደ መንፈሳዊ መሥዋዕት ለእግዚአብሔር በማቅረብ እናመልከዋለን፥

2/ ምስጋናችንን በዝማሬና በምስክርነታችን አማካኝነት በማቅረብ፥

3/ አሥራታችንን፥ መባችንን እንደዚሁም ምስጋናችንን ለመግለጽ ልዩ ልዩ ስጦታዎችን በማቅረብ፥

4/ በጸሎት ከእግዚአብሐር ጋር ጎብረት ስናደርግ ምስጋናን በማቅረብ ይሁን ልመናችንን በማሰማት፥

5/ ቃሉን ስናነብና ስንሰማ እምነታችንን በእርሱ ላይ ስናደርግና ስንታዘዘው እግዚአብሔርን እናመልካለን።

የሚከተለው በዛሬው ዘመን እንደ ክርስቲያን በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ ከአማኞች ጋር በምንሰበሰብበት ጊዜ እግዚአብሔርን እንዴት እንደምናመልከው የሚያሳይ ጥናት ነው። እንዲህ ዓይነቱ የአምልኮ ዘዴ በብሉይ ኪዳንም ውስጥ ይገኝ ነበር። በመሆኑም ብሉይ ኪዳንንና አዲስ ኪዳንን በአንድነት እናጠናለን።

እግዚአብሔርን

ሰውነታችንን በማቅረብ ስለማምለክ

"እንደ ዓቅማቸው መጠን ከዓቅማቸውም የሚያልፍ እንኳን ወደው እንደሰጡ እመሰክርላችዋለሁና.... አስቀድመውም በእግዚአብሔር ፈቃድ ራሳቸውን ለጌታ ለእኛም ሰጡ እንጂ እንዳሰብን አይደሰም" (2ኛ ቆሮ. 8:3-5) ከ 1962 ዓ.ም የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ዕትም የተወሰደ።

እግዚአብሔርን በተለያየ መንገድ እናመልከዋለን። ይሽውም ዝማሬዎችን በማቅረብ፥ ስለ እግዚአብሔር ታማኝነት በመመስከርና መባችንን እና አሥራታችንን በመስጠት ሊሆን ይችላል። ነገር ግን በጣም ጠቃሚ የሆነ እግዚአብሔርን የምናመልክበት መንገድ አለ። በመጀመሪያ እንደ ምስጋና ስጦታ ሰውነታችንን ለጌታ መስጠት አለብን።

በ 2ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 8 ውስጥ የተመለከተችው የመቄዶንያ ቤተ ክርስቲያን እንደ ምሳሌ የተጠቀሰች ናት። ምንም እንኳን ደሀ ቢሆኑም የበዛውን ስጦታቸውን ብቻ አይደሰም በደስታ ያቀረቡት፤ ከዚያም በላይ አስቀድመው ራሳቸውን ለጌታ ሰጡ እንጂ። ራሳችንን አስቀድመን ለጌታ ካልሰጠን እግዚአብሔር የምንሰጠውን ማንኛውም ነገር አይቀበልም።

ጥናት አሥራ አራት

ሰውነታችንን ለእግዚአብሔር ማቅረብ

ሮሜ 12:1

ዓላማው:- ከሮሜ 12:1 ላይ እንደምናነበው፥ እያንዳንዱ ምእመን የራሱን ሰውነት እንደ ሕያው መሥዋዕት በማቅረብ እግዚአብሔርን ማምለክ እንደሚገባው ይገነዘብ ዘንድ ነው፤ እግዚአብሔርን ለመታዘዝ ሰውነታችንን ስንጠቀም እግዚአብሔርን እያመለክን መሆናችንን ሰመረዳት ነው።

የዓላማው ማብራሪያ:- ክርስቲያኖች በአሁኑ ጊዜ ወደ ቤተ ክርስቲያን በመሄድና የቤተ ክርስቲያን አምልኮ በመካፈል እግዚአብሔርን ማምለክ ይወዳሉ። ነገር ግን አስቀድመው እግዚአብሔርን ለመታዘዝ ሰውነታቸውን ሕያው መሥዋዕት አድርገው ሳያስረክቡ ይህንኑ ማድረግ ይፈልጋሉ። ይሁን እንጂ

በመጀመሪያ እግዚአብሔርን ለመታዘዝ ሰውነታችንን ሕያው አድርገን ሳናቀርብ የምናሳየው ግንኙውም የአምልኮ ቅርጽ ወይም መንገድ በእርሱ ዘንድ ተቀባይነት የለውም።

የትምህርቱ አቀራረብ፡- በአንተ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሰዎች እግዚአብሔርን በሰውነታቸው የሚያመልኩት እንዴት ነው? ተወያዩበት። ምናልባት አንዳንዶች በሰውነታቸው፤ በዝማሬ፥ በጭብጨባ፥ በጭፈራ (በሽብሸባ) ወይም በጸሎት በእግዚአብሔር ፊት በመንበርከክ ወይም ደግሞ በሚዘምሩበት ጊዜ በመቆም ሊያመልኩት እንደሚችሉ ይናገሩ ይሆናል። ምናልባት ሰዎች በቤተ ክርስቲያን ስብሰባዎች ሲካፈሉ በሰውነታቸው እግዚአብሔርን ያመልካሉ ብለው ሊያስቡ ይችላሉ።

ነገር ግን እግዚአብሔርን በሰውነታችን የምናመልክበት መንገድ ይህ ብቻ አይደለም። ዛሬ እግዚአብሔርን በሰውነታችን ልናመልክ የምንችልበትን ትልቁን መንገድ ልናጠና እንፈልጋለን። ወደ ሮሜ 12፡1 ሄደን ጥቅሱን እንመልከት።

ሮሜ 12፡1ን አንብቡ።

1- ጳውሎስ በሮሜ 12፡1 ላይ እንድንፈጽም የሚገፋፋን ምንድን ነው? ሰውነታችንን ሕያው መሥዋዕት አድርገን እንድናቀርብ ነው።

2- ጳውሎስ ሰውነታችንን ሕያው መሥዋዕት አድርገን እንድናቀርብ ሲል ምን ማለቱ ነው? በምን ዓይነት መንገድ ነው ሰውነታችን ሕያው መሥዋዕት መሆን የሚችለው? ተወያዩበት። የእስራኤል ልጆች በብሉይ ኪዳን ውስጥ አብዛኛውን ጊዜ እግዚአብሔርን ያመለኩት በመሥዋዕት አማካኝነት ነበር። አንዱ ዓይነት መሥዋዕት በኃጢአታችን ምክንያት የነደደውን የእግዚአብሔርን ቁጣ ለማብረድ የተዘጋጀ ነው። ይህም የኃጢአት መሥዋዕት ነበር። ነገር ግን አዲስ ኪዳን ክርስቶስ ኢየሱስ ስለ እኛ የኃጢአት መሥዋዕት መሆኑን ያስተምረናል። እርሱም የዓለምን ሁሉ ኃጢአት ሊያስወግድ የእግዚአብሔር በግ ሆነ (ዮሐ. 1:29)። ክርስቶስ ኢየሱስ በመስቀል ላይ ሲሞት ኃጢአታችንን ለማስተሰረይ የራሱን ሰውነት እንደ ኃጢአት መሥዋዕት አቀረበ። (ይህም በክርስቶስ ኢየሱስ በምናምንበትና በምንናዘዝበት ጊዜ ኃጢአታችን ይቅር ይባል ዘንድ ነው።) በርግጥ ክርስቲያኖች ያን ዓይነት መሥዋዕት ዛሬ አያቀርቡም። ክርስቶስ ኢየሱስ ለዓለም ኃጢአት ለአንዴና ለመጨረሻ የራሱን ሰውነት አቅርቧል ።

ነገር ግን በብሉይ ኪዳን ሌላው ዓይነት መሥዋዕት ራስን የመለየት መሥዋዕት (ይህ ማለት ስለምትወደው ራስህን ለእግዚአብሔር ማስረከብ) ነው። ለኃጢአት ይቅርታ የሚሆን መሥዋዕት ከቀረበ በኋላ እርሱ ወይም እርሷ ራሳቸውን ጨርሰው የሰጡ መሆናቸውን ለእግዚአብሔር ለማሳየት የሚቃጠል መሥዋዕት ያቀርባሉ። ይህም የፍጹም መለየት ምልክት ነው። ዛሬ ምንም ዓይነት የእንስሳ መሥዋዕት አናቀርብም። ነገር ግን በዚህ ክፍል የመለየት መሥዋዕት አድርገን እግዚአብሔርን ፈጽመን ልንወደውና ልንታዘዘው ራሳችንን በመስጠት ሰውነታችንን እንድናቀርብ ታዝዘናል።

3- ጳውሎስ ሰውነታችንን እንደ መሥዋዕት እንድናቀርብ የሚነግረን ሰምንድን ነው? ተወያዩበት። ከእግዚአብሔር የምሕረት አሠራር የተነሣ ነው። በሮሜ መልእክት ከምዕራፍ 1-3 ሁላችንም ኃጢአተኞች እንደሆንንና የእግዚአብሔርም ፍርድ እንደሚገባን እንግራለን። ነገር ግን እግዚአብሔር በምሕረቱ ከእርሱ ጋር የተስተካከለ ነገር እንዲኖረን ስለ ኃጢአታችን አንዲሞት ክርስቶስ ኢየሱስን ሳከው (ሮሜ 3:21፤ 5:21)። እግዚአብሔር አምላክ ምሕረቱን በእኛ ላይ አብዝቶ ስለገለጸ ጳውሎስ ሰውነታችንን መሥዋዕት አድርገን በማቅረብ እንድናመልክ ይነግረናል (የኃጢአት መሥዋዕት ሳይሆን የመሰጠት መሥዋዕት ሆኖ)። ለእግዚአብሔር ሁለመናችንንና ያለንን ሁሉ ልንሰጥ ይገባናል።

4- በሮሜ 12:1 ጳውሎስ ልንሰጥ የሚገባንን የመሥዋዕት ዓይነት ይገልጻል። ጳውሎስ ሕያው መሥዋዕት ማቅረብ አስቸጋሪ ሲል ምን ለማለት እንደፈለገ ትረዳላችሁ? ተወያዩበት። በብሉይ ኪዳን መሥዋዕቶች በሙሉ አንድ ጊዜ ለመሥዋዕትነት ከቀረቡ በኋላ ይሞታሉ። የእንስሳው ሕይወት ያልፋል። ስለዚህ እንስሳው የሚሠዋው አንድ ጊዜ ብቻ ነው። ከዚያ በላይ ምንም የለም። ነገር ግን በዛሬው ጊዜ መሥዋዕታችን ሕያው መሆን አለበት። ይህም ማለት ከቀን ወደ ቀን የሚቀጥል ማለት ነው (ሁልጊዜ እስከ ሞት ድረስ)። መሥዋዕታችን ለአንድ ቀን ወይም ለሳምንት ብቻ አይደለም። ለግብዣ ወይም ለበዓል አይደለም። ሆኖም ከእግዚአብሔር ምሕረት የተነሣ በየጊዜው በየቀኑ የሚቀጥል ነው ።

5- የትኛው የሚቀልል ይመስላችኋል? አንድ ቀን ስብከት ሰትሰሙ በኃይል ተቀስትሣችሁ ሕይወታችሁን ለጌታ መስጠት ነው ወይስ በየዕለቱ ኑሮአችሁ ሁልጊዜ

ሕይወታችሁን ለእርሱ ማስረከብ? ተወያዩበት። ብዙ ሰዎች አንድ ጊዜ ጌታን ለመቀበል ውሳኔ ያደርጉና ከዚያ በኋላ ለእርሱ ለመኖር የሚያቅታቸው ለምንድን ነው? ተወያዩበት። ለጌታ ለኢየሱስ ክርስቶስ ያለንን እውነተኛ ፍቅር ማሳየት የምንችልበት ብቸኛ መንገድ በሕይወታችን ዘመን ሁሉ እያከበርነው ሰውነታችንን ሕያው መሥዋዕት አድርገን ስናቀርብ ነው።

6- ጳውሎስ "ቅዱስ" መሥዋዕት ሲል ምን ማለቱ ነው? በብሉይ ኪዳን ውስጥ የእንስሳ መሥዋዕት ነውር የሌለው ወይም "ያለ ነውር" (በእንስሳው ላይ ምንም ዓይነት ጉድለት የማይታይበት) መሆን ነበረበት። ዘሌዋውያን 1:3፥10ን ተመልከቱ። ለእግዚአብሔር ማየትና መራመድ የማይችል፥ ወይም በሌላ መንገድ ፍጹም ያልሆነ እንስሳ ማቅረብ ለእርሱ ስድብ ነበር። እግዚአብሔር ከዚያ ይልቅ የተሻለ ክብር ይገባዋል። ስለሆነም ራሳችንን ሕያው መሥዋዕት አድርገን ስናቀርብ ከኃጢአት ርቀን ንጹሕ መሆን አለብን። (1ኛ ጴጥ. 1:15-16) "እኔ ቅዱስ ነኝና ቅዱሳን ሁኑ ተብሎ ስለ ተጻፈ የጠራችሁ ቅዱስ እንደ ሆነ እናንተ ደግሞ በኑሮአችሁ ሁሉ ቅዱሳን ሁኑ" (ከ 1962 ዓ.ም የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ዕትም የተወሰደ)።

7- ጳውሎስ መሥዋዕታችን ተቀባይነት እንዳለው አድርጉ የሚናገረው ለምንድን ነው? መሥዋዕቶች ሁሉ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት የላቸውም? ተወያዩበት። በብሉይ ኪዳን ውስጥ አብዛኛውን ጊዜ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ስላለው መሥዋዕት እናነባለን። እነዚህ መሥዋዕቶች በሚቃጠሉበት ጊዜ ለእግዚአብሔር ደስ የሚል ሽታ ይሰጣሉ (ዘዳ. 29:18-25)። ለእግዚአብሔር ተቀባይነት ያለው መሥዋዕት በምናቀርብበት ጊዜ በሰውነታችን እየታዘዝነው መዓዛ እንዳለው መሥዋዕት የሚታይ ነው። የክርስቶስ የራሱ መሥዋዕት ለእግዚአብሔር መዓዛ እንዳለው ስጦታና መሥዋዕት ተገልጿል (ኤፌ. 5:2)።

8- ሰውነታችንን ለእግዚአብሔር ስንሰጥ በኃጢአት መኖራችንን ብንቀጥል ይህ መሥዋዕት እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ይመስልሃል? በእርሱ ዘንድ ተቀባይነት ያለው ነው? ተወያዩበት። በኃጢአት ከሚኖሩ ሰዎች የሚቀርቡ መሥዋዕቶች በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት አይኖራቸውም። እግዚአብሔር አምላክ የእስራኤል ልጆች ለእርሱ የማይታዘዙ ሲሆኑ እንዲህ በማለት አስጠንቅቆአቸዋል፤ "መልካሙንም መዓዛችሁን

አሳሸትም" (ዘሌ. 26:31)። በእግዚአብሔር ላይ ስላመፁና በኃጢአት ስለኖሩ፥ የእስራኤላውያንን መሥዋዕት እግዚአብሔር አልተቀበለም። "የመሥዋዕታችሁ ብዛት ለእኔ ምን ይረባኛል? እስከ አሁን ያቀረባችሁልኝ የአውራ በግ፥ የተቃጠለ መሥዋዕትና የፍሪዳ ስብ ሰልችቶኛል፤ በበሬና በበግ ጥቦት፥ በአውራ ፍየልም ደም አልደሰትም" (ኢሳ. 1:11)። ሰውነታችንን እግዚአብሔርን ለመታዘዝ እንደ ቅዱስ መሥዋዕት አድርገን ስናቀርብ በእርሱ ዘንድ ተቀባይነት ይኖረዋል።

9- ሰውነታችንን ለእግዚአብሔር እንደ ሕያው መሥዋዕት አድርገን ስናቀርብ ይህ ምን ተብሎ ይጠራል? (ሮሜ 12:1)። መንፈሳዊ የአምልኮ ተግባር ይባላል። ለምን መንፈሳዊ የአምልኮ ተግባር ተብሎ ይጠራል? ተወያዩበት። አብዛኛውን ጊዜ በአምልኮ ነገር ላይ ትኩረት የምናደርገው በዓይናችን የምናየው፥ በእጃችን የምንዳስሰው ወይም በጆሮአችን የምንሰማው ነገር ሲሆን ነው። አምልኮ የሚደረገው ቁሳዊ፥ ውጫዊና ሥጋዊ በሆኑ ሥርዓታዊ ነገሮች ነው። አምልኮ የምንከተለው ውጫዊ ቅርጽ ነው። ነገር ግን የክርስቲያን አምልኮ ከውስጣችንና መንፈሳዊ ከሆነው ነገራችን ይጀምራል። ለእግዚአብሔር እንታዘዘው ዘንድ ሰውነታችንን ሕያውና ቅዱስ መሥዋዕት አድርገን ማቅረብ ይኖርብናል። ልናቀርበው የሚገባን እውነተኛ አምልኮ ይህ ነው (ሮሜ 12:1)።

10- ሰውነታችንን ሕያው መሥዋዕት በማድረግ በተወሰነና ተግባራዊ በሆነ መንገድ ለእግዚአብሔር ልናቀርብ የምንችለው እንዴት ነው? ተወያዩበት። ይህንን ማድረግ የምንችለው ስንታዘዘው፥ ስናምነው፥ ስናከብረውና ስንወድደው ነው። እጃችን እንዲያገለግለው፥ እግራችን ለእርሱ እንዲሠራ፥ ከንፈራችን እርሱን እንዲያከብር፥ለእምሮአችን ስለ እርሱ እንዲያስብ በምናቀርብበት ጊዜ በሰውነታችን አመለክነው ለማለት እንችላለን። ሰውነታችንን የእርሱ ለሆነ አገልግሎት ስንሰጥ በዚያን ጊዜ ሰውነታችንን ሕያውና ቅዱስ መሥዋዕት አድርገን እናቀርባለን።

11- በተወሰነና ተግባራዊ በሆነ መንገድ ይህንን የሐዋርያው ጳውሎስ ማሳሰቢያ እንዴት ችላ ማለት እንችላለን? ሰውነታችንን ለራሳችን ጥቅም፥ ልናምፅበት ለኃጢአተኛ ዓላማችን ብንገለገልበት ያን ጊዜ እግዚአብሔርን በሰውነታችን ማምለክ አልቻልንም። ሁሉም ክርስቲያን ሰዎችን ወደ ኃጢአት ሊመራ የሚችል አሮጌው የኃጢአት ተፈጥሮ አለው።

ክርስቲያኖች በመንፈስ ቅዱስ ካልተሞሉና የሥጋንም ፈተና መቆጣጠር ካልቻሉ እግዚአብሔርን አያስደስቱም።

12- የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያናችሁ አምልኮ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ያለው ይመስላችኋል?

በዚህ ጥቅስ አሳብ ላይ ተወያዩ። አምልኮአችን በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ከማግኘቱ በፊት አማኞች ኃጢአታቸውን እርስ በርሳቸው መናዘዝ አለባቸው፥ የጥላቻን ኃጢአት፥ ኩራትን፥ ጉንቆላን፥ ርኵሰትን፥ ውሸትን፥ ስስትን፥ ምቀኝነትንና ሌሎችንም መተው አለባቸው (ገላ. 5:19-21፤ ኤፌ 5:3-4፤3:5-6፤ ያዕ. 5:16ን ተመልከቱ)።

የእግዚአብሔርን ቃል ተግባራዊ ማድረግ፦ ካነበብነው ቃል ተነሥተን አምልኮአችን በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት እንዳገኘ እርግጠኛ ሆነን መናገር እንችላለን? የራሳችንን ሕይወት አይተን እናስብ።

ጸሎት፦ በንስሐ ጸሎት ወደ እግዚአብሔር እንመለስ። በተወሰኑ ኃጢአቶች ላይ በእግዚአብሔር ፊት ንስሐ እንግባ። ኃጢአታችንን ከተናዘዝን በኋላ እግዚአብሔርን በሁሉም መንገድ ልንታዘዘው ሰውነታችንን ሕያውና ቅዱስ መሥዋዕት አድርገን እናቅርብ።

ምስጋናችንን እያቀረብን

እግዚአብሔርን ማምለክ

"ዘወትር እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ፤ እርሱንም ከማመስገን አልቈጠብም። ስላደረገውም መልካም ነገር ሁሉ፥ እግዚአብሔርን አመሰግንዋለሁ፤ የተጨቈኑም ሁሉ፥ ይህን ሰምተው ደስ ይላቸዋል። የእግዚአብሔርን ታላቅነት ከእኔ ጋር አስታውቁ፤ በጎበረተም ስሙን እናክብር።" (መዝ. 34:1-3)

በመታዘዝ ሕይወት እግዚአብሔርን ያለንግግር ማምለክ እንደምንችል አይተናል። ሰውነታችንን ሕያው መሥዋዕት አድርገን ለእግዚአብሔር ስንሰጥ እርሱ ይከብራል።

ነገር ግን እግዚአብሔርን በንግግራችንም ማለትም በምስክርነትና በመዝሙር እናመልካለን። በመዝሙር አማካኝነት ምስጋናችንን በማቅረብ እግዚአብሔርን እናመልካለን። ይህም የሚገባው ነው።

እንደዚሁም በክርስቶስ ማመናችንንና የእግዚአብሔርን ታማኝነት ለሌሎች በመናገር ስንመሰክር እግዚአብሔርን እናከብራለን።

የሚመሰክር ክርስቲያን ሕያው ስለሆነው እውነተኛ ወንጌል ምስክርነቱን መስጠት የቻለ ነው። እርሱ መስካሪ ነው። በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን በክርስቶስ ስለማመናቸው የሚሰጡት ይህ የአደባባይ ምስክርነት አብዛኛውን ጊዜ ክርስቲያኖችን ለእስራትና ቅጣት ዳርጓቸዋል (ማቴ. 10:18)። በእስር ቤት እንዲጣሉ ወይም ከሌሎች ተለይተው እንዲኖሩና ለሞት እንኳን አልፈው እንዲሰጡ አድርጓቸዋል (የሐዋ. 22:20፤ ራእይ 2:13-17፥ 6)። ከዚህም የተነሣ ምስክርነት ከሰማዕት ጋር የሚመሣሰል ነገር ሆነ። ሰማዕት ከምስክርነቱ ቃል የተነሣ የሚሞት ነው። ሰማዕት (Martyr) የሚለው የእንግሊዝኛው ቃል አንድ ሰው በክርስቶስ ከማመኑ የተነሣ ለሞት የሚጣል ሲሆን፥ የተገኘውም "ምስክር" ወይም "ማርተስ" ከሚለው የግሪኩ ቃል ነው።

ስለዚህ ክርስቲያን በክርስቶስ ላይ ካለው እምነት የተነሣ ለመመስከር የሚደፍር ሰው ነው። በክርስቶስ አያፍርም። በሌሎች ማንገጠጥ ወይም ስድብ ፍርሃት የለውም። ምንም እንኳን ይህ ወደ ሥቃይና ሞት ሊመራው ቢችልም፥ለሌሎች ስለ እግዚአብሔር ፍቅርና ጸጋ ለመናገር ደፋር ነው።

የክርስቲያን ምስክርነት በክርስቶስ ኢየሱስ፥ በሞቱና በሕይወቱ ባሳየው ምድራዊ አገልግሎት፥ በማዳን ኃይሉ፥ በጸጋውና በሕይወታችን ባሳየው በጉነት ግላዊ ልምምድ ላይ ያተኩራል። ክርስቲያናዊ ምስክርነት ወደ ራሳችንና ወደ ልምምዳችን ከማዘንበል ይልቅ ክርስቶስን ስለማክበር የሚናገር የግል ምስክርነት ነው።

ምስክርነት በማቅረብ መመስከር አለብን። እንደዚሁም በከንፈራችን፥ በንግግራችንና በመዝሙር አማካኝነት ለእግዚአብሔር ሕያው ሆኖ በቀረበው ሰውነታችን የዕለት ተዕለት ኑሮ ማክበር አለብን።

ጥናት አሥራ አምስት

በምስክርነት አማካኝነት እግዚአብሔርን ማመስገን

ኢሳይያስ 12:1-6፤ ዕብራውያን 10:23-25

ዓላማው፡- የእግዚአብሔር ልጅ በምስክርነት አማካኝነት እግዚአብሔርን እያከበረ እንዴት ማምለክ እንደሚችል ከኢሳ. 12:1-6 ለማየትና በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በሌሎች አማኞች ፊት ምስክርነት የማቅረብን ጥቅም ከዕብ.10:23-25 ለመማር ነው።

የዓላማው ማብራሪያ፡- መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔርን በተለያየ መንገድ ስለማክበር ያስተምረናል። ምስክርነት ማቅረብ እርሱን ለማክበር አንዱ መንገድ ነው። ነገር ግን አብዛኛው ክርስቲያን አንዱን ዓይነት ምስክርነት ብዙ ጊዜ ሲደጋግመው ይታያል። የሚሉት አዲስ ነገር የላቸውም። እንዴት ልትድን እንደቻልህ የሚያሳይ ምስክርነት መልካም ነው። ነገር ግን በእግዚአብሔር ማደግ አለብን። በየሳምንቱ እግዚአብሔር ስለሚያደርግልን አዳዲስ ነገሮች መመስከር መቻል አለብን። በኢሳይያስ 12:1-6 ያለው ክፍል እግዚአብሔርን በምስክርነታችን እንዴት ማክበር እንዳለብን ያሳያል። ዕብ. 10:23-25 ያለው ክፍል ደግሞ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በሌሎች ፊት የመመስከርን ጥቅም ያስተምረናል።

የትምህርቱ አቀራረብ፡- በምስክርነትና በስብከት መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው? ተወያዩበት። ስብከት ሰዎች እንዲያምኑ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እግዚአብሔር የሚያስተምረንን እንዲያስቡ በማደፋፈር ከቃሉ መልእክት ማቅረብ ነው። ነገር ግን ምስክርነት በግል ሕይወትህ እግዚአብሔር ያደረገልህን ነገር መመስከር ነው።

ለመጨረሻ ጊዜ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሰማኸው ምስክርነት ምን ይመስላል? መልእክት ነበር ወይስ ምስክርነት? አንዳንዶች ለሌሎች በመስበክና ይህንን ወይም ያንን እንዲያደርጉ በመናገር ለመመስከር ይሞክራሉ። ነገር ግን ይኼ ስብከት እንጂ ምስክርነት አይደለም። አሁንም እንዳንዶች ቀደም ሲል ያደርጉ የነበረውን ኃጢአት ሁልጊዜ መናገር ይወዳሉ። የዚህ ዓይነቱ ምስክርነት አማኞችን ሊገነባ የሚችለው እንዴት ነው? ዛሬ የትኞቹ ምስክርነቶች ጠቃሚ እንደሆኑና ምን ዓይነት ምስክርነቶች መሰጠት እንደሚገባን ለማጥናት እንፈልጋለን።

ኢሳይያስ 12:1-6ን አንብቡ።

1- እስራኤላውያን እግዚአብሔርን የሚያመሰግኑት ለምንድን ነው? (12:1) ምክንያቱም በእነርሱ ላይ የነበረው የእግዚአብሔር ቁጣ ስለተመለሰ ነው።

2- እስራኤላውያን እግዚአብሔር ከጠላቶቻቸው ካዳናቸው በኋላ ስለ እርሱ ምን ዓይነት ስሜት አደረባቸው?(12:2) እግዚአብሔር ለእነርሱ የቀረበ መሰላቸው። እግዚአብሔር የእነርሱ አዳኝ ሆነ። ይረዳቸውም ነበር። እግዚአብሔር እንዲመራቸውና የሚያስፈልጋቸውንም እንዲሰጣቸው ተስፋ ያደርጉት ነበር። እስራኤላውያን ይበልጥ ደስ የተሰኙት ስለ ደኅንነታቸው ነበር ወይስ ደኅንነትን ስላመጣላቸው እግዚአብሔር?(12:2) እስራኤላውያን "እግዚአብሔር መድኃኒቴ ነው" አሉ። እግዚአብሔርን ከደኅንነታቸው ነጥለው ማየት አይችሉም ነበር። እግዚአብሔር ራሱ የእርሱ ደኅንነት ለእነርሱ አስደናቂ ነበር። እግዚአብሔር ጸሎትህን በሚመልስበት ጊዜ ስለ ስጦታው የበለጠ ደስተኛ ነህ ወይስ ስለ ሰጪህም እንደዚሁ ደስተኛ ነህ? ተወያዩበት። አንዳንድ ጊዜ ሰዎች እግዚአብሔርን ይረሳሉ። ስለሰጣቸው ነገር ግን የበለጠ ደስተኞች ይሆናሉ። ይኼ ሊሆን አይገባውም።

3- "ከመድኃኒት ምንጭ ቀድተው የሚጠጡት" የሚለው የ12:3 አሳብ ምንድን ነው? ተወያዩበት። እግዚአብሔር ከጠላቶቻቸው አዳናቸው። ነገር ግን በደኅንነታቸው በረከት ደስ መሰኘታቸውን ይቀጥላሉ። አንድ ሰው ውኃ ለማግኘት ጉድጓድ ሲቆፍር በተገኘው ውኃ አንድ ቀን ብቻ ሳይሆን ለሁልጊዜ ተባርኮአል። ከጉድጓዱ ሁል ጊዜ ውኃ መውሰድ ይችላል። የደኅንነታችን በረከት ክርስቶስ ከኃጢአታችን ባዳነን ጊዜ ብቻ የምናገኘው ሳይሆን፥ በየዕለቱም የሚሆን ነው።

4- ኢየሱስ ጠምቶት ከጉድጓድ ስለሚጠጣ ሰው ይናገራል (ዮሐ. 4:13፥ 14፤7:37-39ን ተመልከቱ።) **የውኃው ምንጭ ስለ ማን ይናገራል?** ዮሐ. 7:39ን ተመልከቱ። ስለ መንፈስ ቅዱስ። አንድ ሰው ደኅንነት በሚያገኝበት ጊዜ በውስጡ የሚኖረውን መንፈስ ቅዱስ ይቀበላል። *መንፈስ ቅዱስ ከውስጥህ ካላደረ ደኅንነት አላገኘህም* (ሮሜ 8:9)። መንፈስ ቅዱስ በደኅንነትህ ደስ እንድትሰኝና እግዚአብሔርን እንድትታዘዝ ያስችልሃል። መንፈስ ቅዱስ መጽሐፍ ቅዱስን እንድትረዳና የመጽሐፍ ቅዱስን እውነት የሕይወትህ ክፍል እንድታደርግ ይረዳሃል።

5- እንደ ክርስቲያን ከመድኃኒት ውኃ ምንጭ ውኃ

እንዴት መቅዳት እንችላለን? (ኤፌ. 5:18-20)። ተወያዩበት። ለክርስቲያን ጥማቱን የሚያረካ "ሕያው ውኃ" መንፈስ ቅዱስ ነው። ኃጢአትህን በመናዘዝና መንፈስ ቅዱስ እንዲሞላህ፥ እንዲቆጣጠርህ፥ እንዲያዝህና እንዲመራህ ስትጋብዝ በውስጥህ እርሱ የመንፈስ ቅዱስን ፍሬዎች ያበዛል። በመንፈስ ቅዱስ በመሞላትና፥ ከኃጢአት፥ ከስይጣንና፥ ከዓለም በላይ ለመኖር የምንችልበትን ኃይል ለማግኘት በመንፈስ ቅዱስ ላይ መደገፍን በመማር ከመድኃኒት ውኃ ምንጭ ልንቀዳ እንችላለን።

6- ኢሳይያስ 12:4ን አንብብ። **ክርስቲያን ይህንን ጥቅስ እንዴት ተግባራዊ ሊያደርግ ይችላል?** ተወያዩበት። በምትኖርበት አካባቢ ላላመኑት ምስክርነት በመስጠት። አንዳንድ ክርስቲያኖች ለሌሎች ሰዎች እግዚአብሔር ስላደረገላቸው ነገር አክብሮታቸውንና ምስጋናቸውን ሳይናገሩ ሳምንቱን ያሳልፋሉ።

7- እንደ 12:5-6 አገላለጽ፥ **የአይሁዳውያን ምስክርነት ወደየት ይመራል?** ወደ መዝሙር። እግዚአብሔርን በንግግራችን ውስጥ፤ ምስክርነታችንን በዝማሬ በማቅረብ ልናከብረው እንችላለን።

8- **በሳምንት መካከል በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የምስክርነት ጊዜ አላችሁ ወይ? ካልኖረ ለምን?** በቤተ ክርስቲያናችሁ ውስጥ መቼና እንዴት እግዚአብሔርን ስለ መልካምነቱ ለማክበር ለክርስቲያኖች ዕድል መስጠት እንደሚቻል ተወያዩበት።

ዕብራውያን 10:23-25ን አንብብ።

9- በዕብ. 10:23 ላይ **የተመለከተው "አሁን አምነን የምንመሰክረውን ተስፋ ሳናወላውል አጥብቀን እንያዝ" የሚለው ምን ለማለት ነው?** ዕብራውያን ክርስቲያኖች ከችግራቸው የተነሣ የሚመሰክሩለትን ተስፋ ለመተው ተፈትነው ነበር (10:32-36፤12:4 ያለውን ክፍል ተመልከቱ)። ነገር ግን የሚመሰክሩለትን ተስፋ ላያወላውሉ አጥብቀው እንዲይዙ ተነግሮአቸው ነበር።

10- **እነዚህ አማኞች በራሳቸው ብቻ ምስክርነታቸውን አጥብቀው ለመያዝ ችለው ነበር?** (10:24-25) አይደለም። ከሌሎች ጋር ኅብረት ማድረግ አስፈልጓቸው ነበር።

11- እንደ 10:24 አሳብ **እርስ በርሳቸው ሊረዳዱ የሚችሉት እንዴት ነው?** ክርስቲያን ወገኖች እርስ በርሳቸው

እንዲዋደዱ በክርስቶስ ስላላቸው እምነት የራሳቸውን ምስክርነት በመስጠት እርስ በርሳቸው መልካም ለማድረግ በመበረታታት፥ በመነሣሣትና በመነቃቃት ነው።

12- **እርስ በርሳችን ልንበረታታ የምንችለው እንዴት ነው?** ተወያዩበት። በእያንዳንዱ ቀን ለሌላው ሰው የፍቅርና የመልካም ተግባር ምሳሌ በመተው ነው። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የእምነት ሕይወት ምስክርነታችንን ለሌሎች በመስጠትና ተስፋ ሳይቆርጡ በእምነት መኖር እንዳለባቸው በመናገር ነው። ኮንፍረንሶችን፥ የሽርሽር ፕሮግራሞችንና እርስ በርስ ለመበረታታት በጎበረት ሴሚናሮችን በመካፈል ነው።

13- **ለክርስቲያኖች የጎበረት ጊዜ ምን ያህል ትኩረት እንሰጣለን?** (10:24 እንዴት እንደሆነ ግን አስብ)። እንዴት እርስ በርስ መረዳዳት እንደምንችል ተገቢውን ትኩረት መስጠት አስፈላጊ ነው። በፍቅርና በመልካም ሥራ ለማደግ እርስ በርስ መረዳዳት የክርስትና ሕይወት ነው።

14- **በዛሬው ጊዜ ክርስቲያኖች ጎበረት እንዳያደርጉና እርስ በርስ እንዳይረዳዱ እየከለከላቸው ያለው ምንድን ነው?** ተወያዩበት። ሥራ በጣም ይበዛባቸዋል። የማቴ. 6:33ን አሳብ በመርሣት በቁሣዊ ነገር ብዙ ይጠመዳሉ። የቤተ እምነት ልዩነት ክርስቲያኖች እርስ በርሳቸው ጎበረት እንዳያደርጉ ያግዳቸዋል።

15- **እንደ ክርስቲያኖች እርስ በርሳችን ልንበረታታ የምንችለው በምን ተግባራዊ መንገዶች ነው?** (10:25) ተወያዩበት። ይህ ሊሆን የሚችለው በንግግርና ጎበረት በምናደርግበት ጊዜ በሚታዩ ምሳሌያዊ ነገሮች ነው። **ለማካፈል ምንም ዕድል ባይኖርና በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በየሳምንቱ መካከል ልንመሰክር መድረክ ካላገኘን እርስ በርሳችን ልንበረታታ እንችላለን ወይ?** ተወያዩበት። ቤተ ክርስቲያን ለዓመታት ቃሉን ለመስበክ ትልቅ ቦታ ተሰጥቶአታል። ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ እውነት ነው። ነገር ግን ያ በቂ አይደለም። ብዙዎች በጎበረታቸው አማካኝነት እንደሚያደርጉትና እንደሚመሰክሩት እርስ በርስ ለመበረታታት አንዳንድ ጊዜና አንዳንድ ቦታ አጋጣሚዎችንና ወቅቶችን እንፈልጋለን።

16- **አንድን አንጨት ነጥለው ቢያወጡት ምን ይሆናል?** እሳቱ ይጠፋል። **እንደ ክርስቲያኖች ይህ ለእኛ ምን ትምህርት አለው?** ተወያዩበት። በጎበረት ስብሰባዎች

አማካኝነት እርስ በርሳችን ካልተበረታታን በክርስትና ሕይወታችን መቀጠል አንችልም። የትኞቹ ክርስቲያኖች ናቸው ጠንካሮች? በየጊዜው ከክርስቲያኖች ጋር በመገናኘት ታማኝ የሆኑት ናቸው ወይስ ከክርስቲያኖች ጋር የመገናኘት ዕድል የሌላቸው? ተወያዩበት።

17- የእምነትንና በክርስቶስ የሚገኘውን ድል የሚያበስሩ ምስክርነቶች በመስጠት "እርስ በርስ ለመበረታታት" የምትችለው መቼና የት ነው? ተወያዩበት። በምስክርነት እርስ በርስ ለመበረታታት ምን ተግባራዊ እርምጃ መውሰድ ይቻላል? ተወያዩበት።

ቃሉን ተግባራዊ ማድረግ፦ ባለፈው ወር ጌታ በሕይወታቸው ምን እንዳደረገላቸው እንዲመሰክሩ ለተለያዩ ሰዎች ዕድል ለመስጠት አሁን ጊዜ ውሰድ።

ጸሎት፦ በእምነታችን ለማደግ እንዴት በተሻለ መንገድ እርስ በርሳችን መበረታታት እንደምንችል የጌታን እርዳታ ለማግኘት በጸሎት ወድቀን እንለምነው።

ጥናት አሥራ ስድስት

በዝማሬ ምስጋና ማቅረብ

መዝሙር 100፣ ኤፌ. 5፡18-21

ዓላማው፦ ከመዝሙር ምዕራፍ 100 አንድ አማኝ እንዴት አድርጉ ለጌታ የማክበር ዝማሬን በማቅረብ ማምለክ እንደሚችልና በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የዝማሬን አስፈላጊነት ከኤፌሶን 5፡18-20 ለማየት ነው።

የዓላማው ማብራሪያ፦ ሰዎች መዘመር ይወዳሉ። መዝሙር ክርስቲያኖች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እግዚአብሔርን ልናመልክ የምንችልበት በጣም ጠቃሚ መንገድ ነው። ነገር ግን ክርስቲያኖች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በሚዘምሩበት ጊዜ ለሌሎች ክብር ወይም ለታይታ ሳይሆን እግዚአብሔርን ለማክበር ብቻ መዘመር ይኖርባቸዋል። በዛሬው ዕለት በአምልኮአችን ለእግዚአብሔር

ስለምናቀርበው የምስጋና መዝሙር ጥቅምና ይህንን እንዴት መፈጸም እንደሚገባን ለማየት እንፈልጋለን።

የትምህርቱ አቀራረብ፦ ባለፈው አሑድ በቤተ ክርስቲያናችሁ አምልኮአችሁን የጀመራችሁት በየትኛው መዝሙር ነው? የመዝሙሩን ስም ጥቀስ።

ሦስት ዓይነት የዝማሬ መንገዶች አሉ። እነዚህም ወደ ላይ፥ ወደ ውጭ እና ወደ ውስጥ ናቸው?

ወደ ላይ ወደ እግዚአብሔር እየተመለከትን በዝማሬያችን ልናከብረው እንችላለን። ይህ ንጹሕ አምልኮ ነው። የንጹሕ አምልኮ ዝማሬዎች "ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ ቅዱስ"፥ "መልካም ጌታ ኢየሱስ"፥ "እግዚአብሔር ረዳታችን ሆይ"፥ "እናከብርሃለን እግዚአብሔር ሆይ አንተን"፥ "ብዙ ፍቅር ላንተ፥ "የጥንት አምባ" የተሰኙትን የእንግሊዝኛ መዝሙሮች ያጠቃልላሉ። እነዚህ ሁሉ ክርስቲያኖች በዝማሬያቸው እግዚአብሔርን ለማነጋገር ይረዷቸዋል። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የምንዘምራቸው ጥቂት መዝሙሮች ንጹሕ በሆነ አክብሮትና አምልኮት ለእግዚአብሔር የሚቀርቡ እውነተኛ ዝማሬዎች ናቸው።

ወይም የክርስቶስ አካል ወደ ሆኑት ምእመናን መመልከት እንችላለን። ስንዘምር ወደ እነርሱ በምንመለከትበት ጊዜ በዝማሬያችን ልንመሰክርላቸውና ልናደፋፍራቸው እንችላለን። ወደ ሌላው በምንመለከትበት ጊዜ ልንመሰክርላቸው የሚያስችሉን ክርስቲያናዊ ዝማሬዎች "አስደናቂ ጸጋ"፥ "ክርስቶስ ምን ዓይነት ወዳጅ ነው ያለን?" "ኃጢአቴን ማን ሊያነፃ ይችላል?" "ክርስቶስ ከፍሎታል"፥ "አስደናቂውን ታሪክ እዘምራለሁ" የተሰኙት ናቸው።

እነዚህ ሁሉ ዝማሬዎች እግዚአብሔር ለእነርሱ ያለውን በጐነትና ታማኝነት ክርስቲያኖችን ለሌሎች እንዲመሰክሩ ይረዷቸዋል። አብዛኛውን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የምናቀርባቸው ዝማሬዎች እነኝህን ይመስላሉ።

ወይም ወደ ውስጥ እየተመለከትን መዘመር እንችላለን። ወደ ልባችን ወደ ነፍሳችን እየተመለስን በምንዘምርበት ጊዜ ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን ግንኙነት እናስባለን። እነዚህን የመሰሉ የክርስቲያን ዝማሬዎች "ነፍሴ ሆይ ታገሽ"፥ "እንፃኝ"፥ "ነፍሴ ሆይ ንቂ ንቂ"፥ "የበረከት ሁሉ ምንጭ የሆንህ"፥ "አሁን ሙላኝ"፥ "እዋቂ የሆንከው አዳኜ እትለፈኝ" የተሰኙት ናቸው።

እነዚህ ሁሉ ክርስቲያናዊ መዝሙሮች መልካምና ጠቃሚ ናቸው። ነገር ግን እነዚያ ወደ ላይ የሚቀርቡት ከእግዚአብሔር ጋር

በቀጥታ የሚያነጋግሩን፥ እክብሮታችንና ምስጋናችንን ስናቀርብለት ትክክለኛ የአምልኮ ዝማሬዎች ናቸው።

ባለፈው እሑድ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የዘመራችኋቸው መዝሙሮች ሰዎች እግዚአብሔርን ለማክበር ወደ ላይ እንዲመለከቱ የሚረዱ ነበሩ ወይስ ወደ ውጭ የሚመለከቱ (ስለ ራሳችን ክርስቲያናዊ ልምምድ ለሌሎች ለመመስከር የሚያስችሉ የምስክርነት ዝማሬዎች) ነበሩ? ተወያዩበት። ወደ ላይ በማመልከት ከእግዚአብሔር ጋር እንድትነጋገሩና እንድታከብሩት የሚረዱአችሁ ብዙ ዝማሬዎች አቀረባችሁ? ተወያዩበት። በዛሬው ዕለት የመዝሙር 100 ጸሐፊ በዝማሬ እግዚአብሔርን እንዴት እንዳመለከው እናጠናለን። እንደዚሁም በዛሬው ቤተ ክርስቲያናችን እንደ ኤፌሶን 5:18-20 አሳብ ዝማሬ እንዴት ጠቃሚ እንደሆነ እንመለከታለን።

መዝሙር 100ን አንብብ።

1- የመዝሙረ ዳዊት መጽሐፍ ዓላማ ምን ነበር? የዳዊት ዝማሬዎች የሚያገለግሉት ለምን ነበር? ተወያዩበት። መዝሙረ ዳዊት በዕብራይስጥ "የምስጋና መዝሙሮች" የአይሁዶች የመዝሙር መጽሐፍ ነበር። የመዝሙረ ዳዊት መጻሕፍት በብሉይ ኪዳን ውስጥ አይሁዶች በአምልኮ ጊዜ የሚጠቀሙባቸው የሃይማኖታዊ ግጥሞች ስብስብ ነው። እነዚህ መዝሙሮች ከመንፈስ ቅዱስ የተገኙ ናቸው። እነዚህ የአምልኮ ዝማሬዎች ጥቂት ሰዎች ለአምልኮ በሚሰበሰቡበት ጊዜ ለትናንሽ ጉባዔዎች ያገለግሉ ነበር (ማቴ. 26:30)። እንደገናም የአይሁዳውያን የአምልኮ ስፍራዎች በሆኑት በአይሁድ ምኩራቦች፥ በአገልግሎት ላይ ይውሉ ነበር።

2- እንደ መዝሙር 100 አሳብ ሰዎች ጌታን ያመለኩት እንዴት ነበር? ተወያዩበት። በደስታና በሐሴት ይጮኹና የደስታ ዝማሬዎች ያቀርቡ ነበር። መዝሙር 100:2ን ("እግዚአብሔርን በደስታ አገልግሉት") ከመዝሙር 2:11ጋር("እግዚአብሔርን በፍርሃት አገልግሉት") አወዳድር። እነዚህ ሁለት ጥቅሶች እርስ በርሳቸው ይቃረናሉ ወይ? እግዚአብሔርን በመፍራትና በደስታ እንዴት ማገልገል ይቻላል? ተወያዩበት። አምልኮ በምንፈጽምበት ጊዜ ደስታም ፍርሃትም አስፈላጊዎች ናቸው። እግዚአብሔር ከፍ ያለና በክፍታ ስፍራ የሚገኝ፥ የሁሉም ፈጣሪ፥ የነገሥታት ንጉሥና የጌቶች ጌታ ነው። እግዚአብሔር ፍቅር ነው። ስላዳነንና ስለሚወደን በደስታ ልናመልከው እንችላለን።

3- ምድር ለእግዚአብሔር በደስታ መጮኽ ያለባት

ለምንድን ነው? (መዝ. 100) ተወያዩበት። እግዚአብሔር ፈጣሪያችንና እረኛችን ነው። እኛን መፍጠር ብቻ ሳይሆን፥ መጠበቅ፥ መመገብ፥ መምራትና፥ እንደ እረኛ መንከባከብም ተግባሩ ነው። ፈጣሪያችንና እረኛችንም በመሆኑ የእርሱ ነን። ከፍቅሩ፥ ከታማኝነቱና ከበጐነቱ የተነሣ (ቊ. 5) በአክብሮት እናመልከዋለን።

4- እግዚአብሔር እንደ እረኛ እንዴት ስለ እኛ ይጠነቀቃል? ፍላጐታችንን የሚያሟላው በምን መንገድ ነው? ተወያዩበት።

5- በብሉይ ኪዳን መዝሙር 100ን የሚዘምሩት ሰዎች ስለ እግዚአብሔር ማንነትና ለምን እንደሚያከብሩት ተናግረዋል። የምንዘምራቸው ዝማሬዎች እግዚአብሔርን ለምን እንደምናከብር መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምክንያት በመስጠት ስለ መጽሐፍ ቅዱስ እውነት የሚናገሩ ናቸው? ተወያዩበት። ከመጽሐፍ ቅዱስ እውነት ጋር የማይሄዱ ዝማሬዎችን ምሳሌ መስጠት ትችላለህ? ተወያዩበት።

ለብሔራዊ ክብረ በዓላት የሚያገለግሉ ለየት ያሉ ዝማሬዎችም አሉ። እንደዚህ ካሉት እንዳንዶችን ልታስብ ትችላለህ? ተወያዩበት። እነዚህ መዝሙሮች ስለ ክበረ በዓሉ ምክንያት ይናገራሉ። የምስጋና መዝሙሮቻችን ለምን እግዚአብሔርን እንደምናከብር በመጽሐፍ ቅዱስ እውነት ላይ የተመሠረቱ መሆን ይገባቸዋል።

6- በቊጥር 4 ላይ "እያመሰገናችሁ በመቅደሱ በሮች ግቡ" ሲል የቃላቱ ትርጉም ምንድን ነው?

በብሉይ ኪዳን ውስጥ የእግዚአብሔር ሰዎች ወደ ቤተ መቅደስ ሲሄዱ ለአምልኮ ዓላማ በበሮች ይገባሉ። ወደ ቤተ መቅደሱ እካባቢ ሲገቡ፥ ለአምልኮ መግባታቸው ነው። በየእሑዱ በቤተ ክርስቲያን ወደ እግዚአብሔር ፊት ስንቀርብ መላው አመለካከታችን ምን ይመስላል? ተወያዩበት። ወደ ቤተ ክርስቲያናችሁ ሰዎች እንዴት ሆነው እንደሚገቡ አሰላስል። ወደ እግዚአብሔር ለአምልኮ እንደሚመጡ በውኑ ያውቃሉ ወይስ እርስ በርሳቸው ስላምታ ለመለዋወጥና ለመነጋገር፥ እንደዚሁም ጥሩ የእንድነት ጊዜ እንዲኖራቸው በማሰብ ይመጣሉ? ወደ እግዚአብሔር ፊት በምስጋናና በአክብሮት ልንገባ ይገባል።

ኤፌሶን 5:18-20ን አንብብ።

7- ሰዎች በወይን ጠጅ የሚሰክሩት ለምንድን ነው? (5:18) ተወያዩበት። ችግራቸውን ለመርሳት፥ ደስተኛና ነፃ ለመሆን ስለሚፈልጉ ነው።

8- ችግርን ለመርሳት ከመጠጣት ይልቅ ክርስቲያን ምን ማድረግ አለበት? (5:18) በመንፈስ ቅዱስ መሞላት አለበት።

9- ሐዋርያው ጳውሎስ ስካርንና በመንፈስ ቅዱስ መሞላትን የሚያነጻጽረው ለምንድን ነው? (5:18) የሰከረ ሰው በወይን ጠጅ እንደሚነካ፥ ተጽዕኖ እንደሚደርስበትና በቁጥጥር ሥር እንደሚውል ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ የተሞላው ክርስቲያንም እንደዚሁ ነው። ይህም ማለት በዚህ ኃይል ይነካል፤ ተጽዕኖ ይደርስበታል፤ በቁጥጥርም ሥር ይውላል። በመንፈስ ቅዱስ የተሞሉ ሰዎች በጣም ሰላማዊ ናቸው። ቀጣይነት ባለው፥ ማቋረጫ በሌለው ሰላምና ደስታ የተሞሉ ናቸው። ነገር ግን የሰከረ ሰው ደስታ ፈጣን በሆነና በሚከፋ ችግር ያበቃል።

10- እያንዳንዱ ክርስቲያን በመንፈስ ቅዱስ ይሞላል ወይ? የለም፥ መንፈስ ቅዱስ በእያንዳንዱ ክርስቲያን ይኖራል (ሮሜ 8:9)። ነገር ግን ብዙ ክርስቲያኖች በመንፈስ ቅዱስ የተሞሉ አይደሉም።

11- በመንፈስ ቅዱስ ለመሞላት አንድ ክርስቲያን ምን ማድረግ አለበት? በየዕለቱ ኃጢአቱን መናዘዝና መንፈስ ቅዱስ እንዲሞላው በመጋበዝ መጸለይ ይኖርበታል (ይህም እንዲቆጣጠረው፥ እንዲያነቃቃው፥ እንዲመራውና ለእግዚአብሔር ክብር የራሱ እንዲያደርገው ነው።)

12- በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ሰው አንዱ ውጤት ምንድን ነው? (5:19) ይዘምራል፥ ለእግዚአብሔር ይቀኛልም።

13- አንድ ክርስቲያን ለራሱ በሚዘምርበት ጊዜ ይህ ስለ ሰውየው ምን ያስተምረናል? (ያዕ. 5:13)። ያ ሰው ወይም ያች ሴት በጌታ ደስተኛ ናቸው። ያዘነና ተስፋ የቆረጠ ሰው ይጸልያል። ነገር ግን እንደ ያዕቆብ መጽሐፍ አሳብ ደስተኛ ሰው ለእግዚአብሔር የአክብሮት ዝማሬ ያቀርባል።

14- በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ሰው የሚዘምረው መዝሙር ምን ዓይነት ነው? (5:19) ሦስት ዓይነት መዝሙሮች ተዘርዝረዋል። መዝሙረ ዳዊት፥ መዝሙርና መንፈሳዊ ዜማዎች። በእነዚህ ሦስቱ መካከል ያለው ልዩነት ምን ይመስልሃል?

በመሃከላቸው የጉላ ልዩነት ላይኖር ይችላል። በቀላሉ እግዚአብሔርን ለማክበር የሚረዱ መንፈሳዊ ዜማዎች የተለያዩ ቃላት ሊሆኑ ይችላሉ።

ነገር ግን መዝሙረ ዳዊት አይሁዳውያንና የጥንት ክርስቲያኖች የዘመሩዋቸው የብሉይ ኪዳን የአምልኮ ዝማሬዎችን ሊያመለክቱ ይችላሉ። መዝሙረ ዳዊት አውታር ባለው የሙዚቃ መሣሪያ በመታጀብ አይሁዶች የሚጠቀሙበት የተቀደሰ ዝማሬ ነው። ምናልባት የጥንት ክርስቲያኖችም የብሉይ ኪዳን መዝሙረ ዳዊት ምሳሌዎችን በመከተል መንፈሳዊ ዝማሬዎችን ጽፈው ይሆናል።

ምናልባት ውዳሴዎች እግዚአብሔርን ለማክበር የሚቀርቡ ሌላ ዓይነት ክርስቲያናዊ ዝማሬዎች ነበሩ። በተረፈ መንፈሳዊ ዜማዎች ያለ ዕቅድ ወይም አስቀድሞ ዝግጅት ሳይደረግባቸው በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት የሚቀርቡ አጭር ዝማሬዎች መሆን ይችላሉ።

15- በመጀመሪያ ደረጃ ዝማሬዎች ከየት ይመጣሉ? (5:14) ዝማሬዎች ከልብ ይመነጫሉ።

16- የዝማሬዎች ዓላማ ምንድን ነው? (5:20) ሌሎችን ለማደፋፈርና ለእግዚአብሔር ምስጋናን ለማቅረብ ነው።

17- እግዚአብሔርን ለማክበር የምትዘምሩዋቸው መዝሙሮች፥ ዜማዎች ወይም አዝማችች ምን ዓይነት ናቸው? ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ጋር ሊስማማ የሚችል ቃላት አሏቸው? እነዚህ በትክክል ጌታን ያስከብራሉ? ዝማሬህን ለእግዚአብሔር ክልብህ ለማቅረብ ይረዱሃል? ተወያዩበት። አንዳንድ አዝማችች ጥቂት ብቻ ትርጉም ያላቸው መሆኑ ያሳዝናል። አንዳንዶች አንዳውም የመጽሐፍ ቅዱስን እውነት አያስተምሩም።

18- አንተና መሰል ክርስቲያኖች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በሚካሄደው ዝማሬ አማካኝነት በርግጥ ለእግዚአብሔር ምስጋና እያቀረብን ነው ብለህ ታስባለህ? ተወያዩበት። ዝማሬህንና በመዝሙር ለእግዚአብሔር የምታቀርበውን አምልኮ ለማሻሻል ምን ማድረግ ይኖርብሃል? ተወያዩበት።

የእግዚአብሔርን ቃል ተግባራዊ ማድረግ፦ ለእግዚአብሔር የምታቀርበው የምስጋና ዝማሬ ምን ይመስላል? በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስለምታቀርቡት ዝማሬ አስብ። በምትዘምርበት ጊዜ ለእግዚአብሔር ክልብህ ትዘምራለህ?

ታከብረዋለህ? ወደ ቤተ ክርስቲያን ለአምልኮ በምትገባበት ጊዜ ደስታህን ጮክ ባለ ድምፅ ትገልጻለህ ወይ? የምትዘምራቸው መዝሙሮች ለአምልኮ የሚረዱህ ናቸው ወይ? ምናልባት አዳዲስ የአምልኮ ዜማዎች ወይም አዝማቾች መማር ያስፈልግህ ይሆናል። ወይም አንዳንድ አዳዲስ የምስጋና ዝማሬዎች መጻፍ ሊያስፈልግህ ይችል ይሆናል

ጸሎት፡- አንተና መሰሎችህ ስትዘምሩ እግዚአብሔርን ክልባችሁ ማክበር እንድትችሉ እንዲረዳችሁ አሁን ጠይቁት።

አሥራታችንና መባችንን በማቅረብ

እግዚአብሔርን ማምለክ

"የእግዚአብሔርን ክቡር ስም አመስግኑ፤ መባም ይዛችሁ ወደ መቅደሱ ግቡ፤ ቅዱስ የሆነው እግዚአብሔር በሚገለጥበት ጊዜ በፊቱ ስገዱ" (1ኛ ዜና 16:29)።

ልናምነው፥ ልንታዘዘውና ልንወድደው ሰውነታችንን ሕያው መሥዋዕት አድርገን ስናስረክብ እግዚአብሔርን እንደምናመልክ ተመልክተናል። በምስክርነታችንና በዝማሬያችን ስለ እርሱ የአክብሮት ቃል በምናቀርብበት ጊዜ እግዚአብሔርን በተጨማሪ ማምለክ እንችላለን።

ሌላው እግዚአብሔርን ለማምለክ ጠቃሚው መንገድ ያለንን ስጦታ ማቅረብ ነው። በእጃችን ከሚገባው ገንዘብ ወይም ከተሰበሰበው ሰብል 10% (አሥር በመቶ) መባችንና አሥራታችንን እንደታዘዝነው ለእግዚአብሔር በመስጠት እናከብረዋለን። ያም ሲሆን እግዚአብሔርን ሊያከብር በሚችል መንፈስ ማምጣቱ ጠቃሚ ነው። እግዚአብሔር ከእኛ የሚፈልገውን ስጦታ በአክብሮትና በምስጋና መንፈስ ይዘን ስንቀርብ ያን ጊዜ እግዚአብሔርን በትክክል እናመልከዋለን።

ጥናት አሥራ ሰባት

በስጦታችን እግዚአብሔርን የማክበር ጠቀሜታ

ኢሳይያስ 43:22-24፤ መዝ. 50:7-15፤ 116:12-17

ዓላማው፡- ለእርሱ የሚገባውን ስጦታ በመስጠት እናከብረው ዘንድ በስጦታ የማምለክን ጥቅም የሚያስረዱትን የተለያዩ ጥቅሶች ለማጥናት ነው።

የዓላማው ማብራሪያ፡- እግዚአብሔርን እንደ ምስክርነት፥ ዝማሬና ጸሎት በመሳሰሉ የተለያዩ መንገዶች እናመልከዋለን። ነገር ግን አንዱ ጠቃሚ መንገድ ለእግዚአብሔር ክብር የሚገባውን ስጦታ ማምጣት ነው። የስጦታዎቹ ዓይነቶች በብሉይ ኪዳንና በአዲስ ኪዳን ውስጥ ይለያያሉ። በታሪክ የእግዚአብሔር ሰዎች እንደ ምግብ፥ እንቁላል፥ ዶሮ፥ እንስሳትን የመሳሰሉትን የሥራቸውን ፍሬና የእጃቸውን ሥራ ውጤቶች ወደ እግዚአብሔር ያመጡ ነበር። እንደዚሁም ለእግዚአብሔር የገንዘባቸውንና የሰብላቸውን 10 % አቅርበዋል።

ነገር ግን ለእግዚአብሔር የምናቀርበው ማንኛውም ስጦታ ለታላቅና ቅዱስ ስሙ የሚገባ መሆን አለበት። ስጦታችን እግዚአብሔር ሊቀበል የሚገባውን ክብር የሚያሳይ መሆን ይገባዋል።

የትምህርቱ አቀራረብ፡- ለአንድ ሰው በርካታ አክብሮት መስጠት ስንፈልግ ይህን ማድረግ የምንችልባቸው በርካታ አጋጣሚዎች አሉ። እናታችን ወይም አባታችን፥ ለብዙ ጊዜ ያገለገለ ታማኝ ሠራተኛ፥ ወይም ምናልባት በትምህርት ቤት ፈተና ደህና ውጤት ያመጣ ልጅ ምስጋናን የሚያገኘው እንዴት ነው? ተወያዩበት። አንዱ መንገድ እንደ እንስሳት፥ ገንዘብ ያለ የተለየ ስጦታ በማበርከት ነው። ስጦታው ምንም ይሁን ምን ዓላማው እርሱን ደስ ለማሰኘትና አክብሮትን ለማሳየት ነው።

በዛሬው ዕለት ለእግዚአብሔር ታላቅና ቅዱስ ስም የሚገባውን ስጦታ በማቅረብ እርሱን እንዴት ማምለክ እንደምንችል ለማሰብ እንፈልጋለን።

ኢሳይያስ 43:22-24ን አንብቡ።

1- እግዚአብሔር በእስራኤላውያን ላይ ያቀረበው አቤቱታ ምንድን ነው? እግዚአብሔርን ሰልችተውታል፤

መሥዋዕታቸውንና ስጦታቸውን አላመጡለትም። በዚያ ፈንታ አምላካቸውን አስቸግረውታል። በኃጢአታቸው እንዲታክት አድርገውታል።

2- **ከመሥዋዕት ስጦታ ጋር አምልኮ የተገናኘው እንዴት ነው?** (43:23) እግዚአብሔርን ማክበር ማለት እርሱን ምለክ ነው። ከብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ በማክበር ከምስጋና ጋር መሥዋዕት ለእርሱ ማቅረብ ለእግዚአብሔር አክብሮት መስጠት ነው።

3- **በኢሳይያስ እንደተገለጸው፥ የእስራኤልን ልጆች የሚመስሉ ሰዎች በዛሬው ጊዜ ይገኛሉ? እግዚአብሔርን በስጦታቸው ማክበር ያቃታቸውና ይልቁንም በኃጢአታቸው ያሰለቹት ምን ዓይነት ሰዎች ናቸው?** ተወያዩበት። እነዚህ ሰዎች ወደ ቤተ ክርስቲያን ይመጣሉ። ነገር ግን እግዚአብሔርን ደስ ስለማሰኘት ብዙ የሚገዳቸው አይደሉም። ለእግዚአብሔር ሸክም የሆኑበት በኃጢአታቸው ብቻ አይደለም። ነገር ግን ለስሙ የሚገባውን ዓይነት ስጦታ በማቅረብ እውነተኛ አክብሮት መስጠት አቅቷቸዋል። ለምሳሌ ሰዎች በኳየር ውስጥ እግዚአብሔርን ለማክበር እሑድ ዕለት መዘመር ይችላሉ። ሆኖም በሳምንቱ ክፍለ ጊዜ በሕይወታቸው አያከብሩትም።

4- ብዙ ክርስቲያኖች በዛሬ ጊዜ የእሑድን አምልኮ ምክንያት አድርገው ከገቢያቸው 1% እጅ ያነሰ ገንዘብ ይሰጣሉ። **እግዚአብሔር በስጦታቸው ደስ የሚሰኝ ይመስላችኋል ወይስ ስለዚህ የቅሬታ መንፈስ አለው? በሚያደርጉት ድርጊት እግዚአብሔር ክብር እንዳገኘ ይሰማዋል?** ተወያዩበት። **ይህ ለምን ደስ የማያሰኘው ይመስልሃል?** ተወያዩበት።

መዝሙር 116:12-17ን አንብብ።

1- በመዝሙር 116:12 ላይ የመዝሙረ ዳዊት ጸሐፊ እግዚአብሔር ለእርሱ ስላሳየው በጐነት ሊከፍለው ይሻል። እንደ መዝሙር 116:1-11 አሳብ በምስጋና ሊሞላ ያስቻለውን ምን ነገር ፈጸመለት? የመዝሙረ ዳዊት ጸሐፊ ከሞት ወይም ከመቃብር ጋር ባወዳደረው በጣም አስከፊ ልምምድ ውስጥ አልፎአል። ይህ መዝሙር በጣም ዘግይቶ ነው የተጻፈው። ምናልባትም በምርኮ ከኢየሩሳሌም ርቆ የነበረበትን አስቸጋሪ ልምምድ ከሞትና ከመቃብር ጋር አወዳድሮታል። በአሁኑ ጊዜ እግዚአብሔር ጸሎቱን ሰምቷል።

ትልቅነትም ወደሚሰማው ሕያዋን ምድር ወደ ሆነችው ኢየሩሳሌም መልሶታል።

2- **የመዝሙረ ዳዊት ጸሐፊ ከእግዚአብሔር መልካምነት የተነሣ ሊያደርግለት የሞከረው ምንድን ነው?** (116:13) ተወያዩበት። የደኅንነቱን ቀንድ አነሣ። የእግዚአብሔርንም ስም ጠራ። የደኅንነትን ቀንድ ማንሣት ምን ማለት ነው? ይህ አይሁዶች በፋሲካ ክብረ በዓል ጊዜ የእግዚአብሔርን ስም የሚያከብሩበትንና የእርሱንም በጎነት የሚናገሩበትን ባሕላቸውን የሚያመለክት ነው (ከማቴ. 28:7 ጋር አነጻጽር)። ወይም በመቅደስ ወስጥ ያለውን ቁርባን (ዘኁ. 28:7) ያመለክታል። ምክንያቱም የመዝሙረ ዳዊት ጸሐፊ በመቅደስ ውስጥ ሊሆን ይችላልና። በተጨማሪም በዚህ ቦታ ስለ መሥዋዕት መጥቀሱ ይሆናል (116:17-19)። ምናልባት የሥጋ ቁርባን፥ የመጠጥ ቁርባንና ለእግዚአብሔር የሚቀርቡ መሥዋዕቶችን መጥቀሱ ይሆናል። ከዚያም የመጠጡን ቁርባን ባቀረበበት ጊዜ የጌታን ስም በመጥራት ጸለየ (ቁ. 13ለ)። ይህ እንግዲህ እግዚአብሔር ስላደረገለት መልካም ነገር ለሌሎች እንደመመስከር ያህል ነው።

3- **ስጦታ በማቅረብ እግዚአብሔርን የምናመልከው ለምንድን ነው?** ተወያዩበት። ምክንያቱም እግዚአብሔር አንድ ነገር ስላደረገልን ነው። እኛ ለጌታ ያለን ፍቅር እርሱ ለእኛ ላሳየው ፍቅር ምላሽ ነው። እርሱ ስለ ወደደን ስላዳነንም ስጦታችንን እናቀርብለታለን (መዝ 96:8-9 ን ተመልከቱ)።

4- **ወንጌል ላይገባ በፊት በአያቶቻችሁ ዘመን ስብል በሚሰበሰቡበት ጊዜ ለእግዚአብሔር በጐነት እንዴት ምላሽ ይሰጡ ነበር?** ተወያዩበት። አብዛኛውን ጊዜ አመሰግንሃለሁ ለማለት ያህል የሰብላቸውን በኩራት ያመጡ ነበር።

5- **የመዝሙረ ዳዊት ጸሐፊ ለእግዚአብሔር በጐነት አፀፋውን ለመመለስ ምን ሌላ ነገር አደረገ?** (116:14-18) ። ሕዝቡ ሁሉ በተገኘበት ለጌታ የገባውን ስዕለት ፈጸመ። ምናልባት እግዚአብሔር ከሞት ሲያድነው መዝሙረኛው በስጦታ ሊያመልከው ተስሎ ሊሆን ይችላል። አሁን ደግሞ በእግዚአብሔር ሕዝብ ፊት ስዕለቱን ለመፈጸም ወደ ቤተ መቅደሱ መጥቶአል።

6- **የመዝሙረ ዳዊት ጸሐፊ ወደ ቤተ መቅደስ ይዞ የመጣው ስጦታ ምን ዓይነት ነው?** (116:17-19) ወደ እግዚአብሔር ይዞ የመጣው ስጦታ የምስጋና መሥዋዕት ነበር ለብዙ

ዓመታት በምርኮ ሆነው በባርነት ባሳለፉበት ጊዜ በቤተ መቅደስ ውስጥ ለማምለክ ያልቻለውን ያህል እሁን ደግሞ የገባውን ተስፋ ለመፈጸም ተመልሶ ይገኛል። በሙሴ ሕግ የተጠየቀውን መሥዋዕት ለጌታ ይዞ መጥቶአል። እነዚህ የእንስሳትና የእህል ስጦታዎች ለእግዚአብሔር ምስጋና የማቅረቢያ መንገዶች ናቸው።

መዝሙር 50:7-15ን አንብብ።

1- **በመዝሙር 50:7-8 ውስጥ እንደሚናገረው፥ እግዚአብሔር በእስራኤላውያን ላይ ያለው አመለካከት** ምን ዓይነት ነው? ያርማቸዋል፤ ይገሥጻቸዋልም። እግዚአብሔር እምላክ በእነርሱ ላይ ይመሰክራል።

2- **የሚወቅሳቸውና፤ በእነርሱም ላይ የሚመሰክረው ለምንድን ነው?** (50:7-8) የሚወቅሣቸው መሥዋዕት ማቅረብ ስላቃታቸው አይደለም፤ ያለማቋረጥ መሥዋዕት ያቀርቡ ነበርና። ነገር ግን በትክክለኛው መንገድ ባለማቅረባቸው ያርማቸው ነበር። እስራኤላውያን በመሥዋዕታቸው እግዚአብሔርን ለመመገብ እንደሚፈልጉ ያስቡ ነበር። ከዚያ ይልቅ እግዚአብሔር ያከብሩት ዘንድ ስጦታቸውን ከምስጋና ጋር እንዲያቀርቡ ፈለገ። ስጦታቸውን ያቀርቡ በነበረበት መንገድ እግዚአብሔርን ማክበር አቅቶአቸው ነበር።

3- **እግዚአብሔር ስጦታችንን ይፈልግ ይሆን?** (50:9-13)። እርሱ ሁሉም ስላለው የእኛን ምንም ዓይነት ስጦታ አይፈልግም።

4- **እግዚአብሔር ከእኛ የሚፈልገው ምንድን ነው?** (50:14) ። እርሱ ከእኛ "የምስጋና ስጦታ" እና ቃል የገባነውን ስጦታ መፈጸማችንን ይጠብቃል።

5- **አንድ ነገር በሚያስፈልገን ጊዜ ምን እናድርግ?** (50:15) ጥያቄ በሚኖርህ ጊዜ ወደ እርሱ ጸልይ።

6- **እግዚአብሔር ከመለሰልን በኋላ ምን እናድርግ?** (50:15) "ለእግዚአብሔር ክብር ስጡ" ። እግዚአብሔርን ማክበር የሚገባን በምን ዓይነት መንገድ ነው? ተወያዩበት። ለእግዚአብሔር የምስጋና መሥዋዕታችንን በማቅረብ ነው።

7- **ስጦታህን ለቤተ ክርስቲያን የምትሰጠው ለምንድን ነው?** ተወያዩበት። አንዳንዶች ከልማድና ከወግ የተነሣ ይሰጣሉ። ሌሎች ደግሞ ስለሚፈለግባቸው ወይም ስለሚጠበቅባቸው

ይሰጣሉ። እንዲያውም በገናና በሌሎች የታወቁ በዓላት ወቅት ሰዎች ብዙ ገንዘብ እንዲሰጡ ከፍ ያለ ጫና ይደረግባቸዋል። ነገር ግን ስጦታችንን ለቤተ ክርስቲያን የምንሰጠው ለምንድን ነው? ተወያዩበት። ምክንያቱም ጌታን ስለምንወድ ነው። የእኛ ስጦታ እግዚአብሔር ስላደረገልን ነገር የምስጋና ስጦታ መሆን ይገባዋል። እግዚአብሔርን በእውነተኛ መንገድ በማመስገንና ምስጋናችንንም በምንሰጠው የመሥዋዕት ዓይነት በመግለጽ ልናከብረው ይገባል።

የእግዚአብሔርን ቃል ተግባራዊ ማድረግ፦ ዳግም ልደትን ካገኘህ እግዚአብሔርን ሊያከብር በሚችል መንገድ ልታገለግለው ይገባል። አገልግሎትህ በእግዚአብሔር ዘንድ የቱን ያህል ተቀባይነት አለው? ደስ የሚሰኝበትና የሚከብርበት ነው? አሥራትህንና መባህን እግዚአብሔርን ሊያስከብር በሚችል መንገድ ማቅረብህን ለማሰላሰል ጥቂት ጊዜ ውሰድ።

ጸሎት፦ በስጦታህ እግዚአብሔርን ለማክበር እርሱ እንዲረዳህ በመጠየቅ በጸሎት ስገድለት።

ጥናት አሥራ ስምንት

ስጦታችንን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የምንሰጥበት ክርስቲያናዊ የአፈጻጸም መምሪያ

1ኛ ቆሮንቶስ 16:1-4 ፤ 2ኛ ቆሮንቶስ 9:6-15

ዓላማው፦ በቆሮንቶስ መልእክት ውስጥ የሐዋርያው ጳውሎስን ትምህርት ለማጥናት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስጦታችንን የማቅረብ ክርስቲያናዊ ሕጐችን ለመማር ነው። እነዚህም ሕጐች ስጦታዎቻችንን 1/ ያለማቋረጥ፥ 2/ በልግሥና፥ 3/ በገቢያችን መጠን፥ 4/ ነፃ በሆነ መንፈስ ያለ ተጽዕኖ መስጠት እንደሚገባን የሚያስገነዝቡ ናቸው። 5/ የሚሰጠውም ገንዘብ የሌሎችን አገባብ ያልሆነ አስተሳሰብ ግምት ለመግታት በቤተ ክርስቲያን መሪዎች በታማኝነት መያዝ ይገባዋል።

የዓላማው ማብራሪያ፦ ክርስቲያኖች የአምልኮአቸው ክፍል ስጦታዎችን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ማበርከት እንደሆነ ያውቃሉ።

ነገር ግን አብዛኛዎቹ ክርስቲያኖች ሲሰጡ ሊመሯቸው የሚችሉትን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርቶች አይረዱም። በዛሬው ዕለት ጌታን በስጦታችን ስናመልክ ሊመራን የሚገባውን ሐዋርያው ጳውሎስን ቆሮንቶስ ሰዎች የጻፈውን መልእክት እናጠናለን።

የትምህርቱ አቀራረብ፦ ስጦታዎችን ከለዎች ለመቀበል ብዙዎቹ አብያተ ክርስቲያናት የሚከተሉዋቸው ልማዶች የትኞቹ ናቸው? ተወያዩበት። በጀት ለአጥቢያ ከበላይ አካል (ከአውራጃ ወይም ከክፍለ ማኅበር) ይተላለፋል። ለተወሰኑ ፕሮጀክቶች ማስፈጸሚያ በብዛት እንዲሰጡ ይጠበቅባቸዋል። አንዳንድ ጊዜ ፖስታዎችና ማስታወሻዎች ይታደላሉ። ብዙ ሰብክቶች ክርስቲያኖች እንዲሰጡ ለቅስቀሳ የታለሙ ናቸው። ነገር ግን በየሣምንቱ የሚገኘው ጥቂት ስጦታ ብቻ ነው። ከዚህ የተነሣ እንደገና ስጦታ በዓመቱ ውስጥ በአንዳንድ የስጦታ ጊዜያት ሳይ የተለየ ትኩረት ይደረጋል። ሽማግሌዎች፥ ሴቶች፥ ሠራተኞችና ወጣቶች የሚጠበቅባቸውን ያህል እንዲሰጡ ይነገራቸዋል። አንዳንድ ጊዜ እንግዳ ተጋባኝ በተገኘበት የገንዘብ አሰባሰብ ክፍለ ጊዜ ይካሄዳል። እያንዳንዱ ሰው የሰጠው ገንዘብ መጠን በግልጽ ለጉባኤው ሲነገር ብዙ ገንዘብ ይሰበሰባል።

በዛሬው ዕለት ጳውሎስ የቆሮንቶስ ክርስቲያኖች በኢየሩሳሌም ለሚገኙት አይሁድ ክርስቲያኖች ችግር የሚውል ስጦታ እንዲሰጡ ያደፋፈረበትን ልምዱን ለመመርመር እንፈልጋለን።

> *ታሪካዊ መሠረት፦* ቤተ ክርስቲያን ደኸና፥ ችግረኛ በተለይም የአይሁዳውያንን አማኞችን የመርዳት ልምድ ተምራለች። በኢየሩሳሌም ያሉት ክርስቲያኖች የደኸዩ ይመስላል። ሐዋርያው ጳውሎስ የአሕዛብ ክርስቲያኖች በኢየሩሳሌም ለሚገኙትና ድሆች ለሆኑት የአይሁድ ክርስቲያኖች ፍቅራቸውን እንዲያሳዩ ይፈልጋል። የአይሁድ ክርስቲያኖች በሥጋ የጐደላቸውን ነገር እየሰጡ በመርዳት የአሕዛብ ክርስቲያኖች በዓለም ዙሪያ ያሉት ሰዎች ሁሉ ያለቀለም ልዩነት ለክርስቶስ አንድ መሆናቸውን በግሳየት ለማረጋገጥ ይችላሉ። ስለዚህ ጳውሎስ ለአሕዛብ ክርስቲያኖች በኢየሩሳሌም ያሉትን ወንድሞችና እህቶች በሥጋ የሚያስፈልጋቸውን ነገር ማሰታወቅ ጀመረ። ጳውሎስ እንዲረዱአቸው ያዘጋጃቸው ጀመር። በ 1ኛ ቆሮንቶስ 16፡1-4 ለእግዚአብሔር ሰዎች አርዳታ ስለማሰባሰብ ሲጠቅስ ይህ የመጀመሪያው ነው። ከአንድ ዓመት በኋላ ስለዚህ ስጦታ ለቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ጳውሎስ እንደገና ደብዳቤ ጻፈላቸው (2ኛ ቆሮ. 8፡9)።

1ኛ ቆሮንቶስ 16፡1-4ን አንብብ።

1- በቆሮንቶስ ያሉት ክርስቲያኖች ገንዘባቸውን

ለእግዚአብሔር ቅዱሳን ማሰባሰብ የሚገባቸው እንዴት ነው? (16፡2)። ይህ ሥርዓት ባለው መንገድ ይፈጸም ነበር። ማለትም ስጦታቸውን በየሳምንቱ በፊተኛው ቀን (እሑድ) ወደ ቤተ ክርስቲያን ይዘው ይመጡ ነበር።

2- **ይህን ስጦታ መሰብሰብ የሚገባቸው ለምን ያህል ጊዜ ነው?** (16፡3)ጳውሎስ መጥቶ ስጦታቸውን ወደ ኢየሩሳሌም የሚልክበትን መንገድ እስኪያመቻች ድረስ ለተወሰነ ጊዜ ይህንን መፈጸም ነበረባቸው። ስለሆነም ክርስቲያኖች በየጊዜው ሳምንቱን እየቆጠሩ የተወሰነ ገንዘብ ማስቀመጥ ነበረባቸው።

3- **ክርስቲያኖች እንዲሰጡ የተነገራቸው ምን ያህል ነበር?** (16፡2)። በገቢያቸው መጠን። ከዚህ የተነሣ ድሆች ከባለጠጋዎች ያነሰ ይሰጡ ነበር። የመሰጠቱ ተግባር ከገቢያቸው ጋር የሚሄድ ነበር (ከእርሻቸው ወይም በደመወዝ መልክ ከሚከፈላቸው)።

4- **የገንዘቡ አያያዝና ወደ ኢየሩሳሌም የሚላክበት መንገድ እንዴት ነበር?** (16፡3) ገንዘቡ በየሳምንቱ መሰብሰብ ነበረበት። ከዚያ በኋላ ቤተ ክርስቲያን ገንዘቡን ወደ ኢየሩሳሌም እንዲያደርሱ ሰዎችን መመደብ ነበረባቸው። ጳውሎስ ሰዎቹ ይዘው የሚሄዱትን የስጦታውን ዓላማ የሚገልጽ ደብዳቤ ለኢየሩሳሌም ወገኖች ይጽፋል። ስለዚህ ማንም ሰው ገንዘቡ አለአግባብ ይባክናል ብሎ እንዳያስብ በጥንቃቄ መያዙን እንመለከታለን።

5- **ከሐዋርያው ጳውሎስ ትምህርት ዛሬ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሰሚደረገው የስጦታ አገልግሎት የሚረዳ ምን ጠቃሚ ነገር እንቀስማለን?** ተወያዩበት። ስጦታችን ሥርዓት ያለው ሊሆን ይገባል። ስጦታችን ለችግራችን እግዚአብሔር ባዘጋጀው መንገድ መፈጸም ይኖርበታል። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ታማኝነት ይጐድላቸዋል የሚለውን አሳብ ለመከላከል ስጦታችን በጥንቃቄ መያዝ ይኖርበታል።

2ኛ ቆሮንቶስ 9፡6-15ን አንብብ።

1- **ክርስቲያኖች ስጦታቸውን በምን ያህል መጠን መፈጸም ይገባቸዋል?** (9፡6) "በልግስና"። በልግስና መሰጠት ያለባቸው ለምንድን ነው? (9፡6) በልግስና የሚሰጥ ሰው በምትኩ ከእግዚአብሔር በልግስና ስለሚቀበል ነው። የምሳሌን መጽሐፍ በምናነብበት ጊዜ እንዳንድ ሰዎች ገንዘባቸውን በነጻነት ይበትናሉ ነገር ግን ሀብታቸው እየበዛ ይሄዳል። ሌሎች ደግሞ ያለልክ ለገንዘባቸው ይሳሳሉ። ነገር ግን ድኅነታቸው እየበዛ ይሄዳል። "ለጋስ

ሁን ትበለጽጋለህ። ሌሎችን እርዳ አንተም እርዳታ ታገኛለህ" (ምሳሌ 11:24-25)።

2- ክርስቲያን ምን ያህል መስጠት አለበት? (9:7) በልቡ እንዳሰበ። በልግስና እንዲሰጡ በክርስቲያኖች ላይ ግፊት መደረግ ይኖርበታል ወይ? ተወያዩበት። የለም። መስጠት የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ቅስቀሳ ውጤት መሆን አይገባውም። ክርስቲያኖች ከግፊት ተነሣሥተው መስጠት የለባቸውም። ክርስቲያኖች ለጥያቄው ካሰቡበትና ከጸለዩበት በኋላ እግዚአብሔር እንዲሰጡ የሚፈልግባቸውን በልባቸው እንዳሰቡ መስጠት ይገባቸዋል።

3- ክርስቲያኖች በስጦታችን ለጋስና፣ ሳንገፋፋ ነፃ በሆነ መንገድ መስጠት የሚገባን ለምንድን ነው? (9:7) ምክንያቱም እግዚአብሔር በደስታ የሚሰጠውን ይወዳል። ያም ማለት በከፍተኛ ደስታ የሚሰጠውን ሰው ማለት ነው። ለልመናህ ከእግዚአብሔር መልስ ለማግኘት ልታከብረው ትሞክራለህ ወይ? ተወያዩበት። አብዛኛው ሰው ይህንኑ ያደርጋል። የእግዚአብሔርን በጐነት ለማየት ክርስቲያኖች ከልመናቸው በፊት እግዚአብሔርን በጸሎታቸው አማካኝነት ማክበር ይገባቸዋል ወይ? ተወያዩበት። ውስጣዊ መነሾአችን ወይም ዓላማችን በጣም አስፈላጊ ነው። የእግዚአብሔር ሰዎች ከራስ ወዳድነት በመነጨ መንፈስ እግዚአብሔርን ማምለክ ወይም ማክበር የለባቸውም። እግዚአብሔርን የምናመልከው እግዚአብሔር ታላቅ ስለሆነ እንጂ የእግዚአብሔርን በጐነት በምትኩ የመቀበል ዓላማ ይዘን አይደለም። ነገር ግን ከፍላጐታችን ይበልጥ ለእግዚአብሔር ክብር ሲገደን ለእርሱ ያለንን ታላቅ ከበሬታ እናሳያለን። አብዛኛውን ጊዜ ሰዎች በግፊት በሚሰጡበት ጊዜ ስለ ስጦታቸው ደስተኞች ይሆናሉ ወይ? የተወሰነ ወይም የሚገባቸውን ያህል እንዲሰጡ በሚጠየቁበት ጊዜ በደስታ ያደርጉታል ወይ? ስሜታችሁን በመግለጽ ተወያዩ። በደስታ ባንሰጥ እግዚአብሔር በስጦታችን የሚከብር ይመስልሃል? አይከብርም። በግፊት በሚደረገው ስጦታችን እግዚአብሔርን ካላከበርንና ደስ ካላሰኘን ማንን ይሆናል የምናከብረው? ተወያዩበት። ሌሎችን ደስ ለማሰኘት በመሞከራችንና በሌሎች ፊት ደስ የምናሰኝ ሆነን ለመታየት በመሞከራችን ራሳችንን እናከብራለን።

4- በልግስናና በነፃነት ለመስጠት ምን ሌላ ምክንያት አለን? (9:8-11) ምክንያቱም እግዚአብሔር ብድራታችንን ይሰጠናል። ሰብላችንን ይባርካል (ያሣድጋል)። እኛንም በሁሉም

መንገድ ያበለጽገናል።

5- እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን ሕዝቡ አሥራታቸውን [ከተገኘው ነገር ከምግብ ይሁን ከገንዘብ አሥር ከመቶ (10%)] በታማኝነት እንዲሰጡ አዝዞአቸዋል። አሥራታችንን በተሟላ ሁኔታ ለእግዚአብሔር ባንሰጥ እርሱን ምን እያደረግን ነው? (ሚልክያስ 3:8-9) እርሱን እየሰረቅን ነው። ምክንያቱም እግዚአብሔር ከገቢያችን ከእርሻ ይሁን ከከብቶቻችን ይሁን ከገንዘባችን 1/10ኛውን ለእርሱ እንድንሰጥ ይጠይቀናል። (ዘሌዋ.27:30-33፤ ዘዳ.12:5-19÷ 14:22-29÷ 26:12-15÷ 2ኛ ዜና 31:5-13፤ ነህ.10:37)

6- ለእርሱ የሚገባውን በታማኝነት ብንሰጥ እግዚአብሔር ብድራታችንን እንዴት አድርጐ ይሰጠናል? (ሚል. 3:10) አሥራታችንን በተሟላ ሁኔታ ለእግዚአብሔር ብንሰጥ ምንም እስከማናጣ ድረስ እግዚአብሔር ይባርከናል።

7. በስጦታው ለጋስ ሆኖ ክርስቲያን ድሃ መሆን ይችላል ወይ? (2ኛ ቆሮ. 9:8) የለም። ከፍቅራችን የተነሣ ለእግዚአብሔር በለጋሽነት ብንሰጥ እርሱ ሁልጊዜ ይባርከናል። ለእኛ ከሚያደርግልን በላይ ልንሰጠው አንችልም።

8- የለጋስነት የነፃ ስጦታ (ያለ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ግፊት በራሳቸው ውሳኔ የሆነ) ሌላው ውጤት ምንድን ነው? (9:11-15) ለእግዚአብሔር የማመስገኛ መንገድ ነው። ሰዎች እግዚአብሔርን ያከብራሉ፤ ያመሰግናሉም።

9- ስጦታ እግዚአብሔርን የማምለኪያ መንገድ የሚሆነው እንዴት ነው? (9:7÷11-13) ለእርሱ ለጋሽ በመሆን እግዚአብሔርን ደስ እናሰኛለን። ሰዎች እግዚአብሔርን ያከብሩታል፤ ያመልኩታልም። ለእንግዶቻችሁ ምግባችሁን በልግስና ባታቀርቡላቸው ደስ ይላቸዋል ወይ? ተወያዩበት። ማንም ደስ አይለውም። እግዚአብሔር ታዲያ እንዴት ደስ ይለዋል? ነገር ግን ለእርሱ በልግስና እንስጥ። እርሱ ከእኛ የሚፈልገውን ስናደርግ የዚያን ጊዜ ለስሙ የሚገባውን ክብር እናቀርባለን።

የእግዚአብሔርን ቃል ተግባራዊ ማድረግ:- በጥንቃቄ እናስብ። እግዚአብሔር በንብረታችን አሰጣጥና ምንነት ይከብራል ወይ? እግዚአብሔርን በስጦታችን ታላቅነቱን በመናገር እናመልከዋለን ወይ? ካልሆነ ነገሮቻችን ለማስተካከል ምን ማድረግ

ይኖርብናል?

ጸሎት:- በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስጦታችንን በምናመጣበት ጊዜ እርሱን ደስ በሚያሰኝ መንገድ እናመልከው ዘንድ እግዚአብሔር እንዲረዳን በፊቱ በጸሎት እየሰገድን እንጠይቀው::

በጸሎት ውስጥ ምስጋናችንንና አክብሮታችንን በማቅረብ እግዚአብሔርን ማምለክ

እግዚአብሔርን በተለያዩ መንገዶች እያከበርን እናመልከዋለን:: ፈቃዱን ለማድረግ ሰውነታችንን በማቅረብ፥ በዝማሬ፥ በምስክርነት አክብሮታችንን በማቅረብ፥ እርሱ እንደጠየቀን አስራታችንና ምጽዋታችንን በመስጠት::

እግዚአብሔርን በጸሎታችን ደግሞ ልናመልከው ይገባል:: ጸሎት ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገር ነው:: ጸሎት ስለ ችግራችን እግዚአብሔርን ከመጠየቅ በላይ ነው:: በተጨማሪም ጸሎት ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገሪያ መንገዳችንና ስለ ታላቅነቱና ስለሚሰጠን መልካም ነገር ምስጋናችንንና አክብሮታችንን የምንገልጽበት መንገድ ነው:: እንዲህ ባለው መንገድ እርሱን ልናከብረው እንችላለን::

ጥናት አሥራ ዘጠኝ

በጸሎት አምልኮአችንን ለእግዚአብሔር ማቅረብ

ነህምያ 9:1-38

ዓላማው:- እንደ ነህምያ 9:1-38 አሳብ እግዚአብሔር ባለፉት ጊዜያት ስላከናወናቸው ተግባራት ሌዋውያን እግዚአብሔርን እንዴት እንዳከበሩት ለማየት፥ የወቅቱን ችግራቸውን ከመጥቀሳቸው በፊት ይህ አክብሮታቸው እንዴት እንደቀረበ በመመልከት እኛም ልመናችንን በፊቱ ከማቅረባችን በፊት እርሱን ለማክበርና ለማምለክ እንችል ዘንድ ነው::

የዓላማው ማብራሪያ:- አንዳንድ ጊዜ ለተወሰኑ ችግሮቻችን እግዚአብሔርን ለመጠየቅ ወደ እርሱ እንቀርባለን:: እንደ ነህምያ 9:32-37 አሳብ፥ ሌዋውያን ያደረጉት ይህንኑ ነው:: ይሁንና ብዙው ጸሎታቸው እምልክ ነው (9:5-31):: ሌዋውያን ያደረጉትን ጸሎት በማጥናት እግዚአብሔርን በጸሎት ውስጥ እንዴት ማምለክ እንደምንችል እንማራለን::

የትምህርቱ አቀራረብ:- የአፍሪካውያን ባሕላዊ ሃይማኖት አስተማሪዎች የአፍሪካውያን አምልኮ ዋነኛ ምክንያት ለአምላኪዎች ጥቅምን ለማስገኘት ነው ይላሉ:: እግዚአብሔር ታላቅ ከመሆኑም የተነሣ አክብሮት የሚገባው መሆኑን አውቆ ከማምለክ ይልቅ አፍሪካውያን በልመናቸው መልስ ለማግኘት ይችሉ ዘንድ እግዚአብሔርን ያመልኩታል:: አንድን የትምህርት ቤት ወይም የመንግሥት ባለሥልጣን በተለየ ጥያቄ በምትቀርብበት ጊዜ ለልመናህ ከእግዚአብሔር መልስ ለማግኘት ልታከብረው ትሞክራለህ ወይ? ተወያዩበት:: አብዛኛው ሰው ይህንኑ ያደርጋል:: የእግዚአብሔርን በጎነት ለማየት ክርስቲያኖች ከልመናቸው በፊት አግዚአብሔርን በጸሎታቸው አማካኝነት ማክበር ይገባቸዋል ወይ? ተወያዩበት:: ውስጣዊ መሻሻችን ወይም ዓላማችን በጣም አስፈላጊ ነው:: የእግዚአብሔር ሰዎች ከራስ ወዳድነት በመነጨ መንፈስ እግዚአብሔርን ማምለክ ወይም ማክበር የለባቸውም:: እግዚአብሔርን የምናመልከው እግዚአብሔር ታላቅ ስለሆነ እንጂ የእግዚአብሔርን በጎነት በምትኩ የመቀበል ዓላማ ይዘን አይደለም:: ነገር ግን ከፍላጎታችን ይበልጥ ለእግዚአብሔር ክብር ሲገድደን ለእርሱ ያለንን ታላቅ ከበሬታ እናሳያለን:: ልመናችንን ከማቅረባችን በፊት ለእግዚአብሔር ምስጋናና አክብሮታችንን መስጠት መልካም ነው::

ዛሬ የእስራኤል ሕዝብ ልመናቸውን ከማስታወቃቸው በፊት እርሱ ያደረገላቸውን አስደናቂ ነገር በመናገር እንዴት እንዳከበሩት ከነህምያ ምዕራፍ 9 ጸሎት ለማጥናት እንፈልጋለን::

የዚህ ጸሎት መሠረት በዘሌዋውያን 9:1-4፣ 36-38፣ 7:1፤8:1-18 ተጠቅሶአል:: ለጥበቃ በጣም አስፈላጊ የሆነው የኢየሩሳሌም ቅጥር በነህምያ አመራር ስጭነት ተጠናቆአል (7:1):: ዕዝራ ለበርካታ ቀናት የሙሴን የሕግ መጽሐፍ ለሕዝቡ ያነብብ ነበር (8:1-13):: ሕዝቡም የዳስ በዓል የሚባለውን ያከብሩ ነበር (8:14-18):: እስራኤላውያን የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማወቅና እርሱንም ደስ ሊያሰኙ ፈለጉ:: ምንም እንኳን የከተማው ቅጥር ይሠራ እንጂ ከምርኮ የተመለሱት አይሁዳውያን በምድሩ በነበሩት አሕዛብ ቁጥጥር ሥር እንደ ባሪያ ኑሮአቸውን በመምራት በከፍተኛ ችግር ውስጥ ነበሩ (9:37-38)::

የእግዚአብሔርን ቃል ማንበብ:- ምዕራፉን በሙሉ ከማንበብ ይልቅ ለእያንዳንዱ ጥያቄ የሚመለከተውን ጥቅስ እንዲያነቡ የተለያዩ አባላትን ጠይቅ።

1- **የእስራኤል ልጆች ለእንዲህ ዓይነት ጸሎት ራሳቸውን ለማዘጋጀት ምን አደረጉ** ? (9:1-4) **ለምን**? እስራኤል ማቅ ለብሰው በመጸለይ፥ ትቢያ በራሳቸው ላይ በመነስነስና ከባዕዳን በመለየት እግዚአብሔርን መፈለጋቸውን ቀጠሉ። ከቀኑ የተወሰነውን ከፍል የሙሴን ሕግ አነበቡ። ሌላውን የቀኑን ከፍል ደግሞ ኃጢአታቸውን በመናዘዝ እግዚአብሔርን አመለኩ (ቁ. 3)። ይህን ያደረጉት በከፍተኛ ችግር ውስጥ ስለሚገኙና የእግዚአብሔርን በረከት ለማወቅ ስለፈለጉ ነው።

2- **እንደ ምዕራፍ 9:5 አሳብ እግዚአብሔርን ለማምለክ ምን አደረጉ**? ቆመው እግዚአብሔርን አከበሩ።

3- **እንደ ምዕራፍ 9:6-8 አሳብ ለምንድን ነው ያከበሩት**? ምክንያቱም ያህዌ (እግዚአብሔር) ብቸኛ እምላክ ስለሆነ ነው። እርሱ የሰማይና የምድር ፈጣሪ ነው። እርሱ ሕይወትን የሚሰጥ ነው። የሰማይ ሠራዊት ያመልኩታል። እግዚአብሔር አብርሃምን መረጠ፣ ከእርሱም ጋር ቃል ኪዳን ገባ። ቃሉንም ጠበቀ። ከእነዚህ ምክንያቶች በመነሣት እግዚአብሔርን አከበሩ።

4- **ከቍጥር 9-15 ባለው አሳብ ስለ ምንና ምን ነገሮች ጸለዩ**? ከግብፃውያን ባርነት እስራኤልን ባዳነ ጊዜ የተገለጠውን ታላቁን የእግዚአብሔርን ክንድ አስታወሱ። በሲና ተራራ ላይ እግዚአብሔር እንዴት አድርጉ የሙሴን ሕግ እንደሰጣቸው አስታወሱ።

5- **እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ከግብፅ ባርነት ባወጣ ጊዜ ያሳየውን ታላቅ ሥራ መግለጽ የአምልኮ ሥራ ነው ወይ**? ከሆነስ እንዴት ነው የአምልኮ ሥራ ሊሆን የሚችለው? ተወያዩበት። ባለፈው ጊዜያት እግዚአብሔር ሊያድናቸው ሲፈልግ ኃይሉንና ክብሩን ያሳየባቸውን በርካታ መንገዶች ሲያስቡ ስለ እግዚአብሔር ታላቅነት ይመስክሩ ነበር። እግዚአብሔር ያደረገላቸውን ከአክብሮትና ከምስጋና ጋር ያስቡት ነበር። እግዚአብሔር ስላደረገው ነገር ሁሉ ውስጣቸው በአድናቆት ተሞላ።

6- **በ 9:16-21 ላይ የተገለጸው እና ለአምልኮ ያበቃቸው የእግዚአብሔር አስደናቂ ባሕርይ ምን ነበር**? ምንም እንኳን

እስራኤል እግዚአብሔርን ባይታዘዝም እርሱ ለእነርሱ ፈቃድ ቸር፥ በጐና ርኅሩኅ በመሆን ጸና፣ አሳጠፋቸውምም።

7- **በ 9:22-31 ላይ የተገለጹት የእግዚአብሔር ባሕርያት የትኞቹ ናቸው**? እግዚአብሔር መልካም መሆኑ (9:25)፥ ርኅራኄን መሞላቱ (9:28)፥ እርሱ በእስራኤል ላይ ታጋሽና (9:30) መሐሪ (9:31) መሆኑ ናቸው ።

8- ከቍጥር 7-31 ያለው አብዛኛው ጸሎት የእስራኤልን ታሪክ ዳግም መናገር ነው። **ይሄ የአምልኮ መልክ ያለው በምን ዓይነት መንገድ ነው**? ተወያዩበት። ስለ እግዚአብሔር ታላቅ ሥራ ራሳቸውን ያስታውሱ ነበር። እግዚአብሔር አምላክ ለእነርሱ እንዴት መልካም እንደነበረ ራሳቸውን ያስታውሱ ነበር። እርሱ የምሕረት፥ የትዕግሥት፥ የፍቅር አምላክ ነው። በታሪክ እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን መልካም የሆነበትን በመመስከር እግዚአብሔርን ያከብራሉ።

9- **ከዚህ ጸሎት ምን ዓይነት ትምህርት እንቀስማለን**? **በሕይወታችን እግዚአብሔር ያከናወነውን ታላቅ ነገር በተመለከተ በጸሎታችን ራሳችንን ስለምን ማስታወስ ይገባናል**? ተወያዩበት። በጸሎታችን እግዚአብሔር ለእኛ ያደረገውን አስደናቂ ነገር ሁል ጊዜ መጥቀስ ይኖርብናል። ለምሳሌ እንዴት እድርጉ ደኅንነት እንደሰጠን (ልናስታውስ እንችላለን)፣ ብዙ ጸሎታችንን እንደመለሰ፥ በታመምን ጊዜ እንደፈወሰን፥ ከአደጋም እንዳዳነን ልናስታውስ እንችላለን። ታሪካችንን ወደኋላ መለስ ብለን መቃኘትና እግዚአብሔር ለእኛ ያደረገውን አስደናቂ ነገር መመልከት እንችላለን። እግዚአብሔርን በግል ሕይወታችን ማስታወሳችን በራሱ የአምልኮ ይዘት አለው።

10- **ከቍጥር 32-37 ባለው ክፍል በትክክል ለእግዚአብሔር ያቀረቡት ጥያቄ ምን ነበር**? "የደረሰው መከራ ሁሉ በፊትህ ጥቂት መስሎ አይታይ" (ቍጥር 32)። ሌላ ምንም ጥያቄ አላቀረቡም።

11- **ይሠቃዩበት የነበረው መከራ ምን ነበር**? (9:36-37) በገዛ ምድራቸው ባሪያዎች ነበሩ።

12- **ይህንን ጥያቄ ባቀረቡበት ጊዜ በእግዚአብሔር ላይ ምን ዓይነት አመለካከት ነበራቸው**? (9:32-35)። በተዋረደና በተሰበረ ልብ በእነርሱ ላይ በሆነው ነገር ሁሉ የእግዚአብሔርን ጽድቅና ፍትሐዊ አሠራር መስከሩ። በእጭሩ

እግዚአብሔር ትክክልና እውነተኛ ሲሆን እነርሱ ግን በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት እንዲያገኙ የሚያስችል በጐ ነገር የሌላቸው ኃጢአተኞች መሆናቸውን በመናገር ለእግዚአብሔር ክብር ሰጡ፤ አመሰገኑትም:: ጥያቄአቸውን ባቀረቡበት ጊዜ እንዲህ ዓይነት ትሑትና የተሰበረ ልብ ሊኖራቸው የቻለው ለምን ይመስላችኋል? ተወያዩበት:: ችግራቸው የገዛ ኃጢአታቸው ውጤት እንደሆነ ተገነዘቡ:: እግዚአብሔር ይቀጣቸው የነበረው ከዓመፀኝነታቸው የተነሣ ነበር::

13. በዚህ ጸሎት ምሳሌነት በጸሎታችን እግዚአብሔርን እንዴት አድርገን እናምልከው? እግዚአብሔርን በምን ዓይነት ቃላት እንዴት አድርገን እናክብረው? ተወያዩበት::

14- የእስራኤል ሕዝብ (ልጆች) ይህንን የአምልኮ ጸሎት በሚያቀርቡበት ጊዜ በአእምሮአቸው (በአሳባቸው) የእግዚአብሔር ምሕረት ጥያቄና ካሉበት አስቸጋሪ ሁኔታ ነፃ የመውጣት ፍላጐት ነበረባቸው (9:32-38):: ልመናችንን ወደ እግዚአብሔር ማቅረብ የሚገባንን መንገድ በቶመለከተ በጸሎታቸው አቀራረብ ምን መማር እንችላለን? ምንም እንኳን በኃዘንና በችግር የተሞላን ብንሆንም ከምንም ነገር በላይ ወደ እግዚአብሔር ልመናችንን እያቀረብን እያለን እንኳን እርሱን እያመለክነውና እያከበርነው፥ በፊቱም ኃጢአታችንንና በደላችንን እያስታወስን ስለ እግዚአብሔርና ስለ ክብሩ ግድ ሊለን ይገባል::

የእግዚአብሔርን ቃል ተግባራዊ ማድረግ:- እግዚአብሔርን በግል ጸሎታችንና በቤተ ክርስቲያናችን እንዴት እናምልከው? ልመናችንን ከማቅረባችን በፊት ለስሙ የሚገባውን ክብር ለእግዚአብሔር እናቅርብ? እግዚአብሔርን የምናከብረው ስለ ማንነቱና ስለምንወደው ነው ወይስ ለልመናችን ምላሽ ስለሚሰጠን? በዚህ ሳምንት ጸሎታችንን በሙሉ በአምልኮና ከልባችን እርሱን በማክበር እንጀምር::

ጸሎት:- እግዚአብሔር ያደረገልህን ትልቅ ነገር፥ ምንም ኃጢአተኛ ብትሆንም እንኳን በሕይወትህ ስላላየህ ምሕረት በማስታወስ እግዚአብሔርን በዚህ ጊዜ በጸሎት አምልከው:: ምናልባት በጸሎት አምልኮህ ክፍለ ጊዜ መዝሙር 63:1-8ን ልትጠቀም ትችላለህ::

የእግዚአብሔርን ቃል በምንሰማበትና በምናደርግበት ጊዜ እምነታችንንና መታዘዛችንን እያቀረብንለት እግዚአብሔርን ማምለክ

<አንተ መሥዋዕትንና መባን አትፈልግም፤ እንስሳት በመሠዊያ ላይ እንዲቃጠሉ፥ ወይም ለኃጢአት ስርየት የሚሆን መሥዋዕት እንዲቀርብልህ አትጠይቅም፤ በዚህ ፈንታ የአንተን ትእዛዝ በመስማት እንዳገለግልህ አደረግኸኝ:: ስለዚህ "ስለ እኔ በሕግ መጽሐፍ በተጻፈው መሠረት እነሆ እኔ መጥቻለሁ:: አምላኬ ሆይ! ፈቃድህን ማድረግ በጣም እወዳለሁ፤ ሕግህንም በልቤ አኖራለሁ" አልሁ> (መዝ. 40:6-8)::

በከንፈራችን እግዚአብሔርን ማክበር ቀላልና ባዶ ሊሆን ይችላል:: እንናገራለን ነገር ግን አንፈጽምም:: እግዚአብሔርን ማምለክ የምንችልበት ቀዳሚው መንገድ በእምነትና በመታዘዝ ምላሌ መስጠት ይቻል ዘንድ የእግዚአብሔር ቃል ሲነበብ ወይም ሲሰበክ በጥንቃቄ በማድመጥ ነው:: ይህ የእግዚአብሔርን ቃል የማዳመጥ ነገር እግዚአብሔር ባዘዘን ነገር በእምነት በመታዘዝ ሲዋሃድ ለእግዚአብሔር በእውነት ክበሬታን እናሳያለን:: የቱንም ያህል በከንፈራችን እግዚአብሔርን ብናከብርም (የእግዚአብሔርን ቃል ስናነብ ወይም ስንሰማ) ይህ በእምነት በመታዘዝ ምላሽ የመስጠት ምትክ ሊሆን አይችልም::

ጥናት ሃያ

የእግዚአብሔርን ቃል ስንሰማ እምነታችንንና መታዘዛችንን ለእግዚአብሔር ማቅረብ

ዘዳግም 31:9-13፥ መዝሙረ ዳዊት 40:6-8

ዓላማው:- እንደ ዘዳ. 31:9-13 ና መዝ. 40:6-8 አሳብ፥ የእግዚአብሔር ቃል በሚነበብበትም ሆነ በሚሰበክበት በማንኛውም

ጊዜ በእምነትና በመታዘዝ ምላሽ በመስጠት እግዚአብሔርን ማምለክ እንደሚቻል ለመማር ነው።

የዓላማው ማብራሪያ፡- አምልኮ ለእግዚአብሔር ስም የሚገባውን ክብር ማቅረብ ነው። የሰብከት ዓላማ እንግዲህ ምንድን ነው? ሰብከት እግዚአብሔር ምን ማድረግ እንደሚጠብቅባቸው ለሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል የመንገሪያና የማስተማሪያ ጊዜ ብቻ ነው? ወይስ እግዚአብሔርን በሰብከት ጊዜ ማምለክ ይገባናል? የእግዚአብሔርን ቃል ማወቅ በቂ አይደለም። በእምነትና በመታዘዝ ምላሽ መስጠት ይገባናል። እግዚአብሔር የሚናገረውን ነገር ስናምንና በደስታ ስንታዘዘው ያን ጊዜ ለእግዚአብሔር ስም የሚገባውን ክብር በመስጠት አመለክነው ማለት እንችላለን።

የትምህርቱ አቀራረብ፡- ስለ አምልኮ ማለትም እግዚአብሔርን ደስ በሚያሰኝ መንገድ ማምለክ እንደምንችል እናጠናለን። በቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔርን ቃል ማንበብና ሰብከት ማቅረብ ለአምልኮ የሚረዳን እንዴት አድርጉ ነው? ተወያዩበት። እያንዳንዱ ምእመን አሳቡን እንዲሰጥ በማድረግ። ዛሬ የእግዚአብሔር ቃል ሲነበብና ሲሰበክ በማዳመት የእምነትና የመታዘዝ ምላሽን እየሰጠን እግዚአብሔርን ማምለክ እንደምንችል ለማየት የሚረዱንን በዘዳግምና በመዝሙረ ዳዊት የሚገኙትን ሁለት ክፍሎች ለማጥናት እንፈልጋለን።

ዘዳግም 31:9-13ን አንብብ።

1- **ሙሴ መጻፉን ከጨረሰ በኋላ የሕጉን ቃል የሰጠው ለማን ነበር?** (31:9) ታቦቱን ለሚሸከሙት ለካህናትና ለሌዋውያን ልጆች እንደዚሁም ለሽማግሌዎች ነው። የተጻፈውን ሕግ ሙሴ የሰጣቸው ለምንድን ነው? (ዘዳ. 31:24-27 ያለውን ተመልከቱ)። ካህናት ሕጉን ዋስትና ባለው ጥበቃና እግዚአብሔር ያዘዛቸውን በማስታወስ በቃል ኪዳኑ ታቦት አኖሩት። የካህናትና የሽማግሌዎች ተግባር ለሕዝቡ የሕጉን ቃል ማስተማር ነው። ስለዚህ የሕጉን ቃል እንዲጠብቁት፥ እንዲታዘዙትና ለሕዝቡ እንዲያስተምሩ ተሰጥቶአቸው ነበር።

2- **በዳስ በዓል ጊዜ ሕጉን በተመለከተ እስራኤላውያን ምን ማድረግ ይገባቸው ነበር?** (31:24-27) በሕዝቡ ፊት የእግዚአብሔርን ቃል ማንበብ ነው።

የዳስ በዓል ጠቀሜታ (ዘዳ. 16:13-17፤ ዘሌ. 23:33-36፤ 39-44 ያለውን ከፍል ተመልከቱ)፦

ሀ - በ7ኛው ወር (23:34) በሰብል መሰብሰቢያ ወራት መጨረሻ ላይ (23:39) ምንም ዓይነት ተግባር በማይፈጸምበትና በልዩ ስብሰባ ተጀምሮ በልዩ ስብሰባ በሚያበቃ መልኩ ለስምንት ተከታታይ ቀናት ይከበር ነበር።

ሰ- (ዘሌ. 23:39-44) የዳስ በዓል ተብሎ የተጠራበት ምክንያት እያንዳንዱ እይሁዳዊ ከዘንባባ ወይም ከሌላ ዛፍ ትናንሽ ዳሶች እንዲሠራና በዓሉ በሚካሄድባቸው ስምንት ቀናት ውስጥ በዚያ እንዲኖር ታዝዞ ስለነበር ነው።

ሐ- የዳስ በዓል የሰብል መሰብሰቢያ በዓል ተብሎ ይጠራ ነበር (ዘጸ. 23:16፤ 34:22)። ምክንያቱም የሰብል ጊዜ የደስታ ጊዜ በመሆኑ ነው (16:14)።

መ- የዳስ በዓል ማንም የደረሰ አይሁዳዊ በአምልኮ ወደ ኢየሩሳሌም እንዲሄድ ከሚጠበቅበት በእስራኤል ከሚገኙ ሦስት ታላላቅ በዓላት አንዱ ነው።

3- **ካህናት ለሕዝቡ የሕጉን ቃል እንዲያነቡ የተነገራቸው ለምንድን ነው?** (31:12-13)። ሕዝቡ የእግዚአብሔርን ቃል እንዲሰማ፥ እንዲማር፥ እግዚአብሔርን እንዲፈራ፥ እርሱም የተናገረውን በመታዘዝ ጥንቃቄ እንዲያደርግ ነው።

4- **መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔርን ፍሩ ብሎ ሲያስተምር ምን ማለቱ ነው?** (13:12-13፤ ምሳሌ 1:7ን ተመልከቱ።) ከዳንንና የቅድስና ኑሮ የምንኖር ከሆነ የእግዚአብሔርን ቅጣት መፍራት አስፈላጊ አይደለም። ነገር ግን ቅዱስ ፍርሃት ለእግዚአብሔር ሥልጣን የምናሳየው ከበሬታና ተገቢ ፍርሃት ነው። እግዚአብሔርን በምንፈራበት ጊዜ ቃሉን እንሰማለን። ማንኛውንም ኃጢአት ደግሞ እንጠላለን። እግዚአብሔርን መፍራት ማለት እግዚአብሔርንና ቃሉን ማክበር፥ ተገቢ ፍርሃት ማሳየትና መታዘዝ ማለት ነው።

5- **እግዚአብሔርን በትክክል ሳናመልክ የእግዚአብሔርን ቃል ማንበብ ይቻል ይሆን?** አዎን! እንዴት! ተወያዩበት። በፍርሃትና በመታዘዝ ለእግዚአብሔር ምላሽ ባለመስጠት ነው። እግዚአብሔርን ባለመታዘዝ ቃሉን ማዳመጥ እግዚአብሔርን አለማክበር ነው።

6- **አባት ልጁን አንድ ነገር እንዲፈጽም ቢያዝና ልጁ ግን ላለማድረግ እምቢተኛ ቢሆን ይህ አባትየውን ያስከብረዋል ወይ?** ተወያዩበት። አያስከብረውም። ዓመፀኝነት አባትየውን ያቃልላል (ዘጸ. 20:12)።

7- **ዛሬ ሰማያዊ አባታችንን የምናቃልለው እንዴት አድርገን ነው?** ተወያዩበት። ሳንታዘዘው በምንቀርበት ጊዜ ነው።

8- **በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ቃሉ በሚሰበክበት ጊዜ እንዴት አድርገን ነው በትክክል ማምለካችንን መናገር የምንችለው?** ተወያዩበት:: የእግዚአብሔር ቃል በሚነበብበትና በሚሰበክበት ጊዜ ከበሬታና ልዩ ፍርሃት ሊኖረን ይገባል:: ቃሉን የሚያነበው ሰው ያለምንም ስሕተት ማንበብ ይችል ዘንድ በደንብ መዘጋጀት አለበት:: ለሰዎች ማራኪና የሚያስፈልጋቸው እንደሆነ ተረድተው በሚቀበሉት መንገድ ማንበብ ይገባዋል:: ቃሉን የሚሰብከው ሰው እግዚአብሔርን በመውደድና ኃጢአትን በመጥላት የቅድስና ኑሮ የሚመራ መሆን ይኖርበታል:: ቃሉን የሚያዳምጡት ደግሞ በእምነትና በመታዘዝ በእግዚአብሔር ቃል ትኩረት የሰጡ መሆን ይኖርባቸዋል::

መዝሙር 40:6-8ን አንብብ::

9- **በ 40:6-8 የተጠቀሱትን የተለያዩ ዓይነት መባዎች ዘርዝር::** መሥዋዕቶች (የእንስሳት የደም መሥዋዕቶች) እና መባዎች (የእህል ስጦታዎች)፥ የሚቃጠልና የኃጢአት መሥዋዕቶች::

10- በዛሬይቱ ቤተ ክርስቲያን የእንስሳትን መሥዋዕት የአምልኮአችን አንዱ ክፍል አድርገን አናቀርብም፤ ምክንያቱም ክርስቶስ የእግዚአብሔር በግ ለሁላችን ሞቶአልና:: **እንግዲህ እግዚአብሔርን ዛሬ የምናመልከው በምን ዓይነት መንገዶች ነው?** የቤተ ክርስቲያን የአምልኮ ክፍለ ጊዜያትን በመካፈል፥ ለእግዚአብሔር የምስጋናን መዝሙር በመዘመር፥ በመጸለይ፥ እግዚአብሔር እንዳዘዘን መባችንን በመስጠትና በመሳሰሉት ነው::

11- **እግዚአብሔር እስራኤላውያንን መሥዋዕቶችንና የእህል ቁርባን እንዲያቀርቡ ካዘዘ ለምንድን ነው ዳዊት እግዚአብሔር መሥዋዕትንና መባን አይፈልግም ያለው?** (40:6-8፤ እንደዚሁም ሆሴዕ 6:6፤ አሞጽ 5:21-24፤ ሚኪያስ 6:6-8):: ምክንያቱም ከማንኛውም (እንደ መሥዋዕት ካሉ ስጦታዎች) ውጫዊ የአምልኮ መግለጫዎች ይልቅ እግዚአብሔር ለቃሉ መታዘዝን ስለሚፈልግ ነው (ፍትሕ፥ ጽድቅ፥ በጐነት፥ ትሕትና፥ የእግዚአብሔር ቃል እውቀት ሳሳቸው ነገሮች)::

12- **በዛሬው አምልኮአችን መሥዋዕታችንን ከመስጠት፥ ከመዘመር፥ ከመጸለይና መልእክት ከመስማት በላይ በጣም ተፈላጊው ምንድን ነው?** ተወያዩበት:: እግዚአብሔርንና ያለውን

ሁሉ በማመን ቃሉን መታዘዝ ነው::

13- **ዳዊት "ጆሮዬን ከፈተው" ሲል ምን ማለቱ ነው?** (40:6) እግዚአብሔር ጆሮአችንን የፈጠረው ለመስማት ነው:: ስለዚህ የእኛ ኃላፊነት የእግዚአብሔርን ቃል ለመስማት ጆሮአችንን መጠቀም ነው::

14- **እንስሳትን ከመሠዋትና የእህል ቁርባን ለእግዚአብሔር ከማቅረብ ይልቅ እግዚአብሔር ከእኛ የሚፈልገው ምንድን ነው?** (40:7-8) ልክ እንደ ታዛዥ አገልጋይ በፈቃደኛ መንፈስ በፊቱ በመቆም ለእግዚአብሔር አገልግሎት ዝግጁ መሆን ይገባናል:: የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማድረግ ደስተኞች ልንሆን ይገባናል::

15- **እነዚህን ምንባቦች ፈጽሞ ያሟላው ማን ነው?** (ዕብ. 10:5-7ን ተመልከቱ):: ኢየሱስ ክርስቶስ ፈለጉን እንከተል ዘንድ እግዚአብሔርን የመታዘዝ ፍጹም የሆነ ምሳሌ ሰጥቶናል::

የእግዚአብሔርን ቃል ተግባራዊ ማድረግ:- ቤተ ክርስቲያን የሚካፈል ሁሉ የእግዚአብሔር ቃል ሲሰበክ ይሰማል:: ስብከት የምትሰማው ለምንድን ነው? እንዴትስ ታዳምጣለህ? እግዚአብሔር የሚናገረውን በማመንና በመፈጸም እግዚአብሔርን ታመልካለህ ወይ? ወይስ የሚሻለውን ሁሉ ለማድረግ እየዘነጋህ ማዳመጥን ብቻ ታዳምጣለህ:: አስብበት::

ጸሎት:- ለቃሉ ምንባብና ለቀረበው መልእክት በእምነትና በመታዘዝ ምላሽ ለመስጠት እንድትችል ይረዳህ ዘንድ እግዚአብሔርን ለመጠየቅ በጸሎት ስገድ:: እግዚአብሔርን በእውነት ልናመልክ የምንችለው ይህን በማድረግ ብቻ ነው::

ተቀጥላ

በመጽሐፍ ቅዱስ የአምልኮን ፍች የሚያሳዩ ተጨማሪ አሳቦች

መግቢያ፡-

በዓለም የሚኖሩ ሰዎች ሁሉ ከእነርሱ በላቀ የሥልጣን እርከን ላይ የሚገኙትን ሰዎች የማክበር ግዴታ እንዳለባቸው ያስባሉ። ልጆች ወላጆቻቸውን ያከብራሉ። ወጣቶች ከእነርሱ በዕድሜ ገፋ ያሉትን ያከብራሉ። ጭፍራዎች መሪዎቻቸውን ያከብራሉ። በዕድሜ ገፋ ያሉትን ያከብራሉ። ጭፍራዎች መሪዎቻቸውን ያከብራሉ። ይህም ትክክለኛና ተገቢ እንደሆነ ይሰማናል። ሰዎች ከእነርሱ የበለጠ ሥልጣን ላላቸው ሰዎች ተገቢውን ክበሬታ ቢነፍጉ፥ የማኅበረሰብ (የመንደሮች፥ የከተሞችና የአገሮች) ሕይወት መናጋቱ የማይቀር ነው።

በተመሳሳይና ጻሩ ግን ከዚህ በበለጠ ሁኔታ፥ የሰው ልጆች ለእግዚአብሔር እጅግ ከፍ ያለ አክብሮት፥ የጠለቀ መገዛትና ፍርሃት ሊያሳዩ ይገባል። እግዚአብሔር የሰማይና የምድር ፈጣሪ ስለሆነ፥ የእርሱ ፍጡራን የሆንነው እኛ ተንበርክከን ልንገዛለትና ልናወድሰው ያሻል። እርሱ የታሪክ ሁሉ ታላቁ አስተዳዳሪ በመሆኑ፥ ለእርሱ ብቻ የሚገባውን ፈሪሃ-እግዚአብሔርና ክብር ልንሰጠው ይገባል። እርሱ ብቻ አውነተኛና ሕያው አምላክ እንደሆነ አምነን ልንቀበልና ልንመሰክር ይገባል። ከእርሱ ሌላ ማንም የለውም! እርሱ በእኛ ላይ በሉዓላዊነት የሚገዛ አምላክ ነው። እግዚአብሔር አምላክ በኢየሱስ ክርስቶስ አማካኝነት ተቤዣቸውና አዳኛችን ሊሆን ስለወደደ፥ በክርስቶስ ደም የተዋጀነው እኛ ውዳሴያችንና አድናቆታችንን ሊቀበል የሚገባው እርሱ ብቻ እንደሆነ ልንመሰክር ይገባል። ስሙን ልናከብርና ከፍ ከፍ ልናደርገው ያሻል። ይህንንም አምልኮ እንለዋለን።

ለአምልኮ የተለያዩ ትርጉሞች (ብያኔዎች) ሲሰጡ ኖረዋል።

"አምልኮ እግዚአብሔር ክብር እንደሚገባው የምናውጅበት ጠንካራ ምላሽ ነው።"

"አምልኮ የእግዚአብሔርን ወደር የለሽ ክብር የምናውጅበት የባሕርይ መግለጫ ነው።"

"አምልኮ አማኙ ለሆነው ሁሉ - ለአእምሮው፥ ለስሜቶቹ፥ ለፈቃዱና ለአካሉ - እንዲሁም አግዚአብሔር ለሆነው፥ ለሚናገረውና ለሚያደርገው ሁሉ ምላሽ የሚሰጥበት ነው... ይህም በፈሪሃ- እግዚአብሔር ሚዛናዊነቱን የጠበቀ የፍቅር ምላሽ

በእግዚአብሔር ፍቅርና ፍርሃት ላይ እኩል አጽንኦት የሚሰጥበት ሲሆን፥ አማኙ እግዚአብሔርን ይበልጥ እያወቀው ሲሄድ እያደገና እየጠለቀ የሚሄድ ምላሽ ነው።"

"አምልኮ ክብሩ የሰብአዊ አኗኗር መመዘኛና መነቃቂያ እስኪሆን ድረስ እግዚአብሔር እጅግ የላቀ አክብሮት የሚያገኝበት ነው።"

ስለሆነም እውነተኛ አምልኮ የሚነሣው ፍጡሩ ከፈጣሪው ጋር ካለው ግንኙነት ነው። ከፍጥረትና ከቸርነት ሥራው በታሪክ ውስጥ ያከናወናቸው እና በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ አማካኝነት ከፈጸመው የደኅንነት ተግባር የተነሣ እግዚአብሔርን ልናመልከው እንሻለን።

እግዚአብሔርን ባከበርነው ጊዜ ሁሉ እናመልከዋለን። እግዚአብሔርን ስናመሰግነው፥ ስናወድሰው፥ ስናከብረው፥ ስንታዘዘው፥ ስንወደው፥ ስንፈራው፥ ስለ እርሱ ስንመሰክር፥ ስናገለግለው፥ ስናደንቀው፥ ስንዘምርለት፥ ወደ እርሱ ስንጸልይ፥ ምጽዋታችንንና፥ ራሳችንን ስንሰጠው እናመልከዋለን።

የአምልኮ ጠባብና ሰፊ ትርጉም፡-

የአምልኮ ሰፊ ትርጉም - ንጹሕ አምልኮ ከእግዚአብሔር ጋር በሚደረግ ጎብረት በቀጥታ የሚበረከትለት ውዳሴ፥ ምስጋናና መሰጠት ነው።

የአምልኮ ሰፊ ትርጉም - አምልኮ ከዚህ በላይ በተመለከተው ንጹሕ አምልኮ ብቻ ሊወሰን አይገባውም። በምናደርገው ነገር ሁሉ እግዚአብሔርን ስናስከብር እናመልከዋለን። ስንታዘዘው፥ ስናገለግለውና በሌሎች ፊት አክብሮትን ስናሳየው እግዚአብሔርን እናመልከዋለን። በሕይወታችን ቀናትና ሰዓታት ሁሉ እግዚአብሔርን ልናከብረው፥ ልንታዘዘውና ክብርን ልንሰጠው ይገባል። አምልኮ የክርስቲያኖች የማያቋርጥ ተግባር ሊሆን ያሻል።

ንጹሕ አምልኮ (ጠባቡ የአምልኮ ትርጉም) - በቤተ ክርስቲያን ለእግዚአብሔር የምስጋና መዝሙሮችን ስንዘምር፥ በምስጋናና በመሰጠት ወደ እግዚአብሔር ስንጸልይ፥ አሥራታችንና ምጽዋታችንን በፍቅር ስንከፍል (የገቢያችንን አሥር እጅ)፥ ለተሰበከልን የእግዚአብሔር ቃል የእምነትና የታዛዥነት ምላሽ ስንሰጥ ተግባራዊ ይሆናል።

በተጨማሪም በዕለታዊ የጽሞና ጊዜያችን ከእግዚአብሔር ጋር ጎብረትን ስናደርግ (በእምነትና በታዛዥነት ቃሉን ስናነብ) እና ቀኑን ሁሉ ደስታን በተላበሰ ልብ ለእግዚአብሔር ስንዘምር ወይም ስንጸልይ ንጹሕ አምልኮ ተግባራዊ ይሆናል።

ይሁንና፥ የክርስቲያን ጠቅላላ ሕይወት "የምስጋና መሥዋዕት" ሊሆን ይገባል። ስለሆነም፥ ስትበላ ወይም ስትጠጣ፥ ወይም ማንኛውንም ተግባር ስታከናውን ሁሉንም ለእግዚአብሔር ክብር ልታውለው ይገባል (1ኛ ቆሮ.10:31)። በሰፊው ትርጉም፥ በቃልም ሆነ በተግባር ልናስደስተው በምንፈልግበት ጊዜ ሁሉ እግዚአብሔርን እናመልከዋለን። አእምሮአችን ወደ እግዚአብሔር ቢያዘነብልም ባያዘነብልም፥ ሁልጊዜም በምናደርገው ነገር ሁሉ እግዚአብሔርን ለማስከበር መሻት አለብን። ይህም በሥራ ቦታ፥ ሕፃን ልጅ ስናጠባ፥ በትምህርት ቤት ስንማር፥ ከጓደኞችን ጋር ስንነጋገር፥ ወደ ገበያ ስንሄድ፥ ጓሮአችንን ስናለማ፥ ምርታችንን ስንሸጥ ወይም ማንኛውንም ተግባር ስናከናውን ሊደረግ የሚገባው ነው።

ለአምልኮ ያገለገሉ ቃላት

የአፍሪካውያን ባሕላዊ የአምልኮ ጽንሰ-አሳቦች - ሚስዮናውያን የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ይዘው ከመምጣታቸው በፊት፥ አፍሪካውያን በተለያዩ መንገዶች ለእግዚአብሔር ክብር ለመስጠት በመሻት ያመልኩት ነበር። የራሳችንን የአማርኛ ቋንቋ የወሰድን እንደሆነ፥ የአምልኮን ጽንሰ-አሳብ ለመግለጽ የሚከተሉት ቃላት ከግልጋሎት ላይ ውለው እናገኛቸዋለን።

1. ስግደት - በአንድ ሰው ወይም ነገር ፊት በግንባር በመደፋት ይከናወናል። ሰላምታ ለመስጠት ወይም ደግሞ ለአምላክ ምስጋናና ጸሎት ለማቅረብ ያገለግላል።

2. ውዳሴ - የጀግንነት ተግባራት የፈጸሙትን ሰዎች ለማድነቅ የሚያገለግል ሲሆን፥ ለአምላክም እንጠቀምበታለን።

3. አምልኮ - በአብዛኛው ለአምላክ ወይም ለጣዖታት የሚያገለግል ቃል ነው። ይሁንና፥ ከመጠን ያለፈውን ፍቅር ለመግለጽም እንጠቀምበታለን።

4. ጸሎት - ይህ ወደ አምላክ የሚደረግ ምስጋና፥ ምልጃ ወይም ልመና ነው።

5. አክብሮት - ለሰውም ለአምላክም ያገለግላል።

ከዚህም በላይ እንደ ምልጃ፥ ምስጋና፥ መሥዋዕት፥ ከፍ ከፍ ማድረግ... የመሳሰሉ ቃላት ከአምልኮ ጋር በተያያዘ መልኩ ከሥራ ላይ የሚውሉ ናቸው።

6. ለአምልኮ የእንግሊዝኛ ቃል

"Worship" የሚለው የእንግሊዝኛ ቃል "weorthscipe" ከሚለው

የአንግሎ-ሳክሰን ቃል የተገኘ ነው። በኋላ "worthship" ወደሚለው ተቀየረ፥ ከዚያም "worship" ሆኖ ቀረ። "weorthscipe" ክብሩን የሚቀበለው ሰው ያ አክብሮት እንደሚገባው መመስከር ነው።

የክብር ደረጃዎች፦

የሰው ልጅ ቋንቋ በርካታ ውስንነቶች አሉት። ብዙውን ጊዜ አሳባችንን በቋንቋችን በትክክል ለመግለጽ እንቸገራለን። በብዙ ቋንቋዎች ለእግዚአብሔር አክብሮትን ለማሳየት የሚያገለግሉ ቃላት ለሰዎች ወይም ለሙት መናፍስትም ያገለግላሉ። ይህ በእንግሊዝኛም ሆነ በአፍሪካ ቋንቋዎች ውስጥ የምንመለከተው ነው። እግዚአብሔርንም ሰዎችንም እናወድሳለን።

ይሁንና፥ ክርስቲያኖች እግዚአብሔር ከሰዎች የተለየ ክብር ሊሰጠው እንደሚገባ ያስባሉ። ምንም እንኳ ሰዎችን ብናመሰግንም ይህ ለእግዚአብሔር ከምንሰጠው ምስጋና ጋር አይነጻጸርም፤ ሊነጻጸርም አይችልም። አንድ ዓይነት ቃላትን የምንጠቀመው ከቋንቋ ችግራችን የተነሣ ብቻ ነው።

ስለሆነም ለሌሎች ሰዎች የምናሳየው አክብሮት ደረጃ አለው።ለወላጆቻችን አንድ ዓይነት አክብሮት (ኤፌ.6:2)፥ ለመንግሥት ባለሥልጣናት ሌላ ዓይነት አክብሮት እናሳያለን (ሮሜ 13:7)። ክርስቲያን ያልሆኑ ሰዎች ለመናፍሰት አንድ ዓይነት አክብሮት ያሳያሉ። ነገር ግን አምልኮ ብለን የምንጠራውን ያንን የተለየ ክብርና መሰጠት ሊቀበል የሚገባው እግዚአብሔር ብቻ ነው።

በጥንቱ እንግሊዝኛ ሰዎች ከዳኛ ፊት ሲቀርቡ፥ "አምልኮትዎ"("Your worship") ብለው ይናገሩ ነበር። ዳኛ ሕግን ስለሚተረጉምና ፍትሕን ስለሚተገብር እንደ አስፈላጊ ሰው ይታይ ነበር። ስለሆነም ሰዎች ለዳኛው የተለየ ክብር ይሰጡት ነበር። ከሥልጣኑ የተነሣ ዳኛ አስፈላጊ ሰው ነበር።

ይህ አሮጌ ጽንሰ-አሳብ ሰዎች የከተማን ሹም፥ "አምልኩቱ ሹም"("His Worship the Mayor") እያሉ በሚጠሩበት በኪንያ ባህል ውስጥ ሲንጸባረቅ እንመለከታለን። በዚህ ዓይነት ለከተማዪቱ የመጀመሪያ ዜጎች ክብር ይሰጣቸዋል። ይህም ማለት ሹም ከሚያደርገው፥ ከማንነቱና ከብቃቶቹ የተነሣ ሥልጣኑን መያዝ ይገባዋል ማለት ነው። ስለሆነም "አምልኩቱ" ("his worship") በማለት ሰፍራው እንደሚገባው መቀበላቸውን ይገልጻሉ።

አንድ የጋብቻ ቃል ኪዳን ማስፈጸሚያ መጽሐፍ እንደሚለው፥ ሙሽራው ለሙሽራዪቱ፥ "በአካሌ አመልክሻለሁ" (With my body I thee worship"/I worship you") የሚል ቃል እንደሚገባ ይናገራል። ይህም ባል ለሚስቱ ፍጹም ታማኝነቱንና መሰጠቱን እንደሚገልጽ

ያሳያል። ስለሆነም ለሰዎች የሚሰጡ የተለያየ ደረጃ ያላቸው የክብር መልኮች አንዳሉ እንመለከታለን። ይሁንና፥ አምልኮተ እግዚአብሔር የሚገባው ለፈጣሪው አምላክ ብቻ ነው።

ስለ አምልኮ የሚናገሩ የዕብራይስጥና የግሪክ ቃላት "ከአንድ ሰው ፊት መስገድን" ያመለክታሉ። በዕብራውያንም ሆነ በግሪኮች መካከል ተገቢውን አክብሮት ለማመልከት መሬት ላይ በግንባር ተደፍቶ መስገድ የተለመደ ነበር። በጉልበት መንበርከክ ወይም ዝቅ ማለት የትሕትናና የአክብሮት ምልክት ነው።

የዩጋንዳዎቹ ቡጋንዳዎች ለአንድ ሰው ያላቸውን አክብሮት የሚያሳዩት በመስገድ ነው። እኛም ኢትዮጵያውያን ራሳችንን በማዘንበል የአክብሮት ሰላምታ እናቀርባለን። ይህ ለኬንያ ሰዎች አንግዳ ነገር ይመስላል። ስለሆነም ለአንዳንድ ሰዎች የአምልኮን ከፍተኛ ደረጃ ሊያመለክት ይችላል። ይሁንና፥ ሰዎች አክብሮትን የሚያሳዩበት መንገድ ከባህል ባህል ይለያያል።

በአዲስ ኪዳን የእግዚአብሔር ሰዎች ለመምህር ሰላምታ ለመስጠት (ማር. 10፡17)፥ ወደ ንጉሥ ሲቀርቡ (ማቴ. 27፡29) ወይም ለእግዚአብሔር ሲጸልዩ (ሉቃ.22፡41)፥ ይሰግዱ ወይም ይንበረከኩ ነበር። በብሉይ ኪዳን ሰዎች በእግዚአብሔር ሰው ፊት (2ኛ ነገ.1፡13)፥ በንጉሥ ፊት (1ኛ ዜና 29፡20)፥ ወይም በእግዚአብሔር ፊት በሚጸልዩበት ጊዜ (ኢሳ.45፡23) ይሰግዱ ወይም ይንበረከኩ ነበር።

ስለሆነም መጽሐፍ ቅዱስ ከእኛ በላይ ለሚገኙ ሰዎች የተለያየ ዓይነት የክብር ደረጃ አመዳደብ አንዳለው ልንመለከት ያሻል። አንዳንዶች ከሌሎች የበለጠ ክብር ወይም የተለየ ዓይነት አክብሮት ይገባቸዋል። ነገር ግን ከሁሉም የተለየውን ልዩ አክብሮት ለእርሱ ብቻ እንድንሰጥ እግዚአብሔር ይርዳን። ይህንን "አምልኮ" ብለን እንጠራዋለን።